# ኦሪት ዘሌዋውያን

ምዕራፍ ፩ ።

፩ ወጸውዖ እግዚአብሔር ለሙሴ ወተናገሮ እምውስተ ደብተራ ዘመርጡል ።

፪ ወይቤሎ በሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ወአይድዖሙ ከመ ብእሲ እምኔክሙ ዘአብአ መባአ ለእግዚአብሔር እምእንስሳ ወእምአልሕምት ወእምአባግዕ ታበውኡ መባአክሙ።

፫ ለእመ ለሠዊዕ መባኡ እምአልሕምት ተባዕተ ንጹሐ ያመጽእ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወያበውኦ ሥሙረ ቅድመ እግዚአብሔር ።

፬ ወያነብር እዴሁ ላዕለ ርእሱ ለገብሩ ላሕም ዘአምጽአ ለሠዊዕ ከመ ይሠጠዎ ወያስተሥሪ ሎቱ በእንቲአሁ ።

፭ ወይጠብሕዎ ለውእቱ ላሕም ቅድመ እግዚአብሔር ወያመጽኡ ደቂቀ አሮን ደሞ ለሊሆሙ ካህናት ወይክዕውዎ ላዕለ ምሥዋዕ ዓውዶ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ።

፮ ወይጠብሕዎ ወይፈልጡ መለያልይሁ ዘዘዚአሁ ።

፯ ወይወድዩ እሳተ ደቂቀ አሮን ካህናት ላዕለ ምሥዋዕ ወይሬሥዑ ዕፀወ እሳት ።

፰ ወይሬሥዑ ደቂቀ አሮን ካህናት ዝክተ ዘተመትረ ርእሶኒ ወስብሖኒ ላዕለ ዕፀው ዘላዕለ እሳት ዘዲበ ምሥዋዕ ።

፱ ወንዋየ ውስጡ ወእገሪሁ የሐጽቡ በማይ፥ ወይወዲ ካህን ኵሎ ዲበ ምሥዋዕ መሥዋዕት ውእቱ ወቍርባን ዘመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ።

፲ ወእመሰ እምአባግዕ ውእቱ መባኡ ለእግዚአብሔር እመኒ በግዕ ወእመኒ ማሕስአ ለሠዊዕ ተባዕተ ንጹሐ ያመጽኡ ።

፲፩ ወይጠብሕዎ በገቦ ምሥዋዕ ዘመንገለ መስዕ ቅድመ እግዚአብሔር ወይክዕዉ ደሞ ደቂቀ አሮን ካህናት ላዕለ ምሥዋዕ በዓውዱ ።

፲፪ ወይመትርዎ ካህናት በበመለያልይሁ ርእሶኒ ወስብሖኒ ወይሬሥዕዎ ላዕለ ዕፀው ዘዲበ እሳት ዘላዕለ ምሥዋዕ ።

፲፫ ወንዋየ ውስጡ ወእገሪሁ የሐጽቡ በማይ ወያመጽእ ካህን ኵሎ ወያነብሮ ላዕለ ምሥዋዕ ለቍርባን መሥዋዕት ውእቱ ወመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ።

፲፬ ወእመሰ እምአዕዋፍ ያበውዕ መሥዋዕቶ ቍርባኖ ለእ

ምዕራፍ ፩ ።

እግዚአብሔር ከደብተራ ኦሪት ውስጥ ሆኖ ሙሴን ጠርቶ እንዲህ ሲል ተናገረው ። ዘኍ፥ ፩ ፩ · ፲ ።

ከናንተ ወገን ለእግዚአብሔር መባውን የሚያገባ ሰው ቢኖር ከከብት ወገን ከላሞች ከበጎች መባቹሁን አቅርቡ፥ ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው አለው ።

የሚያቀርቡት መባ ለመሥዋዕት ከሆነ ከላም ወገን ነውር የሌለበትን ተባቱን በእግዚአብሔር ፊት ወዶ እንዲቀበለው አድርጎ ወደ ደብተራ ኦሪት ደጃፍ ያምጡ ።

ሊሠዋውም ያመጣው ሰው በላሙ ራስ ላይ እጁን ይጫንበት ወዶ ተቀብሎ ኃጢአቱን ያስተሠርይለት ዘንድ ።

ላሙንም በእግዚአብሔር ፊት ይረዱት፥ የአሮንም ልጆች ካህናቱ ራሳቸው ደሙን በደብተራ ኦሪት ደጅ ባለ በምሥዋዑ ዙርያ ይረብርቡት ። ዕብ፥ ፲ ፲፩ ።

አርደው አወራርደውም ብልቱን በየዘርፉ ለያይተው ይቍረጡት ። ዘሌ፥ ፳፯ ፲፪፥ ዘሌ፥ ፰ ፳ ።

የአሮን ልጆች ካህናቱም ከመሠውያው ላይ እሳት እንድደው ዕንጨቱን በእሳቱ ላይ ይረብርቡት ።

የአሮን ልጆች ካህናት አርደው ያወራረዱትን ሥጋ ራሱንም ስቡንም በመሠውያው በነደደው እሳት ባለው ዕንጨት ላይ ይደርድሩት ። ዘሌ፥ ፯ ፲፪፥ ፰ ፳ ።

ሆድ ዕቃውንና እግሮቹን በውኃ አጥበው ካህኑ ሁሉንም በምሥዋዑ ላይ ያድርገው (ያሳርገው)፥ ይኸውም እግዚአብሔር ወዶ የሚቀበለው መሥዋዕትና ቍርባን ነው ።

ለእግዚአብሔር የሚቀርበው መባ ከበጎች ወገን ቢሆን ግን በግም ቢሆን ፍየልም ቢሆን፥ ለመሥዋዕት ነውር የሌለበትን ተባት ያምጡ፥ (ያቅርቡ) ።

በእግዚአብሔር ፊት በምሥዋዑ አጠገብ በሰሜን በኩል ይረዱት፥ የአሮን ልጆች ካህናትም ደሙን ተቀብለው በመሠውያው ላይ በዙርያው ይርጩት ።

ካህናቱ ራሱንና ስቡንም ብልት ብልቱን ቈራርጠው ለይተው በመሠውያው አጠገብ በነደደው እሳት አጠገብ ባለው ዕንጨት ላይ ይረብርቡት ። ቍ፥ ፰ ።

ሆድ ዕቃውንና እግሮቹን (ሰኰናውን) ግን በውኃ ይጠቡት፥ ካህኑም ሥጋውን ሁሉን አምጥቶ በምሥዋዑ ላይ ያድርገው (ያቃጥለው)፥ እግዚአብሔር ወዶ የሚቀበለው መሥዋዕት ነውና ። ዘሌ፥ ፩ ፯፥ ፲፪ ፰ ።

ለእግዚአብሔር የሚያቀርብ መሥዋዕት ከአዕዋፍ

ግዚአብሔር ያመጽእ እመ አኮ እማዕነቅ ወእመ አኮ እም ርግብ ቍርባኖ ፤ ያመጽእ ካህን ኀበ ምሥዋዕ ።

ወገን ቢሆን ግን ከዋኖስ ወይም ከርግብ ካህኑ ቍርባኑን ወደ መሠውያው ያምጣ ።

፲፭ ወይመትር ክሳዶ ወያነብሮ ላዕሌ ምሥዋዕ ወያንጸፈጽፍ ደሞ ኀበ መንበረ ምሥዋዕ ።

አንገቱን ገዝግዞ በመሠውያው ያኑረው (ያቃጥለው) ደሙንም ከመሠውያው እግር ያንጠፍጥፈው ።

፲፮ ወያሴስል ንዋየ ውስጡ ምስለ ፀጕሩ ወያነብሮ በገበ ምሥዋዕ ዘመንገለ ጽባሒሁ ኀበ መንበረ ሐመድ ።

ሆድ ዕቃውንም ከጠጕሩ ጋር አመዱ በሚፈስበት ቦታ በመሠውያው አጠገብ በስተምሥራቅ በኩል ያፍስሰው (አውጥቶ ይጣለው) ። ዘሌ፡ ፱ ፲፫ ።

፲፯ ወይሰብሮ ክነፊሁ ወኢይመትሮ ፡ ወያነብሮ ካህን ላዕለ ምሥዋዕ በዲበ ዕፀው ዘላዕለ እሳት ።

ክንፍ ክንፎቹን (ክንፎቹን) ይሰብረው ፡ ቈርጦ አይጣለው (አይለየው) ካህኑም በምሥዋዑ ላይ በእሳቱ በላው ዕንጨት ላይ አድርጎ ያቃጥለው ።

፲፰ ቍርባን ውእቱ ዘመሥዋዕት ወመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ።

ለእግዚአብሔር በጎ መዓዛ ያለው ወዶ የሚቀበለው መሥዋዕት ነውና ። ዘፍ፡ ፲፭ ፲ ።

## ምዕራፍ ፪ ።

## ምዕራፍ ፪ ።

፩ ወእመሰ ሀየንተ ነፍስ ቍርባነ ወመሥዋዕተ ለእግዚአብሔር ያመጽእ ሥንዳሌ ይኩን ቍርባኑ ፡ ወይክዑ ላዕሌሁ ቅብዐ ወይወዲ ዲቤሁ ስኂነ ።

ማናቸውም ሰው ስለ ሰውነቱ ለእግዚአብሔር የእኽል ቍርባን መሥዋዕት ቢያመጣ (ቢያቀርብ) ልጦ ጕረዶ የወጣለት ሥንዴ ልዝብ ዱቄት ይሁን፡ ዘይት ያፍስስበት ነጭ ዕጣን ያድርግበት ። ዘኊ፡ ፲፭ ፬ ።

፪ ወይወስድ ኀበ ደቂቀ አሮን ካህን ወይዘግን እምኔሁ ክህን ምልአ ሕፍኑ እምሥንዳሌ ምስለ ቅብዑ ወኵሉ ስኂኑ ወይወድዮ ለተዝካር ላዕለ ምሥዋዕ ፡ መሥዋዕት ውእቱ ዘመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ።

ወደ ካህናቱ ወደ አሮን ልጆች ይውሰደው ካህኑም በዘይት ከታሸው ዱቄት እጅ ሙሉ ዘግኖ ዕጣኑንም ወስዶ መታሰቢያ ሊሆን በምሥዋዑ ላይ ያቃጥለው እግዚአብሔር ወዶ የሚቀበለው ያማረ መሥዋዕት ነውና።

፫ ወዘተርፈ እመሥዋዕት ለአሮን ወለደቂቁ ቅዱስ ለቅዱሳን እመሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር ።

ከመሥዋዕቱ ጢስለት የተረፈውም ለአሮንና ለልጆቹ ይሁን ፡ ከእግዚአብሔር መሥዋዕት ጢስለት የተረፈው ቅዱስ ለቅዱሳን ነውና ። ዘፀ ፳፱ ፴፯ ፡ ዘኊ፡ ፲፰ ፱ ።

፬ ወእመሰ አብአከ ቍርባነ ለመሥዋዕት ብሱለ በእቶን ኅብስተ ሥንዳሌ ናእተ ልዉሰ በቅብዕ ።

በእሳት የበሰለውን ቍርባን አድርገህ ለመሥዋዕት ብታቀርብ በዘይት የተለወሰ የሥንዴ ዳቦ (ቂጣ) ይሁን ።

፭ ወእመ መሥዋዕተ ቴጕን ቍርባንከ ሥንዳሌ ልዉሰ በቅብዕ ወናእተ ይኩን ወትፌትቶ ወትክዑ ላዕሌሁ ቅብዐ ።

ቍርባንህ በምጣድ የተጋገረ ቢሆን ግን በዘይት የተለወሰ ከመልክም ሥንዴ ዱቄት ያልቦካ ቂጣ ይሁን ፡ ቈርሰህም ዘይት አፍስስበት ።

፮ ወለእመ ብሱል በመቅጹት መሥዋዕትከ ሥንዳሌ በቅብዕ ይትገበር ።

መሥዋዕትህ በምንቸት የተቀቀለ (የተገነፋ) ነገር ቢሆን በዘይት የተለወሰ የሥንዴ ዱቄት ይሁን ።

፯ ወታመጽእ መሥዋዕተ ዘገበርከ እምዝንቱ ለእግዚአብሔር ኀበ ካህን ፡ ወያቀርቦ ካህን ኀበ ምሥዋዕ ።

ከዚህ ሁሉ ያደረግኸውን መሥዋዕትህን ለእግዚአብሔር አምጥተህ ወደ ካህኑ አቅርበው ካህኑም ወደ ምሥዋዑ ያቅርበው ።

፰ ወይነሥእ ካህን እመሥዋዕት ለተዝካር ወይወድዮ ላዕለ ምሥዋዕ መሥዋዕት ውእቱ ወመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ።

ካህኑም መታሰቢያ ሊሆን ከመሥዋዕቱ አምጥቶ በመሠውያው ላይ ያቃጥለው በጎ መዓዛ ያለው ሁኖ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መሥዋዕት ነውና ። ዘፍ፡ ፳፱ ፲፰ ።

፱ ወዘተርፈ እመሥዋዕት ለአሮን ወለደቂቁ ቅዱስ ለቅዱሳን እመሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር ።

ለእግዚአብሔር ከቀረበው መሥዋዕት የቀረው ከከበሩ ለተከበሩት ለአሮን ልጆች ይሁን ። ዘፀ፡ ፳፱ ፴፯ ።

፲ ኵሉ ዘታመጽኡ ለሠዊዕ ለእግዚአብሔር ኢትግበሩ ብሑዓ እምኵሉ ብሑዕ ወእምኵሉ መዓር ኢታምጽኡ ለሠዊዕ ለእግዚአብሔር ለቍርባን ።

ለእግዚአብሔር ብላችሁ የምታመጡትን መሥዋዕት ሁሉ መጻጻ አታድርጉት ፡ መጻጻ ካለበት ነገር ሁሉ ከማርም ሁሉ ቍርባን ሊሆን ለእግዚአብሔር አታምጡ ።

፲፩ ወባሕቱ ለዓሥራት ታበውኡ እምኔሁ ለእግዚአብሔር ለመሥዋዕትሰ ኢትሠውዑ እምኔሁ ለመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ።

ብቻ ለእግዚአብሔር ከምታቀርቡት ከሱ (ከማር) ከሥር አንዱን ታገባላችሁ ፡ በምሥዋዑ ላይ ለእግዚአብሔር በጎ ሽታ ሊሆን ከርሱ አትሠዉ ። ዘፀ፡ ፳፪ ፳፱ ።

፲፪ ወኵሉ ቍርባነ መሥዋዕትክሙ በጼው ይትገበር ወኢይትኃደግ ጼው እንዘ ትሠውዑ ለእግዚአብሔር ውስተ ኵሉ ቍርባንክሙ ትወድዩ ጼወ ።

የመሥዋዕታችሁ ቍርባን ሁሉ በጨው ይጣፍጥ ለእግዚአብሔር ስትሠዉ ጨው አይቅር ፡ በምታቀርቡት ቍርባናችሁ ሁሉ ጨው ጨምሩበት ። ማር፡ ፱ ፵፱ ።

፲፫ ወእመሰ አበእከ መሥዋዕተ እምቀዳሚ እክልከ ለእግዚአብሔር ሐዲሰ ቅሉወ ንጹሐ ወልቱመ ታበውእ መሥዋዕተ እምቀዳሚ እክልከ ።

፲፬ ወትክዑ በላዕሌሁ ቅብዐ ወትወዲ ላዕሌሁ ስኂነ ።

፲፭ ወያበውእ ካህን ለውእቱ እክል ምስለ ቅብዑ ወኵሉ ስኂኑ ለተዝካር መሥዋዕት ውእቱ ለእግዚአብሔር ።

## ምዕራፍ ፫ ።

፩ ወእመሰ መሥዋዕተ መድኃኒት ውእቱ ቍርባኑ ለእግዚአብሔር ለእመ እምአልሕምት አምጽአ እመኒ ተባዕተ ወእመኒ አንስተ ንጹሐ ለያምጽእ ቅድመ እግዚአብሔር ።

፪ ወይወዲ እዴሁ ላዕለ ርእሱ ወይጠብሕዎ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወይክዕዉ ደሞ ደቂቀ አሮን ካህናት ላዕለ ምሥዋዕ በዓውዱ ።

፫ ወያበውኡ እመሥዋዕተ መድኃኒት ቍርባነ ለእግዚአብሔር ስብሐ ዘይገለብብ ከርሦ ወኵሎ ስብሐ ዘውስተ ከርሡ ።

፬ ወክልኤሆን ኵልያቲሁ ወስብሐ ዘላዕሌሆን ዘውስተ ጸራዊቱ ወከብዶ እንተ ትንእስ ምስለ ኵልያቲሁ ያመጽኡ ።

፭ ወያበውኡ ደቂቀ አሮን ላዕለ ምሥዋዕ ዲበ ዕፀው ዘላዕለ እሳት መሥዋዕት ውእቱ ወመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ።

፮ ወእመሰ እምአባግዕ ቍርባኑ ወመሥዋዕተ መድኃኒቱ ለእግዚአብሔር እመኒ ተባዕተ ወእመኒ አንስተ ንጹሐ ያመጽእ ።

፯ ወእመሰ ማሕስአ በግዕ ቍርባኑ ያመጽእ ቅድመ እግዚአብሔር ወይወዲ እዴሁ ላዕለ ርእሰ ቍርባኑ ።

፰ ወይጠብሕ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወይክዕዉ ደቂቀ አሮን ካህናት ደሞ ላዕለ ምሥዋዕ በዓውዱ ።

፱ ወይነሥእ እመሥዋዕተ መድኃኒት ቍርባነ ለእግዚአብሔር ስብሐ ወሐቌሁ ፍጹመ ምስለ ስመጢሁ ይመትሮ ወኵሎ ስብሐ ዘይገለብብ ከርሦ ወኵሎ ስብሐ ዘውስተ ከርሡ ።

፲ ወክልኤሆን ኵልያቲሁ ወስብሐ ዘፀራዊቱ ወከብዶ እንተ ትንእስ ምስለ ኵልያቲሁ ይመትሮ ወይወድዮ ካህን ላዕለ ምሥዋዕ ቍርባኑ ውእቱ ለእግዚአብሔር ።

፲፩ ወእመሰ እምአጣሊ ቍርባኑ ለእግዚአብሔር ያመጽእ ቅድመ እግዚአብሔር ወይወዲ እዴሁ ላዕለ ርእሱ ።

፲፪ ወይጠብሕዎ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወይክዕዉ ደሞ ደቂቀ አሮን ላዕለ ምሥዋዕ በዓውዱ ።

፲፫ ወይነሥእ እምኔሁ ቍርባነ ለእግዚአብሔር ስብሐ ዘይገለብብ ለከርሡ ፡ ወኵሎ ስብሐ ዘውስተ ከርሡ ።

መጀመርያ ከደረሰው እኽልህ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ብታቀርብ ግን ፡ አዲስ የተቈላ የተፈተገ ፡ የተለቀመውን መጀመርያ ከደረሰው እኽልህ አቅርብ ።

በላዩ ላይ ዘይት አፍስስበት ፡ ቍንዶ በርበሬም ጨምርበት ።

ካህኑም ያንን እህል ከዘይቱና ከቍንዶ በርበሬው ጋር ለመታሰቢያ ያግባው ለእግዚአብሔር የሚጤስ መሥዋዕት ነውና ።

## ምዕራፍ ፫ ።

ለእግዚአብሔር የሚቀርበው ቍርባን የደኅንነት መሥዋዕት ሲሆን ከላሞች ወገን ተባትም ቢሆን እንስትም ቢያመጣ ንጹሕ የሆነውን በእግዚአብሔር ፊት ያቅርብ ።

የሚሠዋውም ሰው በሚሠዋው መሥዋዕቱ ላይ እጁን ይጫንበት ፡ በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ይረዱት (ይሠዉት) የአሮን ልጆች ካህናትም ደሙን ተቀብለው በምሥዋዑ ዙርያ ይረብቡት (ይርጩት) ። ዘሌ፡ ፩ ፬ ።

ድኅነት ከሚደረግበት መሥዋዕት ሆዱን የሚሸፍነውን ስብ በሆዱም ውስጥ ያለውን ሁሉ ለእግዚአብሔር ቍርባን አድርገው ያምጡ ። ዘሌ፡ ፲፰ ፬ ፡ ዘፀ፡ ፳፱ ፲፫ ።

ሁለቱንም ኵላሊቱ በርሳቸው ላይ ያለውን ስብ በጭቅናው (በሰብራደው) ላይ ያለውን ስብ ፡ ለምለም ጉበቱን ከሁለት ኵላሊቶቹ ጋራ ያቅርቡ ።

የአሮንም ልጆች ከመሠውያው እሳት በላው ዕንጨት ላይ ያኑሩ (ያቃጥሉት) በጎ መዓዛ ሲሆን ለእግዚአብሔር የሚጤስ መሥዋዕት ነውና ። ዘፀ፡ ፳፱ ፲፰ ።

ለእግዚአብሔርም የደኅንነት መሥዋዕት አድርጎ የሚያቀርበው ቍርባኑ ከበጎች ወገን ቢሆን ፡ ተባት ቢሆን እንስትም ቢሆን ፡ ነውር የሌለበት ንጹሕ ያቅርብ ።

ቍርባኑ የበግ ጠቦትም ቢሆን ፡ በእግዚአብሔር ፊት አምጥቶ እጁን በሚሠዋው መሥዋዕት ራስ ላይ ያኑር ።

በደብተራ ኦሪት ደጃፍም ይሠዋው ፡ የአሮን ልጆች ካህናትም ደሙን ተቀብለው በምሥዋዑ ዙርያ ይርጩት (ይረብርቡት) ።

ደኅንነት ከሚገኝበትም መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ቍርባን አድርጎ ቢያቀርብ ስቡን ጳሌውን ከሽንጡ ጋር ይለየው ፡ ሆድ ዕቃውን (ፈርሱን) የሚሸፍነውን ስቡን ሁሉ ፈቅቶ ይለየው ። ዘሌ፡ ፬ ፲፱ ፡ ዘፀ፡ ፳፱ ፳፪ ።

ሁለቱን ኵላሊቱ በጭቅናው (በሰብራደው) ያለውን ስቡን ግልገል ጉበቱን ከሁለት ኵላሊቱ ጋር ፈቅቶ ይለየው ፡ ካህኑ በምሥዋዑ ላይ ያጢሰው የእግዚአብሔር ቍርባን ነውና ።

ለእግዚአብሔር የሚያቀርበው ቍርባን ከፍየል ወገን ቢሆን በእግዚአብሔር ፊት ያቅርበው ። ሕዝ፡ ፵፬ ፯ ።

በደብተራ ኦሪት ደጃፍ የአሮን ልጆች ካህናትም ደሙን ተቀብለው በመሠውያው ዙርያ ይርጩት ።

ከተሠዋው መሥዋዕት ለእግዚአብሔር የሚያቀርበው ሆድ ዕቃውን በሆድ ዕቃው በፈርሱ በአንጀቱ ያለውን ስብ ሁሉ ።

፲፬ ወክልኤሆን ኵልያቲሁ ወኵሉ ስብሐ ዘላዕሌሆን ወዘ ጸራዊቱ ወከብዶ እንተ ትንእስ ምስለ ኵልያቲሁ ይመትሮ።

ሁለቱ ኵላሊቱን በኵላሊቱ ላይ ያለውን ስብ (ሞራ) በጭቅናው ውስጥ ያለውን ስብ ለምለም ጉበቱን ከሁለቱ ኵላሊቱ ጋራ ይህን ሁሉ አጥጥቶ ያጢሰው።

፲፭ ወያነብሮ ካህን ላዕለ ምሥዋዕ፣ መሥዋዕት ውእቱ ወመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር።

ለእግዚአብሔር በጎ መሥዋዕት ሁኖ የሚቀርብ ነውና ካህኑ ተቀብሎ በመሠዊው ላይ ያኑረው።

፲፮ ወኵሉ ስብሕ ለእግዚአብሔር ሕግ ዘለዓለም ውእቱ በኵሉ መዋዕሊክሙ።

ለእግዚአብሔር የምታቀርቡት ስብ ሁሉ በዘመናችሁ ሁሉ የዘለዓለም ሕግ ነውና።

፲፯ በኵለሄ በኀበ ትነብሩ ኵሉ ስብሐ ወኵሉ ደመ ኢትብልዑ።

በምትኖሩበት (በየሀገራችሁ) ሁሉ ስቡን ሁሉ፣ ደሙንም ሁሉ አትብሉ።

## ምዕራፍ ፬።

፩ ወተናገሮ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል።

እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው ለእስራኤልም ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው አለው።

፪ ወበሎሙ ነፍስ ለእመ አበሰት እምኵሉ ትእዛዘ እግዚአብሔር በኢያእምሮ ዘኢይከውን ለገቢር ወገብረት አሐተ እምኔሁ።

ማንኛይቱም ሰውነት (ነፍስ) በለማወቅ ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ወጥታ ሊሠሩዋት የማትገባውን ሥርዓ ብትበድል አትሥሩ ካለው አንዲቱን ብትሠራ። ዘኁ፣ ፲፭ ፳፪።

፫ ወእመኒ ሊቀ ካህናት ዘቅቡዕ አበሰ እምሕዝብ ያመጽእ ህየንተ አበሳሁ ዘአበሰ ላሕመ ንጹሐ እምአልሕምት ለእግዚአብሔር በእንተ ኀጢአቱ።

ከሕዝቡ ተመርጦ የተሾመው የካህናቱ አለቃም ቢበድል ስለ ሠራው ኃጢአት ከላሞች ወገን መርጦ ነውር የሌለበትን ንጹሕ በሬ ለእግዚአብሔር ያቅርብ።

፬ ወያመጽእ ለውእቱ ላሕም ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ቅድመ እግዚአብሔር፤ ወይወዲ እደዊሁ ላዕለ ርእሰ ላሕም፣ ወይጠብሖ ለውእቱ ላሕም ቅድመ እግዚአብሔር።

ያንንም በሬ በእግዚአብሔር ፊት ወደ ደብተራ ኦሪት ያምጣው እጁንም በላሙ ራስ ላይ ያኑር ያንንም በሬ በእግዚአብሔር ፊት ይሠዋው። ምዕ ፩ ፭።

፭ ወይነሥእ ካህን ዘቅቡዕ ወፍጹም በእዴሁ እምደሙ ለውእቱ ላሕም፣ ወያበውእ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል።

ተቀብቶ የተሾመውም ካህን የበሬውን ደም በእጁ ተቀብሎ ወደ ደብተራ ኦሪት ያግባው። ዕብ፣ ፲፱ ፬።

፮ ወይጠምዕ አጻብዒሁ ውስተ ደሙ ወይነዝኅ እምውእቱ ደም ስብዕ ቅድመ እግዚአብሔር ላዕለ መንጦላዕተ ቅድሳት።

ካህኑም ጣቱን በደሙ እየጠለቀ ከዚሁ ደም በእግዚአብሔር ፊት በቅድስተ ቅዱሳን መጋረጃ ላይ ሰባት ጊዜ ይርጨው። ኢሳ ፶፫ ፲፱፣ ሮሜ ፫ ፳፭።

፯ ወይወዲ ካህን እምደሙ ለውእቱ ላሕም ላዕለ አቅርንተ ምሥዋዕ ዘዕጣን፣ ዘይወድዩ ቅድመ እግዚአብሔር ዘሀሎ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል።

ካህኑም ከዚህ ከበሬው ደም በደብተራ ኦሪት ውስጥ በላው በእግዚአብሔር ፊት ዕጣን በሚያጥኑበት በዕጣኑ ምሥዋዕ ቀንዶች ያድርግ፣ (ይቅባው ይርጨው)።

፰ ወይክዑ ኵሉ ደሞ ኀበ መንበሩ ለምሥዋዕ ዘቍርባን ዘኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል።

በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ባለው ስቡን በሚየጤሱበት መሠውያ እግር ላይ ደሙን ሁሉ ያፍስሰው።

፱ ወኵሉ ስብሐ ለውእቱ ላሕም ዘበእንተ ኀጢአት ያሴስል ወእምስብሕ ዘይገለብብ ንዋየ ውስጡ ወኵሉ ስብሐ ዘውስተ አማዑቱ።

ስለ ኃጢአት የተሠዋውን የዚህን በሬ ስቡን ሁሉ ይለየው፣ ሆድ ዕቃውን ከሚሸፍነው ስብ (ሞራ) ጀምሮ በአንጀቱ ላይ ያለውን ስብ ሁሉ።

፲ ወክልኤሆን ኵልያቲሁ ወስብሐ ዘላዕሌሆን ወዘጸራዊቱ ወከብዶ እንተ ትንእስ ምስለ ኵልያቲሁ ይመትር።

ሁለት ኵላሊቶቹን በጭቅናው በሰብራደው ያለውን ከሁለቱ ኵላሊቱ ጋር ግልገል ኵላሊቱን (ሐሞቱ) ለምለም ጉበቱን ፈቅቶ ይለየው።

፲፩ በከመ ያወጽኡ ዘላሕመ መድኀኒት፣ ወይወድዮ ካህን ላዕለ ምሥዋዕ ዘቍርባን፣ ወማእሰኒ ለውእቱ ላሕም ወኵሎ ሥጋሁ ምስለ ርእሱ፣ ወምስለ ሰኰናሁ፣ ወከርሦ፣ ወከዕሴሁ።

የመሥዋዕተ መድኃኒቱን ስቡን እንዲለዩ፣ ከመሥዋዕተ ኃጢአቱም ስቡን ያምጡ፣ ካህኑም ቍርባኑን በሚያቀርቡበት በመሠውያው ውስጥ ለይቶ ያኑረው፣ የላሙንም ቈርበቱንና ሥጋውንም ሁሉ ከራሱና ከሰኰናዎቹም ጋር ቀፈቱን (ፈርሱን) ከሰንበሩ ጋር ያቃጥለው።

፲፪ ወይወስዱ አፍአ እምትዕይንት ውስተ መካን ንጹሕ ኀበ ይክዕዉ ሐመደ ወያውዕይዎ ላዕለ ዕፀው በእሳት ውስተ ምክዓወ ሐመድ።

ይህን ሁሉ ከከተማ በአፍአ አውጥተው አመዱን ከሚያፈሱበት ከንጹሕ በታ ያፍሱት፣ ሕመቱን ከሚያፈሱበት በታ ወስደው ዕንጨት ረብርበው በእሳት ያቃጥሉት።

፲፫ ወእመሰ ለኵሉ ተዓይን ዘደቂቀ እስራኤል ተስሕቶሙ ወተረስዐት እምአዕይንቲሆሙ ቃል ለተዓይን ወገብሩ እምኵሉ ትእዛዙ ለእግዚአብሔር ዘኢይከውን ለገቢር።

ከእስራኤል ልጆች ማኅበር ሁሉ ቢሳታቸው ግን ከዓይናቸው አንድ ቃል ቢዘነጋባቸው እግዚአብሔር ካዘዘው ትእዛዝ ሁሉ ወጥተው ሊሠሩት የማይገባውን ቢሠሩ።

፲፬ ወእምገዝ ነስሑ ወተዓውቀቶሙ ኃጢአቶሙ እንተ አበሱ ያመጽኡ ትዕይንቶሙ ላሕመ እምአልሕምት ንጹሐ በእንተ ኃጢአቶሙ ወያመጽእዎ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ።

ከዚህ በኋላ ቢመለሱ (ንስሐ ቢገቡ) የሠሩዋት ኃጢአታቸው ብትታወቃቸው የእስራኤል ማኅበር ስለ ኃጢአታቸው ከላሞች ንጹሕ የሆነውን አምጥተው ወደ ደብተራ ኦሪት ያቅርቡት ። ዘፀ፡ ፳፱ ፴ ።

፲፭ ወይወድዩ ሊቃናተ ይእቲ ትዕይንት ላዕለ ርእሱ ለውእቱ ላሕም እደዊሆሙ በቅድመ እግዚአብሔር ወይጠብሕዎ ለውእቱ ላሕም ቅድመ እግዚአብሔር ።

የዚች ጉባኤ ሽማግሌዎችም በእግዚአብሔር ፊት በዚህ በበሬው ራስ ላይ እጆቻቸውን ያኑሩ (ይጫኑ) ያንንም በሬ በእግዚአብሔር ፊት ይረዱት ። ዘፀ፡ ፳፱ ፲ ።

፲፮ ወያበውእ ካህን ዘቅቡዕ እምደሙ ለውእቱ ላሕም ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ።

ተቀብቶ የተሾመውም ካህን የበሬውን ደም ተቀብሎ ወደ ደብተራ ኦሪት ያግባው ።

፲፯ ወይጠምዕ አጽብዒሁ ካህን ውስተ ውእቱ ደም ፡ ወይነዝኅ ሰብዐ በቅድመ እግዚአብሔር ቅድመ መንጦላዕተ ቅድሳት ።

ካህኑ ጣቱን ከዚያው ደም እየጠለቀ በእግዚአብሔር ፊት በቅድስተ ቅዱሳን መጋረጃ ላይ ሰባት ጊዜ ይርጨው ።

፲፰ ወይወዲ እምደሙ ካህን ላዕለ አቅርንተ ምሥዋዕ ቅድመ እግዚአብሔር ዘውስተ ደብተራ ዘመርጡል ፡ ወኵሎ ደሞ ይክዑ ኀበ መንበረ ምሥዋዕ ዘቍርባን ዘሀሎ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ።

ካህኑም ከደሙ ዘግኖ በደብተራ ኦሪት አድሮ ባለው በእግዚአብሔር ፊት ያለውን የመሠውያውን ቀንዶች ይቀባ ፡ ደሙንም ሁሉ በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ባለው ስቡን በሚያጤሱበት በመሠውያው እግር ላይ ያፍስሰው ።

፲፱ ወኵሎ ስብሖ ያሴስል እምኔሁ ወይወድዮ ላዕለ ምሥዋዕ ።

ስቡንም ሁሉ ከርሱ ለይቶ በመሠውያው ያቃጥለው (ያጢሰው) ። ኢሳ፡ ፶፫ ፯ ፡ ማቴ፡ ፳ ፲፯ ።

፳ ወይገብሮ ለውእቱ ላሕም በከመ ይገብርዎ ለላሕም ዘኃጢአት ወያስተሠሪ ሎሙ ካህን ወይትኃደግ ሎሙ ።

ስለ ኃጢአት መሥዋዕት በታረደው በሬ ላይ እንዳደረጉት እንደዚሁ ያድርጉበት ፡ ካህኑም ኃጢአታቸውን ያስተሠርይላቸው ፡ ይሠረይላቸዋልም ። ዘኍ፡ ፲፭ ፳፭ ።

፳፩ ወይወስድዎ ለውእቱ ላሕም አፍአ እምትዕይንት ወያውዕይዎ በከመ ያውዕይዎ ለቀዳማዊ ላሕም ዘኃጢአት እስመ ዘኃጢአተ ትዕይንት ውእቱ ።

(ለሊቀ ካህናቱ) የተሠዋው የፊተኛውን በሬ ሥጋውንና ቁርበቱን ከከተማው አፍአ አውጥተው እንዳቃጠሉት ይህንንም የሕዝቡን መሥዋዕተ ኃጢአት የሆነ ላህም በእሳት ያቃጥሉት ፡ የሕዝቡ ኃጢአት መሥዋዕት ነውና ።

፳፪ ወአመሰ መኰንን አበሰ ወገብረ አሐተ እምኵሉ ትእዛዘ እግዚአብሔር አምላኮሙ ዘኢይከውን ለገቢር በኢያእምሮ ወነስሐ ወተዐውቀቶ ኃጢአቱ እንተ አበሰ ባቲ ያመጽእ ቍርባኖ ሐርጌ እምአጣሊ ንጹሐ ።

የተሾመው አገረ ገዢው ቢበድል ከፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ትእዛዝ ሁሉ ወጥቶ ሊሠሩዋት የማይገባ አንዲት ኃጢአት ሳይታወቀው ቢሠራ ፡ የሠራት ኃጢአቱ ተረድታው ቢመለስ (ንስሐ ቢገባ) ከፍየል ወገን ነውር የሌለበትን ንጹሕ ሙክት ለቍርባኑ ያምጣ ።

፳፫ ወይወዲ እዴሁ ላዕለ ርእሱ ለውእቱ ሐርጌ ወይጠብሕዎ ውስተ መካን ኀበ ይጠብሑ ዘይሠውዑ ቅድመ እግዚአብሔር እስመ ዘኃጢአት ውእቱ ።

እጁንም በፍየሉ ሙክት ራስ ላይ ያኑር ፡ ስለ ኃጢአት የሚቀርብ ነውና ለእግዚአብሔር ከሚያጤሱበት በታ ይሠዉት ።

፳፬ ወይወዲ ካህን እምደም ዘበእንተ ኃጢአት በአጽብዒሁ ላዕለ አቅርንተ ምሥዋዕ ዘዕጣን ።

ካህኑም ከኃጢአቱ መሥዋዕት በጣቱ ወስዶ ዕጣኑን በሚያጤሱበት በአቅርንተ ምሥዋዑ በታች ያድርገው ።

፳፭ ወኵሎ ደሞ ይክዑ ላዕለ መንበረ ምሥዋዕ ዘቍርባን ።

የቀረውን ደም ሁሉ ግን ቍርባን ከሚያቀርቡበት ከእግረ ምሥዋዑ በታች ያፍስሰው ። ቍ፡ ፳ ።

፳፮ ወኵሎ ስብሐ ይወዲ ላዕለ ምሥዋዕ በከመ ስብሐ መሥዋዕት ዘመድኃኒት ፡ ወያስተሠሪ ሎቱ ካህን ወይትኃደግ ሎቱ ኃጢአቱ ።

ስቡንም ሁሉ እንደ መሥዋዕተ መድኃኒቱ ስብ በመሠውያው ላይ ያቃጥለው ፡ ካህኑም እንዲህ አድርጎ ያስተሥርይለት ፡ ኃጢአቱም ይሠረይለታል ። ዘኍ፡ ፲፭ ፳፰ ።

፳፯ ወአመሰ አሐዱ ብእሲ አበሰ እምሕዝበ ምድር በኢያእምሮ ወገብረ አሐተ እምትእዛዘ እግዚአብሔር ዘኢይከውን ለገቢር ፡ ወነስሐ ወተዐውቀቶ ኃጢአቱ እንተ ገብረ ያመጽእ ጠሊተ እምአጣሊ አንስተ ንጽሕተ በእንተ ኃጢአቱ ዘገብረ ።

በአገሩ ካሉት ሕዝብ አንድ ሰው ሳያውቅ ቢበድል ፡ ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ወጥቶ ሊሠሩዋት የማትገባውን አንዲቱን ኃጢአት ቢሠራ ፡ ከዚህ በኋላ ቢጸጸትና የሠራት ኃጢአቱ ብትታወቀው ከፍየል ወገን ነውር የሌለበትን እንስት ፍየል ስለ ሠራት ኃጢአቱ መሥዋዕት ያምጣ ።

፳፰ ወይወዲ እዴሁ ላዕለ ርእሰ ዘአምጽአ በእንተ ኃጢአቱ ወይጠብሕዋ ለይእቲ ጠሊት ዘበእንተ ኃጢአት ውስተ መካን ኀበ ይጠብሑ ዘመሥዋዕት ።

ስለ ኃጢአቱ ያመጣት ሰው በመጣት እንስት ፍየል ራስ ላይ እጁን ያኑር ስለ ኃጢአት ያቀረቢትንም ፍየል መሥዋዕተ ኃጢአቱን ከሚያጤሱበት በታ ይረዷት ።

፳፱ ወይነሥእ ካህን እምደማ በአፃብዒሁ ወይወዲ ላዕለ አቅርንተ ምሥዋዕ ዘዕጣን ፡ ወኵሎ ደማ ይክዑ ላዕለ መንበረ ምሥዋዕ ዘቍርባን ።

ካህኑም ከደምዋ በጣቱ እየጠለቀ ዕጣኑን ከሚያጤሱበት ከአቅርንተ ምሥዋዑ ውስጥ ይጨምረው ፣ የቀረውንም ደሟ ሁሉ ቍርባኑ ከሚያቀርቡበት ከእግረ ምሥዋዑ በታች ያፍሰው ።

፴ ወይመትር ኵሎ ስብሐ በከመ ይመትሩ ስብሐ ዘበእንተ መድኀኒት ።

የመሥዋዕተ መድኀኒቱን ስብ እንዲለዩ ፣ ስቧንም ሁሉ ለይቶ ያጢሰው ። ዘኍ፣ ፲፩ ፳፰ ።

፴፩ ወይወዲ ካህን ላዕለ ምሥዋዕ ለመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ፡ ወያስተሠሪ ሎቱ ካህን ወትትኀደግ ሎቱ ኃጢአቱ ።

ካህኑም ለእግዚአብሔር በጎ መዓዛ አድርጎ በምሥዋዑ ላይ ያኑረው ፣ ካህኑ እንዲህ አድርጎ ኃጢአቱን ያስተሠርይለታል ፣ ኃጢአቱም ይሠረይለታል ።

፴፪ ወእመሰ በግዐ አምጽአ ቍርባኖ በእንተ ኃጢአቱ አንስተ ንጽሕተ ያመጽእ ።

ስለ ኃጢአቱ የሚያቀርበው በግ ቢሆን ግን ነውር የሌለበትን እንስት በግ ያምጣ ። ቍ፣ ፳፰ ።

፴፫ ወይወዲ እዴሁ ላዕለ ርእሳ ዘበእንተ ኃጢአቱ ወይጠብሕዋ ውስተ መካን ኀበ ይጠብሑ ዘይሠውዑ ።

ስለ ኃጢአቱ በቀረበችም በግ ራስ ላይ እጁን ያኑር ፣ መሥዋዕቱን ከሚያቀርቡበት በታም ይረዱዋት ።

፴፬ ወይነሥእ ካህን እምደማ በአፃብዒሁ ወይወዲ ላዕለ አቅርንተ ምሥዋዕ ዘዕጣን ፣ ወይክዑ ኵሎ ደማ ኀበ መንበረ ምሥዋዕ ዘቍርባን ።

ካህኑም ከደሟ በጣቱ ዘግኖ ዕጣን ከሚያጤሱበት ከአቅርንተ ምሥዋዑ ውስጥ ይጨምረው ፣ ደሟንም ሁሉ በቍርባኑ መሠውያ እግር ይርጨው ። ቍ፣ ፴ ።

፴፭ ወይመትሩ ኵሎ ስብሐ በከመ ይመትሩ ስብሐ በግዕ ዘመሥዋዕተ መድኀኒት ወይወድዮ ላዕለ ምሥዋዐ ቍርባን ለእግዚአብሔር ፡ ወያስተሠሪ ካህን በእንተ ኃጢአቱ ወይትኀደግ ሎቱ ።

ስለ መሥዋዕተ መድኀኒት የተሠዋው የበጉን ስብ እንዲለዩ ስቡን ለይቶ ደሙን ለእግዚአብሔር ቍርባን ከሚያቀርቡበት ከምሥዋዑ እግር ያፍሰው ፡ ካህኑም ኃጢአቱን ያስተሥርይለት ፣ ይሠረይለታልም ።

## ምዕራፍ ፭ ።

፩ ወእመሰ አሐዱ ብእሲ አበሰ ዘሰምዐ ከነ ወሰምዐ ቃለ ወእምሐልዎ ወየአምር ወርእየ ለእመ ኢያይድዐ ኃጢአተ ይከውኖ ።

አንድ ሰው ምስክር የሚሆንበትን ቃል ሰምቶ ቢያምሉት አይቶ እያወቀ ባይናገር ዕዳ በደል ይሆንበታል ።

፪ ወእመቦ ብእሲ ዘገሠሠ እምኵሉ ርኵስ አው ምውተ ፣ አው ብላዐ አርዌ ዘኢኮነ ንጹሐ ፣ አው በድነ እንስሳ ርኩስ ፣ አው በድነ ዘይትሐወስ ርኩስ ወዘአልዓለ እምኔሁ ርኩስ ውእቱ ።

ከረከሰ ነገር ሁሉ የዳሠሠ ሰው ወይም የሞተውን ውዳቂ ወይም ንጹሕ ያይደለ አውሬ የነከሰውን ወይም የረከሰ የከብት ወደቃ ወይም በደማዊት ነፍስ የሚንቀሳቀስ ሰውን ወደቃ ቢነካ ቢያነሣውም በደል ይሆንበታል ።

፫ አው ዘገሠሠ እምርኵሰ ሰብእ ፣ ወእምኵሉ ርኩስ ወዘአልዓለ እምኔሁ ይረኵስ ፣ እመኒ እንዘ ኢየአምር ፣ ወእምዝ ተዓውቀ ወነስሐ ።

ወይም ከሰው ርኵሰት ወገን ቢዳስስ ቢነካ ፣ ርኩስ ይሆናል ፡ ሳያውቅም ቢነካና ከዚህ በኋላ ቢታወቀው ከኃጢአቱ ቢመለስ (ቢጠጠት) ።

፬ ወእመኒ ብእሲ መሐለ ወነበበ በከናፍሪሁ ለገቢረ እኩይ ፣ አው ለገቢረ ሠናይ በእንተ ኵሉ እምከመ መሐለ እንዘ ኢየአምር ወእምዝ ተዓውቀ ዘአበሰ በአሐዱ እምዝንቱ ።

ማናቸውም ሰው በጎውንም ክፉውንም ለማድረግ በአንደበቱ ተናግሮ ቢምል ስለ ሁሉም ነገር ሳያውቅ ቢምል ከዚህ በኋላ በደሉ ቢታወቀው ከዚህ በአንዱ በደለኛ ሆነ ።

፭ ወአይድዐ ኃጢአቶ ዘአበሰ በቲ ያመጽእ ለእግዚአብሔር በእንተ ኃጢአቱ ዘአበሰ በግዕተ ንጽሕተ እምአባግዕ ፣ አው ጠሊተ እምአጣሊ ወያስተሠሪ ሎቱ ካህን በእንተ ኃጢአቱ ዘአበሰ ወይትኃደግ ሎቱ ።

የበደለበት ኃጢአቱን ቢናገር (ቢናዘዝ) ስለ ሠራው ኃጢአት ከበጎች ወገን ነውር የሌለበትን እንስት በግ ወይም ከፍየሎች ወገን እንስት ፍየል ለእግዚአብሔር ያምጣ ፣ ካህኑም ስለ ኃጢአቱ ያስተሠርይለታል ኃጢአቱም ይሠረይለታል ።

፮ ወእመሰ አልቦ ውስተ እዴሁ ወኢየአክል ለሢጠ በግዕ ያመጽእ ክልኤተ ማዕነቀ አው ክልኤተ እጐለ ርግብ ለእግዚአብሔር ፡ አሐዱ በእንተ ኃጢአቱ ፡ ወአሐዱ ለመሥዋዕት ።

በግ ፍየል ባይኖረው ወይም ለበግ ለፍየል መግዣ ገንዘብ ባይኖረው ስለ በደለው በደል ፣ ስለ ሠራው ኃጢአት ሁለት ዋኖሶች ወይም ሁለት የርግብ ግልገሎች አንዱን ስለ ኃጢአቱ ፣ አንዱን ለሚቃጠል መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ያቅርብ ።

፯ ወያመጽእ ኀበ ካህን ወይቀውም ወየሐርዶ ካህን ከማሁ ወኢያወቅዮ ርእሶ ።

ያመጣውም ሰው ወደ ካህን ያቅርበው ፣ ካህኑም አስቀድሞ ስለ ኃጢአቱ አቅርቦ አንገቱን አርዶ ይሠዋው ፣ ጨርሶ ግን አይቍረጠው ።

፰ ወይነዝኅ ደሞ ውስተ አረፍተ ምሥዋዕ፡ ወዘተርፈ ደሞ ያንጸፈጽፍ ላዕለ መንበረ ምሥዋዕ፡ እስመ ዘበእንተ ኃጢአት ውእቱ።

ስለ ኃጢአቱ የቀረበውን የመሥዋዕተ ኃጢአቱን ደም የመሠውያውን ግድግዳ ይርጨው፤ የተረፈውንም ደም ከምሥዋዑ እግር ያንጠፍጥፈው ስለ ኃጢአት የተሠዋ ነውና።

፱ ወለካልኡኒ ይገብሮ መሥዋዕተ በከመ ሕጉ ወያስተሥሪ ሎቱ ካህን በእንተ ኃጢአቱ እንተ አበሰ ወይትኃደግ ሎቱ።

ሁለተኛውንም እንደ ሕጉ (እንደ ወጉ) መሥዋዕት አሥምሮ (አድርጎ) ይሠዋው፤ ካህኑ ስለ ሠራው ኃጢአቱ ያስተሠርይለታል፤ ኃጢአቱም ይሠረይለታል።

፲ ወእመሰ አልቦ ውስተ እዴሁ ዘየአክል ለዘውገ ማዕነቅ አው ለክልኤ እጕለ ርግብ ያመጽእ ቍርባኖ በእንተ ኃጢአቱ ሥንዳሌ ዐሥራተ እድ ዘመሥፈርተ ኢፍ።

በእጁ ያለው ገንዘብ ለሁለት ርግብ፤ ለሁለት ዋኖስ ዋጋ ባይበቃው ግን ስለ ኃጢአቱ ቍርባኑን የኢፍ መሥፈሪያ ዓሥረኛ እጅ ልጦ ጕርዶ የወጣለትን የሥንዴ ዱቄት ያምጣ።

፲፩ ወኢይወዲ ውስቴቱ ቅብዐ ወስኂነ፡ እስመ ዘበእንተ ኃጢአት ውእቱ።

ዘይት ቅቤ አያፍስበት፤ ዕጣንም አይጨምርበት፤ ስለ ኃጢአት የቀረበ መሥዋዕት ነውና።

፲፪ ወያመጽእ ኀበ ካህን ወይዘግን እምኔሁ ካህን ምልአ ሕፍኑ በእንተ ተዝካሩ ወይወድዮ ላዕለ ምሥዋዕ በላዕለ ቍርባኑ ለእግዚአብሔር እስመ ዘኃጢአት ውእቱ።

ያቀረበውም ሰው ወደ ካህኑ ያምጣው፤ ካህኑም መታሰቢያ ሊሆን ከቀረበው (ከዳበው ቈርሶ ከቆሎው) እፍኝ ሙሉ ዘግኖ ለእግዚአብሔር ቍርባን ከሚቀርብበት ከምሥዋዑ ላይ ያጢሰው ስለ ኃጢአት የተሠዋ ነውና።

፲፫ ወያስተሥሪ ሎቱ ካህን በእንተ ኃጢአቱ እንተ አበሰ በአሐዱ እምእሉ፡ ወይትኃደግ ሎቱ፡ ወዘተርፈ ይከውን ለካህን ከመ መሥዋዕተ ሥንዳሌ።

ካህኑም ከሊህ በአንዱ (በሥንዴው በበጉ በፍየሉም) ቢሆን ስለ ሠራው ኃጢአት ያስተሠርይለታል፤ ኃጢአቱም ይሠረይለታል ጢስለት የቀረውም እንደ ሥንዴው መሥዋዕት ለካህኑ ይሁን።

፲፬ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፡ ብእሲ ለእመ ረስዐ ወአበሰ በኢያእምሮ ላዕለ ቅድሳተ እግዚአብሔር ያመጽእ በእንተ ኃጢአቱ ወንስሓሁ ለእግዚአብሔር ሐርጌ ንጹሐ እምአባግዕ፡ ዘሤጡ ሰቅሎን ብሩር በሰቅለ ቅዱስ በእንተ ዘንስሐ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፤ አንድ ሰው ሕግን መዘንጋትን ቢዘነጋ ሳያውቅም ለእግዚአብሔር በተለየው ላይ ቢበድል ስለ ጠጠቱና ስለ ንስሐው ከበጎች ወገን ነውር የሌለበትን በተለየ አዋቂ የተመዘነ ዋጋው ምስት ብር የሆነ የበግ አውራ ለእግዚአብሔር ያቅርብ።

፲፭ ወይፈዲ በዘአበሰ ላዕለ ቅድሳት ወይዌስክ ላዕሌሁ ኃምስተ እዴሁ፡ ወይሁብ ለካህን ወያስተሥሪ ሎቱ በውእቱ ሐርጌ ዘንስሓሁ፡ ወይትኃደግ ሎቱ ኃጢአቱ።

በተቀደሰው ላይ በበደለው በደል ዓይነቱን ይክፈል፤ ዳግመኛ በዚያው ላይ (በዓይነቱ ላይ) አምስት እጅ ይጨምር፤ የሚከፍለውም ሰው ለካህኑ ይስጠው ካህኑም ተጸጽቶ ስለ ኃጢአቱ በቀረበው አውራ በግ ምክንያት ኃጢአቱን ያስተሠርይለታል፤ ኃጢአቱም ይሠረይለታል።

፲፮ ወብእሲ እመ አበሰ ወገብረ አሐተ እምትእዛዘ እግዚአብሔር ዘኢይከውን ለገቢር በኢያእምሮ ወተዐውቀ ወነስሐ በእንተ ዘከነቶ ኃጢአት።

ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ወጥቶ ቢበድል በለማወቅም ሊሠሩዋት የማትገባውን አንዲት ኃጢአት ቢሠራ ስለ ሠራት ኃጢአትም አውቆ ተጠጥቶ ቢመለስ።

፲፯ ያመጽእ ሐርጌ እምአባግዕ ንጹሐ ዘሤጡ ሰቅሎን ብሩር በእንተ ንስሓሁ ኀበ ካህን።

ከበጎቹ ወገን ዋጋው ወቄት የሆነ ነውር የሌለበትን አውራ በግ ወደ ካህኑ ያቅርብ። መዝ፡ ፲፱ ፲፪።

፲፰ ወያስተሥሪ ሎቱ ካህን በእንተ ረሲዖቱ ዘረስዐ ወበእንተ ዘኢያእመረ ወይትኃደግ ኃጢአቱ፡ እስመ ንስሐ ቅድመ እግዚአብሔር።

ካህኑም ሳያውቅ ስለ ሳተው ስሕተት ያስተሠርይለታል ኃጢአቱም ይሠረይለታል፤ በእግዚአብሔር ፊት ንስሐ ገብቶአልና።

ምዕራፍ ፮።

ምዕራፍ ፮።

፩ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፡ ብእሲ ለእመ አበሰ ወአስተተ ወተኀየየ ትእዛዘ እግዚአብሔር ወሐሰዎ ለካልኡ በዘአማኅፀኖ፡ አው በዘተሰተሮ፡ አው በዘሄዶ፡ አው ዘዐመፆ ለካልኡ።

እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው እንዲህም አለው፤ አንድ ሰው ቢበድል የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ቸል ብሎ ቢስት አደራ የሰጠው ባልንጀራውን ቢክደው ወይም በአሽሙር ንግድ የሰጠውን ቢክድ ወይም ቢቀማው፤ ወይም ባልንጀራውን ግፍ የሠራበት ሰው ቢኖር።

፪ አው እመ ረከበ ዘገደፉ ወሐሰወ በእንቲአሆሙ ወመሐለ በዐመፃ በአሐዱ እምእሉ ዘይገብር ሰብእ ዘኢይከውን ለገቢር ወለአብሶ በሙ።

ወይም የጣሉትን አግኝቶ ያነን ሸሽጎ አሌ ቢል (ቢክድ) ወድቆ ያገኘውን ጠፍቶ ያገኘውን ሸሽጎ በሐሰት ቢም

ል ሰው ከሚሠራው ሊበድልባቸው ከማይገባው ከዚህ
ኃጢአት ሁሉ አንዱን የሠራ ሰው ቢኖር ።

፫ ወእምከመ አበሰ ወእምዝ ነስሐ ወአግብአ ዘነሥአ ወሄ
ደ ፡ አው ዘዓመፀ ወገፍዐ ፡ አው ማኅፀነ ዘአማኅፀኖ ካልኡ
አው ዘረከበ ዘገደፉ ።

ከበደለ ኃጢአት ከሠራ በኋላ (ከማለ በኋላ) ቢመልስ
ቀምቶ የወሰደውንም ቢመልስ ወይም በግፍ የወሰደበትን
ያታለለውን አሌ ያለውን ቢመልስ ወይም አደራ የሰጠውን
ሰው አሌ ብሎት ከማለ በኋላ ተጸጽቶ ቢመልስ ወይም
የጣሉትን አግኝቶ የወደቀውን አንሥቶ አሌ ብሎ ከማለ
በኋላ ተጠጥቶ ቢመለስ ።

፬ እምኵሉ ዘመሐለ በእንቲአሁ በዓመፃ ወአግብአ ርእሰ
ንዋዩ ይወስክ ኀምስተ እዴሁ ላዕሌሁ ፡ ወያገብእ ለበዓለ
ንዋይ በዕለተ ዘለፍዎ ።

ገንዘቡን ሽሽጎ በሐሰት ከማለበት ገንዘብ ሁሉ በኋላ
ተጠጥቶ ዓይነቱን (ራስ ማሉን) ቢመልስ ዳግመኛ በዓይ
ነቱ ላይ አምስት እጅ ይጨምር ፡ ምስክሮች ከመሰከሩበት
ዳኞች ከፈረዱበት በኋላ አምስት እጅ ጨምሮ ለባለ ገን
ዘቡ ይመልስ ፡ ምዕ፡ ፭ ፲፮ ፡ ዘኍ፡ ፭ ፮ ።

፭ ወያመጽእ በእንተ ንስሐሁ ለእግዚአብሔር በግዐ እም
አባግዕ ንጹሐ ዘሤጠ ሰቅሎን ብሩር ።

እግዚአብሔርን ስለ በደለበት በደል ከበጎች መንጋ
ዋጋ ወቄት የሆነውን ንጹሕ በግ ያቅርብ ። ዘፀ፡ ፲፪ ፭ ።

፮ ወያስተሠሪ ሎቱ ካህን ቅድመ እግዚአብሔር ወይት
ኃደግ ሎቱ በበይነ አሐዱ እምእሉ ዘገብረ ወነስሐ በእ
ንቲአሁ ።

ካህኑ በእግዚአብሔር ፊት ያስተሥርይለት ከሠራው
በደል ሁሉ ኣላበጀሁም ብሎ ከተመለሰበት በአንዱ በመ
ሥዋዕተ ንስሐው ይሠረይለታል ።

፯ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ አዝዞሙ ለአ
ሮን ወለደቂቁ ።

እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው እንዲህም አለው ፤
አሮንንና ልጆቹን እዘዛቸው ፡ እንዲህም በላቸው ።

፰ ወበሎሙ ከመዝ ውእቱ ሕጉ ለመሥዋዕት ውስተ
ምሥዋዕ ተኃድግዎ እስከ ይጸብሕ እንዘ ትነድድ እሳተ
ምሥዋዕ ላዕሌሁ ።

የሚጤሰው መሥዋዕት ሕጉ (ወጉ) እንዲህ ነው ፡ የም
ሥዋዑ እሳት በላዩ ላይ እየነደደ እስኪነጋ ድረስ ሌሊ
ቱን ሁሉ በመሠውያው ላይ ይተዉት ።

፱ ወይለብስ ካህን ልብሰ እኔ ወቃሰ ዘአኔ ላዕለ ሥጋሁ
ወያሴስል ውእተ ሐመደ ዘበልዓት እሳተ መሥዋዕት
እምውስተ ምሥዋዕ ወያነብሮ ቅሩበ ምሥዋዕ ።

ካህኑ በሰውነቱ ላይ የተልባ እግር ቀሚስ ይልበስ ፡
የተልባ እግር ሰናፊል ይታጠቅ ፡ የመሥዋዕቱ እሳት ከም
ሥዋዑ የበላችውን አመዱን ይጥረገው ፡ አንሥቶም ከም
ሥዋዑ አጠገብ ያኑረው ። ዘፀ፡ ፳፰ ፴፱ ፡ ሕዝ፡ ፵፬ ፲፯ ።

፲ ወያሴስል ውእተ አልባሲሁ ወይለብስ ልብሰ ወይወ
ስድ ሐመደ አፍአ እምትዕይንት ውስተ መካን ንጹሕ ።

ያን የለበሰውን ልብስ አውልቆ ሌላ ልብስ ይልበስ ፡
አመዱንም ከከተማው አፍአ አውጥቶ ከንጹሕ ቦታ
ያፍስሰው ።

፲፩ ወእሳትሰ ትነድድ ውስተ ምሥዋዕ በኵሉ ጊዜ ወኢ
ትጠፍእ ።

እሳቲቱ ግን በምሥዋዑ ላይ ሁል ጊዜ ትንደድ አት
ጥፋ ።

፲፪ ወያነድድ ዕፀወ በላዕሌሁ ካህን በበነግህ ፡ ወይዌጥሕ
ላዕሌሁ ዘመሥዋዕት ወይወዲ ውስቴቱ ልብሐ ዘመድኃኒት ።

ካህኑም ማለዳ ማለዳ በእሳቱ ላይ ዕንጨቱን ይረብ
ርብበት በዕንጨቱም ላይ የሚቃጠለውን መሥዋዕት ሥጋ
ያድርግበት በላዩም የመሥዋዕተ መድኃኒቱን ስብ ያቃጥል ።

፲፫ ዝንቱ ውእቱ ሕጉ ለመሥዋዕት ዘያበውኡ ደቂቀ
አሮን ውስተ ምሥዋዕ ቅድመ እግዚአብሔር ።

በእግዚአብሔር ፊት የአሮን ልጆች በምሥዋዑ የሚ
ያቀርቡት የመሥዋዕቱ ሕግ ሥራት ይህ ነው ።

፲፬ ወይነሥእ እምኔሁ በሕፍኑ እምሥንዳሌ ዘመሥዋዕት
ቅድመ እግዚአብሔር ምስለ ቅብኡ ወምስለ ስኂኑ ዘሀሎ
ውስተ መሥዋዕቱ ወይወድዮ ውስተ ምሥዋዕ ።

ካህኑም በእኽሉ መሥዋዕት ላይ ካለው ዕጣን ሁሉ ጋር
ከዘይቱም ጋር ልጠ ጉርዶ ከወጣለት ዱቄት እፍኝ ሙሉ
ዘግኖ በመሠውያው ላይ ያጤሰው (ያቃጥለው) ።

፲፭ እስመ ቍርባን ዝክሩ ለእግዚአብሔር ውእቱ ወመ
ዓዛ ሠናይ ።

እግዚአብሔር ወዶ የሚቀበለው ለመታሰቢያ የሚ
ቀርብ ቍርባን ነውና ። ምዕ፡ ፪ ፪ ።

፲፮ ወዘተርፈ እምኔሁ ይበልዑ አሮን ወደቂቁ ፡ ወናእተ
ይበልዕዎ በመካን ቅዱስ ውስተ ዓፀደ ደብተራ ዘመርጡል ።

ከሱ የቀረውን ግን አሮንና ልጆቹ ይብሉት ሲበሉትም
ቂጣ አድርገው በክቡር ቦታ በልዩ ሥፍራ በደብተራ
ኦሪት ባለው አደባባይ ሁነው ይብሉት ።

፲፯ ወኢያብኅዕዎ ለአብስሎ ክፍሎሙ ውእቱ ዝንቱ ወዘ
ወሀብክዎሙ እመሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር ቅዱስ ለቅ
ዱሳን ፡ ከመ ዘበእንተ ኃጢአት ወዘበእንተ ንስሐኒ ።

ዳቦ አድርገው ሊጋግሩት አያምጹት (አያብኩት) ሳይ
መጽ (ሳይቦካ) ይጋግሩት ፡ ለእግዚአብሔር ከቀረበው መሥ
ዋዕት ከፍዬ የሰጠኋቸው ይህ ዕድል ፈንታቸው ነው ፡
ከክበረ የከበረው ከክበሩ ለክበሩ (ካህናት) ነውና ከመሥ

ዋዕተ ኃጢአቱ ጢስአት የተረፈው ለካህን እንደሆነ ከመሥዋዕተ ንስሐም የተረፈው ለካህን ይሁን ።

፲፰ ኵሉ ተባዕት እምካህናት ይበልዖ ፡ ሕግ ውእቱ ዝንቱ ዘለዓለም ፡ በመዋዕሊክሙ ፡ ወእመሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር ኵሉ ዘገሠሠ ይትቄደስ ።

ከካህናት ወገን ወንዶች ልጆች ይብሉት በዘመናችሁ ሁሉ ይህ የዘለዓለም ሕግ ይሁን ለእግዚአብሔር ከቀረበው ጢስአት የተረፈውን የሚነካው (የሚዳስሰው) ሁሉ ይከብራል ። ዘፀ ፳፱ ፴፯ ፡ ምዕ ፳፪ ፫ ።

፲፱ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ ዝንቱ ውእቱ ዘጸገውክዎ ለአሮን ወለደቂቁ እምዘ ያመጽኡ ለእግዚአብሔር ፡ እምአመ ዕለተ ተቀብዐ ዓሥራተ እድ ዘመስፈርተ ኢፍ ሥንዳሌ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው ፤ ተቀብቶ ከተሾመበት ቀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር ከመጡት ለአሮንና ለልጆቹ የሰጠሁት ይህ ነው ፡ የመሥዋዕተ ኃጢአት የመሥዋዕተ ንስሐ ልኩ መጠኑ ከጥሩ ሥንዴ የኢፍ መሥፈርያ ዓሥረኛ እጅ ነው ። ምዕ ፭ ፲፩ ።

፳ መሥዋዕትሰ በዘኵሉ ጊዜ መንፈቃ ለነግህ ወመንፈቃ ለፍና ሠርክ ምስለ ቅብዕ በጤገን ይገብርዎ ።

በዘወትር የሚቀርበው መሥዋዕት ግን እኩሌታው ለነግህ እኩሌታው ለሠርክ ይሁን ከዘይት ከቅቤ ጋር ለውሰው በብረት ምጣድ ይጋግሩት በዘይት በቅቤ ለውሰው ያምጡት ።

፳፩ ወሰቢሰሙ ያመጽእዎ እስመ መሥዋዕተ ፍተት ውእቱ ወቍርባን ዘመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ።

የሚፈተት የሚቈረስ እንደ ሸና ያለ መሥዋዕት ነውና እግዚአብሔር ወዶ የሚቀበለው በእሳት የሚቃጠል (የሚጤስ) ቍርባን ነውና ።

፳፪ ካህን ዘቅቡዕ ህየንቴሁ እምደቂቁ ይገብሮ ሕግ ውእቱ ዘለዓለም ፡ ወበኵሉ ጊዜ ይትገበር ።

ከልጆቹም በአባቱ (በአሮን) ፈንታ ተተክቶ ደሙን ተቀብቶ የተሾመው ካህን እንደዚህ አድርጎ ያቅርበው ፡ (ይህም) የዘለዓለም ሕግ ሥርዓት ይሁን በየጊዜውም የሚጤስ የሚቃጠል ይሁን ። ዘፀ ፳፱ ፳፯ ፡ ኢሳ ፶፫ ፲ ።

፳፫ ወኵሉ መሥዋዕት ዘካህናት ይነድድ ኵሉ ጊዜ ወእልቦ ዘይትበላዕ እምኔሁ ።

ካህናቱ በየጊዜው የሚያቀርቡት መሥዋዕት ግን በየጊዜው ሁሉ ይቃጠል ፡ ከርሱም የሚበላ አይኑር ።

፳፬ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ንግሮሙ ለአሮን ወለደቂቁ ፡ ወበሎሙ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው ፤ ለአሮንና ለልጆቹ ንገራቸው ።

፳፭ ወከመዝ ውእቱ ሕጋ ለኃጢአት ውስተ መካን ኀበ ይጠብሑ ዘመሥዋዕት በህየ ይጠብሑ ዘበእንተ ኃጢአት በቅድመ እግዚአብሔር ወቅዱስ ለቅዱሳን ውእቱ ።

የመሥዋዕተ ኃጢአት ሕግ ሥርዓቷ እንዲህ ነው በላቸው የዘወትሩን መሥዋዕት በሚያርዱበት ቦታ መሥዋዕተ ኃጢአቱንም በዚያ በእግዚአብሔር ፊት ይረዱት ፡ (ያወራርዱት) ይህ የከበረ ለከበሩት (ካህናት) ነውና ።

፳፮ ካህን ዘይገብሮ ይበልዖ ወበመካን ቅዱስ ይበልዕዎ በኀበ ዐፀደ ደብተራ ዘመርጡል ።

የሠዋው ካህን ይብላው (ይቀበለው) በደብተራ ኦሪት በቅጽሩ አደባባይ በክቡር ቦታ ይብሉት ። ዘኍ ፲፰ ፱ ።

፳፯ ወኵሉ ዘገሠሦ ለውእቱ ሥጋ ይትቄደስ ፡ ወእመበ ኀበ ተነዝኀ እምደሙ ውስተ ልብስ ኀበ ተነዝኀ ላዕሌሁ የሐጽብዎ በመካን ቅዱስ ።

ይህንን ሥጋ የነካው (የዳሰሰው) ሁሉ ይከብራል ፡ ከደሙ የተረጨበት ቢኖር በልብሱ ላይ ቢረጭበት የተረጨበትን በክቡር ቦታ ይጠቡት ። ዘፀ ፳፱ ፴፯ ፡ ፴ ፳፱ ።

፳፰ ወለልሕኵትሰ ዘበቱ አብሰልዎ ይሰብርዎ ፡ ወእመሰ በንዋየ ብርት አብሰልዎ የሐበርትዎ ፡ ወየሐጽብዎ በማይ ።

የሚቀቅሉበትን ሸክላውን ይሰብሩት ፡ በብርት ዕቃ ቢቀቅሉት ግን ይፋቁት ፡ (ይወልውሉት ይሰንግሉት) በውኃ ይጠቡት (ይለቅልቁት) ።

፳፱ ኵሉ ተባዕት እምካህናት ይበልዖ ቅዱስ ለቅዱሳን ውእቱ ።

ከካህናቱ ወገን የሆነ ወንድ ሁሉ ይብላው የከበረ እርሱ ለከበሩ ይገባልና ። ዘፀ ፲፰ ፲ ፡ ፲፰ ፳፩ ።

፴ ወኵሉ ዘበእንተ ኃጢአት ዘያበውኡ እምደሙ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ያስተሠርዩ በቱ ውስተ ቅድስት ኢይትበላዕ በእሳት ያነድድዎ ።

በቅድስተ ቅዱሳን ያስተሠርዩበት ዘንድ ከደሙ ወደ ደብተራ ኦሪት የሚያገቡት መሥዋዕተ ኃጢአት ሁሉ አይበላም ፡ (አይበላ) በእሳት ይቃጠል ።

## ምዕራፍ ፯ ።

፩ ወከመዝ ውእቱ ሕጉ ለንስሐ ቅዱስ ውእቱ ለቅዱሳን ።

የመሥዋዕተ ንስሐ ሕጉ (ሥራቱ) እንደዚህ ነው ፡ ቅዱስ ለቅዱሳን ነው ።

፪ ውስተ መካን ኀበ ይጠብሑ ዘመሥዋዕት በህየ ይጠ

የዘወትሩን መሥዋዕት ከሚሠዉበት (ከሚያርዱበት)

ብሕም ለበግዕ ዘንስሓ ወይክዕዉ ደሞ ውስተ ዓውደ ምሥዋዕ ።

በታ የመሥዋዕተ ንስሐውም በግ በዚያ ይረዱት ያወራር ዱት ደሙንም ከመሠውያው እግር ዙርያ ያፍስሱት ።

፫ ወኵሎ ስብሐ ያመጽእ ወሐቋሁኒ ወስብሐኒ ዘይከድን ንዋየ ውሥጡ፥ ወስብሐ ዘውስተ አማዑቱ ።

ስቡንም ሁሉ ዳሌውን ሆድ ዕቃውን የሚሸፍነውን ሞራ ከአንጀቱ የሚገኘውንም ስብ ያቅርብ ።

፬ ወክልኤሆን ኵልያቲሁ ወስብሐ ዘላዕሌሆን ወዘላዕለ ጸሬሚቱ ወከብዶ እንተ ትንእስ ምስለ ኵልያቲሁ ይመትሮ ካህን ።

ሁለቱንም ኵላሊቶቹና በላያቸው ያለውን ስብ በጭቅ ናው ውስጥ ያለውን ስብ ግልገል ጉበቱን ከሁለቱ ኵላሊቶቹ ጋር ካህኑ ይለየው ። ምዕ ፫ ፬፣ ፬ ፰ ፱ ፳፬ ።

፭ ወይወድዮ ላዕለ ምሥዋዕ ቍርባን ውእቱ ዘመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ዘበእንተ ንስሓ ውእቱ ።

ካህኑም ስለ ንስሐ የቀረበውን መሥዋዕት በእሳት ያቃጥለው፥ እግዚአብሔር ወዶ የሚቀበለው ቍርባን ነውና።

፮ ኵሉ ተባዕት እምካህናት ይበልዖ በመካን ቅዱስ ወቅዱስ ውእቱ ለቅዱሳን ።

ከካህናት ወገን የሆነ ወንድ ሁሉ በተቀደሰ በታ ይብላው፥ የተቀደሰ ለቅዱሳን ነውና ። ቲቶ ፪ ፲፬ ።

፯ በከመ ዘበእንተ ኃጢአት፥ ከማሁ ዘበእንተ ንስሓሂ፥ ወእሐዱ ሕጎሙ ለካህን ዘያስተሠሪ በእንቲአሆሙ ሎቱ ውእቱ ።

ከመሥዋዕተ ኃጢአት ጢስለት የተረፈው ለካህን እንደሆነ ከመሥዋዕተ ንስሐ ጢስለት የተረፈውም እንዲሁ ለካህን ይሁን፥ (የመሥዋዕተ ኃጢአትና የመሥዋዕተ ንስሐ) ሕጋቸው አንድ ነው፥ ስለርሳቸው ኃጢአትን ለሚያስተሠርይ ካህን ይሁን ። ምዕ ፯ ፳፯ ።

፰ ወለካህን ዘያበውእ መሥዋዕተ ሰብእ ማእሰ መሥዋዕቱ ዘውእቱ ሦሀ ሎቱ ውእቱ ።

የማናቸውም ሰው መሥዋዕት ያቀረበው ካህን የሚቃጠለው መሥዋዕት ቍርበት ለዚያው ካህን ይሁን ።

፱ ወኵሉ መሥዋዕት ዘግቡር ለኵሉ ደቂቀ አሮን ዕሩይ ውእቱ ለለአሐዱ ።

በምግድ (በንዶ) የሚበስለው (የእኽል) መሥዋዕት ሁሉ በድስት በመቀሎ ወይም በብረት ምጣድ ላይ የሚበስለው መሥዋዕት ሁሉ የአሮን ልጆች ለያንዳንዱ ትክክል ይሁን ። ዘኍ ፲፰ ፱ ።

፲ ወከመዝ ውእቱ ሕገ መሥዋዕተ መድኃኒት ዘያመጽኡ ለእግዚአብሔር ።

ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት የመሥዋዕተ መድኃኒት ሕግ እንደዚህ ነው ።

፲፩ ወለእመ በእንተ አኰቴት አምጽአ ያመጽእ ውእተ መሥዋዕተ አኰቴት ኅብስተ ሥንዳሌ ዘግቡር በቅብዕ ወጸፊቅ ናእተ ዘሥንዳሌ ዘልዉስ በቅብዕ ።

ስለ መሥዋዕተ አኰቴት ከምስጋናው መሥዋዕት ጋር ቢያቀርበው በዘይት በቅቤ የታሸ የታበቀ ልመ ጉርዶ የወጣለት የሥንዴ ዳቦ ያምጣ፥ በዘይትም የተለወሰ መልክም የሥንዴ ዱቄት ያምጣ ። ዘኍ፥ ፮ ፲፭ ።

፲፪ ወምስለ ኅብስት ዘብሑእ ያመጽእ ቍርባኖ ለመሥዋዕተ አኰቴት ዘመድኃኒት ።

ለምስጋና የሚቀርበውን የደኅንነት መሥዋዕት ከቦካ ዳቦ ጋር ቍርባኑን ያምጣ ። አሞ፡ ፬ ፭ ።

፲፫ ወይወስድ እምኔሁ አሐደ እምኵሉ ቍርባኑ ሃብተ እግዚአብሔር ለካህን ዘይክዕዎ ለውእቱ ደመ አኰቴት ሎቱ ውእቱ፥ ወሥጋኒ ዘመሥዋዕተ አኰቴት ሎቱ ውእቱ።

ከሚቀርበው ቍርባን ሁሉ የእግዚአብሔርን ፈንቃ አንዱን ሙጀራ (ካህኑ) ይውሰድ፥ ጢስለት የቀረው ይህን የመሥዋዕተ አኰቴቱን ደም ለረጨው ለርሱ ለካህኑ ይሁን ከመሥዋዕተ አኰቴቱም የቀረው ሥጋ ለርሱ ይሁን ።

፲፬ ወበዕለተ ያመጽእዎ ይበልዕዎ ወኢይብ ዘያተርፉ ለነግሁ ።

(የመሥዋዕተ አኰቴቱን ሥጋ) በቀረቡበት ቀን ይብሉት፥ ለነገ ብለው ከርሱ የሚያስቀሩት የለም ።

፲፭ ወለእመሰ ዘበ ብፅዓት አው ዘበፈቃዱ ያበውእ ቍርባኖ በዕለተ አምጽአ መሥዋዕቶ ይበልዕዎ ወበሣኒታሂ ።

የስእለት ወይም የፈቃድ ቢሆን ግን ቍርባኑን ያምጣ ቍርባኑን በቀረበበት ቀን መሥዋዕቱን ይብሉት፥ የተረፈውንም በበነጋው ይብሉት ። ምዕ፥ ፲፱ ፯ ።

፲፮ ወለእመ ተርፈ እምሥጋ መሥዋዕቱ እስከ ሣልስት ዕለት በእሳት ያውዕይዎ ።

ከመሥዋዕተ ብፅዓት ከመሥዋዕተ ፈቃድ ሥጋ ግን እስከ ሦስት ቀን ድረስ የተረፈ ቢኖር በእሳት ያቃጥሉት።

፲፯ ወለእመሰ በልዑ እምውእቱ ሥጋ በሣልስት ዕለት ኢይትዌከፎ ለዘአብኦ ወኢይትኌለቆ እስመ ርኩስ ውእቱ ወነፍስ እንተ በልዓት እምኔሁ ይእቲ ትነሥእ ኃጢአታ ።

ከዚህ ከመሥዋዕተ ብፅዓቱ፥ ከመሥዋዕተ ፈቃዱ ሥጋ ተርፎ በሦስተኛው ቀን ቢበሉት ግን መሥዋዕቱን ላቀረበው ሰው አይቀበልለትም፥ ቍርባን ሆኖ አይቈጠርለትም ርኩስ (የተጠላ) ነውና፥ ሦስት ቀን ከደረው የበላች ሰውነት የዚያን (ያቀረበውን) ሰው ዕዳ ትቀበላለች ።

፲፰ ወሥጋኒ እምከመ ለከፎ እምኵሉ ርኩስ ኢይብልዕዎ አላ በእሳት ያውዕይዎ፥ ወኵሉ ንጹሕ ኢይብላዕ እምኔሁ ።

ከርኩስ ወገን ሁሉ የነካው እንደሆነ ሥጋውን በእሳት ያቃጥሉት እንጂ አይብሉት፥ ንጹሕ የሆነ ሁሉም ከዚያ ሥጋ አይብላ ። ምዕ፥ ፯ ፳፬ ።

፲፱ ወነፍስ እንተ በልዐት እምውእቱ ሥጋ ዘመሥዋዕተ መድኃኒት ዘእግዚአብሔር እንዘ ርኵሱ ላዕሌሁ ለትደምሰስ ይእቲ ነፍስ እምሕዝባ ።

ርኵሰቱ በርሱ ላይ ሳለ ለእግዚአብሔር ከቀረበው ከዚህ ከመሥዋዕተ እኩቴት ሥጋ የበላች ነፍስ ያች ሰውነት ከወገኖቿ ተለይታ ትጥፋ ። ምዕ ፲፭ ፫ ።

፳ ወነፍስኒ እንተ ገሠሠት እምኵሉ ርኩስ አው እምር ኩሰ ሰብእ ፤ አው ዘእንስሳ ዘኢኮነ ንጹሐ ወበልዐት እምውእቱ ሥጋ ዘመሥዋዕተ መድኃኒት ዘእግዚአብሔር ለትደምሰስ ይእቲ ነፍስ እምሕዝባ ።

ከማናቸውም ርኩስ ነገር ሁሉ የነካች ሰውነት ወይም ከሰው ርኵሰት ወገን ወይም ንጹሕ ያይደለውን የከብት ውዳቂ የነካች ነፍስ ለእግዚአብሔር ከቀረበው መሥዋዕተ እኩቴት ሥጋ ብትበላ ያች ሰውነት (ነፍስ) ከወገኖቿ ተለይታ ትጥፋ (ትሙት) ። ሕዝ፡ ፬ ፲፬ ፤ ምዕ፡ ፳፬ ፳፫ ።

፳፩ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው ፤ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው እንዲህም በላቸው ።

፳፪ ወበሎሙ ኵሉ ስብሐ ላሕም ወበግዕ ወጠሊ ኢትብልዑ ።

የላሙን ስብ ፤ የበጉንም ስብ ፤ የፍየሉንም ስብ ፤ ሁሉ አትብሉ ።

፳፫ መኵሉ ስብሐ ምዉት ወብላዕ አርዌ ለግብር ይኩን ኵሙ ፤ ወአንትሙሰ ብሕቱ ኢትብልዕዎ ።

የሞተውንም ከብት ሥጋ ስብ ፤ አውሬ የነከሰውንም ከብት ሥጋ ስብ ፡ ለማናቸውንም ተግባር ሁሉ ይሁናችሁ (አድርጉት) እናንተ ግን አትብሉት ።

፳፬ ወኵሉ ዘበልዐ ስብሐ እምዘያመጽኡ ለእግዚአብሔር መሥዋዕተ አመራዕይ ለትደምሰስ ይእቲ ነፍስ እምሕዝባ ።

ለእግዚአብሔር ከሚቀርበው መሥዋዕት ሥጋ ስቡን የበላ ሰው ሁሉ ያች የበላች ሰውነት ከወገኖቿ ተለይታ በሞት ትቀጣ ።

፳፭ ወኵሎ ደመ ኢትብልዑ በኵሉ በኀበ ሀሎክሙ ፤ ኢ ዘእንስሳ ወኢ ዘአዕዋፍ ።

በተቀመጣችሁበት ስፍራ ሁሉ (በላችሁበት ዘመን ሁሉ) ደም አትብሉ ፤ የከብትንም የወፎችንም ደም ቢሆን አትብሉ ። ዘፍ፡ ፱ ፬ ፤ ዘዳግ፡ ፲፪ ፲፯ ፤ ፩ ሳሙ፡ ፲፬ ፴፫ ።

፳፮ ወኵላ ነፍስ እንተ በልዐት ደመ ለትደምሰስ እምሕዝባ ።

ደምን የምትበላ ሰውነት ሁሉ ያች ነፍስ በወገኖቿ ማኸል በሞት ትቀጣ ። ሕዝ፡ ፵፬ ፯ ፤ ግብ፡ ሐዋ፡ ፲፭ ፳ ።

፳፯ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ፤ ወበሎሙ ዘያመጽእ መሥዋዕተ መድኃኒት ለእግዚአብሔር ያመጽእ ቍርበኖ በእደዊሁ ስብሐ ተላዕ ፤ ወከብዶ እንተ ትንእስ ቅድመ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ድኅነት የሚገኝበትን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር የሚያመጣ ሰው የፍሪምባውን ስብ ፤ ቍርበን አድርጎ በእጆቹ ያምጣ ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው ብሎ ሙሴ ነገረው ግልገል ጉበቱን በእግዚአብሔር ፊት ያምጣ ።

፳፰ ወይወድዮ ካህን ለስብሐ ተላዕ ላዕለ ምሥዋዕ ወተላውሰ ይኩን ለአሮን ወለደቂቁ ።

ካህኑም የፍሪምባውን ስብ በመሠውያው ላይ አድርጎ ያጤሰው ያቃጥለው ፍሪምባው ግን ለአሮንና ለልጆቹ ይሁን ። ምዕ፡ ፫ ፭ ፲፭ ።

፳፱ ወአገዳሁ ዘየማን እመሥዋዕተ መድኃኒትክሙ ይሁብ ሃብተ ለካህን ዘያበውእ ደመ መድኃኒቱ ።

መሥዋዕተ መድኃኒት አድርጋችሁ ከቀረባችሁት የቀኝ ወርቹን ፈንታውን የድኅነቱን ደም የሚያቀርብ ለካህን ይስጥ ። ዘኍ፡ ፯ ፳ ።

፴ ወሰብሐኒ ዘደቂቀ እስራኤል አገዳ ዘየማን ለአሮን ወለደቂቁ ክፍሎሙ ውእቱ ።

ከአሮን ልጆች ሁኖ የመሥዋዕተ መድኃኒቱን ደም ይዞ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ላገባው ስቡንም በምሥዋው ላይ ላጤሰው ካህን የቀኝ ወርቹ ዕድል ፈንታው ይሁን ።

፴፩ እስመ ተላዐ ወአገዳ ዘየማን ነሣእኩ እመሥዋዕተ መድኃኒቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ወወሀብክዎ ለአሮን ወለደቂቁ ይኩኖሙ ሕገ ዘለዓለም እምደቂቀ እስራኤል ።

የእስራኤል ልጆች ደኅንነታቸው ሊደረግበት ከቀረቡት መሥዋዕት ፍሪምባውንና የቀኝ ወርቹን ወስጄ ለአሮን ከርሱም በኋላ ለልጆቹ ሰጥቻቸው አለሁና ከእስራኤል ልጆች ተለይቶ የዘለዓለም ሕግ ይሁናቸው ።

፴፪ ዝንቱ ውእቱ ክፍሉ ለአሮን ወለደቂቁ እመሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር እምአመ ይትቀብዑ ይኩኑ ካህናተ ለእግዚአብሔር ።

ለእግዚአብሔር አገልጋዮች ይሆኑ ዘንድ ተቀብተው ከተሾሙበት ጊዜ ጀምሮ ለእግዚአብሔር ከሚቀርበው መሥዋዕት ከፍዬ ለአሮንና ለልጆቹ የሰጠኋቸው ዕድል ፈንታቸው ይህ ነው ። ዘኍ፡ ፲፰ ፲፰ ፤ ዘዳ፡ ፲፰ ፫ ።

፴፫ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር የሀብዎሙ እምአመ ቀብዕዎሙ እምደቂቀ እስራኤል ወይኩኖሙ ሕገ ዘለዓለም በመዋዕሊሆሙ ።

እግዚአብሔር እንዳዘዘ ከእስራኤል ልጆች ለይተው ቀብተው ከሾሙዋቸው ቀን ጀምሮ ይሰጡዋቸው ዘንድ በለ ዘመናቸው የዘለዓለም ሕግ ይሁናቸው ።

| | | |
|---|---|---|
| ወዝንቱ ውእቱ ሕጉ ለቍርባን ወለመሥዋዕት ለዘበእንተ ኀጢአትኒ ወለዘበእንተ ንስሓኒ ወለፍጻሜኒ ወለዘመሥዋዕተ መድኀኒትኒ ። | ፴፯ | የሚቃጠል የእኽል ቍርባንና የሥጋ መሥዋዕት ሕጉ ሥርዓቱ ይህ ነው የመሥዋዕተ ኃጢአትም የመሥዋዕተ ንስሐም ሲሾሙ ደሙን ለሚቀቡበት መሥዋዕትም ለመሥዋዕተ መድኀኒትም ሕጉ ይህ ነው ። ዘፀ፣ ፳፱ ፩ ። |
| በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ በደብረ ሲና በዕለተ አዘዞሙ እግዚአብሔር ለደቂቀ እስራኤል ያብኡ ቍርባኖሙ ቅድመ እግዚአብሔር በገዳም ዘሲና ። | ፴፰ | በሲና ምድረ በዳ በእግዚአብሔር ፊት ቍርባናቸውን ያቀርቡ ዘንድ እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች ባዘዛቸው ቀን እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ሕጉ ይህ ነው ። |

ምዕራፍ ፰ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ንሥኦሙ ለአሮን ወለደቂቁ ። | ፩ | እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው እንዲህም አለው፤ አሮንንና ልጆቹን (ለሹመት) አቅርባቸው ። |
| ወአልባሲሆሙኒ ወቅብዐ ዘይትቀባዑ ፣ ወላሕመ ዘበእንተ ኀጢአት ወክልኤተ አባግዐ ወመሶበ ናእት ። | ፪ | ልብሳቸውንም የሚቀቡትንም ዘይት አምጣ ስለ ኃጢአት የሚቀርበውንም በሬውን ሁለቱንም በጎች እንድ ቂጣ ያለበትንም መሶብ አቅርብ ። ዘፀ፣ ፳፱ ፩-፫ ። |
| ወአስተጋብእ ኵሎ ተዓይነ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ። | ፫ | ሕዝቡንም ሁሉ ወደ ደብተራ ኦሪት ደጃፍ ሰብስብ። ዘፀ፣ ፵ ፳፰፤ ምዕ፣ ፱ ፳፫ ። |
| ወገብረ ሙሴ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ወአስተጋብአ ኵሎ ተዓይነ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ። | ፬ | ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ፣ ሕዝቡንም ሁሉ በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ሰበሰበ ። |
| ወይቤሎሙ ሙሴ ለተዓይን ዝንቱ ውእቱ ቃል ዘአዘዘ እግዚአብሔር ትግበሩ ። | ፭ | ሙሴ ሕዝቡን (ሰብስቦ) ታደርጉት ዘንድ እግዚአብሔር ያዘዘው ቃል ይህ ነው አላቸው ። |
| ወነሥአሙ ሙሴ ለአሮን ወለደቂቁ ወሐፀቦሙ በማይ ። | ፮ | ሙሴም አሮንንና ልጆቹን አቅርቦ በውኃ አጠባቸው፣ |
| ወአልበሶ ለአሮን አልባሰ ቢሦስ ወአቅነቶ ቅናተ፣ ወአልበሶ ጶዴሬ፣ ወወደየ ላዕሌሁ ልብሰ መትከፍት ። | ፯ | አሮንን የነጭ ሐር ቀሚስ አለበሰው፣ ዝናርንም አስታጠቀው፣ እጀ ሰፊ መሉጣ ግምጃንም አለበሰው፣ በእጀ ሰፊው ላይ ኤፉድን አለበሰው ። ዘፀ፣ ፳፰ ፬ ። |
| ወአቅነቶ መልዕልተ ግብረታ ለልብሰ መትከፍት ወአሰራ ቦቱ፣ ወወደየ ላዕሌሁ ልብሰ ሎግዮ ዘተአምር ወዘጽድቅ ። | ፰ | ኤፉድን (የደረት ልብስ) በቋድ አያያዘው በኤፉድም ላይ ምልክት የሚታይበት ጽድቅ የሚሠራበት (ሎግዮ) የደረት ልብስን አደረገለት ። ዘኍ፣ ፳፯ ፳፩ ። |
| ወወደየ አክሊለ ዲበ ርእሱ፣ ወወደየ ላዕለ ውእቱ አክሊል መንገለ ገጹ ቈጽለ ወርቅ ዘቅዱስ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ። | ፱ | በራሱም ላይ ኩፌት አደረገለት (አክሊል ደፋለት) በአክሊሉም ላይ በፊቱ በኩል የተቀደሰውን የወርቅ ቅጠል አደረገለት፣ እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ። |
| ወነሥአ ሙሴ እምቅብዕ ዘይትቀብዑ፣ ወነዝኀ ላዕለ ምሥዋዕ ስብዐ፣ ወቀብዖ ለምሥዋዕ ። | ፲ | ሙሴም ተቀብተው ከሚከብሩበት ዘይት ወስዶ በመሠውያው ላይ ሰባት ጊዜ ረጨ፣ ምሥዋዑንም አከበረ ። |
| ወቀደሰ ኵሎ ንዋዮ ወማእከከኒ ወመንበሮ ቀደሰ፣ ወቀብዖ ለደብተራ ወለኵሉ ንዋያ ። | ፲፩ | ዕቃውን ሁሉ (ንዋየ ቅድሳቱን) ኵስኵስቱን መቀመጫውንም ቀብቶ አከበረ፣ ድንኳኒቱንና ዕቃዋንም ሁሉ ቀብቶ አከበረ ። |
| ወከዐወ ሙሴ እምቅብዕ ዘይትቀብዑ ላዕለ ርእሰ አሮን ወቀብዖ ወቀደሶ ። | ፲፪ | ሙሴ ተቀብተው ከሚከብሩበት ዘይት በአሮን ራስ ላይ ደፋው፣ ቀብቶም አከበረው ። ዘፀ፣ ፳፱ ፯ ፴-፴ ። |
| ወአምጽኦሙ ሙሴ ለደቂቀ አሮን ወአልበሶሙ አልባሰ ወአቅነቶሙ ቅናታተ፣ ወወደየ ላዕሌሆሙ አክሊለ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ። | ፲፫ | ሙሴ የአሮንን ልጆች አቅርቦ ልብሰ ተክህኖውን አለበሳቸው፣ የወርቅ ዝናርንም አስታጠቃቸው በራሳቸውም ላይ ኩፌት (አክሊል) ደፋላቸው፣ እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ። ዘፀ፣ ፳፱ ፰-፱ ። |
| ወአምጽአ ላሕመ ዘበእንተ ኀጢአት ወወደዩ አሮን ወደቂቁ እደዊሆሙ ላዕለ ርእሱ ለውእቱ ላሕም ዘበእንተ ኀጢአት ወጠብሖ ። | ፲፬ | ስለ ኃጢአት የሚሠዋውን በሬ አቀረበ፣ አሮንና ልጆቹም ስለ ኃጢአት በሚቀርበው በዚያ በሬ ራስ ላይ እጃቸውን አኖሩ፣ አረዱትም ። ዘፀ፣ ፳፰ ፲ ። |
| ወነሥአ ሙሴ እምደሙ ወወደየ ላዕለ አቅርንተ ምሥዋዕ በዓውዱ በአፃብዒሁ ወአንጽሖ ለምሥዋዕ ወከዐወ ደሞ ኀበ መንበረ ምሥዋዕ ወቀደሶ ከመ ያስተሥሪ ቦቱ ። | ፲፭ | ሙሴም ከደሙ አምጥቶ በመሠውያው ቀንዶች ዙርያ በጣቱ እየጠለቀ ረጨ፣ መሠውያውንም አነጻው ደሙንም በመሠውያው እግር አፈሰሰው፣ ኃጢአትን ያስተሠርይበት ዘንድ ። ዘፀ፣ ፳፱ ፲፪፤ ሕዝ፣ ፵፫ ፳፯ ። |

፲፮ ወነሥአ ሙሴ ስብሐ ዘውስተ ንዋየ ውስጡ ፡ ወከብዶ እንተ ትንእስ ወክልኤሆን ኵልያቲሁ ፡ ወስብሐ ዘላዕሌሆን ወወደየ ላዕለ ምሥዋዕ ።

ሙሴ በሆድ ዕቃው በአንጀቱ ያለውን ስብ ፡ ለምለም ጉበቱን ግልገል ኵላሊቱን ሁለቱንም ኵላሊቶች በላያቸው ያለውን ስብ ወስዶ በመሠውያው ላይ አቃጠለው ።

፲፯ ወማእሰኒ ወሥጋሁኒ ወክዕሴሁኒ ለውእቱ ላሕም አውዐየ በእሳት አፍአ እምትዕይንት በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

ጠሊሰት የቀረው ሥጋውን ፈርሱን ሰንበሩን ግን ከከተማው አፍአ አውጥቶ በእሳት አቃጠለው ፡ እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ። ዘፀ፡ ፳፱ ፲፬፡ ምዕ፡ ፬ ፲፩ ።

፲፰ ወአምጽአ ሙሴ በግዐ ለመሥዋዕት ወወደዩ አሮን ወደቂቁ እደዊሆሙ ላዕለ ርእሱ ለውእቱ በግዕ ።

ሙሴ ለመሥዋዕት የሚሆነውን በግ አቀረበ ፡ አሮንና ልጆቹም እጆቻቸውን በበጉ ራስ ላይ አኖሩ (ጫኑ) ።

፲፱ ወጠብሖ ሙሴ ለውእቱ በግዕ ወከዐወ ደሞ ውስተ ዓውደ ምሥዋዕ ።

ሙሴም ያንን በግ አርዶ ፡ ደሙንም በመሠውያው ዙርያ አፈሰሰው (ረጨው) ። ዘፀ፡ ፳፱ ፲፰ ።

፳ ወመተሮ ለውእቱ በግዕ በበአባላቲሁ ፡ ወወደየ ሙሴ ርእሶ ወአባላቲሁ ወስብሐ ወከርሦ ወእገሪሁኒ ሐፀበ በማይ።

ያንንም ዳንግሌ በግ በየብልቱ በለተው (ለየው) ቈረጠው ፡ ሙሴ የበጉን ራሱን ብልቱንና ስቡን አቃጠለ ፡ ፈርሱን እግሮቹን ግን በውኃ አጠበ ።

፳፩ ወወደየ ኵሎ ላዕለ ምሥዋዕ ፡ እስመ መሥዋዕት ውእቱ ዘመዓዛ ሠናይ ወቍርባን ውእቱ ለእግዚአብሔር በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

ሙሴ በጉ ሁሉ እንዳለ ሥጋውን ከመሠውያው ላይ አቃጠለው (አጤሰው) እግዚአብሔር ደስ ብሎት የሚቀበለው በእሳት የሚቃጠል የሚጤስ መሥዋዕት ነውና እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ። ዘፀ፡ ፳፰ ፲፰ ።

፳፪ ወአምጽአ ሙሴ ካልአ በግዐ ዘፍጻሜ ፡ ወወደዩ አሮን ወደቂቁ እደዊሆሙ ላዕለ ርእሱ ለውእቱ በግዕ ወጠብሖ

ሙሴ ደሙን የሚቀቡበትን ሁለተኛውን በግ አቀረበ አሮንና ልጆቹም በዚያ በግ ራስ ላይ እጆቻቸውን ጫኑ ፡ አረዱት አወራረዱት ። ዘፀ፡ ፳፱ ፲፱ - ፴፩ ።

፳፫ ወነሥአ ሙሴ እምደሙ ወወደየ ላዕለ ከተማ ዕዝኑ ለአሮን እንተ የማን ፡ ወላዕለ ከተማ እዕባዕተ እዴሁ እንተ የማን ፡ ወላዕለ ከተማ እዕባዕተ እግሩ እንተ የማን ።

ሙሴም ከደሙ ወስዶ የአሮንን የቀኝ ጆሮውን ጫፍ የቀኝ እጁን የአውራ ጣቱን ጫፍ ቀባው ፡ የቀኝ እግሩንም አውራ ጣት ጫፍ ጫፉን ቀባው ።

፳፬ ወአምጽኦሙ ሙሴ ለደቂቀ አሮን ፡ ወወደየ ሙሴ እምውእቱ ደም ላዕለ ከተማ ዕዘኒሆሙ ዘየማን ፡ ወላዕለ ከተማ እፃብዐ እደዊሆሙ ዘየማን ፡ ወላዕለ ከተማ አፃብዐ እገሪሆሙ ዘየማን ፡ ወከዐዎ ሙሴ ለውእቱ ደም ውስተ ዓውደ ምሥዋዕ ።

ሙሴ የአሮንን ልጆች አምጥቶ ከዚያው ደም የቀኝ ጆሯቸውን ጫፍ ፡ የቀኝ እጃቸውንም አውራ ጣት ፡ የቀኝ እግራቸውንም አውራ ጣት ቀባው (አስነካው) ፡ ሙሴ ያንን ደም በምሥዋዑ ዙርያ አፈሰሰው (ረጨው) ።
ዘፀ፡ ፳፱ ፳፪፡ ዕብ፡ ፱ ፲፰ - ፳፩ ።

፳፭ ወነሥአ ሙሴ ስብሐ ወሐቌሁ ወስብሐ ከርሡ ወከብዶ እንተ ትንእስ ወክልኤሆን ኵልያቲሁ ፡ ወስብሐ ዘላዕሌሆን ወእገዳ ዘየማን ።

ሙሴ ስቡን ዳሌውን (ላቱን) በሆድ ዕቃውም ላይ ያለውን ስቡን ግልገል ኵላሊቱን ለምለም ጉበቱን ፡ ሁለቱን ኵላሊቱን በላያቸው ያለውን ስብ የቀኝ ወርቹን አመጣ።

፳፮ ወነሥአ እመሶብ ዘፍጻሜ ዘሀሎ ቅድመ እግዚአብሔር ኅብስተ ናእት አሐተ ፡ ወኅብስተ ዘበቅብዕ አሐተ ፡ ወፀሪቀ አሐተ ወወደዮን ዲበ ስብሕ ወዲበ እገዳ ዘየማን ።

ሙሴም በእግዚአብሔር ፊት ካለው ደሙ ከሚቀቡበት በግ ሥጋ ካለበት መሶብ አንድ ቂጣ (ዳቦ) በዘይት የታበቀ በቅቤ የተለቀለቀ አንድ እንጐቻ (ሙጀራ) ፡ አንድ ድፎ ዳቦ በስቡና በቀኝ ወርቹ ላይ አደረገ (አኖረው) ።

፳፯ ወአንበረ ኵሎ ዲበ እደወ አሮን ወላዕለ እደወ ደቂቁ ወአብአሙ መበአ ቅድመ እግዚአብሔር ።

ሁሉንም በአሮን እጅና በልጆቹ እጅ አደረገ መባ አድርጎም ወደ እግዚአብሔር አገባቸው ። ዘፀ፡ ፳፱ ፳፬ ።

፳፰ ወነሥአ ሙሴ እምእደዊሆሙ ወወደዮ ላዕለ ምሥዋዕ ወዲበ መሥዋዕተ ፍጻሜ ቍርባን ፡ ወመዓዛ ሠናይ ውእቱ ለእግዚአብሔር ።

ሙሴም ከእጃቸው ተቀብሎ የሚቀቡበት መሥዋዕት በለበት በመሠውያው ላይ አኖረው እግዚአብሔር በጎ መዓዛ አድርጎ የሚቀበለው ነውና ። ዘፀ፡ ፳፱ ፳፭ ።

፳፱ ወነሥአ ሙሴ ተላዐ ወመተረ ከመ ይደዮ ቅድመ እግዚአብሔር እምበግዕ ዘፍጻሜ ፡ ወኮነ ክፍሉ ለአሮን በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

ሙሴ ፍርምቢያውን ወስዶ ደሙን ተቀብተው ክህነትን ሊሾሙበት ከታረደው በግ በእግዚአብሔር ፊት ስቡን ከፍርምቢያው ፡ ፍርምቢያውን ከስቡ ለየው እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ፍርምቢያው ለአሮን ዕድል ፈንታ ሆነ ። ዘፀ፡ ፳፱ ፳፯ ፡ ምዕ፡ ፯ ፲፬ ፴፫ ።

፴ ወነሥአ ሙሴ እምቅብዕ ዘይትቀብዑ ፡ ወእምደም ዘምሥዋዕ ፡ ወነዘኀ ላዕለ አሮን ወላዕለ አልባሲሁ ፡ ወላዕለ ደቂቁ ፡ ወላዕለ አልባሰ ደቂቁ ፡ ወቀደሶ ለአሮን ወለአልባሲሁ ፡ ወለደቂቁ ወለአልባሰ ደቂቁ ።

ሙሴም ከሚቀቡት ዘይትና በምሥዋዑ ላይ ካለው ደም ወስዶ በአሮንና በልብሱ ላይ በልጆቹና በልጆቹ ልብሶች ላይ ረጨው ፡ አሮንንም አከበረው ልብሶቹንም ከርሱ ጋር ልጆቹንና የልጆቹንም ልብሶች እንደርሱ አከበረ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወይቤሎሙ ሙሴ ለአሮን ወለደቂቁ ፡ አብስሉ ውእተ ሥጋ በዓፀደ ደብተራ ዘመርጡል ፡ ወበመከን ቅዱስ ወበ ህየ ብልዕዎ ፡ ወኅብስተኒ ዘውስተ መሶብ ዘፍጻሜ በከመ አዘዘኒ እግዚአብሔር ፡ ወይቤለኒ አሮን ወደቂቁ ይብልዕዎ ። | ፴፩ | ሙሴ አሮንንና ልጆቹን ይህንን ሥጋ በደብተራ ኦሪት ደጃፍ በክቡር ቦታ ቀቅላችሁ በዚያው ብሉት አላቸው ፡ ደሙን ተቀብታችሁ ክህነት የተሾማችሁበትን በመሶብ ያለውንም ሙጀራ (ዳቦ ቂጣ) ብሉ ፡ እግዚአብሔር አሮንና ልጆቹ ይብሉት ብሎ እንዳዘዘኝ ። ዘፀ፡ ፳፱ ፳፱ ። |
| ወዘተርፈ እምሥጋ ወኅብስት በእሳት አውዕይዎ ። | ፴፪ | ከሥጋውና ከእንጀራው የተረፈውን በእሳት አቃጥሉት ። ዘፀ፡ ፳፱ ፴፬ ፡ ምሳ፡ ፬ ፲፪ ። |
| ወኢትፃኡ እምኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ሰቡዐ ዕለተ ፡ እስከ አመ ትፈጽሙ ዕለተ ፍጻሜክሙ ። | ፴፫ | የምትቀቡበትንም ቀን እስክትጨርሱ ድረስ ከደብተራ ኦሪት ደጃፍ እስከ ሰባት ቀን አትውጡ ። |
| እስመ ሰቡዐ ዕለተ ይትፌጸም አደዊክሙ ፡ በከመ ተገብረ በዛቲ ዕለት እንተ አዘዘ እግዚአብሔር ከመ ይግበሩ በዘያስተሠርዩ ለክሙ ። | ፴፬ | በሚያስተሠርዩላችሁ ገንዘብ ያደርጉ ዘንድ እግዚአብሔር ባዘዘበት በዚያች ቀን እንደተደረገ እጆቻችሁ ሰባት ቀን ይቀበሉና ። ሕዝ፡ ፵፫ ፳፭ - ፳፮ ። |
| ወንበሩ ውስተ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ሰቡዐ ዕለተ መዓልተ ወሌሊተ ወዕቀቡ ትእዛዘ ለእግዚአብሔር ከመ ኢትሙቱ እስመ ከማሁ አዘዘኒ እግዚአብሔር ። | ፴፭ | ሰባት ቀን ሌሊቱና መዓልቱን በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ተቀመጡ ፡ እንዳትቀሠፉም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቁ ፡ እግዚአብሔር እንደዚሁ አዝዞኛልና ። |
| ወገብሩ አሮን ወደቂቁ ኵሉ ቃለ ዘአዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ። | ፴፮ | አሮንና ልጆቹም እግዚአብሔር ለሙሴ ያዘዘውን ቃል ሁሉ አደረጉ (ፈጸሙ) ። |
| ምዕራፍ ፱ ። | | ምዕራፍ ፱ ። |
| ወኮነ በሳምንት ዕለት ጸውዖሙ ሙሴ ለአሮን ወለደቂቁ ወለአእሩገ እስራኤል ። | ፩ | (ክህነቱ በተቀቡበት) በስምንተኛው ቀን እንዲህ ሆነ፡ ሙሴ አሮንንና ልጆቹን የእስራኤልንም ሽማግሌዎች ጠራቸው ። ሕዝ፡ ፵፫ ፳፯ ። |
| ወይቤሎ ለአሮን ንሣእ ለከ ላሕመ እምአልሕምት ዘበእንተ ኃጢአት ወበግዐ ለመሥዋዕት ወአምጽኦሙ ቅድመ እግዚአብሔር ። | ፪ | አሮንንም እንዲህ አለው ፤ ስለ ኃጢአት ከላሞች አንድ በሬ ለራስህ ውሰድ፡ ለሚቃጠል ለሚጤስ መሥዋዕትም በግ አምጥተህ ወደ እግዚአብሔር ፊት (ወደ ደብተራ ኦሪት) አቅርባቸው ። ዘሌዋ፡ ፰ ፲፱ ። |
| ወንግሮሙ ለአእሩገ እስራኤል ወበሉሙ ንሥኡ አሐደ ሐርጌ እምአጣሊ ዘበእንተ ኃጢአት ወበግዐ ወላሕመ ወማሕስአ ዘዓመት ንጹሐን ለመሥዋዕት ። | ፫ | ለእስራኤልም ሽማግሌዎች ንገራቸው ፡ እንዲህም በሏቸው ስለ ኃጢአት መሥዋዕት የሚሆን ከፍየሎች መንጋ አንድ ሙክት አምጡ ፡ አንድ በግ ፡ አንድ በሬ ዓመት የሆነው ጠበት ነውር የሌለባቸውን ለሚቃጠል ለሚጤስ መሥዋዕት አቅርቡ ። ምሳ፡ ፬ ፳፬ ፡ ዕብ፡ ፯ ፲፯ ። |
| ወላሕመኒ እምአልሕምት ወበግዐኒ ለመሥዋዕተ መድኃኒት ቅድመ እግዚአብሔር ወሥንዳሌ ዘልዉስ በቅብዕ ፡ እስመ ዮም ያስተርኢ ለክሙ እግዚአብሔር ። | ፬ | ከላሞችም ወገን በሬን ውሰዱ ፡ በግንም ድኅነት ለሚደረግበት መሥዋዕት በእግዚአብሔር ፊት አቅርቡ፡ በዘይት የታሸ በቅቤ የታበቀ የእኽል መሥዋዕትንም አቅርቡ መሥዋዕተ መድኃኒቱን በሠዋችሁበት በዚህ ቀን እግዚአብሔር (በረድኤት) ይገለጽላችኋልና ብለህ ንገራቸው ። |
| ወነሥኡ በከመ አዘዞሙ ሙሴ ቅድመ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወመጽኡ ኵሉ ተዓይን ፡ ወቆሙ ቅድመ እግዚአብሔር ። | ፭ | ሕዝቡም ሁሉ ሙሴ ያዘዛቸውን ይዘው መጥተው በእግዚአብሔር ፊት (በታቦቱ ፊት) በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ቆሙ ። |
| ወይቤሎሙ ሙሴ ዝንቱ ውእቱ ቃል ዘይቤለክሙ እግዚአብሔር ግበሩ ወያስተርኢ ለክሙ ስብሐተ እግዚአብሔር ። | ፮ | ሙሴም እንዲህ አላቸው ፤ ታደርጉት ዘንድ እግዚአብሔር ያዘዛችሁ ትእዛዝ (ቃል) ይህ ነው ፡ የእግዚአብሔር ክብር ይገለጽላችኋል ። ዘፀ፡ ፳፬ ፲፮ ። |
| ወይቤሎ ሙሴ ለአሮን ሑር ኀበ ምሥዋዕ ወግበር ዘበእንተ ኃጢአትከ ወዘመሥዋዕትከ ወአስተሥሪ ለርእስከ ወለቤትከ ፡ ወእምዝ ግበር መሥዋዕተ ለሕዝብከ ወአስተሥሪ ሎሙ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ። | ፯ | ሙሴም አሮንን ወደ መሠውያው ሂደህ ስለ ኃጢአትህ የሚቀርበውን መሥዋዕትና የሚቃጠለውን መሥዋዕተ አሥምሮህን ሠዋ ፡ (አስቀድመህ) የራስህን ኃጢአት አስተሥርይ ፡ ከዚህ በኋላ የሕዝቡን መሥዋዕት ሠዋ ፡ እግዚአብሔር እንዳዘዘ መሥዋዕቱን ሠውተህ ኃጢአታቸውን አስተሥርይላቸው ፡ አለው ። |
| ወሖረ አሮን ኀበ ምሥዋዕ ወጠብሐ ላሕመ ዘበእንተ | ፰ | አሮንም ወደ መሠውያው ሂዶ ስለ ኃጢአቱ የሚቀር |

ኃጢአቱ ።
፱ ወአምጽኡ ደቂቀ አሮን ደሞ ኀቤሁ ወጠምዐ አፃብ
ዒሁ ውስተ ደሙ ወወደየ ላዕለ አቅርንተ ምሥዋዕ፣
ወከዐወ ደሞ ላዕለ መንበረ ምሥዋዕ ።
፲ ወስብሐ ወኩልኤሆን ኵልያቲሁ ወከብዶ እንተ ትንእስ
ወደየ ላዕለ ምሥዋዕ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

፲፩ ወሥጋሁሰ ወማእሶ አውዐዮ በእሳት አፍአ እምትዕ
ይንት ።
፲፪ ወጠብሐ ዘመሥዋዕትኒ ወአምጽኡ ደቂቀ አሮን ደሞ
ኀቤሁ ወከዓዎ ዓውደ ምሥዋዕ ።

፲፫ ወመሥዋዕቶኒ አምጽኡ ሎቱ በበመለያልይሁ ወርእ
ሶኒ ወወደዩ ውስተ ምሥዋዕ ።

፲፬ ወሐፀበ ንዋየ ውስጡ ወእገሪሁ ወወደዮ ላዕለ ምሥ
ዋዕ ዲበ መሥዋዕት ።
፲፭ ወአምጽአ አብአ ቍርባኖሙ ለሕዝብ ወነሥአ ለውእቱ
ሐርጌ ዘበእንተ ኃጢአት ዘሕዝብ፣ ወጠብሐ ወአንጽሖ
ወመትሮ ዘከመ ቀዳሚ ።

፲፮ ወአብአ መሥዋዕተ ወገብሮ ዘበሕጉ ።

፲፯ ወአምጽአ እመሥዋዕተ ሠንዴ ምልአ እዴሁ እም
ኔሁ ወወደዮ ላዕለ ምሥዋዕ፣ ዘእንበለ መሥዋዕት ዘነግህ ።

፲፰ ወአምዝ ጠብሐ ላሕመ ወበግዐ ለመሥዋዕተ መድኃ
ኒት ዘሕዝብ፣ ወአምጽኡ ደቂቀ አሮን ደሞ ኀቤሁ፣ ወከ
ዓወ ዓውደ ምሥዋዕ ።

፲፱ ስብሐ ላሕምኒ ወዘበግዕ ወሐቌሁኒ ወስብሐኒ ዘይገለ
ብብ ለከርሥ ወኩልኤሆን ኵልያቲሁ ወስብሐ ዘላዕሌሆን
ወከብዶ እንተ ትንእስ ።
፳ ወአንበረ ስብሐ ዲበ ተላዕ ወወደየ ውስተ ምሥዋዕ ።

፳፩ ወተላዐ ወእገዳ ዘየማን መተረ አሮን እስመ ሀብቱ
ውእቱ ቅድመ እግዚአብሔር በከመ አዘዞ ለሙሴ ።
፳፪ ወአልዓለ አሮን እዴሁ ላዕለ ሕዝብ ወባረኮሙ፣ ወወ
ረደ ገቢሮ ዘበእንተ ኃጢአት ወዘመሥዋዕተ መድኃኒት ።

፳፫ ወቦኡ ሙሴ ወአሮን ውስተ ደብተራ ዘመርጡል፣
ወወጺኦሙ ባረክዎ ለኵሉ ሕዝብ፣ ወአስተርአየ ስብሐተ
እግዚአብሔር ለኵሉ ሕዝብ ።
፳፬ ወወፅአት እሳት እምኀበ እግዚአብሔር ወበልዓት
መሥዋዕቶ ዘላዕለ ምሥዋዕ ወስብሐኒ ወርእዮ ኵሉ ሕዝብ
ወደንገፁ ወወድቁ በገጸሙ ።

በውን እምበሳውን (ጥጃውን) አረደ ።
የአሮንም ልጆች ደሙን ወደርሱ አቀረቡ፣ ጣቱንም
ከደሙ ውስጥ ጠልቆ የመሠውያውን ቀንዶች ቀባበት
(አስነካ) ደሙንም ከመሠውያው እግር ሥር አፈሰሰው ።
ስለ ኃጢአት የተሠዋውን ስቡን ሁለቱ ኵላሊቶቹን
ግልገል ኵላሊቱንና ለምለም ጕበቱን እግዚአብሔር
ሙሴን እንዳዘዘው በምሥዋው ላይ አቃጠለው (አጤሰው)።
ሥጋውንና ቊርበቱን ግን ከከትማው አፍአ አውጥ
ተው በእሳት አቃጠሉት ። ምዕ፤ ፱ ፰ ፰ - ፲፯ ።
መሥዋዕት አሥምሮ የሚሆነውንም በሬ አረደ፣ የአ
ሮንም ልጆች ደሙን ወደ ርሱ አቀረቡ፣ (እርሱም) በመ
ሠውያው ዙርያ ረጨው (ረበረበው) ። ዘሌዋ፤ ፩ ፭ ።
የሚቃጠለውንም መሥዋዕቱን በየብልቱ ለይተው፣
አመጡለት፣ ራሱንም አቀረቡለት (እሱም) በምሥዋው
ላይ አቃጠለው ።
ሆድ ዕቃውንና እግሮቹን ግን እጥቦ መሥዋዕቱ
በሚሠዋበት መሠውያ ላይ አቃጠለው (አጤሰው) ።
ከዚህ በኋላ የሕዝቡን መሥዋዕት ቍርባን አቀረበ፣
ስለ ሕዝቡ ኃጢአት የሚቀርበውን (የሚሠዋውን) የፍየ
ሉን ሙክት ወስዶ አረደው አነጻው፣ እንደ ፊተኛው
ሰየው ። ፪ ቆሮ፤ ፭ ፳፩ ፣ ኤፌ፤ ፭ ፫ ።
የሚቃጠለውና መሥዋዕት አቀርቦ እንደ ሕጉ (እንደ
ሥራቱ) አደረገው (ሠዋው) ።
ከሥንዴውም መሥዋዕት እፍኝ ሙሉ አምጥቶ በነ
ግህ ከሚሠዋው መሥዋዕት በቀር በመሠውያው ላይ
አጤሰው ። ዘፀ፤ ፳፱ ፴፰ ።
ከዚህ በኋላ የሕዝቡን መሥዋዕተ መድኃኒት የሚሆነ
ውን በሬውንና በጉን አረዱ አወራረዱ፣ የአሮንም ልጆች
ደሙን ወደርሱ አቀረቡ፣ እሱም በምሥዋው ዙርያ ረጨ
ው (አፈሰሰው) ።
የበሬውንና የበጉንም ስብ ዳሌውን አንጀቱን ፈርሱን
የሚሸፍነውን ስቡን ሁለቱ ኵላሊቶቹን በላያቸው ያለውን
ስብ ግልገል ኵላሊቱን ለምለም ጕበቱን አመጡለት ።
በፍርምቢያው ላይ ያለ ስቡን አምጥቶ በመሠውያው
ላይ አቃጠለው፣ (አጤሰው) ።
አሮንም ሙሴ እንዳዘዘው በእግዚአብሔር ፊት ፈን
ታው ነውና የቀኝ ወርቹንና ፍርምቢያውን ለየ ።
አሮንም እጁን ወደ ሕዝቡ ዘርግቶ ባረካቸው፣ መሥ
ዋዕተ ኃጢአቱን መሥዋዕተ መድኃኒቱን ከሠዋ በኋላ
ወረደ (ተመለሰ) ። ዘዳግ፤ ፳፩ ፭ ።
ሙሴና አሮንም ወደ ደብተራ ኦሪት ገቡ፣ (ከደብተራ
ኦሪትም) ወጥተው ሕዝቡን ሁሉ ባረኩዋቸው (መረቁዋ
ቸው) የእግዚአብሔርም ክብር (ብርሃን) ለሕዝቡ ሁሉ ታየ።
እሳትም ከእግዚአብሔር ዘንድ (ታዝዞ) ከሰማይ ወርዳ
በምሥዋው ላይ ያለውን መሥዋዕቱንና ስቡን (አቃጠለች)
በላች፣ ሕዝቡም ሁሉ ይህንን አይተው ደነገጡ፣ በግምብ
ራቸውም ወደቁ (ሰገዱ) ። ዘፍ፤ ፬ ፬፣ ዘፀ፤ ፳፰ ፳፱ ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



## ምዕራፍ ፲ ።

፩ ወነሥኡ ደቂቀ አሮን ናዳብ ወአብዩድ አሐዱ አሐዱ ማዕጠንቶሙ ፡ ወወደዩ ውስቴቶን እሳተ ወወደዩ ላዕሌሁ ዕጣነ ወአምጽኡ ቅድመ እግዚአብሔር እሳተ ዘእም ብዕድ ዘኢአዘዞሙ እግዚአብሔር ።

የአሮን ልጆች ናዳብና አብዩድ አንዱም አንዱም ማዕጠንታቸውን (ጥናቸውን) ይዘው በውስጣቸውም ፍም አድርገው ፡ በፍሙም ላይ ዕጣን ጨምረው እግዚአብሔር ያላዘዛቸውን ከሌላ የተሟረውን እሳት በእግዚአብሔር ፊት አቀረቡ ። ዘፀ፡ ፴ ፱ ። ዘኍ፡ ፲፯ ፲፰ ።

፪ ወወፅአት እሳት እምኀበ እግዚአብሔር ወበልዓቶሙ ወሞቱ በቅድመ እግዚአብሔር ።

እሳትም ከእግዚአብሔር ዘንድ ታዝዛ ወጥታ በላቻቸው ፡ በእግዚአብሔር ፊት ሞቱ (ተቀሠፉ) ።

፫ ወይቤሎ ሙሴ ለአሮን ዝውእቱ ዘይቤ እግዚአብሔር በእለ ይቀርቡኒ እትቄደስ ወበኵሉ ተዓይን እሴባሕ ወደንገፀ አሮን ።

ሙሴም አሮንን እንዲህ አለው ፤ እግዚአብሔር ሳይ በቁ በቅተናል ብለው በሚቀርቡኝ እመሰገናለሁ ያለው ይህ ነው ፡ (በርሱም ጥፋት) በሕዝቡ ሁሉ ዘንድ እከብራለሁ (እመሰገናለሁ) አሮንም (ይህን ሰምቶ) ደነገጠ ።

፬ ወጸውዖሙ ሙሴ ለሳሚሳዲ ወለኤልሳፍ ደቂቀ አዚሄል እኁሁ ለአበ አሮን ፡ ወይቤሎሙ ሑሩ ንሥኡ አኃዊክሙ እምቅድመ መቅደስ ወአውፅእዎሙ አፍአ እም ትዕይንት ።

ሙሴም የአሮንን የአባቱ ወንድም የአዚሄልን ልጆች ሳሚሳዲንና ኤልሳፍን ጠርቶ ሂዱችሁ ወንድሞቻችሁን ከቅድስተ ቅዱሳን ፊት (ከመቅደሱ) አንሥታችሁ ከከተማው አፍአ አውጡዋቸው አላቸው ።

፭ ወበኡ ወአውፅእዎሙ በአልባሲሆሙ አፍአ እምትዕይንት ፡ በከመ ይቤሎሙ ሙሴ ።

(እነሱም) ገብተው ሙሴ እንዳላቸው በልብሶቻቸው እየሸበለሉ ከከተማው ወደ ሜዳ አወጡዋቸው ።

፮ ወይቤሎሙ ሙሴ ለአሮን ወለአልአዛር ወለይታምር ደቂቁ ፡ ርእሰክሙ ኢትቅርፁ ወአልባሲክሙ ኢትስጥጡ ከመ ኢትሙቱ ወኢይኩን መንሱት ላዕለ ኵሉ ተዓይን ፡ አኃዊክሙሰ ኵሉ ቤተ እስራኤል ለሙንቱ ይብክይዎሙ ለእለ አውዓዮሙ እግዚአብሔር ።

ሙሴ አሮንን ልጆቹ አልአዛርንና ይታምርን እንዲህ አላቸው ፤ ራሳችሁን አትንጩ ፡ ፀጕራችሁን አትላጩ ፡ ልብሶቻችሁን አትቅደዱ እንዳትሞቱ (እንዳትቀሠፉ) በሕዝቡም ሁሉ ላይ ጥፋት እንዳይሆን ወንድሞቻችሁ ግን እግዚአብሔር ስላቃጠላቸው የእስራኤል ወገን ሁሉ ያልቅሱላቸው ። ሕዝ፡ ፳፬ ፲፯ ፡ ኢዩ፡ ፳፪ ፲፰ - ፳ ።

፯ ወእምኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ኢትፃኡ ከመ ኢትሙቱ ፡ እስመ ቅብዐ ዘይትቀብዑ ዘእግዚአብሔር ሀለወ ላዕሌክሙ ፡ ወገብሩ በከመ አዘዞሙ ሙሴ ።

ከደብተራ ኦሪት ደጃፍ አትውጡ (እናለቅሳለን እናስቀብራለን ብላችሁ ወጥታችሁ) እንዳትሞቱ እግዚአብሔር ያከበረው (ክህነት) የሚቀቡት ዘይት በናንተ ላይ አለና ።

፰ ወነበበ እግዚአብሔር ለአሮን ወይቤሎ ፡ ወይነ ወሜሰ ኢትስተይ አንተ ወደቂቅከ ምስሌከ እንዘ ትበውኡ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ።

እግዚአብሔር አሮንን እንዲህ ሲል ተናገረው ፤ አንተም ልጆችህም ካንተ ጋር ወደ ደብተራ ኦሪት በምትገቡበት ጊዜ ።

፱ አው እንዘ ትበውኡ ኀበ ምሥዋዕ ኢትሙቱ ሕግ ዘለዓለም ውእቱ ።

ወይም ወደ ምሥዋዑ በምትቀርቡበት ጊዜ የወይኑንና የማሩን ጠጅ አትጠጡ እንዳትሞቱ (እንዳትቀሠፉ) ይኸውም ባለ ዘመናችሁ የዘለዓለም ሕግ ነው ።

፲ ዘበቱ ይትፈለጡ ቅዱሳን ወርኩሳን ወንጹሐን ወእለ ኢኮኑ ንጹሐነ ።

በርኩሳንና በቅዱሳን በንጹሐንና በኢንጹሐን መካከል የሚለዩበት ይህ የዘለዓለም ሕግ ነው ። ሕዝ፡ ፳፪ ፳፯ ።

፲፩ ወትሜህሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ኵሎ ሕግየ ዘነገርክዎሙ በእደ ሙሴ ።

በሙሴ ቃል የነገርኳቸውን ሕግ ሁሉ ለእስራኤል ልጆች ታስተምራቸዋለህ ። ኤር፡ ፲፰ ፲፰ ።

፲፪ ወይቤሎሙ ሙሴ ለአሮን ወለአልአዛር ወለይታምር ደቂቁ እለ ተርፉ ንሥኡ መሥዋዕተ ዘተርፈ እምቍርባኑ ለእግዚአብሔር ወብልዑ ናእተ ኀበ ምሥዋዕ ፡ ቅዱስ ለቅዱሳን ውእቱ ።

ሙሴም አሮንንና ከመቅሠፍት የቀሩ ልጆቹን አልአዛርና ይታምርን እንዲህ አላቸው ፤ ለእግዚአብሔር ከሚቀርበው መሥዋዕት የተረፈውን ወስዳችሁ በምሥዋዑ ዘንድ ቂጣ አድርጋችሁ ብሉት ፡ ቅዱስ ለቅዱሳን ነው ።

፲፫ እስመ ሕግ ውእቱ ለከ ወሕጎሙ ውእቱ ለደቂቅከ እመሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር እስመ ከማሁ አዘዘኒ እግዚአብሔር ።

ላንተ ሕግ ነውና (ካንተም በኋላ) ለእግዚአብሔር ከቀረበው ከተቃጠለው መሥዋዕት የቀረው ለልጆችህም ወጋቸው ፈንታቸው ነውና እግዚአብሔር እንዲህ አዝዞኛልና።

፲፬ ወተላየ ዘመባእ ወእንገዱ ዘመባእ ትበልዖ በመካን ቅዱስ አንተ ወደቂቅከ ወቤትከ ምስሌከ ሕግ ውእቱ ለከ ፡ ወሕጎሙ ውእቱ ለደቂቅከ ዘተውህበ ለክሙ እመሥዋዕተ መድኃኒት ዘደቂቀ እስራኤል ።

የመባውን ፍሪምባና ወርቹን አንተና ልጆችህ በክቡር ቦታ ሁናችሁ ብሉት ፡ ወገንህም ካንተ ጋር ይብሉ ፡ ከእስራኤል መሥዋዕተ መድኃኒት ለናንተ የተሰጣችሁ ያንተ ወግህ ፈንታህ የልጆችህም ወጋቸው ፈንታቸው ነውና ።

፲፭ አንዳ ዘመብእ ወተላዕ ዘይፈልጡ እምሰብሕ ዘመሥዋዕት በቅድመ እግዚአብሔር ይኩንክ ለከ ወለደቂቅከ ምስሌከ ሕግ ዘለዓለም በከመ አዘዘኒ እግዚአብሔር ።

የመብውን ወርችና በእግዚአብሔር ፊት በእሳት ከሚቃጠለው መሥዋዕት የሚለዩት ፍሪምብ ላንተም ለልጆችህም ከንተ ጋር ወግ ፈንቃ ይሁን፤ ይኸውም እግዚአብሔር እንዳበዘኝ ለዘለዓለም ጸንቶ የሚኖር ሕግ ነው ።

፲፮ ወኃሠሦ ሙሴ ለሐርጌ ዘበእንተ ኃጢአት ፤ ወዐበ ኃሠሦ ናሁ ውዑይ ወተምዐ ዲበ አልአዛር ወይታምር ደቂቀ አሮን እለ ተርፉ ።

ሙሴም ስለ ኃጢአት የተሠዋውን በልተው በዚህ ሙተው እንደሆን ብሎ ሙክቱን መረመረው፤ በመረመረውም ጊዜ ተቃጥሎ አገኘው፤ ሙሴ ከሞት በቀሩት በአሮን ልጆች በአልአዛርና በይታምር ላይ ተቈጣ ።

፲፯ ወይቤሎሙ ለምንት ኢበላዕክሙ በእንተ ኃጢአት በመከን ቅዱስ እስመ ቅዱስ ውእቱ ለቅዱሳን ።

እንዲህም አላቸው፤ ስለ ኃጢአት የተሠዋውን የፍየሉን ሙክት ለምን በክቡር ቦታ አልበላችሁም አላቸው፤ ቅዱስ ለቅዱሳን ነውና ።

፲፰ ወወሀብክሙ ዘንተ ትብልዑ ከመ ትኅድጉ ኃጢአተ ትዕይንት ወታስተሥርዩ ሎሙ ቅድመ እግዚአብሔር ።

በእግዚአብሔር ፊት የሕዝቡን ኃጢአት እንድትሸከሙ ኃጢአታቸውንም እንድታስተሠርዩላቸው ትበሉ ዘንድ ይህን ሰጥቶአችኋልና ። ሕዝ፡ ፵፬ ፳፱ ።

፲፱ እስመ ለዘቦአ ደሙ ውስተ መቅደስ በቅድሚሁ በውስጥ ትበልዑ በመከን ቅዱስ በከመ ተአዘዝኩ ።

እኔ እንደ ታዘዝሁ ደሙ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የገባለትን መሥዋዕተ ኃጢአት (በደብተራ ኦሪት) ውስጥ በክቡር ቦታ በእግዚአብሔር ፊት ትበሉታላችሁና ።

፳ ወተናገሮ አሮን ለሙሴ ወይቤሎ ዮም ሰበ ቀደሱ ዘበእንተ ኃጢአቶሙ ወመሥዋዕቶሙኒ ቅድመ እግዚአብሔር ዘተ ረከበተኒ ወዮጊ ኢክነ ሠናየ ቅድመ እግዚአብሔር ከመ እብላዕ ዘበእንተ ኃጢአት ፤ ወሰምዐ ሙሴ ወአደሞ ።

አሮንም ሙሴን ተናገረው እንዲህም አለው፤ የእስራኤል ልጆች ከገንዘባቸው ለይተው ያመጡትን መሥዋዕተ ኃጢአታቸውን በእግዚአብሔር ፊት የሚቃጠለው መሥዋዕታቸውንም ዛሬ ሳልበላ ይህች መከራ አገኘችኝ ዛሬስ ስለ ኃጢአት የቀረበውን መሥዋዕተ ኃጢአቱን በልቼ ቢሆን በእግዚአብሔር ፊት በጎ ባልሆነም ነበር አለው፤ ሙሴም ይህን ሰምቶ ደስ አለው ።

## ምዕራፍ ፲፩ ።

፩ ወነበበሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ወይቤሎሙ ንግርዎሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን ለእስራኤል ልጆች እንዲህ በሉዋቸው ብሎ ተናገራቸው ።

፪ ወበልዎሙ ዝንቱ ውእቱ እንስሳ ዘትበልዑ እምኵሉ እንስሳ ዘሀሎ ዲበ ምድር ።

በምድር ካለው እንስሳ ሁሉ ወገን የምትበሉት ይህ ነው ብላችሁ ንገሯቸው ። ዘዳ፡ ፲፬ ፬ ፤ ግ፡ ሐ፡ ፲ ፲፪ ።

፫ ኵሉ እንስሳ ዘንፉቅ ሰኰናሁ ወሥጡቅ ዕፈሪሁ እማእከሉ ወእንተ ክልኤቱ ውእቱ ወዘያመሰኵዕ ኪያሁ ብልዑ ።

ከእንስሳት ሁሉ ሰኰናው የተከፈለውን ማኸል ዕፍሩ የተሰነጠቀውን፤ ሰኰናው ሁለት የሆነውን፤ የሚያመሰኳውን እሱን ብሉ ።

፬ ወዝንቱ ባሕቱ ዘኢትበልዑ፤ እምዘያመሰኵዕ ወእም ዘንፉቅ ሰኰናሁ ገመል፤ እስመ ያመሰኵዕ ወኢኮነ ንፉቀ ሰኰናሁ፤ ዝንቱ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ።

ነገር ግን ከሚያመሰኳው ሰኰናው ከተሰነጠቀው ከተከፈለው ወገን የማትበሉት ይህ ነው፤ ግመል ያመሰኳልና እግሩም የተከፈለ አይደለምና ይህ ለናንተ ርኩስ ነው፤ (አትብሉት) ። መዝ፡ ፪፬ ፲፰ ፤ ምሳ፡ ፲፬ ፳፯ ።

፭ ወዳስጴዳሂ እስመ ያመስኵዕ ወኢኮነ ንፉቀ ሰኰናሁ ዝንቱኒ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ።

ጥንቸልም ያመሰኳልና ነገር ግን ሰኰናው የተከፈለ አይደለምና ይህም ለናንተ ርኩስ ነው ።

፮ ወኪሮግልዮስኒ እስመ ንፉቀ ሰኰናሁ ወሥጡቅ ዕፈሪሁ እማእከሉ ወኢያመሰኵዕ ውእቱኒ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ።

የማትበሉት አሳማ ነው፤ እንደ አሳማ ያለውን አትብሉ ሰኰናው የተሰነጠቀ የተከፈለ ነውና፤ ነገር ግን ምንዛሀ አያወጣምና (አያመሰኳም) ይህም በናንተ ዘንድ ርኩስ ነው ። ፩ ጢሞ፡ ፬ ፬ - ፭ ። ግብ፡ ሐዋ፡ ፲ ፲፬ ።

፯ ወሐራውያኒ እስመ ንፉቀ ሰኰናሁ ወሥጡቅ ዕፈሪሁ እማእከሉ ወኢያመሰኵዕ ውእቱኒ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ።

አሪያም ሰኰናው የተከፈለ ከጥፍሩ ማኸል የተሰነጠቀ ነው፤ ነገር ግን ምንዛሀ አያወጣምና እሱም በናንተ ዘንድ ርኩስ ነው፤ (አትብሉት) ። ኢሳ፡ ፷፭ ፬ ፤ ፷፮ ፫ ።

፰ እምነ ሥጋሆሙ ኢትብልዑ ወበድኖሙኒ ኢትግሥሡ እስመ ርኩሳን ውእቶሙ ለክሙ ።

የነዚህ ሥጋቸውን አትብሉ፤ ጥምባቸውንም አትንኩ (አትዳሰሱ) በናንተ ዘንድ ርኩሳን ናቸውና ።

| | | |
|---|---|---|
| ወዝንቱ ዘትበልዑ እምኵሉ ዘውስተ ማይ ዘቦ ክንፍ ወዘቦ ቅሳር ዘሀሎ ውስተ ማይ ወዘውስተ ባሕር ወዘውስተ አፍላግ ውእቱ ዘትበልዑ ። | ፱ | በውኃ ውስጥ ከሚኖረው ሁሉ የምትበሉት ይህ ነው በውኃና በባሕር ውስጥ የሚኖረውን ክንፍ ገለፈት ያለውን በወንዝም ካለው ሁሉ የምትበሉት ይህ ነው ። |
| ወኵሉ ዘአልቦ ክንፍ ወቅሳር ዘውስተ ማይ ወዘውስተ ባሕር ወዘውስተ አፍላግ ወእምኵሉ ዘይትሐሦ ማይ ወእምኵሉ ነፍስ ሕይወት እንተ ውስተ ማይ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ። | ፲ | ክንፍና ገለፈት የሌለው በውኃ ውስጥ የሚኖረው በባሕርና በፈሳሾች ውስጥ የሚንቀሳቀሰው ውኃው ከሚያስገኘው ሁሉ በውኃው ውስጥ በደማዊት ነፍስ ሕይወት ከምትንቀሳቀስ ከምትኖር ፍጥረት ሁሉ ክንፍ ቅርፊት የሌለው ሁሉ ርኩስ ይሁን ። ዘዳ፣ ፲፬ ፫ ፣ ምዕ፣ ፯ ፲፰ ። |
| ወርኩሰ ይኩንክሙ ፣ እምሥጋሆሙ ኢትብልዑ ወበድኖሙ አስቈርሩ ። | ፲፩ | በናንተ ዘንድ የተጠላ የተጸየፈ ይሁን ከሥጋቸውም አትብሉ ፣ ወደቃቸውንም ተጸየፉት ፣ (አትንኩት) ። |
| ወኵሉ ዘአልቦ ክንፍ ወቅሳር ዘሀሎ ውስተ ማይ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ። | ፲፪ | በውኃ ውስጥ ከሚኖረው ክንፍ ገለፈት (ማጉርጥ) የሌለው ሁሉ በናንተ ዘንድ የተጠላ የተጸየፈ ይሁን ። |
| ወዝንቱ ውእቱ ዘታስቈርሩ እምአዕዋፍ ወዘኢትበልዑ እስመ ርኩስ ውእቱ ንስር ፣ ወግሬጳ ፣ ወአልያጦን ። | ፲፫ | ከወፎችም ወገን የምትጸየፉት የማትበሉት ይህ ነው ንስር ርኩስ ነው ፣ (ግሬጳ) ዘማች አሞራ ፣ (አልያጦን) አበብ ዋጭ አሞራ ። ዘሌዋ፣ ፲፰ ፲፮ ፣ ሕዝ፣ ፴፩ ፱ ። |
| ወጊጳ ፣ ወገላውቃ ፣ ወሆባይ ፣ ወዘአምሳሊሁ ። | ፲፬ | (ጊጳ) አገዳ ሰበር አሞራ ፣ (ገላውቃ) ጫት (አራት ራስ) አሞራ ፣ (ሆባይ) አንጭት አሞራ ይህን የመሰለው ሁሉ ። |
| ወቋዕ ፣ ወኵሉ ዘአምሳሊሁ ። | ፲፭ | (ቋዕ) ቁራ ይህን የመሰለው ሁሉ በየዓይነቱ ። |
| ወሰገኖ ወኵሉ ዘአምሳሊሁ ፣ ወለሮን ፣ ወዘአምሳሊሁ ፣ ወጉዛ ወዘአምሳሊሁ ። | ፲፮ | (ሰገኖ) ሰጐን ይህን የመሰለው ሁሉ በየዓይነቱ (ለሮን) ይብራ (ጠላቋ) (ጉዛ) ጭልፊት (ጭላት) ይህን የመሰለው ሁሉ በየዓይነቱ ። ኢያ፣ ፴፱ ፴፮ ። ዘፍ፣ ፰ ፯ ። |
| ወጉጋ ፣ ወቅጥራቅጥሬን ፣ ወኢብን ። | ፲፯ | (ጉጋ) ጉጉት ቅጥራቅጥሬን ድምቢጥ (ኢብን) የመስቀል ወፍ ። |
| ወጵርፍያና ፣ ወአድገ መረብ ፣ ወቀቀኖን ። | ፲፰ | (ጵርፍያና) ፍላጹት (ቀይ የውኃ ዶሮ) አድገ መረብ (ቀቀኖ) ጋጋኖ ። መዝ፣ ፻፪ ፯ ፣ ሶፎ፣ ፪ ፲፬ ። |
| ወአሮድዮን ፣ ወከራድዮን ፣ ወሄጳጳ ወጵግነት ። | ፲፱ | (አሮድዮን) አፈ ያሬድ ወይም ሲላ አሲዳ (ከራድዮን) ነጭ ወፍ ወይም ሰቢሳ ሽመላ (ሄጳጳ) ጥምብ አሞራ ፣ ወይም እንድርማሚት ጳግነት የሌሊት ወፍ ናቸው ። |
| ወኵሉ ዘይትሐወስ እምአዕዋፍ ዘየሐውር በአርባዕቱ እግሩ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ። | ፳ | በምድር ላይ የሚንቀሳቀሰው ሁሉ በክንፍ ከሚበር ወፍ ጀምሮ በአራት እግር እስከሚሽከረከር ትላትል ሁሉ በናንተ ዘንድ የተጠላ የተጸየፈ ይሁን ። |
| አላ ዝንቱ ውእቱ ዘትበልዑ እምዘይትሐወስ እምአዕዋፍ ዘየሐውር በአርባዕቱ እግሩ ዘቦ አገዳ መልዕልተ እገሪሁ በዘይሠርር መልዕልተ ምድር በቱ ። | ፳፩ | ከሚንቀሳቀሱ ወፎች ወገን የምትበሉት ይህ ነው ፣ በአራት እግሩ የሚሄደው በምድር ላይ በሚበርበቸው ሽብረክ ብሎ በሚዘልበቸው በአራት እግሮቹ ላይ ማጉርጥ ያለው ነው ። |
| ዝንቱ ዘትበልዑ ፣ ወዝንቱ ዘኢትበልዑ እምኔሁ ፣ ደጎብያ ወዘአምሳሊሁ ፣ ወአቃጣን ወዘአምሳሊሁ ፣ ወአፍዮማክን ፣ ወዘአምሳሊሁ ፣ ወአንበጣ ወዘአምሳሊሁ ። | ፳፪ | ከሱ የምትበሉት ይህ ነው ፣ የማትበሉትም ይህ ነው (ደጎብያ) ኩብኩብ የሚመስለው (አቃጣን) ፊንጣ የሚመስለው (አፍዮ ማክን) አሽን የሚመስለውም አንበጣ የሚመስለው ። ኢዮ፣ ፩ ፬ ፣ ማቴ፣ ፫ ፬ ፣ ማር፣ ፩ ፯ ። |
| ወእምዘ ይሠርር በአርባዕቱ እገሪሁ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ፣ ወበሙ ትረኵሱ ። | ፳፫ | በአራት እግሩ የሚሽከረከረው ሁሉ ለናንተ ርኩስ ነው በነሱቸውም ትረክሳላችሁ ። |
| ወኵሉ ዘገሠሠ በድኖሙ ርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ። | ፳፬ | ውዳቂያቸውን የነካ የዳሰሰ ሁሉ እስከ ሠርክ (ማታ) ርኩስ ነው ። |
| ወኵሉ ዘአልዓለ በድኖሙ ይሕፅብ አልባሲሁ ፣ ወርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ። | ፳፭ | ውዳቂያቸውንም የነሣ ሁሉ ልብሱን ያጠብ ፣ እስከ ሠርክም ርኩስ ነው ። ዘሌ፣ ፲፩ ፴፰ ፣ ፲፫ ፮ ። |
| ወእምኵሉ እንስሳ ዘንቁቅ ሰኰናሁ ፣ ወሥጡቅ ዕፈሪሁ ወዘኢያመስኵዕ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ፣ ወኵሉ ዘገሠሠ በድኖሙ ርኩስ ውእቱ ። | ፳፮ | ከእንስሳም ሁሉ ሰኰናው የተከፈለው ጥፍሩ የተሰነጠቀው የማያመሰኳው ለናንተ ርኩስ ነው ፣ ውዳቂያቸውንም የነካ ሁሉ ርኩስ ነው ። |

| | | |
|---|---|---|
| ወኵሉ ዘየሐውር በእደዊሁ እምኵሉ አራዊት ዘየሐውር በአርባዕቱ አገሪሁ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ፤ ወኵሉ ዘገሠሠ በድኖሙ ርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ። | ፳፯ | ከአራዊት ወገን ሁሉ በእጁና በመዳፉ በአራት እግሩ የሚሄደው ሁሉ ለናንተ ርኩስ ነው ፤ ሬሳቸውንም የዳሰሰ ሁሉ እስከ ማታ ርኩስ ነው ። |
| ወዘፆረ በድኖሙ ይሕፅብ አልባሲሁ ወርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ። | ፳፰ | ወደቃቸውን የተሸከመ ልብሶቹን ይጠብ ፤ እስከ ማታም ርኩስ ነው ። |
| ወዝንቱ ዘርኩስ ውእቱ ለክሙ እምዘይትሐወስ ውስተ ምድር ። | ፳፱ | በደማዊት ነፍስ ሕይወት የሚኖረው ተንቀሳቃሽ ወገን ሁሉ ይህ ለናንተ ርኩስ ነው ። ፩ ሳሙ፡ ፲ ፬ ። |
| አንጺዋ ፤ ወጽቍጽቋን ፤ ወሐርገጽ ፤ ወለጽቂት ፤ ወሐንጾን ፤ ወሀንገግ ፤ ወጋሌ ፤ ወከሜሌዎን ፤ ወሰሰሳክስስ ። | ፴ | (እንሺዋ) ኢጺጥ (ጽቍጽቋን) ፈልፈል አዞ (ላጽቂት) እንሽላሊት (ሐንጾን) እንዝዝ (ዓንጎግ) ጉማሬ ፤ (ጋሌ) ጉብና (ከሜሌዎን) እንቃቅላ ፤ (ሰሰሳክስስ) እስስት ናቸው ። |
| ዝንቱ ዘርኩስ ለክሙ ፤ እምኵሉ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር ወኵሉ ዘገሠሠ በድኖሙ ርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ። | ፴፩ | በምድር ላይ ተሐውሶ ያለው ሁሉ ለናንተ ርኩስ ነው ወደቃቸውንም የዳሰሰ ሁሉ እስከ ማታ ርኩስ ነው ። |
| ወኵሉ ዘወድቀ በድኖሙ ላዕሌሁ ርኩስ ውእቱ ። | ፴፪ | ሬሳቸው የወደቀበትም በቃ ሁሉ ርኩስ ነው ። |
| እምኵሉ ንዋየ ዕፅ ፤ ወእመኒ ልብስ ፤ አው ማእስ ፤ አው ሐሰል ፤ ወእምኵሉ ንዋይ ዘይገብሩ ቦቱ ግብረ ውስተ ማይ ይተምዕዎ ፤ ወርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ፤ ወእምዝ ንጹሕ ውእቱ ። | ፴፫ | የዕንጨት ዕቃ (እንደ ሰደቃ ገበታ) ከልብስ ፤ ከቈርበት ከረጢት (እንደ ዳውላ አቍማዳ) ቢሆን ሥራ የሚሠሩበት ዕቃ ሁሉ ከውኃ ይንከሩት እስከ ሠርክም ርኩስ ነው ፤ ከዚያ በኋላ ግን ንጹሕ ነው ። ዘሌዋ፡ ፲፭ ፲፪ ። |
| ወኵሉ ንዋየ ልሕኵት ዘወድቀ ላዕሌሁ እምዝንቱ ኵሉ ውስተ ከርሡ ፤ እምከመ ውስተ ውስጡ ወድቀ ርኩስ ውእቱ ፤ ወይሰብርዎ ። | ፴፬ | ከዚህ (ከወደቀው) በውስጡ የወደቀበት የሸክላ ዕቃ ሁሉ የወደቀበትም በውስጡ ያለው ነገር ሁሉ ርኩስ ነውና ሸክላውን ይሰበሩት ። ምዕ፡ ፳፰ ። |
| ወኵሉ በዘትበልዑ እክለ ፤ ወእመኒ ዘተወድየ ውስቴቱ ማየ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ፤ እመኒ ንዋየ ስቴ በዘቦቱ ትሰትዩ ርኩስ ውእቱኒ ። | ፴፭ | እህልም የምትበሉበት ዕቃ ሁሉ ውኃንም በምትቀዱበት (እንስራ ማድጋ) ላይ ቢወድቅበት ለናንተ ርኩስ ነው ፤ የምትጠጡበት የመጠጥ ዕቃም (ብርሌ ብርጭቆ) ቢሆን ርኩስ ነው ። |
| ወኵሉ ዘወድቀ ላዕሌሁ በድኖሙ ርኩስ ውእቱ ፤ ወእመሰ እቶን ፤ አው መንበረ መቅጹት ትነሥትዎ ፤ እስመ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ። | ፴፮ | በድናቸው የወደቀበትም ሁሉ ርኩስ ነው ፤ ምድጃም ቢሆን የድስት ማስቀመጫም ቢሆን ርኩስ ነውና አፍርሱት ። |
| ዘእንበለ አንቅዕተ ማያት ወዐዘቃት ወአዕያጋተ ማእት ፤ ወዝንቱ ዘንጹሕ ለክሙ ። | ፴፯ | ከጕድጓዱና ከውኃው ምንጭ አልፎ አልፎ ውኃ ከሚቆምበት ኩሬ በቀር ይህ ለናንተ ንጹሕ ነው ። |
| ወእመሰ ወድቀ በድኖሙ ላዕለ ዘርእ ዘይዘራእ ንጹሕ ውእቱ ። | ፴፰ | ጥምባቸው በሚዘራው ዘር ሁሉ ቢወድቅበት ግን ንጹሕ ነው ፤ (አያረክሰውም) ። ዘፍ፡ ፩ ፲ ፤ ዘፀ፡ ፯ ፲፬ ። |
| ወእመሰ ተከዕወ ማይ ላዕለ ኵሉ ዘርእ ዘወድቀ በድኖሙ ላዕሌሁ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ። | ፴፱ | ነገር ግን እኽ (ውኃ) በሚዘራው ዘር ሁሉ ላይ ቢፈስበት ከዚህ በኋላ በድናቸው ቢወድቅበት ይህ ለናንተ ርኩስ ነው ፤ (በድኑ በወደቀበት ላይ ዘሩን አይዝሩ) ። |
| ወእመቦ ዘሞተ እምእንስሳ ዘይከውነክሙ ለበሊዕ ዘገሠሠ በድኖሙ ርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ። | ፵ | ልትበሉት ከሚገባችሁ እንስሳ ወገን የሞተ ቢኖር በድናቸውን የነካ እስከ ሠርክ ድረስ ርኩስ ነው ። |
| ወዘበልዐ ማውታሁ ይሕጽብ አልባሲሁ ወይትሐፀብ ሥጋሁ በማይ ፤ ወርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ወዘአልዐለ በድኖሙ ይሕፅብ አልባሲሁ ፤ ወርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ፤ | ፵፩ | ሙቶ ያደረውን በክቱን የበላ ሰው ልብሱን ይጠብ ፤ ሰውነቱንም በውኃ ይጠብ ፤ እርሱም እስከ ሠርክ ድረስ ርኩስ ነው ፤ ወደቃቸውንም ያነሣ ልብሱን ይጠብ ፤ እስከ ማታም ርኩስ ነው ። ምዕ፡ ፳፪ ፰ ፤ ዘዳ፡ ፲፬ ፳፩ ። |
| ወኵሉ አርዌ ዘይትሐወስ ውስተ ምድር ርኩስ ውእቱ ለክሙ ፤ ወኢትብልዕዎ ። | ፵፪ | በምድር ላይ በልቡ የሚሳበው የሚንቀሳቀሰው አውሬ ሁሉ ለናንተ ርኩስ ነው ፤ (አትብሉት) ። ዘፀ፡ ፲፩ ፳፱ ። |
| ወለኵሉ ዘየሐውር በከብዱ ኢትብልዕዎ ፤ ወለዘየሐውር በአርባዕቱ እግሩ ፤ ወለዘብዙኅ አገሪሁ እምኵሉ አርዌ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር ኢትብልዕዎ ፤ እስመ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ። | ፵፫ | በሆዱ የሚሳበውን በአራት እግሩ የሚሄደውን እግሩ ብዙ የሆነውን (እንደ ሺ እግር) በምድር ላይ ከሚሳበውና ከሚንቀሳቀሰው አውሬ (ትላትል) ሁሉ ለናንተ ርኩስ ነውና አትብሉት ። ዘፍ፡ ፫ ፲፬ ። |
| ወኢታርኵሱ ነፍሰክሙ በኵሉ አራዊት ዘይትሐወስ ውስተ ምድር ፤ ወኢትርኰሱ በእሉ ፤ ወኢትኩኑ ርኩሳነ በሙ ። | ፵፬ | በዚህ ዓለም በሚንቀሳቀሱት አውሬዎች (ትላትሎች) ሰውነታችሁን አታሳድፉ ፤ በነዚህ አትርከሱ ፤ በነሳቸው ርኩሳን አትሁኑ ። ምዕ፡ ፳ ፳፭ ። |

| | | |
|---|---|---|
| እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ፤ ወተቀደሱ ወቅዱሳነ ኩኑ፤ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ቅዱስ አነ፤ ወኢታገምኑ ነፍሰክሙ በኵሉ አራዊት ዘይትሐወስ ውስተ ምድር ። | ፵፬ | ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ንጹሕ ነኝና ንጹሐን ሁኑ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ንጹሕ ነኝና እናንተም ንጹሐን ሁኑ፤ በምድር ላይ በሚኖረው አውሬ ሁሉ ሰውነታችሁን አታሰድፉ ። ዘፀ፥ ፲፱ ፮፤ ፩ ጴጥ፥ ፩ ፲፮ ። |
| እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ዘአውጻእኩክሙ እምድረ ግብጽ ከመ እኩንክሙ አምላክክሙ፤ ወትኩኑ ቅዱሳነ፤ እስመ ቅዱስ አነ ። | ፵፭ | ፈጣሪያችሁ እንደመሆኔ ከግብጽ አገር ያወጣኋችሁ እኔ እግዚአብሔር ንጹሕ ነኝና እናንተም ንጹሐን ሁኑ ። ዘፍ፥ ፴፭ ፩፤ ዘፀ፥ ፮ ፯ ። |
| ዝውእቱ ሕግ ዘበእንተ እንስሳ ወዘበእንተ አዕዋፍ ወዘበእንተ አራዊት ወዘበእንተ ኵሉ ነፍስ እንተ ትትሐወስ ውስተ ማይ ወውስተ ምድር ። | ፵፮ | ስለ እንስሳና ስለ አዕዋፍ ስለ አራዊትና በውኃ ውስጥ ስለምትንቀሳቀሰው ፍጥረት ሁሉ የተሠራ ሕግ ይህ ነው ። |
| ዘይፈልጥ ማእከለ ርኩሳን ወማእከለ ንጹሐን ወታሌብዎሙ ለደቂቀ እስራኤል እምኵሉ ሕያው ዘኢይበልዑ ወዘይበልዑ ። | ፵፯ | ከሚበሉትና ከማይበሉት ሕያዋን ሁሉ በርኩሳንና በንጹሐን መካከል የሚለየውን ለእስራኤል ልጆች አስረዳቸው (ንገራቸው) ። |
| ምዕራፍ ፲፪ ። | | ምዕራፍ ፲፪ ። |
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፤ በሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ወንግሮሙ እንዘ ትብል ። | ፩ | እግዚአብሔር ሙሴን ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው ብሎ ተናገረው ። |
| ብእሲት እመ ፀንሰት ወወለደት ተባዕተ ርኵስት ይእቲ እስከ ሰቡዕ ዕለት፤ በከመ መዋዕለ ትክቶሃ ። | ፪ | ሴት ፀንሳ ወንድ ልጅ ብትወልድ እንደ ግዳጅዋ ወራት እስከ ሰባት ቀን ድረስ የረከሰች ናት ። ዘሌ፥ ፲፭ ፲፱ ። |
| ወበሳምንት ዕለት ታገዝሮ ከተማ ነፍስቱ ። | ፫ | በስምንተኛውም ቀን የሰውነቱን ሰንኰፍ ታስገዝረው። |
| ወሠላሳ ወሠለስተ ዕለተ ትንበር በእንተ ደማ ለንጺሖታ እምኵሉ ርኵስ ወእምኵሉ ቅዱስ ኢትግሥሥ፤ ወቤተ መቅደስ ኢትባእ እስከ ትፌጽም መዋዕለ ንጽሓ ። | ፬ | ስለ ደሟ ከረከሰው ሁሉ መንጻት የሚገባት ስለሆነ፥ ሠላሳ ሦስት ቀን ከሰው ተለይታ ትቀመጥ፤ አርበው ቀን እስኪፈጸም ድረስ የነጻውን ሁሉ አትንካ፤ የንጽሕናዋን ወራት እስክትጨርስ ድረስ ወደ መቅደስ አትግባ ። |
| ወእመሰ ወለደት አንስተ ርኵስት ይእቲ ዐሠርተ ወአርባዕተ መዋዕለ በከመ ትክቶሃ፤ ወስሳ ወስድስተ ዕለተ ትነብር በእንተ ደማ ለንጺሖታ ። | ፭ | ሴት ልጅ ብትወልድ ግን እንደ ግዳጅዋ ወራት ዐሥራ አራት ቀን የረከሰች ናት፤ ስለ ደሟ ንጽሕና የሚያሻት ስለሆነ ስሳ ስድስት ቀን ከሰው ተለይታ ትቀመጥ ። |
| ወአመ ተፈጸመ መዋዕለ ንጽሓ እመኒ በእንተ ወልድ ወእመኒ በእንተ ወለት ታመጽእ በግዐ ዘዓመት ለመሥዋዕት ። | ፮ | የንጽሕናዋም ወራት በተፈጸመ ጊዜ ስለ ወንድ ልጅም ቢሆን ስለ ሴት ልጅም ቢሆን አንድ ዓመት የሆነውን በግ ታምጣ ። |
| ወእመኒ እጕለ ርግብ፤ አው ዘማዕነቅ በእንተ ኃጢአት ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ኀበ ካህን ። | ፯ | ስለ ኃጢአት ከርግብ ወገንም ቢሆን ከዋኖስ ወገንም ቢሆን ካህን ወዳለበት ወደ ደብተራ ኦሪት ደጃፍ ታምጣ። |
| ወያበውእ ካህን ቅድመ እግዚአብሔር ወያስተሠሪ ላቲ ካህን ወያነጽሓ እምነቅዐ ደማ ዝንቱ ውእቱ ሕጉ ለእንተ ትወልድ፤ እመኒ ተባዕተ ወእመኒ አንስተ ። | ፰ | ካህኑም በእግዚአብሔር ፊት አቅርቦ ኃጢአቷን ያስተሥርይላት ከደሟም ያንጻት ወንድ ወይም ሴት ልጅ ለምትወልድ ሴት ሕጉ ሥራቱ ይህ ነው ። ዘሌ፥ ፳ ፲፰ ። |
| ወእመሰ አልቦቲ ውስተ እዴሃ ወኢተአክል ለበግዕ፤ ታመጽእ ክልኤተ ማዕነቀ፤ አው ክልኤተ እጕለ ርግብ፤ አሐዱ ለመሥዋዕት ወአሐዱ ዘበእንተ ኃጢአት፤ ወያስተሥሪ ላቲ ካህን ወትነጽሕ ። | ፱ | ነገር ግን በእጅዋ ገንዘብ ባይኖራት ለበግ መግዣም ባይበቃት ሁለት የርግብ ግልገሎች ወይም ሁለት ዋኖሶች አንዱን ለመሥዋዕት አንዱን ስለ ኃጢአት ታምጣ፤ ካህኑም ከኃጢአቷ ያንጻት፤ ኃጢአቷንም ያስተሥርይላት ። |
| ምዕራፍ ፲፫ ። | | ምዕራፍ ፲፫ ። |
| ወነበበሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ወይቤሎሙ፤ እመቦ ብእሲ ዘወጽአ ውስተ ኀብረ ማእሱ ትእምርት ከመ ርምየት ወፃዕደወት ወኮነት ውስተ ማእሱ ኀብረ ለምጽ ለይሑር ኀበ አሮን አው ኀበ አሐዱ እምደቂቁ ካህናት ። | ፩ | እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን ተናገራቸው እንዲህም አላቸው በሰውነቱ እንደ እትራት (መፈቃት መበጣት) የወጣበት ሰው ቢኖር ብትነጣ በሥጋው ቊርበት ላይ የለምጽ መልክ ብትሆን ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ አሮን ይሂድ ወይም ከካህናት ልጆቹ ወደ አንዱ ይሂድ ። |
| ወይርአያ ካህን ለይእቲ ኀብር እንተ ውስተ ኀብረ ማእሱ እመ ተወለጠ ሥዕርታ ለይእቲ ኀብር ወፃዕደወት ። | ፪ | በገላው መልክ ላይ ያለችውን ያችን መልክ ካህን ይያት የዚህች ቍስል መልክ ጠጕሯ ለውጦ ብትነጣ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ወእመኒ እኩይ ርእየታ ለይእቲ ኀብር ዘውስተ ኀብረ ማእሱ ወኀብረ ለምጽ ይእቲ፤ ይርአያ ካህን ወያርኵሳ ። | ፫ | በገላው መልክ ላይ ያለችው የዚች መልክ መታየቷ ክፉ ቢሆን ካህን አይቶ ርኩስ ነህ ይበለው ። |
| ወእመሰ ፀዓዳ ኀብር ይእቲ ውስተ ኀብረ ማእሱ ወኢ ከነ እኩየ ርእየታ፤ ወኢተወለጠ ሥዕርታ ወኢፃዕደወ ወይእቲኒ ኢታስተርኢ በሕቁ፤ ያጽንሖ ካህን ሰቡዐ ዕለተ በእንተ ይእቲ ኀብር ። | ፬ | በገላው መልክ ያለች ይህች ቍስል ነጭ ብትሆን መልኳ ተለይቶ ባይታወቅ፤ የጠጕሯም መልክ ባይለወጥ ነጭ ሆናም ብትታይ ይህችውም ፈጽማ ጐልታ ብትታይ ካህን ስለዚያች መልክ ሰባት ቀን ያቈያት (ሰውየውን ሰባት ቀን ዘግቶ ያስንብተው) ። |
| ወበሳብዕት ዕለት ይሬእያ ካህን ለይእቲ ኀብር ወናሁ ሀለወት ዓዲሃ ይእቲ ኀብር ቅድሜሁ ወኢኃደገት ይእቲ ኀብር እማእሱ ያጽንዖ ካህን ካልአ ሰቡዐ ዕለተ ። | ፭ | በሰባተኛውም ቀን ካህን ያችን የለምጽ መልክ ይያት ያች የለምጽ መልክ እነሆ በፊቱ ገና እንደነበረች ብትሆን ያች መልክ ከገላው ባትለይ ምልክት ናትና ካህኑ ሰባት ቀን ያቈየው (ቈይ ይበለው) ። ዘሌዋ፤ ፲፬ ፴፰፤ ፲፬ ፷ ። |
| ወይርአያ ካህን ዳግመ በሳብዕት ዕለት፤ ወናሁ ኢታስተርኢ በሕቁ ይእቲ ኀብር፤ ወኢኀደገት እማእሱ ይእቲ ኀብር ያነጽሖ ካህን እስመ ትእምርት ይእቲ ወየሐጽብ አልባሲሁ ወንጹሐ ይከውን ። | ፮ | ዳግመኛ በሰባተኛው ቀን ካህኑ ይያት፤ ያች መልክ ጐልታ ባትታይ ያች የለምጽ ምልክት ከገላው ባትጠፋ ምልክት ናትና ካህን ያንጻት (ንጹሕ ነህ ይበለው) ልብሶቹን ይጠብ፤ ከዚያ በኋላ ንጹሕ ይሆናል ። |
| ወእመሰ ተወለጠት ይእቲ ኀብር ወከነት እኪተ ውስተ ማእሱ እምድኅረ ርእዮ ካህን ወአንጽሖ የሐውር ዳግመ ኀበ ካህን ። | ፯ | ነገር ግን ካህን ካየው በኋላ ያች ምልክት ብትለወጥ በገላውም ላይ ብትሰፋ ዳግመኛ ወደ ካህን ይሂድ ። |
| ወይሬእያ ካህን ወናሁ አከየት ይእቲ ኀብር ውስተ ማእሱ ያረኵሶ ካህን እስመ ለምጽ ይእቲ ። | ፰ | ካህንም ይያት እነሆ ያች የለምጽ ምልክት በቆዳው ላይ ሰፍታ ብትታይ ለምጽ ናትና ካህኑ ርኩስ ነህ ይበለው ። |
| ወኀብረ ለምጽ እመ ወፅአት ላዕለ ብእሲ የሐውር ኀበ ካህን ። | ፱ | የለምጽ ምልክት በሰው ላይ ብትወጣ ወደ ካህን ይሂድ ። ፪ ነገሥ፤ ፭ ፫ ። |
| ወይሬእዮ ካህን ወናሁ ከመ ርእየተ ፀዓዳ ይእቲ ውስተ ማእሱ ወአውጽእት ሥዕርተ ፀዓዳ ውስተ ማእሱ ወጐንደየት ውስተ ሥጋሁ ውስተ ዘዳኅን ኀብረ ማእሱ ይእቲ ትእምርት ፀዓዳ፤ ያረኵሶ ካህን ወኢያነጽሖ እስመ ርኩስ ውእቱ ። | ፲ | ካህን ይየው እነሆም በገላው ላይ እንደ እትራት ያለ ነጭ ብትሆን በሰውነቱ ነጭ ጠጕር ብታወጣ በደህናው አካሉ ላይ ብትዘገይ ባትጠፋ ያች ምልክት ለምጽ ናትና ካህኑ ርኩስ ነህ ይበለው፤ አያንጻው ርኩስ ነውና ። |
| ወእመሰ ወጽአ ለምጽ ውስተ ማእሱ ወከደነ ኀብረ ለምጽ ኵሎ ማእሶ እምርእሱ እስከ እገሪሁ ኵለንታሁ ይሬእዮ ካህን ። | ፲፩ | በሰውነቱ ላይ ለምጹ ሰፍቶ ቢወጣበት ከእግር እስከ ራሱ ድረስ ሁለንተናውን የለምጽ መልክ ቢሸፍነው ካህኑ ይየው ። ዘሌ፤ ፫ ፬፤ ፪ ነገ፤ ፲ ፲፪ ። |
| ወርእዮ ካህን ከመ ከደነ ኀብረ ለምጽ ኵሎ ማእሶ እምርእሱ እስከ እገሪሁ ያነጽሖ ካህን፤ እስመ ኵለንታሁ ተወለጠ ወፃዕደወ ወበእንተ ዝንቱ ንጹሕ ውእቱ ። | ፲፪ | ካህኑ ገላውን ሁሉ ከራስ እስከ እግሩ ለምጽ እንደሸፈነው ካየው በኋላ ንጹሕ ነህ ይበለው፤ ሁለንትና ገላው ተለውጦ ነጭ ሁኗልና፤ ስለዚህ ንጹሕ ነው ። |
| ወበዕለተ አስተርአየ ላዕሌሁ ኀብር ዘዳኅን ይረኵስ ። | ፲፫ | ደኅና በሆነ ሰውነቱም ምልክት በታየበት ቀን ይረክሳል ። |
| ወይሬእዮ ካህን ለውእቱ ኀብር ዘዳኅን ወያረኵሶ ውእቱ ኀብር ዘዳኅን ወበእንተ ዝንቱ ርኩስ ውእቱ፤ እስመ ለምጺ ከነ ። | ፲፬ | ደኅና በሆነ ሰውነቱም ያለ ያንን መልክ ካህን ይየው ደኅና በሆነ ሰውነቱ ያ ያለ ያ መልክ ያረክሰዋል፤ ስለዚህ ለምጽ ሁኗልና ርኩስ ነው ። ዘዳ፤ ፳፬ ፰ ። |
| ወእመሰ ኃደጎ ውእቱ ኀብር ዘዳኅን ወተወለጠ ወኢፃዕደወ የሐውር ኀበ ካህን ። | ፲፭ | ደኅና በሆነ ሰውነቱ ያለ ያ መልክ ቢተወው ወደ ለምጽነት ቢለወጥ ባይነጣም ወደ ካህን ይሂድ ። |
| ወይሬእዮ ካህን ወናሁ ኢተወለጠት ይእቲ ኀብር ወኢፃዕደወት ያነጽሖ ካህን ለይእቲ ኀብር፤ እስመ ንጹሐ ከነ ። | ፲፮ | ያች መልክ ወደ ነጭነት የተመለሰች እንደሆነ ካህን አይቶ ያችን መልክ ያንጻት ንጹሕ ሁኗልና ። |
| ወለእመ ፈርገገ ሥጋ ውስተ ርምየተ ቍስሉ ሐይዎ ወወፅአ ውስተ ውእቱ መካነ ቍስሉ ፀዓዳ ከመ ርምየት እንተ ታስተርኢ ፀዓድዒድ አው ቀያሕይሕተ ያሬእዮ ለካህን ። | ፲፯ | ከዳነም በኋላ በቍስሉ እትራት ላይ እንደገና ቢያትር በት (ቢሰፋ) ነጭ ወይም ቀይ ሁና እንደምትታይ እትራት ዝንጕርጕር በቍስሉ ቦታ ቢወጣበት ለካህን ያሳየው ። |
| ወርእዮ ካህን ወናሁ እኪት ይእቲ እማእሱ ወሥዕርታኒ ተወለጠ ወፃዕደወ ያረኵሶ ካህን ። | ፲፰ | ካህኑ አይቶ እነሆ ወደ ቆዳው ውስጥ ጠልቃ ብትሰፋ ጠጕሯም ተለውጦ ወደ ነጭነት ቢመለስ ካህኑ ርኩስ ነህ ይበለው ። ዘዳ፤ ፳፰ ፳፯፤ ፪ ነገ፤ ፳ ፯ ። |
| እስመ ኀብረ ለምጽ ይእቲ ወውስተ ርምየት ወፅአት ። | ፲፱ | የለምጽ ምልክት ናትና በእትራት ላይ ወጥታለችና ። |
| ወእመሰ ርእዮ ካህን ከመ አልቦ ውስቴታ ሥዕርት ፀ | ፳ | ነገር ግን ካህኑ በቍስሉ ቦታ ላይ ነጭ ጠጕር እንደ |

| | | |
|---|---|---|
| ዓዳ ፡ ወኢኮነት እኪተ ውስተ ኅብረ ማእሱ ወለሊሃኒ ኢታስተርኢ ያጸንሖ ካህን ሰቡዐ ዕለተ ። | ፳፩ | ሌላ አይቶ በገላውም ላይ እንዳልሰፋች ቢያይ እጸም ብትታይ ካህን ሰባት ቀን ያቈየው ። |
| ወለእመ ተክዕወት ውስተ ማእሱ ያረኵሶ ካህን እስመ ኅብረ ለምጽ ይእቲ ፡ ወውስተ ርምየት ወዕአት ። | ፳፪ | በሰውነቱ ላይ ብትሰፋ የለምጽ ምልክት ናትና በአትራትም ላይ ወጥታለችና ካህን ርኩስ ነህ ይበለው ። |
| ወእመሰ በመከና ነበረት ይእቲ ኅብር ወኢተከሰወት ርምየተ ቍስል ይእቲ ያነጽሖ ካህን ። | ፳፫ | ያች የለምጽ መልክ በበታዋ ፀንታ ወደ ሌላ በታ ባትሰፋ የቍስል እትራት (መዳ ጠባሳ) ናትና ካህን ያንጻት ፥ ንጹሕ ነህ ይበለው ። ማቴ፡ ፰ ፬ ፡ ሉቃ፡ ፭ ፲፬ ፡ ፲፯ ፲፬ ። |
| ወለእመ ፈርገገ ሥጋሁ እማእሱ እመኒ ውስተ ውዕየተ እሳት ወወዕአት ውስተ ማእሱ ዘዳኅን እምውዕየተ እሳት ወአስተርአየት ኅብር እንተ ታቀየሐይሕ አው ፀዓይዓዴ ይሬእያ ካህን ። | ፳፬ | በቆዳው ላይ አልፎ አልፎ አንደ ነቍጣ ቢያትርበት የእሳት እትራትም ቢሆን በእሳቱ እትራት በታ ነጭ ወይም ቀይ ቋቍቻ የሆነች መልክ ብትታይ ካህን ይያት ። |
| ወናሁ ወለጠት ኅብረ ፀዓዳ ወሥዕርተ ፥ ወአስተርአየት ወርእየታኒ እኩይ እማእሱ ለምጽ ይእቲ ፡ ወውስተ ውዕየት ወጽአት ፥ ያረኵሳ ካህን እስመ ኅብረ ለምጽ ይእቲ ። | ፳፭ | እነሆም ነጭ መልክ ነጭ ጠጕር ለውጣ ብትታይ መልኳም ከሰውነቱ ሰፍቶ ቢታይ ለምጽ ናት በእሳቱም እትራት ላይ ወጥታለችና የለምጽም መልክ ናትና ካህን ርኩስ ነህ ይበለው ። |
| ወእመሰ ርእዮ ካህን ወናሁ አልቦ ውስቴታ ሥዕርት ፀዓዳ ዘያስተርኢ ፥ ወኢኮነት እኪተ እማእሱ ወለሊሃኒ ኢታስተርኢ ፡ ያጸንሖ ካህን ሰቡዐ ዕለተ ። | ፳፮ | ካህኑም አይቶ እነሆ የሚታይ ነጭ ጠጕር በውስጧ ባይኖር በሰውነቱ ላይ ሰፍታ ባትታይ ካህን ሰባት ቀን ያቈየው ። |
| ወይሬእያ ካህን በሳብዕት ዕለት ፡ ወለእመ ተክዕወት ውስተ ማእሱ ያረኵሶ ካህን እስመ ኅብረ ለምጽ ይእቲ ፡ ወውስተ ውዕየት ወጽአት ። | ፳፯ | በሰባተኛውም ቀን ካህን ይያት ከቆዳው በላይ ብትሰፋ ካህን ርኩስ ነህ ይበለው ፥ የለምጽ ምልክት ናትና በእሳቱ ጠባሳ ላይ ወጥታለችና ። ኤር፡ ፲፫ ፲፪ ። |
| ወእመሰ በመከና ነበረት ይእቲ ኅብር ወኢተክዕወት ውስተ ማእሱ ወለሊሃኒ ኢታስተርኢ ርምየተ ውዕየት ይእቲ ወያነጽሖ ካህን ፡ እስመ መከነ ውዕየት ይእቲ ። | ፳፰ | ያች ቋቍቻ በበታዋ ላይ ባትቆም በሰውነቱም ላይ ባትሰፋ እጸ.ም ባትታይ የትኩሳት እባጭ ናት ፡ ካህን ንጹሕ ነህ ይበለው ፡ እሳት ያቃጠለው በታ ናትና ። |
| ወእመበ ብእሲ አው ብእሲት ዘወጽአ ኅብረ ለምጽ ውስተ ርእሱ አው ውስተ ጽሕሙ ይሬእያ ካህን ለይእቲ ኅብር ። | ፳፱ | በሽንጉበቱና በራሱ ላይ የለምጽ መልክ የወጣበት ወንድም ቢኖር ሴት ብትኖር ካህን ያችን መልክ ይያት ። |
| ወናሁ ርእየታ እኩይ እማእሱ ወበ ውስቴታ ሥዕርት ፀዓዳ ቀጣን እንተ ወጽአት ያረኵሶ ካህን ፥ እስመ ትእምርተ ለምጽ ይእቲ ዘርእስ አው ዘጽሕም ። | ፴ | እነሆ በቈዳው ላይ ሰፍታ ብትታይ ከራሱ ከሽንጉበቱ ላይ የበቀለች ቀጭን ብጫ ጠጕር በውስጧ ቢኖር በራሱ ወይም በሽንጉበቱ ያለች የለምጽ ምልክት ናትና ካህኑ ርኩስ ነህ ይበለው ። ዘዳ፡ ፳፬ ፰ ፥ ኢሳ፡ ፫ ፲፯ ። |
| ወእመሰ ርእዮ ካህን ኅብራ ለይእቲ ትእምርት ወኢኮነ እኩየ ርእየታ እማእስ ወሥዕርትኒ ፀዓዳ አልቦ ውስቴታ ያጸንሖ ካህን ሰቡዐ ዕለተ ። | ፴፩ | የምልክቷቱም መልክ ካህን አይቶ ከገላው ላይ ሰፍቶ ባይታይ በውስጧም ነጭ ጠጕር ባይኖር ካህን ይህ ምልክት የወጣበትን ሰው ሰባት ቀን ያቈየው ። |
| ወይሬእያ ካህን በሳብዕት ዕለት ወናሁ ኢተከዕወት ኅብር ወሥዕርትኒ ፀዓዳ አልቦ ውስቴታ ወርእየታኒ ለይእቲ ኅብር ኢኮነ እኩየ እማእሱ ። | ፴፪ | ካህን በሰባተኛው ቀን አይቶ ፡ እነሆ ያች መልክ ካልሰፋች ሰፍቶ ባይታይ ጠጕሩን ይላጭ ። |
| ወሰበ ይትላፀይ ውስተ ይእቲ መከነ ማእሱ ኢትወስእ ይእቲ ኅብር ያጸንሖ ካህን ለይእቲ ኅብር ካልእ ሰቡዐ ዕለተ ። | ፴፫ | በተላጨ ጊዜ ለምጹ ከነበረበት በታ ላይ ያች ለምጽ ባትወጣ ካህን ያችን መልክ ሁለተኛ ሰባት ቀን ያቈያት ፥ (ቈይ ይበለው) ። |
| ወይሬእያ ካህን ለይእቲ ኅብር በሳብዕት ዕለት ወናሁ ኢተከዕወት ይእቲ ኅብር ውስተ ማእሱ እምድኅረ ተላፀየ ወርእየታኒ ኢኮነ እኩየ እማእሱ ያነጽሖ ካህን ፥ ወየሐፅብ አልባሲሁ ወንጹሐ ይከውን ። | ፴፬ | ካህንም በሰባተኛው ቀን ያችን መልክ ይያት ፡ እነሆ ከተላጨ በኋላ ያች መልክ በሰውነቱ ላይ ካልሰፋች መልኳም ከሰውነቱ ተለይቶ ካልታወቀ ካህን ንጹሕ ነህ ይበለው ፥ ልብሱንም ይጠብ ፡ የነጻም ይሆናል ። |
| ወእመሰ ተከዕወት ኅብር ውስተ ማእሱ እምድኅረ አንጽሖ ይሬእዮ ካህን ። | ፴፭ | ንጹሕ ነህ ካሉት በኋላ በሰውነቱ ላይ ብትሰፋ ግን ካህን ይየው ። |
| ወናሁ ተከዕወት ይእቲ ኅብር ውስተ ማእሱ ኢይፈትን ካህን ሥዕርተ ፀዓዳ እስመ ርኩስ ውእቱ ። | ፴፮ | እነሆ ያች መልክ በሰውነቱ ከሰፋች ርኩስ ነው ፥ ካህን ነጭ ጠጕር አይመርምር ርኩስ ነውና ። |

| | | |
|---|---|---|
| ወእመሰ ውስተ መከና ነበረት ይእቲ ኀብር ወሥዕርትኒ ጸሊም ወፅአ ውስቴታ ሕያውት ይእቲ ኀብር ወንጹሕ ውእቱ፡ ወያነጽሖ ካህን ። | ፴፯ | ነገር ግን ፡ ያች መልክ በቦታዋ ብትቆም (ብትሰፋ) በውስጧም ነጭ ጠጕር ከበቀለ ያች መልክ ደኅና ናት እሱም ንጹሕ ነውና ካህን ያንጻው ንጹሕ ነህ ይበለው ። |
| ለብእሲኒ አው ለብእሲትኒ እመቦ ዘወፅአ ውስተ ማእሰ ሥጋሁ በራኅርኅት አው በዓድዒድ ይሬእያ ካህን ። | ፴፰ | በወንድም ቢሆን በሴትም ቢሆን በሰውነቱ ላይ ቋቁቻ ወይም የጥቁር ነጭ ነቍጣ የወጣበት ቢኖር ካህን ይያት። |
| ወናሁ ውስተ ማእሰ ሥጋሁ በራኅርኅት አው ፀዓድዒድ ኅንብርብሬ ይእቲ ወፅአት ውስተ ማእሰ ሥጋሁ ንጹሕ ውእቱ ። | ፴፱ | እነሆ በሰውነቱ ቋቁቻ ወይም የነጭ ቀይ የጥቁር ነጭ ዝንጕጕር ብትወጣበት እርሱ ንጹሕ ነው ። |
| ወእመቦ ዘተመልጠ ርእሱ በራኅ ውእቱ ወንጹሕ ውእቱ ። | ፵ | ራሱ የተመለጠ በሃ መላጣ ሰው ቢኖር ግን በራነውና ንጹሕ ነው ። ዘሌዋ፡ ፲፫ ፵፩ ፡ አሞ፡ ፰ ፲ ። |
| ወእመሰ መንገለ ፍጽሙ ተመልጠ ርእሱ ዘስንሒት ውእቱ ወንጹሕ ውእቱ ። | ፵፩ | ራሱ በስተፊቱ በኩል ቢመለጥ ራሰ በራ ፡ ራሰ ሰደዳ ነውና ንጹሕ ነው ። |
| ወእመሰ ወፅአት ውስተ ብርሐቱ ወውስተ ስንሐቱ ኀብር ፀዓዳ አው ቀያሕይሕት ለምጽ ይእቲ ። | ፵፪ | በሰደዳውና በበራው ላይ ነጭ መልክ ወይም ቀይ መልክ ብትወጣ ግን ለምጽ ናት ። |
| ወይሬእያ ካህን ወናሁ ርእየተ ኀብራ ፀዓዳ አው ቀያሕይሕት ውስተ ብርሐቱ አው ውስተ ስንሐቱ ከመ ርእየተ ለምጽ ውስተ ማእሰ ሥጋሁ ፡ ዘለምጽ ውእቱ ብእሲሁ ። | ፵፫ | ካህን አይቷት እነሆ የመልኳ መታየት ነጭ ወይም ቀይ መስሎ እንደሆነ በበራው ወይም በሰደዳው ላይ በቆዳው ላይ የለምጽ ምልክት ወጥቶበት እንደሆነ ያ ሰው ለምጻም ነው ። ሕዝ፡ ፳፪ ፳፯ ። |
| ወምዕረ ይሬእያ ካህን ለይእቲ ኀብር እንተ ውስተ ርእሱ አው እንተ ውስተ ስንሐቱ ። | ፵፬ | ካህን በራሱ ላይ ወይም በሰደዳው ላይ ያለችውን ያችን መልክ አንድ ጊዜ ይያት ። |
| ወለዘለምጽኒ ዘሀለወት ላዕሌሁ ይእቲ ኀብር ዘለምጽ ውእቱ ፍቱሐ ይኩን አልባሲሁ ወርእሱኒ ክሡተ ይኩን ወይገልብብ አፉሁ ወርኩሰ ይሰመይ ። | ፵፭ | የለምጽ ደዌ ያለበት ሰው ልብሱ የተቀደደ ፡ ራሱም የተገለጠ ይሁን ፡ አይከናነብ አፉን ይሸፍን ርኩስ ተብሎ ይጠራ ። ሕዝ፡ ፳፬ ፲፯ ፡ ሚክ፡ ፫ ፯ ፡ ራእ፡ ፳፩ ፬ ። |
| ኵሉ መዋዕለ መጠነ ሀሎ ላዕሌሁ ለምጽ ርኩስ ውእቱ ወዕሉለ ይንበር ፡ ወአፍአ እምትዕይንት ይኩን ምንባሩ ። | ፵፮ | ለምጽ በለበት ዘመን ሁሉ ርኩስ ነው ፡ ከሰው ተለይቶም ለብቻው ይኑር ፡ መኖሪያውም ከከተማ በአፍአ ይሁን ። ዘኁ፡ ፭ ፪ ፡ ፲፪ ፲፬ ፡ ሉቃ፡ ፲፯ ፲፪ ። |
| ወውስተ ልብስኒ እመ ወፅአ ትእምርተ ለምጽ እመኒ ውስተ ልብሰ ፀምር ፡ ወእመኒ ውስተ ልብሰ አጌ ። | ፵፯ | የለምጽም ምልክት በልብስ ላይ ቢወጣ፡ በብዝት ሐር ልብስም ላይ ቢሆን በሻድሬ ልብስ ላይም ቢሆን ቢወጣ ። ዘሌዋ፡ ፲፫ ፶፩ ። |
| እመኒ ውስተ ስፍሑ ወእመኒ ውስቴ ፋእሙ እመኒ ውስተ ፀምር ወእመኒ ውስተ አጌ ወእመኒ ውስተ ማእስ፡ ወእመኒ ውስተ ኵሉ ግብረ ማእስ ። | ፵፰ | በድሩም በማጉም ላይ ቢወጣ በበግ ጠጕር ልብስም ቢሆን በአቍማዳው በዳውላው ወይም በጆንዲው በነቱ በእጐዛው በዓፅፉ በዳባው በደበሎው በቊርበቱ ሥራ ላይ ሁሉ ቢሆን ። ኢሳ፡ ፷፬ ፯ ፡ ዘካ፡ ፫ ፬ ። |
| ወወፅአት ኀብር እንተ ታሕመለምል አው እንተ ታቀየሐይሕ ውስተ ልብሰ ፀምር ወአጌ፡ እመኒ ውስተ ስፍሑ ፡ ወእመኒ ውስተ ፋእሙ ፡ አው ውስተ ማእስ ፡ አው ውስተ ኵሉ ንዋየ ማእስ፡ ወኀብረ ለምጽ ይእቲ ያሬእያ ለካህን። | ፵፱ | አረንጓዴ ወይም ቀይ የምትመስል የለምጽ ምልክት በቀይ ሐር ልብስ ላይ፡ በነጭ ሐር፡ በድሩም በማጉም ቢሆን ወይም በቊርበቱ ፡ ወይም በቊርበቱ ሥራ ሁሉ ላይ ብትወጣ የለምጽ ምልክት ናትና ለካህን ያሳያት ። |
| ወይሬእያ ካህን ለይእቲ ኀብር ወያጸንሐ ሰቡዐ ዕለተ ። | ፶ | ካህንም ያችን የለምጽ ምልክት አይቶ ሰባት ቀን ያቈያት ። |
| ወይሬእያ ካህን በሳብዕት ዕለት ወለእመ ተከዕወት ይእቲ ኀብር ውስተ ውእቱ ልብስ እመኒ ውስተ ስፍሑ ፡ ወእመኒ ውስተ ፋእሙ ፡ አው ውስተ ማእስ ፡ አው ውስተ ኵሉ ንዋየ ማእስ ፡ ለምጽ እንተ ኢትትኃደግ ይእቲ ። | ፶፩ | ካህን በሰባተኛው ቀን ያችን ለምጽ ምልክት ያያል ፡ በዚያ ልብስ ላይ ብትሰፋ በዘሃው በማጉም ቢሆን በቊርበቱና በቊርበቱ ሥራ ሁሉ ላይ ቢሆን የማትለቅ ለምጽ ናት ። ሕዝ፡ ፳፰ ፳፬ ። |
| ያውዕዮ ለውእቱ ልብስ ዘፀምር ፡ ወእመኒ ዘአጌ ፡ ወእመኒ ማእስ ፡ ወለኵሉ ንዋየ ማእስ ውስተ ዘወፅአት ይእቲ ኀብር ፡ እስመ ለምጽ ይእቲ እንተ ኢትትኃደግ በእሳት ያውዕዮ ። | ፶፪ | ያንንም የሱፍ ልብስ በእሳት ያቃጥሉት፡ የተልባ እግር ልብስም ቢሆን የብዝት ልብስም ቢሆን ከቊርበት የተሠራ ዕቃ ሁሉም ቢሆን የማትተው ለምጽ ናትና፡ ያች የለምጽ ምልክት የወጣችበትን ዕቃ ሁሉ በእሳት ያቃጥሉት ። |
| ወእመሰ ርእዮ ካህን ወኢተከዕወት ይእቲ ኀብር ውስ | ፶፫ | ነገር ግን ያች የለምጽ ምልክት በዚያ ልብስ ላይ እን |

ተ ውእቱ ልብስ እመኒ ውስተ ስፍሑ፡ ወእመኒ ውስተ ፋእሙ፡ ወእመኒ ውስተ ኵሉ ንዋየ ማእስ፡ የአዝዝ ካህን ይሕፅቡ ኀበ ወዕአት ይእቲ ኅብር ።

፶፬ ወይጸንሐ ካህን ለይእቲ ኅብር ዳግመ ሰቡዐ ዕለተ ወይሬእያ ካህን ለይእቲ ኅብር እምድኅረ ሐጸብዋ ።

፶፭ ወለእመ ኢኃደጋ ኅብረ ርእየታ ወለእመኒ ተዘርወት ይእቲ ኅብር ርኩስ ውእቱ ወበእሳት ያውዕይዎ፡ እስመ ወዕአት ውስተ ውእቱ ልብስ አው ውስተ ስፍሑ አው ውስተ ፋእሙ ።

፶፮ ወለእመሰ ርእዮ ካህን ኢታስተርኢ ይእቲ ኅብር እምድኅረ ሐፀብዋ ያሴስሉ መከና እምውስተ ውእቱ ልብስ እመኒ እምውስተ ስፍሑ ወእመኒ እምውስተ ፋእሙ፡ ወእመኒ እምውስተ ማእስ ።

፶፯ ወእመሰ ዳግመ አስተርአየት ውስተ ውእቱ ልብስ እመኒ ውስተ ስፍሑ፡ ወእመኒ ውስተ ፋእሙ እምውስተ ኵሉ ንዋየ ማእስ፡ ለምጽ ይእቲ ወበእሳት ያውዕይዎ ለዘ ውስቴቱ ወዕአት ይእቲ ኅብር ።

፶፰ ወለእመሰ ተሐጺቦ ውእቱ ኅብር እመኒ ዘውስተ ስፍሑ፡ ወእመኒ ዘውስተ ፋእሙ ወእመኒ ውስተ ኵሉ ንዋየ ማእስ፡ ኃደገቶ ይእቲ ኅብር የሐጽብዎ ዳግመ ወንጹሐ ይከውን ።

፶፱ ዝንቱ ውእቱ ሕጉ ለዘኅብረ ለምጽ ዘይወፅእ ውስተ ልብስ እመኒ ዘፀምር፡ ወእመኒ ዘአጌ፡ እመኒ ውስተ ስፍኑ፡ ወእመኒ ውስተ ፋእሙ ወእመኒ ዘውስተ ኵሉ ንዋይ ዘማእስ በዘያነጽሕዎ ወበዘያረኵስዎ ።

ምዕራፍ ፲፬ ።

፩ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፡ ዝንቱ ውእቱ ሕጉ ለዘለምጽ በዕለተ ነጽሐ የሐውር ኀበ ካህን ።

፪ ወይወፅእ ካህን አፍአ እምትዕይንት ወይሬእዮ ካህን ወናሁ ኀደገ ኅብረ ለምጹ ለዘለምጽ ።

፫ ወሐዊሮ ኀቤሁ ካህን ያመጽእ ውእቱ ዘነጽሐ ክልኤተ ደዋርሀ ሕያዋተ ወንጹሐተ ወዕፀ ጽሕድ ወለየ ክዑበ ወቈጽለ ሁስጼ ።

፬ ወይኤዝዝ ካህን ይጥብሕዋ ለአሐቲ ዶርሆ ውስተ ማይ ጥዑም ውስተ ንዋየ ልሕኵት ።

፭ ወይነሥአ ካህን ለካልእት ዶርሆ እንተ ሕያውት፡ ወለዕፀ ጽሕድ ወለለይ ክዑብ፡ ወለቈጽለ ሁስጼ ።

፮ ወይጠምዖሙ በደማ ለእንታክቲ ዶርሆ እንተ ጠብሕዋ ውስተ ማይ ጥዑም ወይነዝኆ ስብዓ ለውእቱ ዘነጽሐ እምለምጽ ወንጹሐ ይከውን ።

፯ ወይፌንዋ ለዶርሆ እንተ ሕያውት ውስተ ገዳም ወየሐጽብ አልባሲሁ ውእቱ ዘነጽሐ ወይትላጸይ ኵሎ ሥዕርቶ ወይትሐፀብ በማይ፡ ወንጹሐ ይከውን ።

ዳልሰፋች በድሩም በማጉም ቢሆን ከቁርበት በተሠራም ዕቃ ሁሉ ላይ ቢሆን ካህን ያች የለምጽ ምልክት ያለች በትን ያጥቡ ዘንድ እጠቡ ብሎ ይዘዝ ።

ካህን ያች የለምጽ ምልክት ያለችበትን ልብስ ዳግመኛ ሰባት ቀን ያቈያት፡ ካጠቧትም በኋላ ካህኑ ያችን የለምጽ ምልክት ይያት ።

የመታየቷ ምልክትም በይለቅ ያችም የለምጽ ምልክት ብትሰፋ ያ ልብስ ርኩስ ነውና በእሳት ያቃጥሉት፡ በዚያ ልብስ በድሩም በማጉም መጥታለችና ።

ካህኑ ያችን የለምጽ ምልክት ካጠቡዋት በኋላ እንዳልሰፋች ቢያይ ግን፡ ከወጣችበት ልብስ ከዘሃውም ቢሆን ከማጉም ቢሆን ከጀንዲውም ላይ ቢሆን የለምጽ ምልክት የታየበትን በታ ቀደው ያርቁ (ያውጡ) ።

ዳግመኛ በዚያ ልብስ ላይ ወጥታ የታየች እንደሆነ በዘሃው በማጉም ላይ ቢሆን ከቁርበት በተሠራው ዕቃ ሁሉ ላይም ቢሆን ለምጽ ናትና፡ ያች የለምጽ ምልክት የወጣችበትን በታ በእሳት ያቃጥሉት ።

ያ ልብስ ከታጠበ በኋላ ድሩንም ማጉንም ቢሆን የቁርበቱን ዕቃ ሁሉም ቢሆን ያች የለምጽ ምልክት ብትተወው ዳግመኛ ይጠቡት ንጹሕ ይሆናል ።

በልብስ ላይ የሚወጣው የለምጽ ምልክት ሕጉ ሥርዓቱ ይህ ነው፡ ከበግ ጠጕር የተሠራ ፀምርም ቢሆን ከተልባ እግር የተሠራም ቢሆን በዘሃውና በማጉም በቈርበቱ ዕቃም ቢሆን በሚያነጹት በሚያረክሱት ገንዘብ የለምጽ ምልክት ለወጣበት ሕጉ ሥርዓቱ ይህ ነው ።

ምዕራፍ ፲፬ ።

እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው እንዲህም አለው፤ ለምጽ ለያዘው ሰው ሕጉ ሥራቱ ይህ ነው፡ ከለምጽ በነጻበት ቀን ወደ ካህን ይሂድ ። ማቴ፡ ፰ ፪ - ፬ ።

ካህኑ ከከተማ ወደ ውጭ ወጥቶ ይየው፡ እነሆ ለምጻሙን የያዘው የለምጹ መልክ ትቶት እንደሆነ ቢያይ ።

ካህኑ ወደሱ ከሄደ በኋላ ያ ከለምጹ የነጻ ሰው ሁለት ንጹሐን ዶሮዎች በሕይወታቸው ያመጣ ዘንድ ይዘዘው፡ የጥድ ዕንጨት ዕጥፍ ሁኖ የተሠራ ቀይ ሐር፡ የአሸክት ቅጠል ያመጣ ዘንድ ይዘዘው ። ዘኍ፡ ፲፱ ፮ ።

ካህኑ አንዷን ዶሮ አርደው ደሟን ተቀብለው ጥሩ ውኃ ካለበት ሸክላ ይጨምሩ ዘንድ ይዘዝ ።

ካህን የጥድ ዕንጨት የተጕነጐነ ቀይ ሐር፡ የአውብን የሰሚዛ ቅጠል አምጥቶ ያልታረደችውን ሁለተኛይቱን ዶሮ በታረደችው ዶሮ ደም ጠምቶ ይውሰዳት ።

ካህን ይህን ሁሉ ተቀብሎ የታረደችው ዶሮ ደም ካለበት ጥሩ ውኃ ውስጥ ነክሮ፡ ከለምጽ የነጻውን ሰው ሰባት ጊዜ ይርጨው ከዚህ በኋላ ንጹሕ ይሆናል ።

ሰባት ጊዜ ረጭቶ ከነጻው በኋላ ያልታረደችውን ደኅነኛይቱን ዶሮ ትበር ዘንድ ወደ በረኻ ይስደዳት፡ ያም ከለምጹ የነጻ ሰው ልብሶቹን ይጠብ፡ ጠጕሩን ሁሉ ይላ

፰ ወእምዝ ይበውእ ውስተ ትዕይንት ወይነብር አፍአ እምቤቱ ሰቡዐ መዋዕለ ።

፱ ወበሳብዕት ዕለት ይትላፀይ ኵሎ ሥዕርተ ርእሱ፤ ወጽሕሞ ወሐንገዘ ወኵሎ ሥዕርቶ ይትላፀይ፤ ወየሐፅብ አልባሲሁ ወሥጋሁኒ የሐፅብ በማይ ወንጹሐ ይከውን ።

፲ ወበሳምንት ዕለት ያመጽእ ክልኤተ አባግዐ ንጹሐነ አለ ዓመት ሎሙ፤ ወዓዲ አሐደ በግዐ ንጹሐ ዘዓመት ወሠለስተ መስፈርተ ሥንዳሌ ለመሥዋዕት ዘልዉስ በቅብዕ ወአሐደ ግምዔ ቅብዐ ።

፲፩ ወያቀውሞ ካህን ለውእቱ ብእሲ ዘነጽሐ፤ ወዝክቱኒ ቅድመ እግዚአብሔር ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ።

፲፪ ወይነሥእ ካህን አሐደ በግዐ ወያበውእ በእንተ ንስሓ ወለውእቱኒ ግምዔ ቅብዕ ወይፈልጦሙ ፍልጣነ ቅድመ እግዚአብሔር ።

፲፫ ወይጠብሕዎ ለውእቱ በግዕ ውስተ መካን ኀበ ይጠብሕዎ ዘመሥዋዕት ወዘበእንተ ኃጢአትኒ በመካን ቅዱስ እስመ ዘበእንተ ኃጢአት ከመ ዘንስሓ ውእቱ ለካህን ቅዱስ ለቅዱሳን ውእቱ ።

፲፬ ወይነሥእ ካህን እምደም ዘንስሓ ወይወዲ ውስተ ከተማ ዕዝኑ እንተ የማን ለዘነጽሐ፤ ወላዕለ ከተማ እዴሁ እንተ የማን፤ ወላዕለ ከተማ እግሩ እንተ የማን ።

፲፭ ወይነሥእ ካህን እምቅብዕ ዘውስተ ግምዔ ወይሠውጥ ውስተ እዴሁ እንተ ጸጋም ።

፲፮ ወይጠምዕ ካህን አጽባዕቶ እንተ የማን ውስተ ውእቱ ቅብዕ ዘሀሎ ውስተ እዴሁ እንተ ጸጋም ወይነዝኅ እምውእቱ ቅብዕ ስብዓ ቅድመ እግዚአብሔር ።

፲፯ ወለዘተርፈ ቅብዕ ዘሀሎ ውስተ እዴሁ ይወድዮ ላዕለ ከተማ ዕዝኑ እንተ የማን ለውእቱ ዘነጽሐ፤ ወላዕለ ከተማ እዴሁ እንተ የማን፤ ወላዕለ ከተማ እግሩ እንተ የማን፤ በመካነ ደም ዘነዝሐ ።

፲፰ ወለዘተርፈ ቅብዕ ውስተ እዴሁ ይወድዮ ካህን ላዕለ ርእሱ ለዘያነጽሖ ወያስተሠሪ ሎቱ ቅድመ እግዚአብሔር ።

፲፱ ወይገብር ዘበእንተ ኃጢአት ወያስተሠሪ ሎቱ ለውእቱ ዘነጽሐ በእንተ ኃጢአቱ፤ ወእምዝ ይጠብሕ ካህን ዘመሥዋዕት ።

፳ ወያበውእ ዘመሥዋዕትኒ ወዘቍርባንኒ ላዕለ ምሥዋዕ ቅድመ እግዚአብሔር ወያስተሠሪ ሎቱ ወይነጽሕ ።

፳፩ ወእመሰ ነዳይ ውእቱ ወአልቦ ውስተ እዴሁ ያመጽእ ማሕስአ በግዕ አሐደ ዘይፈልጡ በእንተ ንስሓ በዘያስተሠርዩ ሎቱ፤ ወአሐተ መስፈርተ ሥንዳሌ ዘልዉስ በቅብዕ ለመሥዋዕት፤ ወአሐደ ግምዔ ቅብዕ ።

፳፪ ወክልኤ ማዕነቅ አው ክልኤ እጕለ ርግብ፤ ዘበቱ ውስተ እዴሁ፤ ወትከውን አሐቲ ዘበእንተ ኃጢአት፤ ወአሐቲ ለመሥዋዕት ።

ጭ፤ ንላውን በውኃ ይጠብ ንጹሕ ይሆናል ።

ከዚህ በኋላ ወደ ከተማ ይግባ ከቤቱም አፍአ ሰዋቶ ሰባት ቀን ይሰንብት ። ዘሌዋ፡ ፲፭ ፳፭፤ ዘኍ፡ ፲፪ ፲፭ ።

በሰባተኛውም ቀን የራስ ጠጕሩን ሁሉ ራሱንና ጢሙን ብብቱን የገላውን ጠጕር ሁሉ ይላጭ፤ ልብሱንም ገላውንም በውኃ ይጠብ፤ ንጹሕም ይሆናል ።

በስምንተኛውም ቀን ዓመት የሆናቸው ሁለት ንጹሐን በጎችን ያምጣ ዓግመኛም ዓመት የሆነው አንድ ንጹሕ በግ ያምጣ፤ በቅቤ የተለወሰ የምስት መስፈሪያ ሥንዴ ዱቄት አንድ ማሰሮ ዘይትን ለሚበላ ቍርበን ያምጣ ።

ካህኑም ያን የነጻውን ሰው አቁሞ ያንጻው የሚያቆመውም በደብተራ ኦሪት ደጃፍ በእግዚአብሔር ፊት ነው።

ካህኑ አንዱን በግ መሥዋዕተ ንስሐ አድርጎ ያቅርበው ያንንም አንድ የማሰሮ ቅቤ ያቅርበው፤ በእግዚአብሔር ፊት መለየትን ይለያቸው ። ዘፀ፡ ፳፱ ፳፬ ።

ያንንም በግ ለመሥዋዕተ ንስሐ ሲሆን የኃጢአቱንና የመሥዋዕቱን በግ በሚያርዱበት በክቡር ቦታ ይረዱት ያወራርዱት ከመሥዋዕተ ንስሐ ጢስለት የቀረው ለካህን እንደሆነ ከመሥዋዕተ ንስሐ የቀረውም ለካህን ነውና፤ የከበረ ለክቡራን ካህናት ነው ። ምዕ፡ ፯ ፫ ፯፤ ፳፩ ፳፪ ።

ካህኑም ስለ ንስሐ መሥዋዕት ከታረደው ደም ወስዶ ከለምጽ የነጻውን ሰው የቀኝ ጆሮውን ጫፍ ይቀባው፤ የቀኝ እጁን ጫፍና የቀኝ እግሩንም ጫፍ ይቀባው ።

ካህኑ በማሰሮው ውስጥ ካለው ዘይት ወስዶ በግራ እጁ ይያዝ ።

ካህን የቀኝ እጁን በግራ እጁ ካለው ዘይት እየጠለቀ ከዚያ ዘይት በእግዚአብሔር ፊት ሰባት ጊዜ ይርጭ ።

በግራ እጁ ካለው ቀብቶለት የተረፈውን ዘይት ከለምጽ የነጻውን ሰው የቀኝ ጆሮውን ጫፍ በረጨበት በደሙ ቦታ የቀኝ እጁንና የቀኝ እግሩን ጫፍ ይቀባው ።

በእጁ የቀረውን ዘይት ግን ካህን ከለምጽ በነጻው በዚያ ሰው ራስ ላይ ያፍስሰው እንዲህም አድርጎ በእግዚአብሔር ያስተሥርይለት ። ዘኍ፡ ፲፭ ፳፭፤ ዕብ፡ ፱ ፱ ።

ካህን የኃጢአቱን መሥዋዕት ሠውቶ ከለምጹ የነጻውን ሰው ኃጢአቱን ያስተሥርይለት፤ ከዚህ በኋላ ካህን የሚቃጠለውን መሥዋዕት ይረድ ።

የቍርባኑንና የመሥዋዕቱን በመሠውያው ላይ አግብቶ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአቱን ያስተሥርይለት፤ እሱም ይነጻል ። ዘሌ፡ ፲፬ ፲ ፩፤ ዮሐ፡ ፩ ፯ ።

ድኻ ቢሆን ግን በእጁ ገንዘብ ባይኖረው ኃጢአቱን በሚያስተሠርይለት ገንዘብ ስለ ንስሐ የሚለዩትን አንድ የበግ ጠቦት ያምጣ፤ በዘይትም የታሸ አንድ ላዳን የሥንዴ ዱቄት ዳበ ለመሥዋዕት ያቅርብ፤ አንድ ማሰሮ ዘይትም ያምጣ ። ምዕ፡ ፭ ፯፤ ፲፪ ፰፤ ሕዝ፡ ፴፭ ፲ ።

ሁለት ዋኖሶች ወይም በእጁ ባለው ገንዘብ ሁለት የርግብ ግልገሎች ለመሥዋዕት ያምጣ፤ አንዲቱ ስለ ኃጢአት አንዲቱ ለመሥዋዕት ትሁን ። ዘሌ፡ ፲፪ ፰ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወያበውኦን በሳምንት ዕለት በዘያነጽሖ ፡ ወይወስድ ኀበ ካህን ውስተ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ቅድመ እግዚአብሔር ። | ፳፫ | በሚያነጹትም ገንዘብ በስምንተኛው ቀን ያግባቸው ወደ ደብተራ ኦሪትም ወስዶ በእግዚአብሔር ፊት ያቅርባቸው ። ዘሌ፡ ፲፬፡ ፲ - ፲፩ ። |
| ወይነሥእ ካህን ለውእቱ በግዐ ዘንሥሐ ወለውእቱ ኆምጼ ዘቅብእ ወያነብሮ ለቊርባን ቅድመ እግዚአብሔር ። | ፳፬ | ካህኑም ያንን የንስሐውን መሥዋዕት በግና ያን አንድ ማሰሮ ዘይት ተቀብሎ ወስዶ ቊርባን አድርጎ በእግዚአብሔር ፊት ያኑረው ። ዘሌ፡ ፲፬ ፲፪ ። |
| ወይጠብሖ ለውእቱ በግዐ ዘንስሐ ወይነሥእ እምደሙ ለዘንስሐ ፡ ወይወዲ ላዕለ ከተማ ዕዝኑ ዘየማን ፡ ወላዕለ ከተማ እዴሁ እንተ የማን ፡ ወላዕለ ከተማ እግሩ እንተ የማን ለዘነጽሐ ። | ፳፭ | ካህንም ያነን የንስሐ በግ ይረደው ያወራርደው ካህኑ ለመሥዋዕተ ንስሐ ከታረደው በግ ደም ወስዶ ከለምጹ የነጻውን ሰው የቀኝ ጆሮውን ጫፍ ይቀባው ፡ የቀኝ እግሩንና የቀኝ እጁን ጫፍ ዐጽቅ ዐጽቁን ይቀባው ። |
| ወይሠውጥ ካህን እምውእቱ ቅብዕ ውስተ እዴሁ እንተ ጸጋም ። | ፳፮ | ካህኑ በማሰሮው ውስጥ ካለው ዘይት ወስዶ በግራ እጁ ይያዝ ። |
| ወይነዝኅ በአፅባዕቱ እንተ የማን እምውእቱ ቅብዕ ዘውስተ እዴሁ እንተ ጸጋም ስብዐ ቅድመ እግዚአብሔር ። | ፳፯ | በግራ እጁ ካለው ከዚያ ዘይት በቀኝ እጁ ጣት እየጠለቀ በእግዚአብሔር ፊት ሰባት ጊዜ ይርጨው ። |
| ወእምውእቱኒ ቅብዕ ዘሀሎ ውስተ እዴሁ ይወዲ ካህን ላዕለ ከተማ ዕዝኑ ዘየማን ለውእቱ ዘነጽሐ ፡ ወላዕለ ከተማ እዴሁ ዘየማን ፡ ወላዕለ ከተማ እግሩ እንተ የማን ፡ በመካነ ደሙ ለዘነጽሐ ። | ፳፰ | በእጁ ካለው ከዚያም ዘይት አምጥቶ ስለ ንስሐ ከተሠዋው በግ ደም በቀባበት ቦታ ላይ ከለምጽ የነጻውን ሰው የቀኝ ጆሮውን ጫፍ የቀኝ እጁንና የቀኝ እግሩን ጫፍ ይቀባው ። |
| ወለዘተርፈሰ ቅብዕ እምዘሀሎ ውስተ እዴሁ ይወድዮ ካህን ላዕለ ርእሱ ለውእቱ ዘነጽሐ ወያስተሠሪ ሎቱ ቅድመ እግዚአብሔር ። | ፳፱ | በእጁ ካለው ዘይት የቀረውን ግን ካህኑ ከለምጽ የነጻውን ሰው ራሱን ይቀባው ፡ እንዲህም አድርጎ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአቱን ያስተሥርይለት ። |
| ወይገብር አሐተ እምውእቶን መዓንቅ ወእመኒ እምእጕለ ርግብ እምዘበጽሐ ውስተ እዴሁ ። | ፴ | ከነዚያው ሁለቱ ዋኖሶች በእጁ ካለው ገንዘብ ከሁለት የርግብ ግልገሎች አንዷቱን ያቅርብ ። |
| አሐቲ በእንተ ኃጢአት ወአሐቲ ለቊርባን ምስለ መሥዋዕት ፡ ወያስተሠሪ ሎቱ ለውእቱ ዘነጽሐ ቅድመ እግዚአብሔር ። | ፴፩ | አንዷቱን ስለ ኃጢአት አንዷቱን ለቊርባን ከመሥዋዕት ጋር ይሠዋ ፡ ለዚያ ለነጻው ሰው በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአቱን ያስተሥርይለት ። |
| ዝንቱ ውእቱ ሕጉ ለዘወጽአ ኀበረ ለምጽ ላዕሌሁ ፡ ወለዘአልበኒ ውስተ እዴሁ በዘያነጽሖ ። | ፴፪ | የለምጽ ምልክት ለወጣበት ሰው በሚያነጹት ገንዘብ በእጁ ለሌለው ሰው ሕጉ ሥራቱ ይህ ነው ። |
| ወነበቦሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ወይቤሎሙ ፡ እምከመ በእክሙ ውስተ ምድረ ከነዓን እንተ እሁበክሙ አነ ትረስዋ እሌኑ ትእምርተ ለምጽ ውስተ አብያቲሃ ለይእቲ ምድር እንተ ታጠርይዋ ። | ፴፫ | እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን ተናገራቸው ትወርሷት ዘንድ እኔ ወደ ምሰጣችሁ ወደ ከነዓን ምድር በገባችሁ ጊዜ በወረሳችኋትና ገንዘብ በደረጋችኋት በዚያች ምድር በሠራችኋቸው ቤቶች ላይ የለምጽ ምልክት አመጣለሁ አላቸው ። ዘፍ፡ ፲፯ ፰ ፡ ዘዳ፡ ፴፪ ፵፱ ። |
| ወእመበ ዘወጽአ ውስተ ቤቱ ይንግር ለካህን ወይበል ከመ ትእምርተ ለምጽ ርኢኩ ውስተ ቤትየ ። | ፴፬ | በቤቱ የለምጽ ምልክት የወጣበት ሰው ቢኖር ሂዶ ለካህን ይንገረው ። መዝ፡ ፺፩ ፲ ፡ ዘካ፡ ፭ ፬ ። |
| ወየአዝዝ ካህን ያውጽኡ ንዋዮ ለውእቱ ቤት እንበለ ይባእ ካህን ለርእየቱ ለውእቱ ቤት ፡ ወለይእቲ ትእምርተ ለምጽ ፡ ወኢያረኵስ ኵሉ ዘሀሎ ውስተ ውእቱ ቤት ። | ፴፭ | ካህኑ ያነን የለምጽ ምልክትና ያነን ቤት ለማየት ገና ሳይገባ በቤቱ ውስጥ ያለውን ዕቃ ያወጡ ዘንድ ይዘዝ ፡ በዚያ ቤት ያለውንም ሁሉ አያረክስም ። ሚክ፡ ፫ ፩ ። |
| ወእምዝ ይበውእ ካህን ወይሬእዮ ለውእቱ ቤት ፡ ወለይእቲ ትእምርተ ለምጽ ። | ፴፮ | በዚህ በኋላ ካህን ገብቶ ያነን ቤት ይየው ፡ ያችንም የለምጽ ምልክት ይያት ። |
| ወናሁ ሀለወት ይእቲ ትእምርተ ለምጽ ውስተ ኆረፍቱ ለውእቱ ቤት ፡ ወእመኒ ታሕመለምል ፡ ወእመኒ ታቅየሐይሕ ወርእየታኒ የአክል እምአረፍት ። | ፴፯ | እነሆ ያች የለምጽ ምልክት በዚያ ቤት ኖራ ላይ ብትኖር ፡ ብትነጣም ብትቀላም መልኳ ከኖራው ላይ ቢሰፋ ። |
| ወወጺአ ካህን እምውእቱ ቤት ኀበ ኆኅት ያጸንሖ ለውእቱ ቤት ሰቡዐ ዕለተ ። | ፴፰ | ካህኑ ከዚያ ቤት ወደ ደጃፍ ወጥቶ ያንን ቤት ሰባት ቀን ያቈየው ። |
| ወይመጽእ በሳብዕት ዕለት ወይሬእዮ ለውእቱ ቤት ፡ ወናሁ ተዘርወት ይእቲ ኀብር ውስተ አረፍቱ ለውእቱ ቤት ። | ፴፱ | በሰባተኛው ቀን መጥቶ ያንን ቤት ይየው እነሆ ያች የለምጽ መልክ በዚያ ቤት ኖራ ላይ ብትሰፋ ። |
| ወይኤዝዝ ካህን ያውፅኡ እበኒሁ ዘሀለወት ቦቱ ይእቲ | ፵ | ካህን የለምጽ ምልክት ያለችባቸውን ድንጊያዎች ያ |

ትእምርተ ለምጽ፡ ወያውጽእዋ አፍአ እምይእቲ ሀገር ውስተ መካን ርኩስ ።

፵፩ ወያመጽኡ ካልአ እብነ ውቁረ ወይወድዩ ውስተ መካኖን ለውእቶን እበን ።

፵፪ ወያመጽኡ ካልአ መሬተ ወይመርግዎ ለውእቱ ቤት ።

፵፫ ወእመሰ ገብአት ካዕበ ይእቲ ኅብር ወወጽአት ውስተ ውእቱ ቤት፡ እምድኅረ አውጽኡ እበኒሃ ወእምድኅረ ገሠሥዎ ለውእቱ ቤት ወእምድኅረ መረግዎ ይበውእ ካህን ወይሬኢያ ።

፵፬ ወለእመ ተዘርወት ይእቲ ኅብር ዘውስተ ውእቱ ቤት፡ ለምጽ እንተ ኢትትኃደግ ይእቲ ውስተ ውእቱ ቤት ወርኩስ ውእቱ ።

፵፭ ወይነሥትዎ ለውእቱ ቤት ዕፀዊሁኒ ወእበኒሁኒ ወኵሉ መሬቶ ለውእቱ ቤት ይከዕዉ አፍአ እምሀገር ውስተ መካን ርኩስ ።

፵፮ ወዘቦአ ውስተ ውእቱ ቤት በኵሉ መዋዕል እምዘአፅለልዎ ርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ።

፵፯ ወዘቤተ ውስተ ውእቱ ቤት የሐፅብ አልባሲሁ ወይትሐፀብ ሥጋሁ በማይ፡ ርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ፡ ወዘበልዐ በውእቱ ቤት ይሕፅብ አልባሲሁ ።

፵፰ ወእመሰ መጽአ ካህን ወቦአ ወርእዮ ወናሁ ኢተዘርወት ይእቲ ኅብር ውስተ ውእቱ ቤት እምድኅረ መረግዎ ያነጽሖ ካህን ለውእቱ ቤት፡ እስመ ኃደገቶ ይእቲ ኅብር ።

፵፱ ወይነሥእ ካህን በዘያነጽሖ ለውእቱ ቤት ክልኤ ደዋርሃ ወዕፀ ጽሕድ ወለየ ክውብ፡ ወቄጽለ ሁስጱ ።

፶ ወይጠብሕዋ ለአሐቲ ዶርሆ ውስተ ንዋየ ልሕኵት፡ ውስተ ማይ ጥዑም ።

፶፩ ወይነሥእ ዝክተ ዕፀ ጽሕድ ወለየ ክውብ፡ ወቄጽለ ሁስጱ ወዶርሆ እንተ ሕያውት፡ ወይጠመቅዎሙ ውስተ ውእቱ ደመ ዶርሆ፡ እንተ ጠብሕዋ ውስተ ማይ ጥዑም ይነዝኃ ለውእቱ ቤት ስብዐ ።

፶፪ ወያነጽሖ ካህን ለውእቱ ቤት በደማ ለይእቲ ዶርሆ ወበማይ ጥዑም ወበዶርሆ እንተ ሕያውት፡ ወበዕፀ ጽሕድ ወበቄጽለ ሁስጱ፡ ወበለይ ክውብ ።

፶፫ ወይፌንዋ ለይእቲ ዶርሆ እንተ ሕያውት አፍአ እምሀገር ወያግዕዛ ውስተ ገዳም፡ ወያስተሠሪ በእንተ ውእቱ ቤት፡ ወይነጽሕ ውእቱ ቤት ።

፶፬ ዝንቱ ውእቱ ሕጉ ለኵሉ ትእምርተ ለምጽ ወኅብሩ ለዘለምጽ፡ ለልብስኒ፡ ወለቤትኒ፡ ወለትእምርተ ርምየትኒ ወዘኅንብርብሬኒ በዘተእምሩ ።

፶፭ እመ ርኩስ ውእቱ፡ ወእመ ንጹሕ ውእቱ ዝንቱ ውእቱ ሕጉ ለዘለምጽ ።

ወጡ ዘንድ ይዘዝ፡ ከከተማ ውጭ ርኩስ ወደ ሆነው ቦታ ያውጡት ። ምዕ፡ ፲፫ ፵፯ ።

ያንን ቤት በስተውስጥ ዙርያውን ይጥረቡት (ይፋቁት) የተፋቀውንም (ጥራቢውን) ከከተማ አውጥተው ወደ ረከሰ ቦታ ያፍሱት ።

ሌላ የለዘበ ደንጊያን አምጥተው በነዚያ በጣሉዋቸው ደንጊያዎች ቦታ ይተኩት (ያግቡት) ።

ሌላም መሬት አምጥተው ያንን ቤት ይምረጉት፡ ደንጊያዎቹን አውጥተው ሌሎች ደንጊያዎች ተክተው ሠርተው ከፃሰሱት በኋላ ሌላም ጭቃ አምጥተው ከመረጉት በኋላ፡ ያች የለምጽ ምልክት ዳግመኛ ተመልሳ በዚያ ቤት ላይ ብትወጣ ካህን ገብቶ ይያት ።

ካህን ገብቶ አይቶ በዚያ ቤት ያለችው ያች የለምጽ ምልክት በቤቱ ላይ ብትሰፋ በዚያ ቤት የማትቀር (የማትጠፋ) ለምጽ ናትና የረከሰ ነው ። ዘሌ፡ ፲፫ ፶፩፡ ዘካ፡ ፭ ፬ ።

ያንንም ቤት ዕንጨቶቹንና ደንጊያዎቹን ያፍርሱት፡ የዚያን ቤት አፈሩን ምርጉን ሁሉ ከሰፈሩ ውጭ አውጥተው በረከሰ ቦታ ያፍሱት ።

ርኩስ ብለው ከለዩትም በኋላ፡ ርኩስ በተባለበት ወራት ሁሉ ወደዚያ ቤት የገባ ሰው እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ነው፡ (ርኩስ ይሁን) ። ዘኍ፡ ፲፱ ፯፡ ፩ ቆሮ፡ ፲፭ ፴፫ ።

በዚያ ቤት ውስጥ ያደረ ሰው ልብሱን ይጠብ፡ ገላውንም በውኃ ይታጠብ፡ እስከ ማታም ድረስ ርኩስ ነው፡ በዚያም የበላ ሰው ልብሱን ይጠብ ። ምዕ፡ ፲፩ ፳፬ ።

ካህኑ ገብቶ አይቶ ያች በቤቱ ውስጥ የወጣችው የለምጽ ምልክት ያንን ቤት ከመረጉት በኋላ ብትሰፋ ያች መልክ ለቃዋለችና ካህን ያንን ቤት ያንጻው፡ (ንጹሕ ነው ይበለው) ። ዘኍ፡ ፴፪ ፴፱፡ ኢዮብ ፭ ፲፰ ።

ካህኑ ያንን ቤት ረጭቶ በሚያነጻው ገንዘብ ሁለት ዶሮዎች የጥድ ቅጠል የተጐነጐነ ቀይ ሐር፡ የእንዶድ የስሚዝ ቅጠል ያምጣ ። ምዕ፡ ፲፬ ፵፪፡ ፬ ፲፭ ።

ከዶሮዎቹ አንዲቱን ዶሮ በሸክላ ዕቃ አድርገው በጥሩ ውኃ አጠገብ ይረዷት ።

ያንን የጥድ ዕንጨት ዝንጣፊ የተጐነጐነ ቀይ ሐር ፈትል የአሸክት ቅጠል፡ ያልታረደችውን ዶሮ አምጥቶ በጥሩ ውኃ አጠገብ ባረዷት በዚያች ዶሮ ደም ጠምቶ፡ ያንን ቤት ሰባት ጊዜ ይርጨው ። መዝ፡ ፶፩ ፯ ።

ካህኑም ያንን ቤት በዚያች ዶሮ ደም በጥሩ ውኃ በጥድና በአሸክት ቅጠል፡ ዕጥፍ ሁኖ በተሠራ ቀይ ሐር፡ ያንጻው ።

ያችንም ያልታረደችውን ዶሮ ከመታረድ ነጻ አውጥቶ ከከተማ ወደ በረኻ ይስደዳት ለምጽ የወጣበትን ቤት እንዲህ አድርጎ ያንጻው፡ ያም ቤት ይነጻል ።

የለምጽ ምልክት ሁሉ የለምጽ መልክ የወጣበት ሰው ሁሉ ሕጉ ሥራቱ ይህ ነው፡ ለምጽ የወጣበትም ልብስና ቤትም ሕጉና ሥራቱ ይህ ነው፡ የቋቍቻ የብጉርና ለቋጥልጣሉም ለምጽ ሕጉ ሥራቱ ይህ ነው ።

ንጹሕም ርኩስም ቢሆን በምታውቁ ገንዘብ ለምጽ ለወጣበት ሰው ሕጉ ሥራቱ ይህ ነው ። ዘፀ፡ ፲፰ ፳፯ ።

## ምዕራፍ ፲፭ ።

፩ ወነበቦሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን እንዘ ይብ
ል ንግርዎሙ ለደቂቀ እስራኤል ።
፪ ወበልዎሙ ብእሲ ብእሲ እመብ ዘይትከዓዎ ዘርእ እም
ነፍስቱ ፡ በእንተ ውእቱ ዘይትከዓዎ ርኩስ ውእቱ ።
፫ ወዝንቱ ውእቱ ሕገ ርኵሱ ለዘይትከዓዎ ዘርኡ እምነ
ፍስቱ ፡ ወነበረ ከማሁ ውስተ ነፍስቱ ዘይትከዓዎ ፡ ውእቱ
ርኩስ ዘላዕሌሁ ኵሉ መዋዕለ ዘነበረ እንዘ ይትከዓዎ እም
ነፍስቱ ውእቱ ዘይትከዓዎ ያረኵስ ።
፬ ወኵሉ ዓራት ዘሰከበ ላዕሌሁ ርኩስ ውእቱ ፡ ወኵሉ
ንዋይ ዘነበረ ላዕሌሁ ይረኵስ ።
፭ ወብእሲኒ ዘገሠሠ ዓራቶ ይሕጽብ አልባሲሁ ፡ ወይት
ሐፀብ ሥጋሁ በማይ ፡ ወርኵስ ውእቱ እስከ ሠርክ ።
፮ ወዘነበረኒ ላዕለ ንዋይ ዘውእቱ ነበረ ላዕሌሁ ፡ ይሕፅብ
አልባሲሁ ወይትሐፀብ በማይ ወርኵስ ውእቱ እስከ ሠርክ ።
፯ ወዘገሠሠኒ ለውእቱ ዘይትከዓዎ ዘርኡ ይሕፅብ አልባ
ሲሁ ወይትሐፀብ ሥጋሁ በማይ ፡ ወርኩስ ውእቱ እስከ
ሠርክ ።
፰ ወእመ ወረቀ ዲበ ዘንጹሕ ይሕጽብ አልባሲሁ ወይት
ሐፀብ በማይ ፡ ወርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ።
፱ ወኵሉ ሕንባላት ዘላዕሌሁ ነበረ ፡ ርኩስ ውእቱ እስከ
ሠርክ ።
፲ ወኵሉ ዘገሠሠ እምኵሉ ዘነበረ ላዕሌሁ ርኩስ ውእቱ
እስከ ሠርክ ፡ ወዘርእዮኒ የሐፅብ አልባሲሁ ወይትሐፀብ
ሥጋሁ በማይ ፡ ወርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ።
፲፩ ወዘገሠሦኒ ለዘገሠሦ ለውእቱ ዘይትከዓዎ ዘርኡ እን
በለ ይትሐፀብ እደዊሁ ይሕፅብ አልባሲሁ ወየትሐፀብ
ሥጋሁ በማይ ፡ ርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ።
፲፪ ወለኵሉ ንዋየ ልሕኵት ዘውእቱ ገሠሦ ይስብርዎ ፡
ወለንዋየ ዕፀ ይሕጽብዎ በማይ ወንጹሐ ይከውን ።
፲፫ ወእመሰ ኀደገ ውእቱ ዘይትከዓዎ ይኄልቍ ሎቱ ሰቡ
ዐ መዋዕለ ለአንጽሖቱ ወየሐፅብ አልባሲሁ ወይትሐፀብ
ሥጋሁ በማይ ንጹሕ ፡ ወንጹሐ ይከውን ።
፲፬ ወበሳምንት ዕለት ይነሥእ ሎቱ ክልኤ መዓንቀ ፡ አው
ክልኤ እጕለ ርግብ ፡ ወያመጽኦን ቅድመ እግዚአብሔር
ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ፡ ወይሁብ ለካህን ።
፲፭ ወይገብር ካህን አሐተ በእንተ ኃጢአት ፡ ወአሐተ
ለመሥዋዕት ፡ ወያስተሠሪ ሎቱ ካህን ቅድመ እግዚአብ
ሔር በእንተ ኵሉ ዘይትከዓዎ ።
፲፮ ወእመብ ብእሲ ዘሰከበ ምስለ ብእሲት ይትሐፀብ በማይ
ኵሉ ሥጋሁ ወስዑብ ውእቱ እስከ ሠርክ ።
፲፯ ወኵሉ ልብስ ፡ ወኵሉ ማእስ ፡ ዘበጽሐ ላዕሌሁ ዝን
የቱ የሐፅብዎ በማይ ወርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ።
፲፰ ወብእሲትኒ ለእመ ሰከበት ምስለ ብእሲ ትትሐፀብ

## ምዕራፍ ፲፭ ።

እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ሲል ተናገራቸው ።

አንዱም አንዱም ሰው ከሰውነቱ ዘሩ የሚፈስበት ቢኖር ስለሚፈሰው ዘር ርኩስ ነው በሉዋቸው ።

ከሰውነቱ ዘሩ የሚንጠባጠብበት የርኩስነቱ ሕግ ይህ ነው ፡ ይህ የሚፈሰው ዘሩ እንዲህ እየተንጠባጠበበት ቢኖር በኖረበትም ዘመን ሁሉ ዘሩ ከአካሉ ሲፈሰው ቢኖርያ ከሰውነቱ የሚፈሰው ዘር ራሱንም ሌላውንም ያሰድፈዋል ።

የተኛበትም አልጋ ሁሉ ርኩስ ነው ፡ ዘሩ የሚፈስበት ሰው የተቀመጠበትም ዕቃ ሁሉ የረከሰ ነው ።

አልጋውንም የዳሰሰ ሰው ልብሱን ይጠብ ፡ ገላውንም በውኃ ይታጠብ ፡ እሱም እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ነው ።

እሱ በተቀመጠበት ዕቃ ላይ የተቀመጠም ልብሱን ይጠብ ፡ ገላውም በውኃ ይታጠብ ፡ እስከ ሠርክም ርኩስ ነው ። ምዕ፡ ፲፭ ፯፡ ዘኍ፡ ፭ ፪፡ ዕብ፡ ፱ ፲ ።

ዘሩ የሚፈሰውን ሰው ገላውን የነካ ሰውም ልብሱን ይጠብ ፡ ገላውንም በውኃ ይታጠብ ፡ እሱም እስከ ሠርክ ድረስ ርኩስ ነው ። ራእ፡ ዮሐ፡ ፯ ፲፱ ።

ዘሩ የሚፈስበት ሰው በንጹሑ ሰው ላይ ቢተፋበት ልብሱን ይጠብ ፡ ገላውንም በውኃ ይታጠብ ፡ እሱም እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ነው ። ዘኍ፡ ፲፪ ፲፬ ።

የተቀመጠበትም ኮርቻ (መደላድል) ሁሉ እስከ ሠርክ ድረስ ርኩስ ነው ።

እሱ የተቀመጠበትንም ዕቃ ሁሉ የዳሰሰ ሰው እስከ ሠርክ ድረስ ርኩስ ነው ፡ ያየውም ሰው ልብሱን ይጠብ ፡ ገላውንም በውኃ ይታጠብ ፡ እስከ ማታም ርኩስ ነው ።

ዘሩ የሚፈሰው ሰው እጁን ሳይታጠብ የነካውን ሰው የነካ ሁሉ ልብሱን ይጠብ ፡ ገላውንም በውኃ ይታጠብ ።

እሱ የነካውን የሸክላ ዕቃ ሁሉ ይሰበሩት ፡ የዕንጨቱን ዕቃ ግን (ገበታው ሰደቃው) በውኃ ይጠቡት ንጹሕም ይሆናል ። ምዕ፡ ፯ ፳፰ ፡ ፲፩ ፴፫ ።

ያ የሚፈሰው ዘሩ ቢተወው ንጹሕ ለመሆን ሰባት ቀን ይቍጠሩለት ፡ ልብሱን ይጠብ ፡ ገላውንም በውኃ ይታጠብ ፡ ንጹሕም ይሆናል ። ዘኍ፡ ፲፱ ፲፩ ።

በስምንተኛው ቀን ሁለት ዋኖስ ወይም ሁለት የርግብ ግልገሎች ይዞ በእግዚአብሔር ፊት ወደ ደብተራ ኦሪት ደጃፍ አምጥቶ ለካህን ይስጠው ።

ካህኑ አንዲቱን ስለ ኃጢአት መሥዋዕት ፡ አንዲቱን ለሚቃጠል መሥዕት አድርጎ ይሠዋ ፡ ካህኑ ዘሩ ስለሚፈሰው በእግዚአብሔር ፊት ያስተሥርይለት ።

ከሴት ጋር የተኛ ሰው ቢኖር ገላውን ሁሉ በውኃ ይታጠብ ፡ እስከ ማታም ድረስ ኃጢአተኛ ነው ።

ዝንየቱ የፈሰሰበት ጀንዴውን ሁሉ በውኃ ይጠቡት ፡ እስከ ሠርክም ድረስ ርኩስ ይሁን ።

ሴትም ከወንድ ጋር ብትተኛ በውኃ ትታጠብ ፡ እስከ

| | | |
|---|---|---|
| በማይ ፡ ወርኩስት ይእቲ እስከ ሠርክ ። | | ሠርክም ድረስ የረከሰች ናት ። ፩ ሳሙ፡ ፳፩ ፬ ። |
| ወእመ ብእሲት እንተ ይትከዓዎ ደም ወነበረ እንዘ ይትከዓዎ እምነፍስታ ፡ ሰቡዐ መዋዕለ ውእቱ ዘትክቶሃ ፡ ወኵሉ ዘገሠሣ ርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ። | ፲፱ | ደም የሚፈስባት ሴት ብትኖር ከሰውነቷ እየፈሰሳት ብትሰነብት የግዳጅዋ ወራት ሰባት ቀን ነው ፡ የነካትም ሁሉ እስከ ሠርክ ርኩስ ነው ። ሕዝ፡ ፴፮ ፲፯ ። |
| ወኵሉ ዘሳዕሌሁ ሰከበት እንዘ ትክት ይእቲ ፡ ርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ፡ ወኵሉ ዘነበረት ላዕሌሁ ይረኵስ ። | ፳ | በግዳጅዋም ሳለች የተኛችበት ሁሉ ርኩስ ነው ፡ የተቀመጠችበትም ሁሉ የረከሰ ነው ። |
| ወኵሉ ዘገሠሠ ዓራታ ይሕፅብ አልባሲሁ ወይትሐፀብ ሥጋሁ ርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ። | ፳፩ | አልጋዋንም (ምንጣፏን) የነካ ሁሉ ልብሱን ይጠብ ፡ ገላውንም በውኃ ይታጠብ እስከ ሠርክም ርኩስ ነው ። |
| ወኵሉ ዘገሠሠ እምኵሉ ንዋይ ዘነበረት ላዕሌሁ የሐፅብ አልባሲሁ ፡ ወይትሐፀብ ሥጋሁ በማይ ፡ ወርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ። | ፳፪ | እርሷ የተቀመጠችበትን ዕቃ ሁሉ የነካ ሰው ልብሱን ይጠብ ፡ ሰውነቱም በውኃ ይታጠብ ፡ እስከ ሠርክም ርኩስ ነው ። ፪ ቆሮ፡ ፯ ፩ ፡ ዕብ፡ ፲ ፳፪ ። |
| ወእመኒ እንዘ ሀለወት ላዕለ ዓራታ አው ላዕለ ንዋይ ዘዲቤሁ ትነብር ይእቲ ፡ ዘገሠሠ ርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ። | ፳፫ | በአልጋዋ ሳለች ቢሆን ወይም በተቀመጠችበት ነገር ሁሉ ላይ ቢሆን በላዩ ሳለች የነካው ሰው እስከ ሠርክ ድረስ ርኩስ ነው ። |
| ወዘሰከበ ምስሌሃ ብእሲ ላዕሌሁ ይገብእ ርኵሳ ፡ ወርኩሰ ይከውን ሰቡዐ መዋዕለ ፡ ወኵሉ ዓራት እንተ ላዕሌሁ ሰከበ ርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ። | ፳፬ | በግዳጅዋ ወራት ሳለች የደረሰበት ሰው እደፏ ወደ ርሱ ይመለስበታል ፡ ሰባት ቀንም ርኩስ ይሁን ፡ የተኛበትም አልጋ (ምንጣፍ) ሁሉ ርኩስ ነው ። ምዕ፡ ፳ ፲፰ ። |
| ወእመበ ብእሲት እንተ ይትከዓዎ ደም ብዙኀ መዋዕለ ፡ ወፈድፋደ እመዋዕለ ትክቶሃ ፡ ወእመኒ እምድኅረ መዋዕለ ትክቶሃ ተከዐዎ በኵሉ መዋዕል ዘይትከዓዎ ርኵሰት ይእቲ በከመ መዋዕለ ትክቶሃ ከማሁ ። | ፳፭ | ብዙ ቀን ደም የሚፈሳት ሴት ብትኖር ከግዳጅዋ ወራት ይልቅ ፡ ከግዳጅዋም በኋላም ቢፈሳት በሚፈስበት ወራት ሁሉ የረከሰች ናት ፡ እንደ ግዳጅዋ ወራት ርኩስ ትሁን ። ማቴ፡ ፱ ፳ ፡ ማር፡ ፭ ፳፭ ። |
| ወኵሉ ዓራት ዘላዕሌሁ ሰከበት በኵሉ መዋዕል ዘይትከዓዎ ከመ ዓራተ ትክቶሃ ውእቱ ፡ ወኵሉ ንዋይ ዘላዕሌሁ ነበረት ርኩስ ውእቱ ፡ በከመ ርኵሰ ትክቶሃ ። | ፳፮ | ደም በሚፈስበት ወራት ሁሉ የተኛችበት አልጋ (ምንጣፍ) በግዳጅዋ ወራት እንደምትተኛበት አልጋ ነው ፡ የተቀመጠችበትም ዕቃ ሁሉ እንደ ግዳጅዋ ወራት የኀጢአት ጊዜ ነው ። |
| ወኵሉ ዘገሠሣ ርኩስ ውእቱ ወየሐፅብ አልባሲሁ ወይትሐፀብ ሥጋሁ በማይ ፡ ወርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ። | ፳፯ | የነካትም ሁሉ ርኩስ ነው ፡ ልብሱን ይጠብ ፡ ሰውነቱንም በውኃ ይታጠብ ፡ እስከ ሠርክም ርኩስ ነው ። |
| ወእመሰ ኀደጋ ውእቱ ዘይትከዓዋ ይኌልቁ ላቲ ሰቡዐ መዋዕለ ፡ ወእምድኅሬሁ ንጽሕተ ትከውን ። | ፳፰ | ይህ የሚፈሳት ደም መፍሰሱ ቢተዋት ግን ሰባት ቀን ይቍጠሩላት ፡ ከዚያ በኋላ ንጽሕት ትሆናለች ። |
| ወበሳምንት ዕለት ትንሥእ ላቲ ክልኤ መዓንቀ ፡ አው ክልኤ እጕለ ርግብ ፡ ወታመጽእ ኀበ ካህን ውስተ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ። | ፳፱ | በስምንተኛውም ቀን ሁለት ዋኖሶች ወይም ሁለት የርግብ ግላግሌቶች ይዛ ወደ ካህኑ ወደ ደብተራ ኦሪት ደጃፍ ታምጣ ። ዘኍ፡ ፮ ፲ ። |
| ወይገብር ካህን አሐተ በእንተ ኀጢአት ፡ ወአሐተ ለመሥዋዕት ፡ ወያስተሠሪ ላቲ ካህን ቅድመ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ውእቱ ርኩስ ዘተከዐዎ ። | ፴ | ካህኑም አንዲቱን ስለ ንስሐ ፡ አንዲቱን ለመሥዋዕት ይሠዋ ፡ ስለሚፈሳትም ደም ርኩስነት በእግዚአብሔር ያስተሥርይላት ። ፪ ቆሮ፡ ፭ ፲፰ ፡ ኤፌ፡ ፪ ፲፱ ። |
| ወንጹሐነ ረስይዎሙ ለደቂቀ እስራኤል እምርኵሶሙ ከመ ኢይሙቱ በእንተ ርኵሶሙ ፡ ወከመ ኢያርኵሱ ፡ ደብተራየ እንተ ኀቤሆሙ ። | ፴፩ | የእስራኤልን ልጆች (እንዲህ አድርጋችሁ) ከርኩስነታቸው ንጹሐን አድርጓቸው በነርሱ ዘንድ ያለች ማደሪያዬን እንዳያረክሱ ፡ በርኩስነታቸው ምክንያት እንዳይቀሥፉ ። ዘዳ፡ ፳፪ ፳ ፡ ማቴ፡ ፳፫ ፡ ዘኍ፡ ፭ ፫ ። |
| ዝንቱ ውእቱ ሕጉ ለዘይትከዓዎ ዘርኡ ፡ ወለዘሰከበ ምስለ ብእሲት ፡ ወሰዐበ ከነ በቲ ። | ፴፪ | ዘር ለሚፈስበትና ከሴትም ጋር ለሚተኛና ላደረሰበት ሰው ሕጉ ሥራቱ ይህ ነው ። |
| ወለዘይትከዓዎኒ ደም በትክቶሃ ፡ ወለዘይትከዓዎኒ ዘርኡ በመዋዕለ ይትከዓዎሙ ለተባዕትኒ ወለአንስትኒ ፡ ወለብእሲኒ ዘሰከበ ምስለ ብእሲት ትክት ። | ፴፫ | በግዳጅዋ ጊዜ ደም ስለሚፈስባት ሴት ዘሩም ስለሚፈስበት ሰው ለወንድም ለሴትም በሚፈስባቸው ወራት ፡ በግዳጅ ከደፈች ሴት ጋር ለሚተኛም ሰው ሕጉ ሥራቱ ይህ ነው ። |

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



| ምዕራፍ ፲፮። | | ምዕራፍ ፲፮። |
|---|---|---|
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ፥ እምድኅረ ሞቱ ክልኤሆሙ ደቂቀ አሮን በእንተ ዘአምጽኡ እሳተ እምበዕድ ቅድመ እግዚአብሔር። | ፩ | ሁለት የአሮን ልጆች በእግዚአብሔር ፊት እሳት ከሌላ ስላመጡ ከሞቱ በኋላ፥ እግዚአብሔር ለሙሴን እንዲህ ብሎ ነገረው። |
| ወይቤሎ በሎ ለአሮን እኁከ፥ ኢይበእ በኵሉ ሰዓት ውስተ መቅደስ፥ ውስተ ውሣጤ መንጦላዕት ቅድመ ምስሐል ዘመልዕልተ ታቦት ወኢይሙት በሕቱ እምከመ አስተርአይኩ በደመና። | ፪ | በደመና አድሬ ከታየሁ በኋላ እንጂ እንዳይቀሠፍ በየጊዜው በታቦቱ ላይ ባለው ሥርየት በሚገኝበት በመግጠሚያው አንጻር ወደ መጋረጃው ውስጥ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን እንዳይገባ ለወንድምህ ለአሮን ንገረው ብሎ። |
| ወእምዝ ይበእ አሮን ውስተ ቅድሳት ምስለ ላሕም ዘእምአልሕምት ዘበእንተ ኃጢአት ወበግዕ ለመሥዋዕት። | ፫ | ከዚህም በኋላ ስለ ኃጢአት ከላሞች የተመረጠ በሬን ለመሥዋዕትም በግን ይዞ አሮን ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይግባ። ዘሌዋ፡ ፬ ፫፡ ዘፀ፡ ፴ ፲። |
| ወልብሰ አኄ ቅዱሰ ይልበስ፥ ወድርግንቀ ዘአኄ ይደይ ላዕለ ሥጋሁ፥ ወቅናተ ዘአኄ ይቅንት፥ ወአክሊለ ዘአኄ ያንብር ዲበ ርእሱ፥ እስመ አልባሰ ቅዱሳን እሙንቱ ወተሐፂቦ በማይ ኵሉ ሥጋሁ ይልበሶሙ። | ፬ | የከበረ የተልባ እግር ልብስን ይልበስ፥ በሰውነቱም ላይ የነጭ ሐር ልብልብን ይታጠቅ፥ የነጭ ሐር ዝናርንም ይታጠቅ፥ የነጭ ሐር ኵፌትንም በራሱ ላይ ይድፋ፥ እነዚህ የከበሩ ልብሶች ናቸውና ሰውነቱን ሁሉ በውኃ ታጥቦ ይልበሳቸው። ዘፀ፡ ፴ ፳፡ ዘሌዋ፡ ፮ ፲፡ ፰ ፲። |
| ወእምተዐይኖሙ ለደቂቀ እስራኤል ይንሣእ ክልኤተ ሐራጊተ እምአጣሊ ዘበእንተ ኃጢአት፥ ወአሐደ በግዐ ለመሥዋዕት። | ፭ | ከእስራኤል ልጆች ወገኖችም ስለ ኃጢአት ከፍየሎች ሁለት ሙክቶች ለሚቃጠል መሥዋዕትም አንድ በግ ያምጣ። ዘሌዋ፡ ፬ ፲፬፡ ዘኍ፡ ፳፱ ፲፩። |
| ወያበውእ አሮን ላሕመ ዘበእንተ ኃጢአት ወያስተሠሪ ለርእሱ ወለቤቱ። | ፮ | አሮንም ስለ ኃጢአት አንድ በሬ ሠውቶ፥ የራሱንና የወገኑን ኃጢአት ያስተሥርይ። ዕብ፡ ፱ ፮፡ ፯ ፳፯። |
| ወእምዝ ያመጽኦሙ ለእልክቱ ክልኤቱ ሐራጊት፥ ወያቀውሞሙ ቅድመ እግዚአብሔር ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል። | ፯ | ከዚህ በኋላ እነዚያን ሁለት ሙክቶች አምጥቶ በደብተራ ኦሪት ደጃፍ በእግዚአብሔር ፊት ያቁማቸው። |
| ወይወዲ አሮን ላዕለ ክልኤሆሙ ሐራጊት ዕፀወ ዘበቱ ያስተዓፁ፥ አሐዱ ዕፀ ዘእግዚአብሔር፥ ወአሐዱ ዕፀ ለዘ አብአ። | ፰ | አሮን በነዚያ ሁለት ሙክቶች ላይ ዕጣ የሚያጣጥል በትን ዕንጨት ያኑር እነዚያም አንዱ የእግዘአብሔር፥ አንዱ መሥዋዕቱን ያቀረበው ሰው ነው። ዘሌ፡ ፲፮ ፲። |
| ወያመጽእ አሮን ለሐርጌ ዘወድቀ ላዕሌሁ ዕፀ እግዚአብሔር፥ ወያበውእ በእንተ ኃጢአት ለአስተሥርዮ። | ፱ | አሮንም የእግዘአብሔር ዕጣ የወደቀበትን ሙክት አምጥቶ ኃጢአትን ለማስተሥረይ መሥዋዕተ ኃጢአት አድርጎ ያቅርበው (ይሠዋው)። |
| ወለሐርጌሰ ዘወድቀ ላዕለ ዕፀ ዘአምጽአ ያቀውሞ ሕያዎ ቅድመ እግዚአብሔር ከመ ያስተሥሪ ሎቱ ወከመ ይፈንዎ ኀበ ያግዕዝዎ፥ ወኀበ የኀድግዎ ውስተ ገዳም። | ፲ | ያመጣው ሰው ዕጣ የወደቀበትን ሙክት ግን ኃጢአት አስተሥርዮበት ከመታረድ ነፃ አውጥተው ወደሚተውበት ምድረ በዳ ይለቀው ዘንድ በሕይወቱ በእግዚአብሔር ፊት ያቁመው። ኢሳ፡ ፶፫ ፲፡ ሮሜ ፫ ፳፭። |
| ወያበውእ አሮን ላሕመ ዘበእንተ ኃጢአት ወያስተሥሪ ሎቱ ወለቤቱ፥ ወይጠብሖ ለውእቱ ላሕም ዘበእንተ ኃጢአት። | ፲፩ | አሮንም የራሱንና የወገኖቹን ኃጢአት የሚያስተሥርይበትን ወይፈን አቅርቦ ስለ ኃጢአት ያመጣውን ያንን ወይፈን ይረደው ያወራርደው። ዘሌ፡ ፲፮ ፮። |
| ወይነሥእ ማዕጠንተ ወይመልእ እሳተ እምአፍሐም ዘውስተ ምሥዋዕ ዘቅድመ እግዚአብሔር፥ ወይመልእ እደዊሁ እምዕጣን ዘእፉን ወድቁቅ፥ ወይበውእ ውስተ መንጦላዕት። | ፲፪ | ጥናውን አምጥቶ በእግዚአብሔር ፊት ካለው ከፍሙ እሳት መልቶ ከተለቀመውና ከደቀቀው እፍኝ ዕጣን በእጁ ይዞ ወደ መጋረጃው ውስጥ ይግባ። ዘፍ፡ ፲፮ ፵፮። |
| ወይወዲ ውእተ ዕጣነ ውስተ ማዕጠንት ቅድመ እግዚአብሔር፥ ወይከድን ጢሱ ለውእቱ ዕጣን ምስሐለ ዘዲበ ታቦት ወኢይሙት። | ፲፫ | ያንንም ዕጣን በጥናው አድርጎ በእግዚአብሔር ፊት ያጢሰው እንዳይሞትም የዚያ ዕጣን ጢሱ በታቦቱ ላይ ያለውን ሥርየት የሚገኝበት መግጠሚያውን ይሸፍነው። |
| ወይነሥእ እምደሙ ለውእቱ ላሕም ወይነዝኅ በአጻብዒሁ ቅድመ ምስሐል ለመንገለ ሠርቅ ውስተ ገጹ ለምስሐል፥ ወይነዝኅ ስብዐ ቅድመ እግዚአብሔር እምውእቱ ደም በአጻብዒሁ። | ፲፬ | ከዚያም የበሬ ደም አምጥቶ በመግጠሚያው አንጻር በምሥራቅ በኩል በጣቱ ይርጨው፥ ከዚያም ደም በጣቱ በእግዚአብሔር ፊት ሰባት ጊዜ ይርጭ። ዘሌ፡ ፬ ፮። |

| | | |
|---|---|---|
| ወይጠብሖ ሐርጌኒ ዘበእንተ ኃጢአት፤ ዘእምኅበ ሕዝብ ወያበውእ እምደሙ ውስጠ እመንጦላዕት ወይገብሮ ለደሙ በከመ ገብረ ደመ ላሕም ወይነዝኆ እምደሙ ላዕለ ምስሐል መንገለ ገጹ ለምስሐል ። | ፲፭ | ከሕዝቡ የመጣውን ስለ ሕዝቡ መሥዋዕተ ኃጢአት የሚሆነውን ሙክት ይሠዋው፤ ከደሙም ከመጋረጃው ወደ ውስጥ ያግባ፤ ደሙንም የበሬውን ደም እንዳደረገው ያድርገው፤ ከደሙም ሥርየት የሚሰጥበት መግጠሚያውን በመክደኛው ፊት በኩል ይርጭ ። |
| ወያስተሠሪ በመቅደስ እምርኵሶሙ ለእስራኤል ወበእንተ ኵሉ ዓመፃሆሙ ወበእንተ ኵሉ ኃጣውኢሆሙ ። | ፲፮ | በመቅደስም እስራኤልን ከርኵስነታቸው ያስተሥርይላቸው፤ ስለ በደሉት በደላቸውና ስለ ሠሩትም ኃጢአታቸው ያንጻቸው ። |
| ወከመዝ ይገብር በደብተራ ዘመርጡል እንተ ተኃድር ውስቴቶሙ በማእከለ ርኵሶሙ ። | ፲፯ | በርኵስነታቸውም መካከል በምትኖር በደብተራ ኦሪት እንዲሁ ያድርግ ። ዘፀ፡ ፴፱ ፲፮ ። |
| ወአልቦ ዘይሄሉ ሰብእ ወኢመኑሂ ሰበ ይበውእ ውስተ መቅደስ ከመ ያስተሥሪ እስከ ይወጽእ፤ ወያስተሠሪ ለርእሱ ወለቤቱ፤ ወለኵሉ ተዐይኖሙ ለእስራኤል ። | ፲፰ | ኃጢአታቸውን ያስተሠርይ ዘንድ ወደ መቅደስ በገባ ጊዜ ለራሱ ለቤተ ሰቡና ለወገኖቹ አስተሥርዮ እስኪወጣ ድረስ ማንም ማን ሰው የሚኖር የለም (አይኑር) ። |
| ወይወጽእ ኀበ ምሥዋዕ ዘሀለወ ቅድመ እግዚአብሔር ወያስተሠሪ ቦቱ ወይነሥእ እምደመ ላሕም ወእምደመ ሐርጌ ወይወዲ ላዕለ አቅርንቲሁ ለምሥዋዕ በዓውዶሙ ። | ፲፱ | በእግዚአብሔር ፊት ወዳለው መሠዊያ ወጥቶ ያስተሥርይበት ከወይፈኑና ከፍየሉም አውራ ደም ወስዶ በመሠውያው ቀንዶች ላይ በዙርያቸው ይርጨው ። |
| ወይነዝኅ ላዕሌሁ እምውእቱ ደም በአፅባዕቱ ስብዐ ወያነጽሖ ወይቄድሶ እምኵሉ ርኵሶሙ ለደቂቀ እስራኤል ። | ፳ | ከዚህም ደም በጣቱ እየጠለቀ ሰባት ጊዜ በመሠውያው ላይ ይርጭ፤ ከእስራኤል ልጆች ርኵሰት ሁሉ ያንጻው (ይለየው) ። ሕዝ፡ ፵፫ ፭ ። |
| ወይፌጽም አስተሥርዮ በመቅደስ ወበደብተራ ዘመርጡል፤ ወበምሥዋዕ ወያመጽእ ሐርጌ ዘሕያው ። | ፳፩ | ኃጢአት ማስተሥረያንም በቅድስተ ቅዱሳን በደብተራ ኦሪት በምሥዋዑም ይፈጽም፤ ያልተሠዋውንም ሙክት ያቅርብ ። ሕዝ፡ ፵፫ ፱ ፳፮ ። |
| ወይወዲ አሮን ክልኤሆን እደዊሁ ላዕለ ርእሱ ለውእቱ ሐርጌ ዘሕያው፤ ወይትነሣይ በላዕሌሁ ኵሎ ኃጣውኢሆሙ ለደቂቀ እስራኤል፤ ወኵሎ ዓመፃሆሙ፤ ወኵሎ አበሳሆሙ፤ ወያነብሮ ላዕለ ርእሱ ለውእቱ ሐርጌ ዘሕያው፤ ወይፌንዎ ሐቅለ ምስለ ብእሲ ዘተረሠየ ። | ፳፪ | አሮንም ሁለት እጆቹን በዚያ ባልታረደው የፍየል አውራ ራስ ላይ ያኑር፤ የእስራኤል ኃጢአታቸውን ሁሉ ዓመፃቸውንና በደላቸውን ሁሉ ያስተሥርይ፤ (ይናዘዝ)፤ ኃጢአታቸውን በዚህ ባልታረደው የፍየል አውራ ራስ ላይ ያኑረው፤ ለመሄድ ከተዘጋጀውም ሰው ጋር ወደ በረኻ ይስደደው ። |
| ወይነሥእ ዝክቱ ሐርጌ ላዕለ ርእሱ ኃጣውኢሆሙ ወየኀድጎ ለውእቱ ሐርጌ ውስተ ምድረ በድው ኀበ አልቦ ዕፅ ። | ፳፫ | ይህ የፍየል አውራ ኃጢአታቸውን በራሱ ላይ ይሸከም፤ ይህንንም ሙክት እኽል ተክል ወደ ሌለበት ምድረ በዳ ይተወው ። ኢሳ፡ ፶፫ ፲፩፤ ማቴ፡ ፰ ፲፯ ። |
| ወይበውእ አሮን ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ወያሰስል አልባሲሁ ዘአኀዘ ዘይለብስ ለበዊእ ውስተ መቅደስ ወያነብሮ ህየ ። | ፳፬ | አሮንም ወደ ደብተራ ኦሪት ገብቶ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ሲገባ የሚለብሰውን ነጭ ሐር አውልቆ ከዚያው ያኑረው ። ሕዝ፡ ፵፬ ፲፱፣ ፵፱ ፲፱ ። |
| ወይትሐፀብ ሥጋሁ በማይ በመካን ቅዱስ ወይለብስ አልባሲሁ፤ ወወፂአ ይገብር መሥዋዕቶ፤ ወመሥዋዕተ ሕዝብኒ ። | ፳፭ | ገላውን በክቡር ቦታ በውኃ ታጥቦ የዘወትር ልብሱን ይልበስ፤ ከዚያም ወጥቶ የራሱንና የሕዝቡን መሥዋዕት ይሠዋ ። |
| ወያስተሠሪ ለርእሱ ወለቤቱ ወለሕዝብኒ ወለስብሕኒ ዘበእንተ ኃጢአት ይወድዮ ላዕለ ምሥዋዕ ። | ፳፮ | የራሱንና የወገኖቹን የቤተ ሰቡንም ኃጢአት ያስተሥርይ የኃጢአቱንም ስብ በመሠውያው ላይ ይጨምረው (ያቃጥለው) ። |
| ወዝክቱኒ ዘአውፅአ ለሐርጌ ዘፈለጡ ከመ ያግዕዞ ኀበ ገዳም፤ የሐፅብ አልባሲሁ ወይትሐፀብ ሥጋሁ በማይ፤ ወእምዝ ይበውእ ውስተ ትዕይንት ። | ፳፯ | ከመታረድ ነጻ ያወጣው ዘንድ የለዩትም ሙክት ወደ በረኻ የወሰደው ሰው ልብሱንና ገላውን በውኃ ይታጠብ፤ ከዚህ በኋላ ወደ ሰፈር ይግባ ። ምዕ፡ ፲፭ ፭ ። |
| ወላሕምኒ ዘበእንተ ኃጢአት ወሐርጌኒ ዘበእንተ ኃጢአት ዘአብኡ ደሞሙ ከመ ያስተሥርዩ ቦቱ በውስተ መቅደስ ያወጽእዎሙ አፍአ እምትዕይንት ወያውዕዩዎሙ በእሳት፤ ወአምእስቲሆሙኒ ወሥጋሆሙኒ ወከዕሴሆሙኒ ። | ፳፰ | በቅድስተ ቅዱሳን ኃጢአታቸውን ያስተሠርዩበትም ዘንድ ደማቸውን ያገቡት መሥዋዕተ ኃጢአት የሆኑትን ወይፈንና ሙክት ከከተማ አፍአ አውጥተው በእሳት ያቃጥሉዋቸው፤ ሥጋቸውንና ቍርበናቸውን ሰንበራቸውንም ያቃጥሉዋቸው ። ዕብ፡ ፲፫ ፲፩ ። |
| ወዝክቱ ዘአውዓዮሙ የሐፅብ አልባሲሁ ወይትሐፀብ | ፳፱ | ያቃጠላቸውም ሰው ልብሱን ይጠብ ... |

ሥጋሁ በማይ ፡ ወእምዝ ይበውእ ውስተ ትዕይንት ፡ ወዝንቲኒ ሕገ ይኩንክሙ ለዓለም ።

በውኃ ይታጠብ ፡ ከዚህ በኋላ ወደ ከተማ ይግባ ፡ ይህም የዘለዓለም ሕግ ሥራት ይሁናችሁ ። ኢሳ፡ ፶፫ ፲ ።

፴ ወበሳብዕ ወርኅ አመ ዐሡሩ ለሠርቅ አሕምምዋ ለነፍስክሙ ፡ ወኵሎ ግብረ ኢትግበሩ በቲ ዘእምፍጥረቱኒ ወዘግዩርኒ ዘሀለወ ኀቤክሙ ።

በሰባተኛውም ወር በአሥረኛው ቀን ሰውነታችሁን አሳዝኗት ፡ ከምትሠሩትም ሥራ ሁሉ አትሥሩበት ትውልዱ (ከእስራኤል) የሆነ ከናንተ ዘንድ ያለ መጻተኛም ቢሆን ሥራን አትሥሩበት ።

፴፩ እስመ በይእቲ ዕለት ያስተሠሪ በእንቲአክሙ ከመ ያንጽሕክሙ እምኵሉ ኃጣውኢክሙ ቅድመ እግዚአብሔር ወትነጽሑ ፡ እስመ ሰንበተ ሰንበታት ይእቲ ለክሙ ።

በዚች ቀን ከኃጢአታችሁ ያነጻችሁ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት ያስተሠርይላችኋልና ከኃጢአታችሁም ትነጻላችሁ ። መዝ፡ ፶፱ ፱ ፡ ፩ ዮሐ፡ ፩ ፯ ።

፴፪ ወአሕምምዋ ለነፍስክሙ ፡ ወሕግ ውእቱ ለክሙ ዘለዓለም ።

ለናንተ በሱባዔ የምትቈጠር በዓል ናትና ፡ ሰውነታችሁን አሳዝኗት ፡ ይህም ለናንተ ለዘለዓለም ሕግ ይሁናችሁ ።

፴፫ ወያስተሠሪ ካህን ዘቀብዕዎ ወዘፈጸሙ እደዊሁ ከመ ይኩን ካህነ እምድኅረ አቡሁ ፡ ወይለብስ አልባሰ እጌ አልባሰ ቅድሳት ።

ከአባቱ ቀጥሎ ሊቀ ካህናት ይሆን ዘንድ እጆቹን ቀብተው የሾሙት ካህን ኃጢአታችሁን ያስተሠርይላችሁ ፡ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ሲገባ የሚለብሰውን የነጭ ሐር ልብስ ይልበስ ። ዘፀ፡ ፳፱ ፳፱ ፡ ዘኍ፡ ፳ ፳፮ ።

፴፬ ወያስተሠሪ በቅድስተ ቅዱሳን ፡ ወበደብተራ ዘመርጡል ፡ ወበምሥዋዕ ያስተሠሪ ሎቱ ፡ ወበእንተ ካህናትኒ ፡ ወበእንተ ኵሉ ተዐይን ያስተሠሪ ።

በቅድስተ ቅዱሳን (አሥሩ ክንድ) በደብተራ ኦሪት ፡ (ሃያ ክንድ) በመሠውያውም ኃጢአታችሁን ያስተሥርይ የካህናቱንና የሠራዊቱን ሁሉ ኃጢአት ያስተሥርይ ።

፴፭ ወዝንቱ ሕገ ይኩንክሙ ዘለዓለም ፡ ከመ ያስተሥሪ በእንተ ደቂቀ እስራኤል እምኵሉ ኃጢአቶሙ ፡ ወምዕረ ለለዓመት ይገብሮ ፡ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

ይህም የእስራኤልን ልጆች ከኃጢአታቸው ያነጻቸው ዘንድ ለዘለዓለም ሥርዓት ይሁናችሁ ፡ እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው በዓመት አንድ ጊዜ ያድርገው ።

## ምዕራፍ ፲፯ ።

፩ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ በሎሙ ለአሮን ወለደቂቁ ፡ ወለኵሎሙ ደቂቀ እስራኤል ፡ ወንግሮሙ ዘንተ ቃለ ዘአዘዘ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው እንዲህም አለው ፤ ለአሮንና ለልጆቹ እግዚአብሔር ያዘዘውን ይህን ቃል ንገራቸው ።

፪ ወይቤ ብእሲ ብእሲ እምቤተ እስራኤል ፡ እመበ ዘጠብሐ ላሕመ ፡ አው በግዐ ፡ አው ጠሌ በውስተ ትዕይንት ፡ ወእመኒ በአፍአ እምትዕይንት ፡ ኢያምጽእ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ከመ ይግበሮ መሥዋዕተ ፡ አው ዘመድኃኒት ዘኀሩይ ለመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ።

ከእስራኤል ልጆች ወገን አንዱም ሰው በከተማው ውስጥ ወይም ከከተማው ውጭ በሬ ወይም በግ ወይም ፍየል የሠዋ ቢኖር ፡ እግዚአብሔር ወዶ ሊቀበለው ወይም የተመረጠ መሥዋዕተ መድኃኒት አድርጎ ወደ ደብተራ ኦሪት አያምጣው ።

፫ ወእምከመ ጠብሖ በባዕድ ኢያምጽኦ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ከመ ያብእ ቍርባነ ለእግዚአብሔር ቅድመ ደብተራሁ ለእግዚአብሔር ።

በሌላም ቦታ ካረደው በኋላ ፡ ለእግዚአብሔር ማደርያ ደጃፍ አያምጣው ።

፬ እስመ ቀተለ ነፍስ ይከውኖ ለውእቱ ብእሲ ፡ ወከዓዊ ደም ውእቱ ፡ ለትሠሮ ይእቲ ነፍስ እምሕዝባ ፡ ከመ ኢያምጽኡ ደቂቀ እስራኤል መሥዋዕቲሆሙ ኵሎ ዘይሠውዑ በገዳም ።

በዚያ ሰው ላይ ነፍስ መግደል ይሆንበታልና ፡ ደም አፍሳሽም ነውና ፡ የእስራኤል ልጆች በምድረ በዳ የሠዉትን መሥዋዕታቸው እንዳያመጡ ያች ሰውነት ከወገኖቿ ተለይታ ትጥፋ ።

፭ ወያበውእዎ ለእግዚአብሔር ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ኀበ ካህን ፡ ወይሠውዕዎ መሥዋዕተ መድኃኒት ለእግዚአብሔር ።

ለእግዚአብሔር ወደ ደብተራ ኦሪት ደጃፍ ወደ ካህን ያግቡት ፡ መሥዋዕተ መድኃኒትም አድርገው ለእግዚአብሔር ይሠዉት ። ዘፍ፡ ፳፩ ፳፫ ፡ ዘዳ፡ ፲፪ ፱ ።

፮ ወይክዑ ካህን ደሞ ላዕለ ምሥዋዕ ፡ ቅድመ እግዚአብሔር ኀበ ኆኅተ ደብደራ ዘመርጡል ፡ ወይገብር ስብሐ ለመዓዛ ሠናይ ቅድመ እግዚአብሔር ።

ካህን ደሙን ከደብተራ ኦሪት ደጃፍ በእግዚአብሔር ፊት በመሠውያው ላይ ያፍሰው ፡ ስቡንም እግዚአብሔር ወዶ ሊቀበለው በጎ መዓዛ አድርጎ በምሥዋዑ ላይ ያጢሰው ። ዘፍ፡ ፰ ፳፩ ፡ ዘሌዋ፡ ፱ ፴፩ ።

፯ ወኢይሡዑ መሥዋዕቶሙ ለከንቱ በዘበቱ ይዜምዉ ድኅሬሆሙ ፡ ወከመዝ ይኩንክሙ ሕገ ዘለዓለም በመዋዕሊክሙ ።

ጣዖቱን ተከትለው (አምልከው) የሚሰስኑበት መሥዋዕታቸውን በከንቱ አይሠው ፡ ባለ ዘመናችሁም እንዲህ ሥርዓት ይሁናችሁ ። ዘፀ፡ ፴፬ ፲፩ ፡ ዘዳ፡ ፴፩ ፲፮ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወበሎሙ ብእሲ ብእሲ እምደቂቀ እስራኤል አው እምግዩራን እለ ሀለዉ ኀቤክሙ ዘገብረ መሥዋዕተ መድኀኒት ለእግዚአብሔር፣ አው ቍርባነ ኢያምጽአ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ከመ ይግበሮ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር ለትሠሮ ይእቲ ነፍስ እምሕዝባ። | ፰ | ከእስራኤል ልጆች ወገን ወይም ከናንተ ዘንድ ከሚኖሩት መጻተኞች ወገን አንዱም አንዱም ለእግዚአብሔር መሥዋዕት የሠዋ፣ ወይም ቍርባን ያገባ ሰው ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ያደርገው ዘንድ ወደ ደብተራ ኦሪት ደጃፍ ባያመጣው ያች ሰውነት ከወገኗ ተለይታ ትጥፋ። |
| ወብእሲ ብእሲ እምደቂቀ እራኤል፣ አው እምግዩራን እለ ሀለዉ ኀቤክሙ፣ ዘበልዐ እምኵሉ ደም አቀውም ገጽየ ላዕለ ይእቲ ነፍስ እንተ በልዐት ደመ፣ ወእደመስሳ እምሕዝባ። | ፱ | ከእስራኤል ልጆች ወገን ወይም ከናንተ ዘንድ ከሚኖሩት ስደተኞች አንዱም አንዱም ሰው ከደሙ ቢበላ፣ በዚያች ሰውነት ገጽ መዓቴን አጸናባታለሁ፣ ከወገኖቿም ለይቼ አጠፋታለሁ። ዘፍ፣ ፱ ፬፣ ፩ ሳሙ፣ ፲፬ ፴፫። |
| እስመ ደም ነፍሱ ውእቱ ለኵሉ ዘሥጋ፣ ወአነ ረሰይክዎ ለክሙ ለመሥዋዕት በዘቦቱ ያስተሠርዩ በእንተ ነፍስክሙ፣ እስመ በደሙ ትትቤዘ ነፍስክሙ። | ፲ | ደም ለሥጋዊ (ፍጥረት) ሁሉ ነፍሱ ነውና፣ እኔም ኃጢአት በሚያስተሠርዩላችሁ ገንዘብ ለነፍሳችሁ መዳኛ ሊሆን ለናንተ መሥዋዕት አደረግሁት ነፍሳችሁ በደሙ ምክንያት ትድናለችና። ማር፣ ፲፬ ፳፬፣ ሮሜ ፭ ፱። |
| ወበእንተ ዝንቱ እቤለክሙ ለደቂቀ እስራኤል ኵላ ነፍስ እንተ እምኔክሙ ኢትብላዕ ደመ፣ ወግዩር ዘሀሎ ኀቤክሙ ኢይብላዕ ደመ። | ፲፩ | ስለዚህም ነገር እናንተን የእስራኤል ልጆች እንዲህ አልኋችሁ፣ ከናንተ ወገን የሆነች ሰውነት ሁሉ ደሙን አትብላ፣ ከናንተ ዘንድ ያለ መጻተኛም ደም (ብርንዶ) አይብላ። |
| ወብእሲ ብእሲ እምደቂቀ እስራኤል፣ አው እምግዩራን እለ ሀለዉ ኀቤክሙ፣ እመቦ ዘነሠአ ንዴወ፣ ወቀተለ እምእንስሳ፣ አው ዖፈ እምዘይከውነክሙ ለበሊዕ ይክዑ ደሞ፣ ወይደፍኖ በመሬት። | ፲፪ | ከእስራኤል ልጆች ወገን ወይም በመካከላችሁ ከሚኖሩት ስደተኞች ወገን፣ አደን ቢያድን ልትበሉት ከሚገባችሁ ወገን (እንደ ድኩላ፣ አጋዘን፣ ቆቅ፣ ዥግራ) ያለውን ደሙን አፍስሶ አፈር ያልብሰው። ዘዳ፣ ፲፪ ፲፮። |
| እስመ ደሙ ለኵሉ ዘሥጋ ነፍሱ ውእቱ። | ፲፫ | የሥጋዊ ደማዊ ፍጥረት ሁሉ ደሙ ነፍሱ ነውና (ነፍሱ ደሙ ነውና)። |
| ወይቤሎሙ ለደቂቀ እስራኤል፣ ደሞ ለኵሉ ዘሥጋ ኢትብልዑ፣ እስመ ደሙ ለኵሉ ዘሥጋ ነፍሱ ውእቱ፣ ወኵሉ ዘበልዖ ለይሠሮ። | ፲፬ | የእስራኤልን ልጆች የሥጋዊ ፍጥረት ሁሉ ደሙ ነፍሱ ነውና፣ የሥጋዊን የደማዊን ሁሉ (ብርንዶ) አትብሉ የበላውም ሁሉ ይጥፋ አላቸው። ዘፍ፣ ፱ ፬። |
| ወኵሉ ነፍስ ዘበልዐ ምውተ፣ አው ብላዐ አርዌ፣ እመኒ ዘእምፍጥረቱ እስራኤል፣ ወእመኒ ግዩር፣ የሐፅብ አልባሲሁ፣ ወይትሐፀብ በማይ ሥጋሁ ወርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ። | ፲፭ | የሞተውን በክት ወይም የአውሬ ትራፊን የበላ ሁሉ ትውልዱ ከእስራኤል ወይም ከስደተኛ ወገን ቢሆን ልብሱን ይጠብ፣ ሰውነቱንም በውኃ ይታጠብ እስከ ሠርክም ርኩስ ነው። ዘፀ፣ ፳፪ ፴፩፣ ሕዝ፣ ፬ ፲፬። |
| ወእመሰ ኢሐፀበ አልባሲሁ፣ ወኢተሐፅበ ሥጋሁ በማይ ይከውን ኃጢአት ላዕለ ርእሱ። | ፲፮ | ልብሱን ባያጥብ፣ ሰውነቱንም በውኃ ባይታጠብ ግን በራሱ ላይ ኃጢአት በደል ይሆንበታል። ዘኍ፣ ፲፱ ፳። |

## ምዕራፍ ፲፰።

| | | |
|---|---|---|
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ፣ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ በከመ ምግባሮሙ ለምድረ ግብጽ ዘነበርክሙ ባቲ ኢትግበሩ። | ፩ | እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው፣ እኔ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ነኝና በአገራቸው ተቀምጣችሁ እንደ ነበራችሁባቸው እንደ ግብጻውያን ያለ ሥራ አትሥሩ ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው አለው። |
| ወበከመ ምግባሮሙ ለምድረ ከነአን ዘአነ አበውአክሙ ህየ ኢትግበሩ፣ ወኢትሑሩ በሕጎሙ። | ፪ | እኔ በዚያ በማገባችሁ በከነዓን ምድር ብትኖሩ እንደ ከነዓን ሰዎች ያለ ሥራ አትሥሩ፣ በሕጋቸውም አትኑሩ። |
| ኵነኔ ዚአየ ግበሩ፣ ወትእዛዝየ ዕቀቡ፣ ወባቲ ወሑሩ፣ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ። | ፫ | ፍርዴን ፍረዱ (አድርጉ) ትእዛዜንም ጠብቁ በርሷም ጸንታችሁ ኑሩ፣ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ። |
| ዕቀቡ ትእዛዝየ ወኵሎ ኵነኔየ ወግበርዎ፣ እስመ ዘገብሮ ሰብእ የሐዩ ቦቱ፣ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ። | ፬ | ሕጌንና ትእዛዜን ሁሉ ጠብቁ፣ አድርጉትም የሠራው ሰው በሱ ይድናልና ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ። |
| ብእሲ ብእሲ ኀበ ኵሉ ሰብኡ ወሥጋሁ ዘይከውን ኢይባእ ይክሥት ኃፍረቶ፣ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ። | ፭ | ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና አንዱም አንዱም ሰው ወደ ወገኑ ሚስት አይድረስ፣ ዘመዱ ወደሚሆንም ሁሉ ኃፍረቱን ይገልጥ ዘንድ አይቅረብ። ዘሌ፣ ፳ ፲፱። |
| ኃፍረተ አቡከ ወኃፍረተ እምከ ኢትክሥት፣ እስመ እምከ ይእቲ። | ፮ | እናትህ ናትና የእናትህን ኃፍረት አትግለጥ፣ (አትድረስባት)። |

| | | |
|---|---|---|
| ኃፍረተ ብእሲተ አቡከ ኢትክሥት፡ እስመ ኃፍረተ አቡከ ውእቱ ። | ፯ | ያባትህን ሚስት ኀፍረት አትግለጥ፡ ያባትህ ኀፍረት ነውና ። ፩ ቆሮ፡ ፭ ፩ ። |
| ኃፍረተ እኅትከ እንተ እምአቡከ አው እንተ እምእምከ ኢትክሥት ። | ፰ | ከአባትህ የተወለደች ወይም ከናትህ የተወለደች የእኅትህ ኀፍረት አትግለጥ ። ፪ ሳሙ፡ ፲፫ ፲፪ ። |
| ወእመኒ እንተ በአፍአ ተወልደ፡ ወእመኒ እንተ እምአዝማዲከ ይእቲ ኢትክሥት ኃፍረታ ። | ፱ | በውጭም የተወለደች ብትሆን ከዘመዶችህ የተወለደችም ብትሆን ኀፍረቷን አትግለጥ ። ሕዝ፡ ፳፪ ፲፩ ። |
| ኃፍረተ ወለተ ወልድከ፡ አው ወለተ ወለትከ ኢትክሥት ኃፍረቶ፡ እስመ ኃፍረትከ ውእቱ ። | ፲ | የወንድ ልጅህን ልጅ፡ የሴት ልጅህን ልጅ ኀፍረት አትግለጥ ኀፍረትህ ነውና ። |
| ኃፍረተ ወለተ ብእሲተ አቡከ ኢትክሥት፡ እስመ እኅትከ ወወለተ እምከ ይእቲ ። | ፲፩ | ያባትህን ሚስት ልጅ (የንጀራ ናትህ) ኀፍረት አትግለጥ፡ የእንጀራ እናትህ ልጅ እኅትህ ናትና ። |
| ኃፍረተ እኅተ አቡከ ኢትክሥት፡ እስመ ቤተ አቡከ ይእቲ ። | ፲፪ | ያባትህን እኅት ኀፍረት አትግለጥ፡ ያባትህ ወገን ናትና ። |
| ኃፍረተ እኅተ እምከ ኢትክሥት፡ እስመ እምቤተ እምከ ይእቲ፡ | ፲፫ | የናትህን እኅት ኀፍረት አትግለጥ፡ የናትህ ወገን ናትና ። |
| ኃፍረተ ብእሲተ እኁሁ ለአቡከ ኢትክሥት፡ እስመ ዘመድከ ይእቲ ። | ፲፬ | የአባትህን ወንድም የአጐትህን ሚስት ኀፍረት አትግለጥ፡ ዘመድህ ናትና ። |
| ኃፍረተ ብእሲተ ወልድከ ኢትክሥት እስመ ብእሲተ ወልድከ ይእቲ ። | ፲፭ | የልጅህን ሚስት ኀፍረት አትግለጥ፡ የልጅህ ሚስት ናትና ። ዘፍ፡ ፴፰ ፳፯ ። ሕዝ፡ ፳፪ ፲፱ ። |
| ኃፍረተ ብእሲተ እኁከ ኢትክሥት፡ እስመ ኃፍረተ እኁከ ውእቱ ። | ፲፮ | የወንድምህን ሚስት ኀፍረት አትግለጥ፡ የወንድምህ ኀፍረት ነውና ። ዘዳ፡ ፳፭ ፭፡ ማቴ፡ ፳፪ ፳፬ ። |
| ወኃፍረተ ብእሲት ምስለ ወለታ ኢትክሥት፡ ወኢዘወለተ ወልዳ፡ ወኢዘወለተ ወለታ ኢትግበር ከመ ትክሥት ኃፍረቶን፡ እስመ ቤትከ ውእቶን፡ ወኃጢአት ውእቱ ። | ፲፯ | የሴቲቱን ኀፍረት ከልጅዋ ጋር አትግለጥ፡ የወንድ ልጅዋንና የሴት ልጅዋን ልጅ ኀፍረት አትግለጥ፡ ኀፍረተ ሥጋቸውን ትገልጥ ዘንድ ኃጢአትም ነውና ወገኖችህ ናቸውና ። ዘሌዋ፡ ፳ ፲፬ ። |
| ወብእሲት ምስለ እኅታ ኢታውስብ፡ ከመ ኢታስተቃንእን፡ ወኢትክሥት ኃፍረቶን፡ ለዘቲኒ ወለእንታክቲኒ እንዘ ዓዲሃ ሕያውት ይእቲ ። | ፲፰ | ሚስትህ በሕይወት ሳለች እንዳታቃናቸው (እኅቷ ጣውንቷ እንዳትሆን) እኅትማማችን አታግባ፡ የሁለቱንና የዚያችን ኀፍረት አትግለጥ ። ፩ ሳሙ፡ ፩ ፯ ። |
| ወኀበ ብእሲት ትክት ኢትባእ፡ ዘእንበለ ትንጻሕ፡ ከመ ትክሥት ኃፍረታ፡ እንዘ ዓዲሃ ርኵስት ይእቲ ። | ፲፱ | ገና በግዳጅዋ ሳለች ከአደፏ ሳትነጻ ኀፍረቷን ትገልጥ ዘንድ በግዳጅ ወዳለች ሴት አትግባ ። |
| ወኢትባእ ኀበ ብእሲተ ካልእከ፡ ከመ ትስክብ ምስሌሃ ወኢትዝራእ ዘርአከ ላዕሌሃ ። | ፳ | ከርሷ ጋር ትተኛ ዘንድ ወደ ባልንጀራህ ሚስት አትግባ፡ ዘርህንም በርሷ አትዝራባት ። ምሳ፡ ፯ ፳፱ ። |
| ወኢታብተፃምድ ለመልአክ ወልደከ፡ ወኢታርኵስ ስሞ ለቅዱስ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክከ ። | ፳፩ | ልጅህን (ለአሕዛብን) አለቃ አታሳድር፡ (ከአሕዛብ አለቃ አታጋባ) የቅዱስም ስሙን አታስነቅፍ ፈጣሪህ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ። ዘፍ፡ ፳፪ ፭፡ ዘፀ፡ ፲፫ ፲፪ ። |
| ወምስለ ተባዕት ኢትስክብ፡ ከመ አንስት እስመ ርኩስ ውእቱ ። | ፳፪ | ከሴት ጋር እንደምትተኛ ከወንድ ጋር አትተኛ፡ የረከሰ ነውና ። ዘፍ፡ ፳ ፲፫፡ ሮሜ ፩ ፳፯ ። |
| ወኢትሑር ኀበ እንስሳ፡ ከመ ኢታውዕእ ዘርአከ ላዕሌሃ፡ ከመ ኢትርኰስ ባቲ፡ ወብእሲትኒ ኢትሑር ኀበ እንስሳ ከመ ይስክብ፡ እስመ ርኩስ ውእቱ ። | ፳፫ | ዘርህን እንዳትዘራባት በሷም እንዳትረክስ ወደ እንስሳ አትቅረብ፡ ሴትም ይደርስባት ዘንድ ወደ እንስሳ አትሂድ፡ የረከሰ ነውና ። ዘሌዋ፡ ፳ ፲፭፡ ዘፀ፡ ፳፪ ፲፱ ። |
| ወኢታርኵሱ ርእሰክሙ በዝንቱ ኵሉ፡ እስመ በዝንቱ ኵሉ ረኵሱ አሕዛብ እለ አነ አወፅኦሙ እምቅድሜክሙ ወአገመንዋ ለምድር ። | ፳፬ | እኔ ከፊታችሁ የማወጣቸው አሕዛብ በዚህ ሁሉ ረክሰዋልና፡ ምድርንም አርክሰዋታልና፡ በዚህ ሁሉ ራሳችሁን አታርክሱ ። ማቴ፡ ፲፭ ፲፰፡ ፩ ቆሮ፡ ፫ ፲፯ ። |
| ወበእንተ ዝንቱ ፈደይክዎሙ፡ ወተቈጥዖቶሙ ምድር ለእለ ይነብሩ ላዕሌሃ ። | ፳፭ | ስለዚህም ፍዳቸውን አመጣሁባቸው ምድርም የሚኖሩባትን ሰዎች ተቈጣቻቸው ። ኢሳ፡ ፳፯ ፳፩፡ ኤር፡ ፱ ፱ ። |
| ወዕቀቡ ኵሎ ሕግየ ወኵነኔየ፡ ወኢትግበሩ ምንተኒ እምዝንቱ ኵሉ ርኩስ፡ ወኢዘእምፍጥረቱ እስራኤል፡ ወኢግዩር ዘሀለወ ኀቤክሙ ። | ፳፮ | ሕጌን ጠብቁ ፍርዴንም ጠንቅቁ ነውር ከሆነው ከዚህ ሁሉ ምንም ምን አትሥሩ፡ ትውልዱ ከእስራኤልም ቢሆን ከናንተ ዘንድ የሚኖር መጻተኛም ቢሆን ይህን ሁሉ አትሥሩ ። ዘሌዋ፡ ፲፰ ፬ - ፭ ። |
| እስመ ዘንተ ኵሎ ርኵሰ ገብሩ ሰብእ እለ እምቅድሜ | ፳፯ | ከናንተ አስቀድሞ በዚህ ዓለም የተፈጠሩ ሰዎች ይህ |

ኩሙ ተፈጥሩ ውስተ ምድር ፡ ወአንመንዋ ለምድር ።
፳፰ አንትሙኒ ዑቁ ከመ ኢትትቄማዕክሙ ምድር ለእመ አርኰስክምዋ ፡ በከመ ተቄየቶሙ ለአሕዛብ እለ እም ቅድሜክሙ ።
፳፱ እስመ ኵሉ ዘገብረ እምዝንቱ ኵሉ ርኵስ ትሠሮ ይእቲ ነፍስ እምሕዝባ፡እንተ ገብረቶ ።
፴ ወዕቀቡ ትእዛዝየ ከመ ኢትግበሩ እምኵሉ ሕጎሙ ለርኩሳን ፡ ዘኮኑ እምቅድሜክሙ ፡ ወኢትርኰሱ በሙ ፡ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ።

ምዕራፍ ፲፱ ።

፩ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ በሎሙ ለኵሉ ተዐይነ ደቂቀ እስራኤል ፡ ቅዱሳነ ኩኑ እስመ ቅዱስ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ።
፪ አሐዱ አሐዱ እምኔክሙ ይፍራህ አበሁ ወእሞ ወሰንበታትየ ዕቀቡ ።
፫ ወኢትትልዉ አማልክተ ፡ ወኢትግበሩ ለክሙ አማልክተ ዘስብክ ፡ እስመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክክሙ ።
፬ ወእመ ሦዕክሙ መሥዋዕተ መድኃኒት ለእግዚአብሔር እንዘ ሐክሙ ሡዑ ።
፭ ወበዕለተ ትሠውዑ ይበልዕዎ ፡ አው በሳኒታ ፡ ወለአመ ዘተርፈ በሣልስት ዕለት ያውዕይዎ በእሳት ።
፮ ወለእመሰ በልዕዎ ውስተ ብትክ ይትኄለቍ ወኢይት ሜከፎ ።
፯ ወለዘበልዖ ኃጢአተ ይከውኖ ፡ እስመ አርኰሰ ቅድሳቶ ለእግዚአብሔር ፡ ለትሠሮ ይእቲ ነፍስ እንተ በልዓቶ እምሕዝባ ።
፰ ወእመ ዓእረርሙ ሰብ ተዓፅዱ እክለ ምድርክሙ ፡ ኢታንጽሑ ዓጺደ ገራህትክሙ ፡ ወኢትእርዩ ዘወድቀ እክለ እንዘ ተዓፅዱ ።
፱ ወዓፀደ ወይንክኒ ኢታዐተናጽሕ ቀሪመ ወኢትትቀረም ኅንበበተ ወይንከ ዘወድቀ ለነዳይ ወለግዩር ተኅድጎ ፡ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ።
፲ ወኢትሰርቁ ወኢተሐስዉ ፡ ወአልቦ ዘይትዔገል ካልአ ።
፲፩ ወኢትምሐሉ በስምየ በሐሰት ፡ ወኢታርኵሱ ስሞ ቅዱሰ ለአምላክክሙ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ።
፲፪ ወኢተዓምፅ ካልአከ ወኢትሂድ ፡ ወኢይቢት ዓቤከ ዓስቡ ለዓሳቢከ እስከ ይጸብሕ ።
፲፫ ወኢትንብብ ሕሡመ ላዕለ ጽሙም ፡ ወኢትደይ ዕቀፍተ ቅድመ ዕውር ፡ ወፍርሆ ለእግዚአብሔር አምላክከ ፡ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ።
፲፬ ወኢትግበሩ ዓመፃ በውስተ ፍትሕ ፡ ወኢታድልዉ ለገጸ ነዳይ ፡ ወኢታድልዉ ለገጸ ዓቢይ ፡ በጽድቅ ኰንኖ ለካልእከ ።
፲፭ ወኢትሑር በጕሕሉት ውስተ ሕዝብከ ፡ ወኢትቁም

ን ሁሉ ኃጢአት ሠርተዋልና ምድርንም አስድፈዋታልና።
 ከናንተ አስቀድሞ በነበሩ አሕዛብ እንደ ተበሳጨችበቸው ብታስድፍዋት ምድር እንዳትቄጣባችሁ እናንተም ዕወቁ ። ዘሌዋ፡ ፲፰ ፳፭ ፡ ፳ ፳፱ ።
 ከዚህ ከማይገባ ርኩሰት ሁሉ የሠራ ሰው ሁሉ ያች ኃጢአትን የሠራች ሰውነት ከወገኗ ተለይታ ትጥፋ ።
 ከናንተ አስቀድሞ ይሠሩት የነበሩ የአሕዛብን ሥራ ሁሉ እንዳትሠሩ ትእዛዜን ጠብቁ ፡ በነርሱም አትርከሱበቸው ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ። ዘፀ፡ ፲፰ ፱ ።

ምዕራፍ ፲፱ ።

እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው እንዲህም አለው ፤ ለእስራኤል ልጆች ወገኖች ሁሉ እኔ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ በላቸው ። ዘፀ፡ ፲፱ ፮ ።
 ከናንተ አንዱም አንዱ እናት አባቱን ይፍራ (ያክብር) ሰንበታቴንም ጠብቁ ። ዘፀ፡ ፳ ፲፪ ፡ ዘሌ፡ ፲፱ ፴ ።
 ጣዖታትንም አታምልኩ ፡ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ተመትተው የተሠሩ ጣዖታትን አታቁሙ ።

 ድኅነት የሚገኝበት መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር ብትሠዉ ንጹሐን፡ሁናችሁ ሠዉ ። ዘሌዋ፡ ፲፩ ፲፰ ።
 በሠዋችሁበት ቀን ወይም በማግሥቱ ይብሉት ስሦስተኛው ቀን የተረፈ ቢኖር ግን በእሳት ያቃጥሉት ።
 ቢበሉት ግን በከት ከመብላት ይቈጠርባቸዋል (እግዚአብሔርም) አይቀበለውም ። ዘሌዋ፡ ፲ ፲፰ ።
 በበላውም ሰው ዕዳ በደል ይሆንበታል ፡ የተቀደሰውን የእግዚአብሔር መሥዋዕት አርክሷልና ፡ ይህንንም የበላች ሰውነት ከወገኗ ተለይታ ትጥፋ ።
 የምድራችሁንም አዝመራ በምታጭዱበት በዓጨዳችሁ ወራት የእርሻችሁን ድንበር አጥርታችሁ አትጨዱ ፡ ስታጭዱም የወደቀውን እኽል አትልቀሙ ።
 የወይንህንም ብታ አጥርተህ አትልቀም ፡ የወይንህንም ዘለላ አትልቀም ፡ የወደቀውን ለደኻ ለመጻተኛ ተውለት ፈጣሪህ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ። መክ፡ ፭ ፰ ።
 አትስረቁ ፡ ሐሰትንም አትናገሩ ፡ ባልንጀራውን የሚቀማ አይኑር ። ኤፌ፡ ፬ ፳፭ ፡ ዘፀ፡ ፳ ፲፭ ።
 ስሜንም ጠርታችሁ በሐሰት፡ አትማሉ ፡ የከበረውን የአምላካችሁን ስም አታስነቅፉ ፡ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ። ዘሌዋ፡ ፲፰ ፳፩ ።
 ባልንጀራህን አትበድል ፡ አትቀማው የሞያተኛህንም ደመወዝ እስኪነጋ ድረስ በአንተ ዘንድ አይደር ።
 በደንቆሮው ክፉ ነገር አትናገር ፡ በዕውርም ፊት ዕንቅፋት አታኑር ፡ ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ፍራው ፡ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ። ዘዳ፡ ፳፯ ፲፰ ።
 በፍርድም ጊዜ ሐሰት አትፍረዱ ፡ ለባለጸጋም ለድኻም አታድሉ ፡ ለባልንጀራህ በእውነት፡ ፍረድለት (ፍረድበት) ። ዘፀ፡ ፳፫ ፲ ፡ ዘዳ፡ ፩ ፲፯ ፡ ያዕ፡ ፪ ፱ ።
 ወደ ወገኖችህም በተንኰል (በሸንገላ) አትሂድ ፡ በበ

ላዕለ ነፍሰ ካልእከ፤ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክከ ።

ልንጀራህ ሰውነት ላይ በጠላትነት አትነሣ፤ ፈጣሪህ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ።

፲፮ ወኢትዓምፆ ለካልእከ ፡ ወኢትጽልአ በልብከ ፡ ዝልፎ ወአይድዖ እንተ ተኀይሶ ለካልእከ፡ ወኢትግበር በእንቲአሁ ኃጢአተ ።

ባልንጀራህን አትበድለው፤ ገልጸህ ዝለፈው (ምከረው) እንጂ በልብህ አትጥላው፤ ባልንጀራህንም የምትነቅፈውን ገልጸህ ንገረው፤ ስለሱም ኃጢአት አትሥራ ።

፲፯ ወኢትትበቀል ለሊከ ፡ ወኢትትቀየም ላዕለ ደቂቀ ሕዝብከ፤ ወአፍቅር ካልእከ ከመ ነፍስከ፡ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክከ ።

አንተ ቂም በቀል አትያዝ፤ በወገኖችህም ልጆች አትቀየም፤ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ፤ ፈጣሪህ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ። ዘዳ፡ ፱ ፲ ።

፲፰ ወዕቀብ ሕግየ፡ ወኢትሕርስ ብዕራየከ በዘባዕድ አርዑት፤ ወኢትትክል ውስተ ዓፀደ ወይንከ ዘዘዚአሁ፤ ወልብስኒ ዘእምክልኤቱ እንመቱ ኃፍረት ውእቱ ወኢትልበስ ።

ሕጌን ጠብቅ፡ በሬህንም በሌላው ቀንበር አትረስ፤ በወይንህም ቦታ እየራሱ የሆነ ተክል አትትክል፤ ኀፍረት ነውና፤ ሥራው ሁለት የሆነ ልብስን አትልበስ ።

፲፱ ወዘሰከበ ምስለ ብእሲት እንተ ዕቅብት ይእቲ ለብእሲ ግብር፡ እንተ ቤዛሃ ኢተውህበ ላቲ፤ ወግዕዛነ ኢተግዕዘት ይኤይኑ ሎቱ ዘይሁብ፡ ወኢይመውት እስመ ኢግዕዘት ።

ለወንድ ብርያ የተጠበቀች (የታጨች) ዋጋዋን ያልተሰጠላት ሴት ብርያን ከክብር ያሳነሰ፤ የሚከፍለው ዋጋዋን ይገምግሙለት፤ ነፃ አልወጣችምና ይሙት በቃ አይፈረድበትም ።

፳ ወያመጽእ ዘበእንተ ንስሓሁ በግዐ ለእግዚአብሔር ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ።

እሱም ስለ ንስሐ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ወደ ደብተራ ኦሪት ያምጣ ። ዘሌዋ፡ ፭ ፲፭ ።

፳፩ ወያስተሠሪ ሎቱ ካህን በውእቱ በግዕ ቅድመ እግዚአብሔር፤ እስመ ነስሐ በዘአበሰ፤ ወትትኀደግ ሎቱ ኃጢአቱ እንተ አበሰ ።

ካህንም ስለ ኃጢአቱ የቀረበውን በግ በእግዚአብሔር ፊት ሠውቶ ያስተሥርይለት፤ በበደለው በደል ተጠጥቷልና፤ የበደላትም በደል ትሠረይለታለች ።

፳፪ ወእመ በእክሙ ውስተ ምድር እንተ ይሁበክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ፡ ወተከልክሙ እምኵሉ ዕፅ ዘይበልዑ ታነጽሕዎ እምኵሉ ርኵስ፤ ወፍሬሁኒ ዘሠለስቱ ዓም ርኩስ ውእቱ ለክሙ ኢትብልዕዎ ።

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ወደሚሰጣችሁ ምድር በገባችሁ ጊዜ የሚበሉት ተክላ - ተክል ሁሉ ብትተክሉ ከኃጢአት ሁሉ ንጹሕ አድርጉት፡ የሦስተኛውም ዘመን ፍሬው ለናንተ ርኩስ ነውና አትብሉት ። ዘፀ፡ ፯ ፲፱ ።

፳፫ ወበራብዕ ዓም ይኩን ኵሉ ፍሬሁ ቅዱስ ወስቡሕ ለእግዚአብሔር ።

በአራተኛው ዓመት ያፈራው ፍሬ ሁሉ ግን ለእግዚአብሔር የከበረ የተመሰገነ ይሁን ። ዘዳ፡ ፲፱ ፲፯ ።

፳፬ ወበሐምስ ዓም ብልዑ፡ ውእቱ ለክሙ ፍሬሁ፡ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ።

በአምስተኛው ዘመን ያፈራው ፍሬው ለናንተ ነው፤ ብሉት፤ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ።

፳፭ ወኢትብልዑ በውስተ አድባር፡ ወኢትርከሱ፡ ወኢትጠየሩ በዖፍ ።

መሥዋዕቱንም በተራራዎች ላይ ሁናችሁ አትብሉት አትርከሱም፤ በዖፍም አታምልኩ፤ (አታሟርቱ) ሞራ ገላጭም አትሁኑ ። ዘሌዋ፡ ፫ ፲፯፤ ዘዳ፡ ፲፰ ፲፬ ።

፳፮ ወኢትግበሩ ለክሙ ቈናዝዐተ እምፀጕረ ርእስክሙ፤ ወኢትላጽዩ ጽሕመ ገጽክሙ ።

ከራሳችሁም ጠጕር ጉትያ (ቍንጮ) አታውጡ (አታጕትጉ) የፊታችሁንም ጢም አትላጩ ።

፳፯ ወእመበ ዘሞተ መላጼ ኢታቅርቡ ውስተ ሥጋክሙ፤ ወኢትፍጥሩ ለክሙ ፈጠራ፤ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ።

የሞተም ሰው ቢኖር ወደ ሰውነታችሁ ምላጭ አታቅርቡ አዲስ መልክ አትፍጠሩ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ። ኢሳ፡ ፲፭ ፪፤ ኤር፡ ፱ ፳፯ ።

፳፰ ወኢታርኵስ ወለተከ ፡ ወኢታዘምዋ ፡ ወኢትዘሙ ምድር ወኢትምላእ ምድር ዓመፃ ።

ሴት ልጅህን ክብሯን አሳንሰህ ሴሰኛ አታሰኛት ምድር አትሰስን፤ ምድር ዓመፅን አትምላ ። ዘዳ፡ ፳፫ ፲፯ ።

፳፱ ዕቀቡ ሰንበታትየ፤ ወፍርሁ እምቅዱሳንየ፡ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ።

ቅዳሜ ቅዳሜን አክብሩ፤ ከቅዱሳን (ነቢያት ካህናት) የተነሣም ፍሩ፤ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝና ።

፴ ወኢትትልዉ ሰብአ ሐረስ ፡ ወሰብአ ሥራይ ከመ ኢትርከሱ በሙ፡ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ።

መናፍስት ጠሪዎችንና ሟርተኞችን ሰዎች አትከተሉ በነርሱ እንዳትረክሱ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝና ።

፴፩ ቅድመ ዘሲበት ተንሥእ፡ ወአክብር ገጸ አረጋዊ፡ ወፍራህ እግዚአብሔርሃ አምላክከ፡ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ።

ሽማግሌ ሰው ሲመጣ ከፊቱ ተነሥ፤ የሽማግሌን ፊት አክብር፤ ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ፍራ፤ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ። ምሳ፡ ፳ ፳፱፤ ፩ ጢሞ፡ ፭ ፩ ።

፴፪ ወለእመቦ ዘመጽአ ኀቤክሙ ግዩር ኢትሣቅይዎ በውስተ ምድርክሙ ከመ ዘእምፍጥረቱ ይኩን ለክሙ ግዩር ዘመጽአ ኀቤክሙ ።

ወደናንተ የመጣ ስደተኛም ቢኖር በአገራችሁ መከራ አታጽኑበት ወደናንተ የመጣ ስደተኛ ለናንተ (ከእስራኤል) እንደ ተወለደ ይሁንላችሁ ። ዘፀ፡ ፳፭ ፳፩ ።

፴፬ ወአፍቅርዎ ከመ ርእስክሙ እስመ ግዩራን ክንክሙ
በምድረ ግብጽ ፡ እነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክክሙ ።

እናንተም በግብጽ አገር መጻተኞች ነበራችሁና እንደ
ራሳችሁ አድርጋችሁ ውደዱት ፡ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአ
ብሔር ነኝና ። ዘፀ፡ ፲፱ ፵፭፡ ዘዳ፡ ፲ ፲፱ ።

፴፭ ወኢትግበሩ ዓመፃ በውስተ ፍትሕ ወኢ በውስተ ኍ
ልቈ ሐሳብ ፡ ወኢ በመስፈርት ፡ ወኢ በመዳልው ።

በፍርድ በግምት አቈጣጠር በመስፈሪያ በላዳን በሚ
ዛን ዓመፅን አታድርጉ ። ዘፀ፡ ፳፮ ፱፡ ዘሌ፡ ፲፱ ፲፭ ።

፴፮ መዳልዊክሙ ዘበጽድቅ ይኩን ፡ ወመስፈርትክሙ ዘበጽ
ድቅ ይኩን ፡ ወእእብኒክሙ ዘበጽድቅ ይኩናክ ፡ እስመ እነ
እግዚአብሔር አምላክክሙ ዘአውፃእኩክሙ እምድረ
ግብጽ ።

ሚዛኖቻችሁ የእውነት ሚዛኖች ይሁኑ ፡ መስፈሪያህም
የእውነት መስፈሪያ ይሁን ፡ ደንጊያዎችህም (ኢዋቂዎችህ)
የእውነት ይሁኑልህ ፡ ከግብጽ አገር ያወጣኋችሁ ፈጣሪያ
ችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ። ዘዳ፡ ፳፭ ፲፫ ።

፴፯ ወዕቀቡ ኵሉ ሕግየ ፡ ወኵሉ ትእዛዝየ ወግበርዎ ፡
እስመ እነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ።

ሕጌንና ትእዛዜን ጠብቁ ፡ ፈጽሙትም ፈጣሪያችሁ
እኔ እግዚአብሔር ነኝና ። ዘዳ፡ ፬ ፲፭ ፡ ዘሌ፡ ፲፰ ፬ ።

## ምዕራፍ ፳ ።

## ምዕራፍ ፳ ።

፩ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ በሎሙ ለደ
ቂቀ እስራኤል ።

እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው ፤ የእስራኤልን ልጆ
ች እንዲህ በላቸው አለው ።

፪ እመበ እምደቂቀ እስራኤል አው እምግዩራን እለ ገብ
ኡ ውስተ እስራኤል ዘአስተፃመደ ወልዶ ለሞሌክ ሞተ
ለይሙት ፡ ወሕዝብ እለ ውስተ ምድር ለይውግርዎ በእብን፤

ከእስራኤል ልጆች ወይም በእስራኤል ዘንድ ከሚቀ
መጡት ስደተኞች ማናቸውም ሰው ልጁን ለአሕዛብ አለ
ቃ ያጋባ ቢኖር ይገደል ፡ በአገር ያሉ ወገኖች በደንጊያ
ይውገሩት ። ዘሌዋ፡ ፲፰ ፪ ።

፫ ወአነኒ አቀውም ገጽየ ላዕለ ውእቱ ብእሲ ፡ ወእደመ
ስሶ እምሕዝቡ ፡ እስመ ወሀበ ወልዶ ይጸመድ ለሞሌክ ፡
ከመ ያርኵስ ቅድሳትየ ፡ ወከመ ያርኵስ ስመ ቅዱሳንየ ።

እኔም በዚያ ሰው ገጸ መዓቴን አጸናበታለሁ ፡ ከወገኖ
ቹም ለይቼ አጠፋዋለሁ ፡ ክብሬን ያረክስ ዘንድ የወዳጆቼ
ንም (የቅዱሳን) ስም ያዋርድ ዘንድ ልጁን ለአሕዛብ አለ
ቃ ሰጥቷልና ። ዘሌዋ፡ ፲፯ ፲ ፡ ዘፀ፡ ፴ ፴፫ ።

፬ ወእመሰ ተዓወርዎ ሰብአ ይእቲ ምድር ለውእቱ ብእ
ሲ ፡ ወሠወሩ አዕይንቲሆሙ እምኔሁ እንዘ ያስተፃምድ
ወልዶ ለሞሌክ ወኢቀተልዎ ፡ አቀውም ገጽየ ላዕለ ው
እቱ ብእሲ ፡ ወላዕለ አዝማዲሁ ወእደመስሶ ሎቱ ።

ነገር ግን የዚያች አገር ሰዎች ያንን ሰው ቸል ቢሉት
ልጁን ለአሕዛብ አለቃ ሲሰጥ ዐይኖቻቸውን ከሱ ቢሠ
ውሩ በይገድሉትም ፡ በዚያ ሰውና በዘመዶቹ ገጸ መዓቴን
አጸናለሁ ፡ እሱንም አጠፋዋለሁ ። ዘዳ፡ ፲፯ ፲፯ ፡ ፱ ፭ ።

፭ ወለኵሎሙ እለ ኃብሩ ምስሌሁ ፡ ከመ ይዘምዉ በመ
ላእክት እምሕዝቦሙ ።

ከወገኖቻቸው ተለይው በጣኦታቱ ይሴስኑ ዘንድ ከሱ
ጋር የተባበሩትንም ሁሉ አጠፋቸዋለሁ ። ዘፀ. ፴፬ ፲፭ ።

፮ ወእመበ ብእሲ ዘተለወ ሰብአ ሐረስ ፡ ወሰብአ ሥራይ
ከመ ይዘሙ ድኅሬሆሙ አቀውም ገጽየ ላዕለ ውእቱ ብ
እሲ ወላዕለ አዝማዲሁ ወእደመስሶ እምሕዝቡ ።

እነሱቸውን ተከትሎ ይሴስን ዘንድ ሥር ማሾችንና
ሟርተኞችን የተከተለ ሰው ቢኖር ፡ በዚያ ሰውና በዘመ
ዶቹ ላይ ገጸ መዓቴን አጸናለሁ ፡ ከወገኖቹም ለይቼ አጠ
ፋዋለሁ ። ዘሌዋ፡ ፲፱ ፴፩ ፡ ፲፯ ፲ ።

፯ ወኩኑ ቅዱሳነ እስመ እነ እግዚአብሔር አምላክክሙ
ቅዱስ እነ ወዕቀቡ ሕግየ ወትእዛዝየ ወግበርዎ ፡ እስመ
እነ እግዚአብሔር ዘእቄድሰክሙ ።

እኔ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ቅዱስ ነኝና እናንተም
ቅዱሳን ሁኑ ፡ የማከብራችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ሕጌ
ንና ትእዛዜን ጠብቁ፡ አድርጉት ፈጽሙት ።

፰ ወለእመበ ብእሲ ዘነበበ ኅሡመ ላዕለ አቡሁ ወእሙ
ሞተ ለይሙት እስመ ጌጉይ ውእቱ ።

በአባቱና በናቱ ክፉ ነገር የተናገረ ሰው ቢኖር በደ
ለኛ ነውና የሞት ሞት ይሙት ። ዘፀ፡ ፳፩ ፲፯ ።

፱ ወለእመበ ብእሲ ዘዘመወ በብእሲተ ብእሲ ፡ አው በብ
እሲተ ካልኡ ሞተ ለይሙት ፡ ዘዘመወኒ ወእንተ ዘሞወትኒ።

በሌላ ሰው ሚስት ወይም በባልንጀራው ሚስት ያመ
ነዘረ ሰው ቢኖር ፈጽሞ ይሙት ፡ የሴሰነና የሴሰነች (ሁለ
ቱ ይሙቱ) ። ዘዳ፡ ፳፪ ፳፪፡ ዘሌዋ፡ ፲፰ ፳ ።

፲ ወለእመበ ዘሰከበ ምስለ ብእሲተ አቡሁ ፡ ከሠተ
ኃፍረተ አቡሁ ፡ ሞተ ለይሙት ፡ ወክልኤሆሙ ጌጉያን
እሙንቱ ።

ከአባቱ ሚስት ጋር የተኛ ሰው ቢኖር ፡ ያባቱን ኀፍ
ረት ገልጧልና ሁለቱም በደለኞች ናቸውና ይገደሉ ።

፲፩ ወለመእበ ዘሰከበ ምስለ ብእሲተ ወልዱ ፡ ሞተ ለይ
ሙቱ ክልኤሆሙ ፡ እስመ ኃጢአተ ገብሩ ፡ ወጌጉያን
እሙንቱ ።

ከልጁ ሚስት ጋር የተኛ ሰው ቢኖር ፡ ኃጢአት ሠር
ተዋልና በደለኞችም ናቸውና ሁለቱም ይሙቱ ።

፲፪ ወለእመበ ዘሰከበ ምስለ ተባዕት ከመ አንስት ርኩሰ
ገብሩ ፡ ሞተ ለይሙቱ ክልኤሆሙ ጌጉያን እሙንቱ ።

ከሴት ጋር እንደ ሚተኛ ፡ ከወንድ ጋር የተኛ ሰው
ቢኖር ሁለቱም በደለኞች ናቸውና ይሙቱ ፡ ዘፀ፡ ፳፫ ፲፯ ።

፲፫ ዘነሥአ ወለተ ምስ እማ ኃጢአት ውእቱ፡ ወበእሳት ለያውዕይዎሙ ኪያሁ ወኪያሃ፡ ወኢትምጻእ በላዕሌክሙ ኃጢአት ።

ልጂቱን ከናቷ ጋር ቢያገባ ኃጢአት ነው፡ ይህች ኃጢአት ወደናንተ እንዳትመጣ እሱንም እሷንም በእሳት አቃጥሏቸው ። ዘሌዋ፡ ፲፰ ፲፯፡ ዘዳ፡ ፳፯ ፳፫ ።

፲፬ ወዘሰከበ ምስለ እንስሳ ሞተ ለይሙት፡ ወእንስሳሁኒ ቅትሉ ።

በእንስሳም የደረሰ ይሙት፡ ከብቱንም ግደሉት ።

፲፭ ወብእሲትኒ ለእመ ሖረት ኀበ እንስሳ ከመ ይስክብ፡ ብእሲተኒ ቅትሉ፡ ወእንስሳሁኒ ውግሩ ።

ይደርስባት ዘንድ ሴትም ወደ እንስሳ ብትሄድ፡ ሴቲቱን ግደሏት፡ ከብቱንም በደንጊያ ወግራችሁ ግደሉት ።

፲፮ ወዘሰከበ ምስለ እኅቱ፡ እመኒ እንተ እምአቡሁ፡ ወእመኒ እንተ እምእሙ፡ ወርእየ ኀፍረታ፡ ወይእቲኒ ርእየት ኀፍረቶ ፅዕለት ውእቱ፡ ለይሠረዉ በቅድመ ደቂቀ ዘመዶሙ፡ እስመ ከሠተ ኀፍረተ እኅቱ፡ ጌጋየ ይከውኖ ።

ከአባቱ ወይም ከናቱ የተወለደች ብትሆንም ከእኅቱ ጋር የተኛ ኀፍረቷን ቢያይ እሷም ኀፍረቱን ብታይ ጸያፍ ነው፡ የእኅቱን ኀፍረት ገልጧልና በዘመዶቻቸው ልጆች ፊት ይጥፉ፡ ዕዳ በደል ሆኖባቸዋልና ። ዘሌ፡ ፲፰ ፱ ።

፲፯ ወዘሰከበ ምስለ ብእሲት ትክት ወርእየ ኀፍረታ ወከሠተ ነቅዐ ደማ፡ ወይእቲኒ ከሠተት ነቅዐ ደማ፡ ለይሠረዉ ክልኤሆሙ እሙላዶሙ ።

በግዳጅዋ ካለችው ሴት የደረሰ ኀፍረቷን ቢያይ የደሟን ፈሳሽ አይቷልና፡ እሷም የደሟን ፈሳሽ ገልጣለችና፡ ሁለቱም ከዘመዶቻቸው ተለይተው በሞት ይቀጡ ።

፲፰ ወኢትክሥት ኀፍረተ እኅተ አቡከ ወእኅተ እምከ፡ እስመ ዘመዶሙ ለእመ ከሠቱ ኃጢአተ ይከውኖሙ ።

የአባትህንና የእናትህን እኅት ኀፍረት አትግለጥ፡ ዘመዶቻቸው ናቸውና ኀፍረተ ሥጋቸውን ቢገልጡ ኃጢአት ይሆንባቸዋልና ። ዘሌዋ፡ ፲፰ ፲፪ ፡ ፲፫ ፳፬ ።

፲፱ ወዘሰከበ ምስለ እንተ ዘመዱ ከሠተ ኀፍረ ዘመዱ ዘእንበለ ውሉድ ለይሙቱ ።

ከዘመዱ (ከአጐቱ) ሚስት የደረሰ፡ የዘመዱን ኀፍረተ ሥጋ ገልጧልና፡ ልጅ ሳይወልዱ ይሙቱ ።

፳ ወብእሲኒ ዘሰከበ ምስ ብእሲተ እኁሁ ከሠተ ኀፍረተ እኁሁ፡ ዘእንበለ ውሉድ ለይሙቱ ።

ከወንድሙ ሚስት ጋር የተኛ፡ የወንድሙን ኀፍረት ገልጧልና ልጅ ሳይወልዱ ይሙቱ ። ዘሌ፡ ፲፰ ፲፮፡ ፲፱ ፩ ።

፳፩ ወዕቀቡ ኵሎ ትእዛዝየ ወግበርዎ፡ ወኢትትበአሰክሙ ምድር እንተ ውስቴታ አነ አበውአክሙ ከመ ትንበሩ ።

ሕጌን ጠብቃችሁ ሥሩት፡ ትኖሩበት ዘንድ እኔ ወደርሷ የማገባችሁ ምድር እንዳትበቀላችሁ ። ዘሌ፡ ፲፰ ፳፭ ።

፳፪ ወኢትሖሩ በሕገ አሕዛብ እለ አወፅአሙ እምኔክሙ፡ እስመ ዘንተ ኵሎ ገብሩ ወአስቆረርክዎሙ ።

ይህን ሁሉ አድርገዋልና እኔም ተጸይፌአቸዋለሁና ከናንተ በማወጣቸው በአሕዛብ ሕግ ጸንታችሁ አትኑሩ ።

፳፫ ወእቤለክሙ አንትሙ ዘትወርስዋ ለምድሮሙ፡ ወአነ እሁበክሙ ከመ ታጥርይዋ ለምድር እንተ ታውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ዘፈለጥኩክሙ እምኵሉ አሕዛብ ።

ምድራቸውን የምትወርሷት እናንተ ናችሁ፡ ማርንና ወተትን የምታፈስውን ምድር ትገዟት ዘንድ እኔ እሰጣችኋለሁ አልኳችሁ፡ ከአሕዛብ ሁሉ የለየኋችሁ እኔ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ነኝ ። ዘፀ፡ ፫ ፴፫፡ ፲፱ ፫ ።

፳፬ ወፈለጥኩ ለክሙ ማእከለ እንስሳ ዘንጹሕ፡ ወዘኢኮነ ንጹሕ፡ ወማእከለ አዕዋፍ ዘንጹሕ ወዘኢኮነ ንጹሕ፡ ወማእከለ ኵሉ ዘይትሐወስ ውስተ ምድር፡ ወኢታርኵሱ ነፍሰክሙ በእንስሳ ወበአዕዋፍ፡ ወበኵሉ ዘይትሐወስ ውስተ ምድር ዘፈለጥኩ ለክሙ ዘርኩስ ።

ከእንስሳት ንጹሕ የሆነውን፡ ንጹሕ ያልሆነውን ከአዕዋፍም የሚበላውንና የማይበላውን በምድርም ላይ የሚንቀሳቀሰውን ሁሉ ለየሁላችሁ፡ አትብሉ ብዬ የለሁላችሁ እንስሳንና አዕዋፍን በዚህም ዓለም የሚንቀሳቀሰውን ሁሉ በመብላት ሰውነታችሁን አታርክሱ ። ዘሌ፡ ፲፱ ፱ ።

፳፭ ወትከውኑኒ ቅዱሳነ፡ እስመ ቅዱስ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ዘፈለጥኩክሙ እምኵሉ አሕዛብ ከመ ትኩኑኒ ሊተ ።

ለኔ ወገኖቼ ትሆኑኝ ዘንድ ከአሕዛብ ሁሉ የለየኋችሁ እኔ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ንጹሕ ባሕርይ ነኝና እናንተም ንጹሐን ሁኑ ። ፩ ጴጥ፡ ፩ ፲፮፡ ዘሌ፡ ፳፮ ፳፬ ።

፳፮ ብእሲኒ ወብእሲትኒ ለእመቦ ዘኮኑ ሐራስያነ፡ አው ዘሥራይ ሞተ ለይሙቱ፡ ወበእብን ለይውግርዎሙ እስመ ጌጉያን እሙንቱ ።

ወንድ ወይም ሴት ሟርተኞች ሥርማኞች (ቀጠል በጣሾች) ቢሆኑ ፈጽመው ይሙቱ፡ በደለኞች ናቸውና በደንጊያ ወግረው ይግደሉዋቸው ። ዘሌ፡ ፲፱ ፴፩፡ ፳፬ ፱ ።

## ምዕራፍ ፳፩ ።

፩ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፡ በሎሙ ለካህናት ለደቂቀ አሮን፡ ንግሮሙ ከመ ኢይርኵሱ በነፍስ እንተ እምሕዝበሙ ።

እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው አለውም፤ ከቅርብ ዘመዳቸው በተወለዱ ልጆች እንዳይረክሱ ለአሮን ልጆች ለካህናት ንገራቸው አለው ። ሕዝ፡ ፴፬ ፳፭ ።

፪ ወእምቤት ዘቅሩበሙ፡ እመኒ ዘአቡሆሙ፡ አው ዘእምእሞሙ፡ አው ዘእምደቂቆሙ፡ አው ዘእምአዋልዲሆሙ አው ዘእምእኁሁ አው ዘእምእኅቱ ።

ያባታቸውና የናታቸውም ወገን ወይም ከሴቶች ልጆቻቸውና ከወንዶች ልጆቻቸው ወይም ከወንድሙና ከእኅቱ ወገን የተወለዱ ቢሆኑ ።

፫ እው በድንግል እንተ ቅርብት ይእቲ ሎቱ እንተ ኢኮነት ለብእሲ፣ በእሉ ኢይርኩሱ በዘእምሕዝቦሙ ከመ ኢይኩኖሙ ጽእለተ ።

ወይም ለባል ያልታጨች ለሱ አቅራቢያ በሆነች ድንግል ቢሆን ነቀፋ እንዳይሆንበቸው ከወገኖቻቸው በተወለዱ በነዚህ እንዳይረከሱ ንገራቸው ።

፬ ወኢትላጽዩ ርእሰክሙ ላዕለ ዘሞተ ወኢትላጽዩ ጽሕመ ገጽክሙ ወኢትጥብሑ ሥጋክሙ ።

በሞተ ሰው ራሳችሁንና የራሳችሁን ጢም አትላጩ፤ ሬሳችሁንም አትንጩ ። ሕዝ፡ ፵፬ ፳፩ ፡ ፳፬ ፲፯ ።

፭ ወይኩኑ ቅዱሳነ ለአምላክሙ ወኢያርኵሱ ስመ አምላክሙ፣ እስመ እሙንቱ ያቀርቡ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር አምላክሙ ወይኩኑ ቅዱሳነ ።

የፈጣሪያቸውን ስም እንዳያስነቅፉ ለፈጣሪያቸው ንጹሐን ይሁኑ፣ እነሱ ለፈጣሪያቸው እግዚአብሔር መሥዋዕትን ያቀርባሉና ከኃጢአት የተለዩ (የነጹ) ይሁኑ ።

፮ ብእሲተ ዘማ ወጽእልተ ኢያውስቡ፣ ወብእሲተኒ እንተ አውፅአ ምታ እስመ ቅዱስ ውእቱ እግዚአብሔር አምላኩ ።

ለፈጣሪው ለእግዚአብሔር የተለየ ነውና፣ በነውር የተነቀፈችውንና ጋለሞታን ባሏ የፈታትንም ሴት አያግቡ።

፯ ወትቄድሶ እስመ ቍርባኖ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ውእቱ ያቀርብ ።

እሱ የፈጣሪያችሁ የእግዚአብሔርን መሥዋዕት ያቀርባልና አክብረው ።

፰ ወይኩን ቅዱሰ፣ እስመ ቅዱስ አነ እግዚአብሔር ዘአቄድሶ ።

የማነጻው እኔ እግዚአብሔር ንጹሕ ብሆርይ ነኝና ንጹሕ ይሁን ። ዘሌዋ፡ ፳፩ ፲፭፣ ፳፮ ፰ ።

፱ ወለተ ብእሲ ካህን ለእመ አጽአሰት በዝሙት ስመ አቡሃ፣ ያውሥርዋ ላቲ ወበእሳት ያውዕይዋ ።

የካህን ሰው ሴት ልጅ በዝሙት ያባቷን ስም ብታስነቅፍ ይግረፉዋት፣ በእሳትም ያቃጥሏት ። ዘፍ፡ ፴፰ ፳፬ ።

፲ ወካህን ዘየዐቢ እምአኃዊሁ ዘሦጡ ቅብዐ ዲበ ርእሱ ዘቡሩክ ወዘፍጹም ውእቱ እደዊሁ ዘይለብስ ዘቅድሳት፣ ርእሶ ኢይላጺ ወአልባሲሁኒ ኢይሥጥጥ ።

ከወንድሞቹ የሚበልጥ እጁንና ራሱን የከበረ ቅብዐ ክህነት ተቀብቶ የከበረው ልብሰ ተክህኖ የሚለብሰው ካህን ራሱን አይላጭ፣ ልብሶቹንም አይቅደድ ።

፲፩ ወኀበ ኵሉ ነፍስ እንተ ሞተት ኢይበእ፣ ወኢኀበ አቡሁ ወኢኀበ እሙ ከመ ኢይርኩስ ።

ነፍስ ከሞተበት ቤት ሁሉ አይግባ፣ እንዳይረክስ ከባቱም ከናቱም ዘንድ ቢሆን አይግባ ።

፲፪ ወእምውስተ መቅደስ ኢይፃእ ወኢያርኵስ ስሞ ቅዱሰ ለአምላኩ፣ እስመ ቅብዐ ቅዱስ ዘይትቀብዑ ዘአምላኩ ሀለወ ላዕሌሁ፣ እስመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ።

ከቤተ መቅደስም አይውጣ፣ የፈጣሪው የከበረ ስሙንም እንዳያስነቅፍ ተቀብተው የሚከብሩበት የፈጣሪው ቅብዐ ክህነት በላዩ ላይ አለና፣ ፈጣሪው እኔ እግዚአብሔር ነኝና ። ዘሌዋ፡ ፲፯ ፱ ፲፪ ።

፲፫ ወይንሣእ ብእሲተ ድንግለ እምነገዱ ።

ከነገዱ የተወለደች ክብሯን ያላስወሰደች ሴት ያግባ።

፲፬ ብሕተ መበለተ ወእንተ አውፅአ ምታ ወጽእልተ፣ ወዘማ እላንተ ኢያውስብ፣ አላ ድንግለ እምዘመዱ ወእምነገዱ፣ ይንሣእ ሎቱ ብእሲተ ።

ነገር ግን ባሏ የፈታትን ጋለሞታን ክብሯን አስወስዳ የተነቀፈችውን ሴት እነዚህን አያግባ፣ ከወገኑ ከዘመዱ የተወለደች ድንግልን ያግባ እንጂ ። ሕዝ፡ ፵፬ ፳፪ ።

፲፭ ወኢያርኵስ ውሉዶ በውስተ ሕዝቡ፣ ወአነ እግዚአብሔር ዘእቄድሶ ።

በወገኖቹም ዘንድ ልጆቹን አያጕስቍል የምቀድሰው እኔ እግዚአብሔር ነኝ ። ዘሌዋ፡ ፳፩ ፰ ።

፲፮ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ንግሮ ለአሮን ወበሎ፣ ብእሲ ዘእምነገድከ በመዋዕሊክሙ፣ እመበ ዘቦቱ እምኵሉ ዘከነ ወዘኢኮነ ንጹሐ ኢይበእ ያቅርብ ቍርባኖ ለአምላኩ ።

እግዚአብሔር ሙሴን አሮንን እንዲህ ብለህ ንገረው ብሎ ተናገረው፣ በዘመናችሁ ከወገንህ ንጹሕ የሆነ ንጹሕም ያልሆነ ሰው ቢኖር የፈጣሪውን መሥዋዕት ያቀርብ ዘንድ አይግባ ።

፲፯ ኵሉ ብእሲ ዕውር፣ ወሐንካስ፣ ወኢዘበሕቁ ሐፂር፣ ወኢምቱረ ዕዝን ።

ዕውር ሁሉ፣ አንካሳ፣ ጆሮ ቁራጣ፣ አጭር (ድ. ክ) ።

፲፰ ወኢስብረት ቦ ውስተ እዴሁ፣ አው ዘስቡር እግሩ ።

በእጁ ስብራት ያለበት፣ ወይ እግሩ የተሰበረ (እግረ ሽባ) ጉብጣ ። ዘኍ፡ ፲፯ ፩፣ መዝ፡ ፷፩ ፬ ።

፲፱ ወኢ ዘስናም፣ ወኢ ዘነውር ቦ፣ ወኢ ዘጸምላዋ አዕይንቲሁ ።

ጥርሳም (ጥርሰ ገጣጣ) ነውር ያለበት ዓይነ መጭማጫ (ዓይነ ሸውራራ)፣ እከክ (ደረመን) ቋቍቻ ያለበት ፍሬው አንድ የሆነ ። ዘሌዋ፡ ፳፪ ፳፪፣ ዘዳ፡ ፳፫ ፩ ።

፳ ወኢ ብእሲ ዕቡቅ፣ ወኢ ዘጸርንዕት በቱ፣ ወኢ ዘአሐቲ እስኪቱ ።

ነውር ነቀፋ የሌለበት ንጹሕ ያልሆነ ከአሮን ልጆች የተወለደ ካህን ሁሉ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ይሠዋ ዘንድ አይቅረብ፣ ንጹሕ አይደለምና ።

፳፩ ኵሉ ዘነውር ቦቱ ወዘኢኮነ ንጹሐ እምዘርአ አሮን ካህን ኢይቅረብ ከመ ያብእ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር እስመ ኢኮነ ንጹሐ ።

የፈጣሪውን ቍርባን ያቀርብ ዘንድ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን አይግባ፣ ነገር ግን የለዩለትን ተረፈ መሥዋዕት ይብላ ። ዘሌዋ፡ ፪ ፫፣ ፯ ፲፯፣ ዘኍ፡ ፲፰ ፲፱ ።

፳፪ ወኢይባእ ያቅርብ ቍርባነ እምላኩ እምቅዱሰ ቅዱሳን ፡ ወዘቀደሱ በሕቱ ይብላዕ ።

፳፫ ወኀበ መንጦላዕት ኢይባእ ፡ ወኀበ ምሥዋዕ ኢይቅረብ እስመ ኢኮነ ንጹሐ ፡ ከመ ኢያርኵስ ቅድሳተ ፡ እስመ አነ እግዚአብሔር ዘእቄድሰክሙ ።

፳፬ ወነገሮሙ ሙሴ ለአሮን ወለደቂቁ ፡ ወለኵሎሙ ደቂቀ እስራኤል ።

ምዕራፍ ፳፪ ።

፩ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ንበሎሙ ለአሮን ወለደቂቁ ከመ ይትዓቀቡ እምቅድሳቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ወኢያርኵሱ ስምየ ቅዱሰ በኵሉ ዘይቄድሱ ሊተ አነ እግዚአብሔር ።

፪ ዘእቤሎሙ በመዋዕሊክሙ ፡ ኵሉ ብእሲ ዘይበውእ ውስተ መቅደስ ዘእምቅድስት ዘርእክሙ ፡ ውስተ ኵሉ ዘይቄድሱ ደቂቀ እስራኤል ለእግዚአብሔር እንዘ ርኵሱ ላዕሌሁ ሰይሠሮ እምሕዝቡ ፡ እስመ አነ እግዚአብሔር ።

፫ ወለእመቦ እምዘርአ አሮን ዘለምጽ ፡ አው ዘይትከዓው ዘርኡ ፡ ኢይብላዕ እምቅድሳት እስከ አመ ይነጽሕ ።

፬ ወዘገሠሠ እምኵሉ ርኵሰ ነፍስ ፡ ወእመኒ ብእሲ ዘወጽአ እምኔሁ ዘርኡ አው ዘገሠሠ እምኵሉ ዘይትሐወስ ዘያረኵስ እምኵሉ ፡ ርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ።

፭ ወኢይብላዕ እምቅድሳት ለእመ ኢተሐጽበ ሥጋሁ በማይ ።

፮ ወእምከመ ዓረበት ፀሐይ ንጹሕ ውእቱ ፡ ወይእተ ጊዜ ይብላዕ እምቅድሳት እስመ ሲሳዩ ውእቱ ።

፯ ወማውታ ፡ ወብላዐ አርዌ ኢትብልዑ ከመ ኢትርኵሱ በሙ ፡ እስመ አነ እግዚአብሔር ።

፰ ዕቀቡ ትእዛዝየ ከመ ኢይኩንክሙ ኃጢአተ ፡ ወከመ ኢትሙቱ በእንቲአሁ ።

፱ ወለእመ ኢረኵሱ በቱ አነ እግዚአብሔር ዘእቄድሶሙ ፤

፲ ወኵሉ ዘእምባዕድ ዘመድ ኢይብላዕ እምቅድሳት ፡ ኃደርቱኒ ለካህን ወገብአቱኒ ኢይብልዑ እምቅድሳት ።

፲፩ ወለእመሰ በ ዘአጥረየ ካህን ገብረ ዘተሣየጠ በወርቁ ውእቱ ለይብላዕ ፡ እስመ ሲሳዩ ውእቱ ፡ ውሉድኒ ዘቤቱ እሙንቱ ይብልዑ ሲሳዮሙ ውእቱ ።

፲፪ ወወለተ ብእሲኒ ካህን ለእመ አውሰበት ዘእምካልእ ዘመድ ኢትብላዕ እምዓሥራት ዘቅድሳት ።

፲፫ ወበሕቱ ለእመ ኮነት መበለተ ወኃደጋ ምታ ለትግባእ ውስተ ቤተ አቡሃ ከመ አመ ንእሳ ለትብላዕ እምሲሳየ አቡሃ ፡ ወኵሉ ዘእምባዕድ ዘመድ ኢይብላዕ እምኔሁ ።

፲፬ ወለእመቦ ብእሲ ዘበልዐ እምቅድሳት በኢያእምሮ ይወስክ ሐምስተ እዴሁ ላዕሌሁ ፡ ወየሀበ ለካህን ዘቅድሳት ።

፲፭ ወኢያርኵሱ ቅድሳቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ዘያመጽኡ ለእግዚአብሔር ።

የፈጣሪውን ቍርባን ያቀርብ ዘንድ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን አይግባ ነገር ግን የለዩለትን ተረፈ መሥዋዕት ይብላ ።

ወደ መጋረጃው አይግባ ፡ ንጹሕ አይደለምና ፡ ፈጣሪው የሚመሰገንበትን መሥዋዕት እንዳያረክስ ወደ መሠዊያውም አይቅረብ ፡ የማነጻችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና።

ሙሴም ለአሮን ለልጆቹና ለእስራኤል ልጆች ሁሉ (ይህን ትእዛዝ) ነገራቸው ። ዘሌ፡ ፪ ፫ ፡ ፮ ፲፯ ።

ምዕራፍ ፳፪ ።

እግዚአብሔር የእስራኤል ልጆች ለኔ ከሚለዩዋቸው ነገሮች ራሳቸውን እንዲለዩ ክቡር ስሜንም እንዳያስነቅፉ ለአሮንና ለልጆቹም ንገራቸው ብሎ ለሙሴ ነገረው ።

የምነግራችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝ የእስራኤል ልጆች ከገንዘባቸው ለይተው ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡትን በዘመናችሁ ከዘራችሁ ሁሉ በኃጢአት ሁኖ ወደ መቅደስ የሚገባ ሰው (ካህን) ሁሉ ፡ ከወገኑ ተለይቶ ይጥፋ ያልኋችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ። ዘሌዋ፡ ፮ ፳ ።

ከአሮን ልጆች ወገን ለምጽ ያለበት ወይም ዘሩ የሚፈሰው ሰው ቢኖር እስኪነጻ ድረስ ከተቀደሰው መሥዋዕት አይብላ ። ዘሌ፡ ፲፭ ፪ ፡ ፪ ፲፫ ።

ርኩስ የሆነውም ቢሆን ዘሩ ከሱ የሚፈስበትም ቢሆን ወይም ከሚንቀሳቀሰውና ከሚያረክስ ሁሉ ጋር የሚነካ ሰው ቢኖር እስከ ሠርክ ድረስ ርኩስ ነው ።

ሰውነቱን በውኃ ካልታጠበ ከተቀደሰው መሥዋዕት አይብላ ። ፲፭ ፭ ፡ ዕብ፡ ፲ ፮ ።

ፀሐይ ከገባች በኋላ ግን ንጹሕ ነውና ያን ጊዜ ከተቀደሰው ተረፈ መሥዋዕት ይብላ ፡ ምግቡ ነውና ።

በነሳቸው እንዳትረክሱ አውሬ የነከሰውንና ሙቶ ያደረውን (በክት) አትብሉ ፡ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ።

ኃጢአት እንዳይሆንባችሁ ስለሱም እንዳትሞቱ ትእዛዜን ጠብቁ ።

በሱም ካልረከሱ የማከብራቸው እኔ እግዚአብሔር ነኝ።

ከነገደ ሌዊ ያልተወለደ ከተቀደሰው መሥዋዕት አይብላ ፡ የካህኑም ምንደኞቹና ቤተ ሰቦቹ ከመሥዋዕቱ አይብሉ ። ፩ ሳሙ፡ ፳፩ ፮ ፡ ዘፀ፡ ፳፱ ፴፫ ።

ካህን በወርቁ የገዛው ባርያ ቢኖር ግን ምግቡ ነውና እሱ ይብላ ፡ የቤቱ ውላጆችም ምግባቸው ነውና እነሱም ይብሉ ። ዘኍ፡ ፲፰ ፲፩ ፲፫ ።

ከነገደ ሌዊ ያልተወለደውን ሰው ያገባች የካህን ሴት ልጅ ከተቀደሰው አሥራት አትብላ ። ዘሌዋ፡ ፳ ፫ ።

ነገር ግን ባሏ ፈትቷት ፈት ብትሆን ዘርም ብትተካ ፡ እንደ ሕጻንነቷ ጊዜ ወደ አባቷ ቤት ተመልሳ በአባቷ ምግብ ትብላ ፡ ከባዕድ ወገን የተወለደ ግን ከሱ አይብላ።

ባለማወቅ ከተቀደሰው መሥዋዕት የበላ ሰው ቢኖር በዓይነቱ ላይ አምስት እጅ ጨምሮ የተቀደሰውን ለካህኑ ይስጠው ። ዘፍ፡ ፴፰ ፲፩ ፡ ዘሌዋ፡ ፬ ፪ ፡ ፭ ፲፭ ።

የእስራኤል ልጆች ከገንዘባቸው ለይተው ለእግዚአብሔር ያመጡትን መሥዋዕታቸውን አያርክሱ ።

፲፮ ወይከውኖሙ ኃጢአተ እምከመ በልዑ ቅድሳቶሙ፡ ንስሐ ላዕሌሆሙ፡ እስመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ዘእቄድሶሙ ።

በኃጢአት ሳሉ ከተቀደሰው መሥዋዕት ከበሉ ግን ኃጢአትና በደል ይሆንባቸዋል፡ ንስሐ አለባቸው፡ የማነጻቸው እኔ እግዚአብሔር ነኝና ። ዘሌዋ፡ ፲፬ ፲፮ ።

፲፯ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፡ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ለአሮን ወለደቂቁ ወለኵሎሙ ተአይነ ደቂቀ እስራኤል ወለግዩራን እለ ሀለዉ ውስተ እስራኤል ።

እግዚአብሔር ለአሮንና ለልጆቹ ለእስራኤልም ልጆች ወገን ሁሉ እንዲህ ብለህ ንገራቸው ብሎ ለሙሴ ነገረው፤ ከእስራኤል ልጆች አንዱም አንዱም ሰው፡ ወይም በእስራኤል ዘንድ ካሉት ከመጻተኞቹ ወገን ቢሆን ።

፲፰ ዘአምጽኡ ቊርባኖሙ በእንተ ኵሉ ዘበጽዑ፡ አው በእንተ ኵሉ ዘሐለዩ፡ ዘያመጽኡ ለእግዚአብሔር ።

ስለ ተሳለው ስለት ሁሉ መሥዋዕት ብፅዓቱን ቢያመጣ፡ ወይም ስላሰበው ነገር ሁሉ መሥዋዕት ፈቃዱን ቢያመጣ ለሚቃጠል መሥዋዕት ለእግዚአብሔር የሚያመጡትን ሁሉ ቢያቀርብ ።

፲፱ እምዘይኄይስ ይኩን ተባዕተ ንጹሐ እመራዕይ፡ ወእምአባግዕ፡ ወእምአጣሊ ።

ይሠምርላቸው ዘንድ ከመንጋዎች የሚሻለው በሬ ከበጎችም ከፍየሎችም መንጋ ነውር የሌለበት ንጹሕ ተባት ይሁን ። ዘሌዋ፡ ፲ ፲፫ ። ዕብ፡ ፱ ፲፬ ፡ ፩ ጴጥ፡ ፩ ፲፱ ።

፳ ኵሎ ዘቦቱ ነውር ኢያምጽኡ ለእግዚአብሔር፡ እስመ ኢይሰጠወክሙ ።

ነገር ግን አይቀበላችሁምና ነውር ነቀፋ ያለበትን ሁሉ ለእግዚአብሔር አያምጡ ። ዘዳ፡ ፲፭ ፳፩ ።

፳፩ ወብእሲኒ ለእመ በ ዘአምጽአ መሥዋዕተ መድኃኒት ለእግዚአብሔር በእንተ ዘበፅዐ፡ አው በፈቃዱ እመራዕይ አው እምአባግዕ፡ ንጹሐ ይኩን ዘይሠጠዎ ኵሉ ዘአልቦቱ ነውር ።

ስለ ተሳለው ወይም በፈቃዱ ከመንጋው ወይም ከበጎቹ መሥዋዕተ መድኃኒት የሚያመጣ ሰው ቢኖር፡ እግዚአብሔር የሚቀበለው ነውር ነቀፋ የሌለበት ንጹሕ ይሁን ።

፳፪ ዕውርሰ ወስቡረ፡ ወምቱረ ልሳን ወሕሡረ፡ ወዕቡቀ፡ ወዘጽርንዕት ቦቱ ኢያምጽኡ ለእግዚአብሔር፡ ወለቍር ብንኒ ኢተሀቡ እምኔሆሙ ውስተ ምሥዋዑ ለእግዚአብሔር ።

ነገር ግን ሰባራና ዕውር ቀዘናምና ምላሱ የተቈረጠ፡ (የተሰነጋ) ሕሡሬ፤ ፎናናውን፡ (ዕቡቀ) እከክሙን፡ (ጽርንዕት) ቋቍቻ ያለበትን ለእግዚአብሔር አያምጡ፡ ከነዚህም በእግዚአብሔር መሠዊያ ለመሥዋዕት አትስጡ ።

፳፫ ለላሕምኒ ወለበግዕ፡ ዘምቱረ ዕዝን፡ አው ዘምቱረ ዘነብ ተኀትሞ፡ ወጥሬተ ርእሰከ ትሬስዮ፡ ለብፅዓቲከሰ ኢይሠጠወከ ።

በሬውን በጉንም ጆሮ ቈራጣ፡ ጅራት ጕማዳ ከሆነ ለራስህ ቈጥረህ ገንዘብ አድርገው፡ ለስለትህ ግን አይቀበልህም ። ዘፀ፡ ፲፪ ፲፪፡ ዘሌዋ፡ ፳፩ ፲፰ ።

፳፬ ዘጽንጽው፡ ወዘጽቱም፡ ወዘምቱር፡ ወዘአጥራቂ ኢያምጽእዎ ለእግዚአብሔር፡ ወበምድርክሙኒ ኢትግበርዎ ።

(ጽንጽው) ቆልማማ (ጽቱም) ሰባራ (ምቱር) ላተ ቆራጣ (አጥራቂ) ቀዘናሙን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርገው አያምጡት፡ በአገራችሁም አትረዱት ።

፳፭ እምኀበ ባዕድኒ ዘመድ ኢታብኡ ዘከመዝ ቍርባነ ለአምላክክሙ እምዝንቱ ኵሉ፡ እስመ ሙስን ውእቱ ወነውር ቦቱ ወኢይሠጠወክሙ ።

የተበላሸ ነውና ነውር ነቀፋም ያለበት ነውና፡ እግዚአብሔርም አይቀበላችሁምና ከዚህ ሁሉ ከሌላ ወገን ከሌላ ዘመድ ተቀብላችሁ እንደዚህ ያለውን ቍርባን ፈጣሪያችሁ አታቅርቡ ። ዘሌዋ፡ ፳፩ ፲፰፡ ዘኍ፡ ፲፩ ፲፮ ።

፳፮ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፡ ለእመ ወለደት እጐልት፡ አው በግዕት፡ አው ጠሊት ሰቡዐ ዕለተ የሀሉ እንተ ኀበ እሙ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፤ ጊደር ወይም በግ ወይም ፍየል ብትወልድ እንበሳዋ ግልገሏ ከናቱ ጋር ሰባት ቀን ይሰንብት ። ዘፀ፡ ፳፪ ፴ ።

፳፯ እመ ሳምንት ዕለት ወእምድኅሬሁኒ ይሠጠወክሙ ለቍርባን መሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር ።

በስምንተኛውም ቀን ከዚያም በኋላ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጋችሁ ብታቀርቡት ይቀበላችኋል ።

፳፰ ወኢትጥብሑ እጐልተ፡ አው በግዕተ፡ አው ጠሊተ ምስለ እጓላ በአሐቲ ዕለት ።

ጊደርን ወይም በግን ወይም ፍየልን ከልጅዋ ጋር በአንዲት ቀን አትሠዉ ። ዘፀ፡ ፲፪ ፫፡ ዘዳ፡ ፳፪ ፯ ።

፳፱ ወለእመ ሦዕከ መሥዋዕተ ብፅዓት ትፍሥሕትከ ለእግዚአብሔር ዘይሠጠወክሙ ሡዑ ሎቱ ።

ደስታህ የተፈጸመበት ስለትህን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ብታቀርብ የሚቀበላችሁን ሠዉለት ።

፴ ወበይእቲ ዕለት ይብልዕዎ፡ ወኢያትርፉ እምሥጋሁ ለነግህ ።

በዚያች ቀን ይብሉት፡ ከሥጋውም ለነገ ብለው አያሳድሩ ። ዘሌዋ፡ ፯ ፲፭፡ መዝ ፻፮ ፳፱ ።

፴፩ ወዕቀቡ ትእዛዝየ ወግበርዎ፡ እስመ አነ እግዚአብሔር፤

እኔ እግዚአብሔር ነኝና ትእዛዜን ጠብቃችሁ ሥሩት።

፴፪ ወኢታርኵሱ ስምየ ቅዱሰ፡ ወእትቄደስ በማእከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል እስመ አነ እግዚአብሔር ዘእቄድሶሙ ።

ክቡር ስሜን አታስነቅፉ፡ በእስራኤልም ልጆች መካከል እመሰገናለሁ፡ የማከብራችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና።

፴፫ ዘአውፃእክዎሙ እምድረ ግብጽ ከመ እኩንክሙ አም
ላክክሙ አነ እግዚአብሔር ።

ፈጣሪያችሁ (የፍቅር አባት) እሆናችሁ ዘንድ (አባቶቻ
ችሁን) ከግብጽ ምድር ያወጣኋቸው እኔ እግዚአብሔር
ነኝ ። ዘሌዋ፡ ፲፩ ፵፭ ፡ ፲፱ ፴፯ ፡ ዘኁ፡ ፲፭ ፵፩ ።

## ምዕራፍ ፳፫ ።

## ምዕራፍ ፳፫ ።

፩ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ ንግሮሙ ለደ
ቂቀ እስራኤል ወበሎሙ በዓላቲሁ ለእግዚአብሔር ዘሰመ
ይክሙ በቅዱስ አስማት እሉ እሙንቱ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው ፤ ለእስ
ራኤል ልጆች እንዲህ በላቸው ፡ በክቡር ስም የጠራችኋ
ቸው የእግዚአብሔር በዓላት እሊህ ናቸው ።

፪ ሰዱሰ ዕለተ ትገብር ግብረከ ፡ ወበሳብዕት ዕለት ሰንበት
ይእቲ ፡ ወዕረፍተ ቅድስተ ተሰምየት ለእግዚአብሔር ፡
ኵሎ ግብረ ኢትግበሩ ባቲ በኵሉ በሐውርቲክሙ እስመ
ሰንበቱ ለእግዚአብሔር ይእቲ ።

ስድስት ቀን ሥራህን ሥራ ፡ በሰባተኛይቱ ቀን ግን
የእግዚአብሔር ዕረፍት ስለ ሆነች ክብርት ተብላለችና
በሃገራችሁ ሁሉ ሥራችሁን አትሥሩበት ።

፫ እሉ እሙንቱ በዓላቲሁ ለእግዚአብሔር ዘሰመይክሙ
በቅዱስ ስም በውስተ መክፈልትክሙ ።

ዕድል ፈንታ ሁኖ በተሰጣችሁ በአገራችሁ በክቡር
ስም የጠራችኋቸው የእግዚአብሔር በዓላት እሊህ ናቸው።

፬ በቀዳሚ ወርኅ ፡ አመ ዕለተ ዓሥሩ ወረቡዑ ለሠርቀ
በጊዜ ዕርበት ፋሲካሁ ለእግዚአብሔር ።

በመጀመሪያ ወር (ሚያዝያ) በባተ በአሥራ አራተ
ኛው ቀን ሲመሽ የእግዚአብሔር ፋሲካው ነው ።

፭ ወአመ ዕለተ ዓሡሩ ወሐሙሱ ለሠርቀ ዝንቱ ወርኅ ፡
በዓለ ናእት ዘእግዚአብሔር ሰቡዐ ዕለተ ናዕተ ብልዑ ።

ይህ ወር በባተ በአሥራ አምስተኛው ቀንም ፡ ቂጣ
የሚበሉበት የእግዚአብሔር በዓል ነውና ፡ ሰባት ቀን
ቂጣ ብሉ ። ዘፀ፡ ፲፪ ፲፯ ።

፮ ወቀዳሚት ዕለት ቅድስተ ትሰመይ ለክሙ ኵሎ ግብረ
ዘትትቀነዩ ኢትግበሩ ።

መጀመሪያይቱም ቀን ለናንተ የከበረች ተብላለችና
የምትሠሩትን ሥራ ሁሉ አትሥሩበት ።

፯ ወአብኡ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር ሰቡዐ ዕለተ ወሳ
ብዕትኒ ዕለት ቅድስተ ትሰመይ ለክሙ ኵሎ ግብረ ዘት
ትቀነዩ ኢትግበሩ ባቲ ።

ሰባት ቀን ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን ሠዉ ፡ ሰባተ
ኛይቱ ቀን ግን ለናንተ የከበረች ተብላለችና የምትሠሩ
ትን ሥራ ሁሉ አትሥሩበት ። ዘኁ፡ ፳፰ ፲፰ ።

፰ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ ንግሮሙ ለደ
ቂቀ እስራኤል ወበሎሙ አመ በእክሙ ውስተ ምድር እ
ንተ እሁበክሙ አነ ፡ ወዐፀድክሙ ማእረራ ታበውኡ ከላ
ስስተ እምቀዳሚ ማእረርክሙ ኀበ ካህን ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው ፤ ለእስ
ራኤል ልጆች እንዲህ በላቸው ፤ እኔ ወደ ማወርሳችሁ ም
ድር ብትገቡ መከሯንም በአጨዳችሁ ጊዜ መጀመሪያ
ከደረሰው አዝመራችሁ እሸቱን(ነዶውን)ወደ ካህን አምጡ።

፱ ወያበውእ ካህን ለውእቱ ክልስስት ቅድመ እግዚአብ
ሔር ፡ ከመ ይሠጠወክሙ ፡ ወበሳኒታሃ ለቀዳሚት ሰንበት
ያበውእ ካህን ።

ካህኑም ይቀበላችሁ ዘንድ ያነን ነዶውን በእግዚአብ
ሔር ፊት ያቅርበው ፡ በመጀመሪያይቱም ቀን ማግሥት
ካህን ያግባው ። ዘፀ፡ ፳፱ ፳፬ ፡ ዘሌዋ፡ ፳፪ ፳፩ - ፳፱ ።

፲ ወትገብሩ በዕለት እንተ አምጻእክሙ ውእተ ክልስ
ስተ በግዐ ንጹሐ ዘአሐቲ ዓመቱ ለመሥዋዕት ለእግዚአ
ብሔር ።

እሸት ነዶውን በመጣችሁበትም ቀን አንድ ዓመት የሆ
ነውን ነውር ነቀፋ የሌለበትን በግ ለእግዚአብሔር መሥ
ዋዕት አድርጋችሁ ሠዉ ።

፲፩ ወቍርባኑ ክልኤቱ ዓሥራት ዘሥንዳሌ ዘግቡር በቅ
ብዕ ፡ ለመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ፡ ወሞፃሕቱ ራብዕተ
እዴሃ ለኢን ወይን ።

እግዚአብሔር በጎ መዓዛ አድርጎ ሊቀበለው ቍርባኑ
በዘይት የተለወሰ የሁለት ቁና ሥንዴ ዳቦ ፍልቅ የሚያደ
ርጉትም የወይን ጠጅ የኢን አራተኛ እጅ ይሁን ።

፲፪ ወይእተ ዕለተ እንተ ባቲ ታበውኡ ቍርባኖ ለአምላ
ክክሙ ፡ ኢትብልዑ ኅብስተ ሐዲሰ ወኢቅልወ ፡ እስከ
ታበውኡ ቍርባኖ ለአምላክክሙ በይእቲ ዕለት ፡ ወሕገ
ዶኩንክሙ ዘለዓለም በመዋዕሊክሙ ፡ በኵሉ በሐውር
ቲክሙ ።

የፈጣሪያችሁን ቍርባን በምታቀርቡበት በዚያች ቀን
የፈጣሪያችሁን ቍርባን እስክታገቡ ድረስ የአዲስ እህል
ቆሎና ዳቦ አትብሉ ፡ በየሀገራችሁ ሁሉ በዘመናችሁ የዘለ
ዓለም ሥራት ይሁናችሁ ። ዘሌዋ፡ ፪ ፲፬ ።

፲፫ ወትኌልቁ እምሳኒታ ሰንበት እምይእቲ ዕለት ፡ እንተ
ባቲ አባእክሙ ውእተ ከላስስተ ዘይሠርዑ ።

እሸት ነዶውን ካገባችሁበት ከመጀመሪያይቱ ሱባዔ
ማግሥት ጀምራችሁ ሰባቱን ሱባዔ ቍጠሩ ።

፲፬ ሰቡዐ ሰናብተ ትኌልቁ ፍጹመ እስከ ሳኒታሃ ለደኃሪት
ሰንበት ሐምሳ ዕለተ ።

እስከ መጨረሻይቱ ሱባዔ ማግሥት ድረስ አምሳውን
ቀን ፈጽማችሁ ቍጠሩ ፡ (ከሚያዝያ ፲፯ እስከ ሰኔ ፮)።

፲፭ ወታበውኡ መሥዋዕተ ሐዲሰ ለእግዚአብሔር ዘእም
ውስተ ምድርክሙ ።

በዚች በአምሳኛይቱ ቀን ከምድራችሁ የተገኘውን
አዲሱን የእህል ቍርባን ወደ እግዚአብሔር አቅርቡ ።

፲፮ ታበውኡ ኅብስተ ዘይሠርዑ ክልኤተ ኅብስተ ዘዘክል

ካህናቱ ሠርተው የሚያቀርቡት አንዱ ኅብስት የሁ

| | | |
|---|---|---|
| | ኤቱ ዓሥራት ዘሥንዳሴ ይኩን እሐቲ ኅብስቱ፤ ወአብኡ እክሙ ታበስልዎ እምቀዳሚ እክልክሙ ለእግዚአብሔር ። | ለት የሁለት ላዳን ሥንዴ ዱቄት ሁለት ዳቦ አምጡ፤ መጀመሪያ ከደረሰው እህላችሁ ለእግዚአብሔር አቡኩታችሁ አቅርቡ ። ዘፀ፣ ፳፱ ፳፬፣ ፳፫ ፲፯፣ ዘኍ፣ ፲፰ ፲፯ ። |
| ፲፯ | ወታበውኡ ምስለ ውእቱ ኅብስት ሰብዓተ አባግዐ ዘዘዓመት፤ ወአሐደ ላሕመ እመራዕይ፤ ወሐራጊተ ክልኤተ ንጹሐነ፤ ወይኩን ቍርባኖሙ ወመሥዋዕቶሙ ወሞ ፃሕቶሙ መሥዋዕተ መዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ። | ከዚያም ዳቦ ጋር ዓመት የሆናቸው ሰባት በጎች ከመንጋውም አንድ በሬ፤ ነውር ነቀፋ የሌለባቸው ሁለት ሙክቶች አቅርቡ፤ እግዚአብሔር የበጎ መአዛ መሥዋዕት አድርጎ ሊቀበለው መሥዋዕትነታቸውና ቍርባንነታቸው ወይናቸውም ለእግዚአብሔር ይሁን ። |
| ፲፰ | ወግበሩ አሐደ ሐርጌ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት፤ ወክልኤተ አባግዐ ዘዘዓመት ለመሥዋዕተ መድኃኒት ። | ከፍየሎችም አንድ ሙክት ለመሥዋዕተ ኃጢአት፤ እንዳንድ ዓመት የሆናቸውም ሁለት በጎች ለመሥዋዕተ መድኃኒት ሠዉ ። ዘሌዋ፣ ፬ ፳፫ ፳፯፣ ዘኍ፣ ፳፰ ፴ ። |
| ፲፱ | ወያበውእ ካህን ምስለ ውእቱ ኅብስት ዘቀዳሚ እክል፤ ክልኤተ አባግዐ፤ ወይሠርዮ ቅድመ እግዚአብሔር፤ ቅዱስ ውእቱ ለእግዚአብሔር፤ ወለካህን ለዘአብአ ሎቱ ይኩን ። | ካህንም መጀመሪያ ከደረሰው የእህል መሥዋዕት ጋራ ሁለት በጎች አግብቶ በእግዚአብሔር ፊት ይሠዋው፤ የከበረው መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ነው፤ ጠቦቱን የተረፈውም ላቀረበው ካህን ይሁን ። ዘኍ፣ ፲፰ ፲፪ ። |
| ፳ | ወይሰምይዋ ለዛቲ ዕለት ቅድስተ፤ ኵሎ ግብረ ዘትት ቀነዩ ኢትግበሩ በቲ፤ ሕገ ዘለዓለም ይኩንክሙ በመዋዕሊክሙ በኵሉ ኀበ ሀሎክሙ ። | ይህችን ቀን የከበረች ዕለት ብለው ይጥሯት፤ የምትሠሩትንም ሥራ ሁሉ አትሥሩባት፤ ባላችሁበትም ዘመን ሁሉ ይህ የዘለዓለም ሥራት ይሁናችሁ ። |
| ፳፩ | ወአመ ተዐፅዱ እክለ ምድርክሙ ኢትጠናቀቁ ዓፂደ ዘተርፈ ውስተ ገራህትክሙ፤ ወዘወድቀ ኢትእርዩ፤ ለነዳይ ወለግዩር ኅድግዎ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ። | የእርሻችሁንም ሰብል በጨዳችሁ ጊዜ በእርሻችሁ ውስጥ የቀረውን አትጠናቀቁ፤ (አጥርታችሁ አትጨዱ) ስታጭዱ የወደቀውንም አትልቀሙ፤ ለስደተኛ ለደኃ ተዉት፤ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ። |
| ፳፪ | ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፤ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ። | እግዚአብሔር ሙሴን ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው ብሎ ተናገረው ። |
| ፳፫ | በሳብዕ ወርኅ አመ ርእሰ ሠርቀ ወርኅ ዕረፍተ ትኩንክሙ ተዝካረ ዘመጥቅዕ ቅድመ እግዚአብሔር ቅድስተ ትሰመይ ። | የሰባተኛው ወር (ጥቅምት) ከወሩም በመባቻው ቀን መታሰቢያ ልትሆን ነጋሪት እየመታችሁ አዋጅ የምትነግሩባት ስሟ ለእግዚአብሔር የተለየች ዕረፍት ትሁንላችሁ ። ዘኍ፣ ፳፱ ፩፣ ዘሌዋ፣ ፳፭ ፱ ። |
| ፳፬ | ኵሎ ተግባረ ዘትትቀነዩ ኢትግበሩ በቲ፤ ወአብኡ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር ። | የምትሠሩትን ሥራ ሁሉ አትሥሩበት፤ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን አቅርቡበት እንጂ ። |
| ፳፭ | ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፤ አመ ዓሡሩ ለሳብዕ ወርኅ ዕለተ አስተርእዮ ይእቲ፤ ቅድስተ ትሰመይ ለክሙ ። | እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፤ በሰባተኛው ወር አሥረኛይቱን ቀን ኃጢአት የሚሠረይበት በረድኤት የምገለጥበት ናትና፤ ለናንተ የከበረች ትሁንላችሁ ። ዘሌዋ፣ ፲፯ ፳፱፣ ዘፀ፣ ፲፫ ፲ ። |
| ፳፮ | ወአሕምምዋ ለነፍስክሙ ወአብኡ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር፤ ወኵሎ ግብረ ዘትትቀነዩ ኢትግበሩ በይእቲ ዕለት ። | በዚህችም ቀን ሰውነታችሁን አስጨንቋት፤ (በጾም፤ በጸሎት) ለእግዚአብሔርም መሥዋዕትን ሠዉ፤ በዚህችም ቀን የምትሠሩትን ሥራ ሁሉ አትሥሩ ። |
| ፳፯ | እስመ ዕለተ አስተርእዮትክሙ ይእቲ፤ እንተ በቲ ያስተሠርዩ በእንቲአክሙ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ ። | ይህች ቀን (ካህናት) በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር ፊት ስለ ኃጢአታችሁ የሚያስተሠርዩበት፤ በረድኤት የምገለጽበት ቀን ናትና ። ዘኍ፣ ፳፱ ። |
| ፳፰ | ወኵላ ነፍስ እንተ ኢታሐምም ርእሳ ትሠሮ በይእቲ ዕለት ወትደምሰስ እምሕዝባ ። | በዚህች ቀን ሰውነቷን የማታስጨንቅ ሰውነት ሁሉ ከወገኗ ተለይታ ትጥፋ ። ዘፀ፣ ፴ ፴፫፣ ዘፍ፣ ፲፯ ፬ ። |
| ፳፱ | ወኵላ ነፍስ እንተ ትገብር ግብረ በይእቲ ዕለት ለትደምሰስ እምሕዝባ፤ ሕገ ዘለዓለም ይኩንክሙ በመዋዕሊክሙ በኵሉ ኀበ ሀሎክሙ ። | በዚች ቀን ሥራን የምትሠራ ሰውነት ሁሉ ከወገኗ ተለይታ ትጥፋ፤ ባላችሁበት አገር ሁሉ ባለ ዘመናችሁ ለዘለዓለም ሕግ ሥራት ይሁናችሁ ። ዘሌዋ፣ ፳፫ ፭ ፯ ። |
| ፴ | ሰንበተ ሰንበታት ይእቲ ለክሙ አሕምምዋ ለነፍስክሙ እምተሱዑ ለወርኅ፤ እምሠርከ እስከ ሠርከ ዓሡሩ ለወርኅ፤ አሚሃ አሰንብቱ ሰንበተክሙ ። | ለናንተ በሱባዔ የምትቈጠር በዓል ናትና፤ ከወሩ ከዘጠነኛው ቀን ማታ ጀምራችሁ እስከ አሥረኛው ቀን ማታ ድረስ ሰውነታችሁን አስጨንቋት፤ ያን ጊዜ በዓላችሁን አክብሩ፤ (ዕረፍት አድርጉ) ። ዘሌዋ፣ ፳፭ ፪ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፤ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ። | ፴፩ | እግዚአብሔር ሙሴን ለእስራኤል ልጆች እንዲህ በላቸው ብሎ ተናገረው ። |
| አመ ዓሡሩ ወሐሙሱ ለውእቱ ወርኅ በዓለ መጸለት ሰቡዐ ዕለተ ለእግዚአብሔር ። | ፴፪ | በዚህ በሰባተኛው ቀን ከአሥራ አምስተኛው ቀን ጀምሮ (ዳስ ጥሎ ድንኳን ተክሎ የሚከበረውን) በዓለ መጸለት ለእግዚአብሔር ሰባት ቀን አክብሩ ። ዘኁ፣ ፳፱ ፲፪ ። |
| ወዕለት ቀዳሚት ቅድስተ ትሰመይ ለክሙ፣ ወኵሎ ግብረ ዘትትቀነዩ ኢትግበሩ በቲ ። | ፴፫ | መጀመሪያይቱ ቀን ለናንተ የከበረች ትሁንላችሁ፣ የምትሠሩትንም ሥራ ሁሉ አትሥሩበት ። |
| ሰቡዐ ዕለተ ታበውኡ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር፣ ወሰምኒትኒ ዕለት ቅድስተ ትሰመይ ለክሙ ፣ ወአብኡ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር፣ እስመ ዘፀአት ውእቱ ' ኵሎ ግብረ ዘትትቀነዩ ኢትግበሩ በቲ ። | ፴፬ | ሰባት ቀን ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን ሠዉ፣ ስምንተኛይቱም ቀን ለናንተ የከበረች ትሁን፤ መሰነባበቻ ነውና ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን አቅርቡ፣ የምትሠሩትንም ሥራ ሁሉ አትሥሩበት ። ዘኁ፣ ፳፱ ፴፭ ። |
| እሉ እሙንቱ በዓላቲሁ ለእግዚአብሔር ዘሰመይክምሙ በስም ቅዱስ፣ በዘበሙ ያበውኡ መባአ ለእግዚአብሔር ፣ ወቍርባነ ፣ ወመሥዋዕቶሙኒ ፣ ወሞጻሕቶሙኒ ዘኵሉ አሚር ። | ፴፭ | ቍርባናቸውንና መባቸውን ሁሉ ጊዜ የሚያቀርቡት ወይናቸውንና መሥዋዕታቸውን የሚያመጡባቸው በክበረ ስም የጠራኋቸው የእግዚአብሔር በዓላቶች እኒህ ናቸው ። ዘፀ፣ ፳ ፲፫ ፲፱፣ ፩ ነገሥ፣ ፰ ፶፱ ። |
| ዘእንበለ ሰናብቲሁ ለእግዚአብሔር፣ ወዘእንበለ ዘመባእክሙ፣ ወዘእንበለ ዘኵሉ ብፅዓቲክሙ፣ ወዘእንበለ በፈቃድክሙ ዘታበውኡ ለእግዚአብሔር ። | ፴፮ | ከእግዚአብሔር ሰንበታት ሌላ ከምትሰጡት መባችሁ ሌላ፣ ከስእለታችሁም ሌላ፣ ለእግዚአብሔር በፈቃዳችሁ ከምታቀርቡት መሥዋዕተ ፈቃድ ሌላ ናቸው ። |
| ወአመ ዕለተ ዓሡሩ ወሐሙሱ ለውእቱ ሳብዕ ወርኅ አመ ፈጸምክሙ አስተጋብአተ እክለ ምድርክሙ ትገብሩ በዓለ ለእግዚአብሔር ሰቡዐ ዕለተ፣ ወዕለት ቀዳሚት ዕረፍት ይእቲ፣ ወዕለትኒ ሳምኒት ዕረፍት ይእቲ ። | ፴፯ | በዚያ በሰባተኛው ወር፣ በአሥራ አምስተኛው ቀን፣ የምድራችሁን ሰብል ሰብስባችሁ በጨረሳችሁ ጊዜ ለእግዚአብሔር ሰባት ቀን በዓል አድርጉ፣ መጀመሪያይቱ ቀን ዕረፍት ናት ስምንተኛይቱም ቀን ዕረፍት ናት ። |
| ወትነሥኡ ለክሙ አመ ዕለተ ቀዳሚት እምፍሬ ዕፀ ዘሠናይ፣ ወጸበርትኒ፣ ወበቀልተ ተመርት፣ ወእምዕፀ ቈጽለ አዕፁቅ፣ ወዘኵሐኒ፣ ወዘአምነ ፈለግኒ አዕፁቀ ዘንጹሕ ወትትፌሥሑ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ ሰቡዐ ዕለተ በበዓመት ። | ፴፰ | በመጀመሪያቱ ቀን፣ ያማረው የዛፍ ፍሬ የሰሌን ቀርንጫፍ የዘንበባ ዕንጨት በወንዝ ዳር ያለው የሀያ ዛፍ በቅርንጫፉ ላይ ካለው ቅጠል የለመለመውን ይዛችሁ በየዓመቱ በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር ፊት ሰባት ቀን ደስ ይበላችሁ ። ነህ፣ ፰ ፲፭፣ ዘዳ፣ ፲፮ ፲፬ ። |
| ሕገ ዘለዓለም ይኩንክሙ በመዋዕሊክሙ ከመ ትግበሩ በዓለ መጸለት በሳብዕ ወርኅ ። | ፴፱ | በየዓመቱ በሰባተኛው ወር (በጥቅምት) በዘመናችሁ በዓል ታደርጉ ዘንድ ይህ የዘለዓለም ሕግ ሥራት ይሁናችሁ ። ዘሌዋ፣ ፲፮ ፳፱፣ ዘፀ፣ ፴ ፲ ። |
| ወትነብሩ ውስተ መጸለት ሰቡዐ ዕለተ ኵሉ ዘእምፍጥረቱ እስራኤል ይንበር ውስተ መጸለት ። | ፵ | ሰባት ቀን ዳስ ጥላችሁ፣ ድንኳን ተክላችሁ ተቀመጡ ትውልዱ ከእስራኤል የሆነ ሁሉ ዳስ ጥሎ ድንኳን ተክሎ ይሰንብት ። ዘዳ፣ ፴፩፣ ፲ - ፲፫ ። |
| ከመ ይርአዩ ትውልድክሙ ከመ በምጽላል አንበርክዎሙ ለእስራኤል አመ አውጻእክዎሙ እምድረ ግብጽ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ። | ፵፩ | ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ አገር በወጣኋቸው ጊዜ በጥላ እንዳስቀመጥኋቸው ልጆቻችሁ ያዩ ዘንድ ። |
| ወነገሮሙ ሙሴ ለደቂቀ እስራኤል ኵሎ በዓላቲሁ ለእግዚአብሔር እግዚእ ። | ፵፪ | ሙሴም የጌታ የእግዚአብሔርን በዓላት ሁሉ ለእስራኤል ልጆች ነገራቸው ። ዘሌዋ፣ ፳፫ ፪ ። |
| **ምዕራፍ ፳፬ ።** | | **ምዕራፍ ፳፬ ።** |
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣ አዝዞሙ ለደቂቀ እስራኤል ያምጽኡ ለከ ቅብዐ ዘይት ንጹሐ፣ ወውጉአ ለማኅቶት በዘተኃትዉ ማኅቶተ ኵሎ ጊዜ፣ አፍአ እመንጦላዕት ዘደብተራ መርጡል ። | ፩ | እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፤ መብራቱን ከደብተራ ኦሪት ውጭ ሁሉ ጊዜ እንድታበሩበት ለመብራት ተወቅጦ የተጠለለውን ጥሩ የወይራ ዘይት ያመጡልህ ዘንድ የእስራኤልን ልጆች እዘዛቸው ። |
| ወያኀትዉ አሮን ወደቂቁ እምሠርክ እስከ ነግህ፣ ቅድመ እግዚአብሔር ለዘልፍ፣ ሕገ ዘለዓለም ይኩንክሙ በመዋዕሊክሙ ። | ፪ | አሮንና ልጆቹ ከማታ እስከ ማታ ድረስ በእግዚአብሔር ፊት ዘወትር ያብሩ ይህም የዘለዓለም ሕግ ይሁናችሁ ። ዘፀ፣ ፳፯ ፯፣ ፳፭ ፴፯ ። |
| ወዲበ መራናት እንተ ንጽሕት አኅትዉ ውእተ ማኅቶተ ቅድመ እግዚአብሔር እስከ ይጸብሕ ። | ፫ | ያንንም መብራት በጠራች መቅረዝ ላይ እስኪነጋ ድረስ በእግዚአብሔር ፊት አብሩ ። ዘፀ፣ ፴፩ ፲፰ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ወንሥኡ ሥንዳሌ ወግበሩ ዓሠርተ ወክልኤተ ኅብስተ ዘክልኤቱ ዐሥራት ይኩን አሐዱ ኅብስቱ ። | ፬ | ሥንዴ አምጥታችሁ ዐሥራ ሁለት ዳቦ ጋግሩ፤ ሁለት ቀና ሥንዴ አንድ ዳቦ ይሁን ። |
| ወትሠርዕዎ ምክብዒተ፤ስድስተ ኅብስተ፤ ወትሠርዕዎ አሐተኔ ዲበ ማእድ ንጽሕት ቅድመ እግዚአብሔር ። | ፭ | ስድስቱን ዳቦ ዕጥፍ አድርጋችሁ በንጹሕ ሰደቃ ላይ በእግዚአብሔር ፊት ሥሩት ። ዘፀ፣ ፴፱ ፴፯ ። |
| ወትሠርዑ ምስሌሁ ስኂነ ንጹሐ፤ወጼወ፤ ወይኩን ውእቱ ኅብስት ለተዝካር ሥሩዐ ቅድመ እግዚአብሔር ። | ፮ | ከዳቦውም ጋር ጥሩ ቍንዶ በርበሬንና ጨውን ጨምራችሁ አዘጋጁ (ሥሩት) ያም መታሰቢያ የሚሆን ዳቦ በእግዚአብሔር ፊት የተዘጋጀ ይሁን ። |
| ወበዕለተ ሰንበት ትሠርዕዎ ለዘልፍ በኀበ ደቂቀ እስራኤል ወሕግ ዘለዓለም ውእቱ ። | ፯ | ዕረፍት በሚደረግበትም ቀን በእስራኤል ልጆች ዘንድ ዘወትር አዘጋጁት፤ እሱም የዘለዓለም ሥራት ይሁናችሁ ። ፩ ዜና መዋ፣ ፱ ፴፪፣ ፪ ዜና መዋ፣ ፪ ፬ ። |
| ወይኩን ለአሮን ወለደቂቁ፤ ወይብልዕዎ በመካን ቅዱስ እስመ ቅዱስ ዘቅዱሳን ውእቱ፤ ሎቱ እምዘይሠውዑ ለእግዚአብሔር ሕግ ዘለዓለም ውእቱ ። | ፰ | ለአሮንና ለልጆቹ ይሁን፤ ለእግዚአብሔር ከሚሠዉት የእስራኤል መሥዋዕት ለነሱቸው የከበረ ነውና፤ በከበረ ቦታ ላይ ሁነው ይብሉት፤ ይህም የዘለዓለም ሕግ ሥራት ይሁን ። ፩ ሳሙ፣ ፳፩ ፯፣ ማቴ፣ ፲፪ ፬ ። |
| ወወፅአ ወልደ ብእሲት እስራኤላዊት፤ ወአቡሁሰ ግብጻዊ በማእከለ ደቂቀ እስራኤል፤ ወተበአሱ በውስተ ትዕይንት ወልደ ብእሲት እስራኤላዊት ወብእሲ እስራኤላዊ ። | ፱ | አባቱ ግብጻዊ፤ እናቱ እስራኤላዊት የሆነ ያንዲት ሴት ልጅ በእስራኤል ልጆች መካከል ወጣ፤ (በነገር ተነሣ) የእስራኤላዊት ሴት ልጅና አንድ እስራኤላዊ በሰፈር ተጣሉ። |
| ወሰመየ ወልዳ ለእንታክቲ ብእሲት እስራኤላዊት ወረገመ ስመ እግዚአብሔር፤ ወአምጽእዎ ኀበ ሙሴ፤ ወስማ ለእሙ ሰሎሚት ወለተ ዳቤር ዘእምነገደ ዳን ። | ፲ | የዚያች እስራኤላዊት ሴት ልጅ የእግዚአብሔርን ስም ሰደበ (አቃለለ) ይዘውም ወደ ሙሴ አመጡት፤ እናቱም ከዳን ወገን የተወለደ የዳቤር ልጅ ሰሎሚት ትባላለች ። |
| ወወደይዎ ውስተ ሞቅሕ እስከ ይኴንኖ በትእዛዘ እግዚአብሔር ። | ፲፩ | በእግዚአብሔር ትእዛዝ እስኪቀጣው ድረስ በግዞት ቤት አኖረው ። ዘኁ፣ ፲፭ ፴፬፣ ዘፀ፣ ፲፰ ፲፭ ። |
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፤ አውጽኦ አፍኣ ለዘረገመ እምትዕይንት፤ ወይደዩ እደዊሆሙ ዲበ ርእሱ ኵሎሙ እለ ሰምዕዎ ወይውግርዎ በእብን ኵሎሙ ትዕይንት ። | ፲፪ | እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፤ የተሳደበውን ከሰፈር አፍኣ አውጣው፤ የሰሙትም ሁሉ እጃቸውን በራሱ ላይ ይጫኑበት፤ ሕዝቡም ሁሉ በደንጊያ ወግረው ይግደሉት ። |
| ወንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ብእሲ ብእሲ ለእመ ረገመ አምላኮ ጌጋየ ይከውኖ ። | ፲፫ | አምላክ ነኝ ያለ ሰው ቢኖር፤ ፈጣሪውን ቢሰድብ ዕዳ በደል ይሆንበታል ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው ። |
| እስመ ሰመየ ስመ እግዚአብሔርሞተ ለይሙት፤ ወበእብን ለይውግርዎ ኵሉ ትዕይንት ። | ፲፬ | የእግዚአብሔርን ስም ጠርቷልና ፈጽሞ ይሙት፤ ሕዝቡም ሁሉ በደንጊያ ወግረው ይግደሉት ። |
| እመኒ ግዩር፤ ወእመኒ ዘአምፍጥረቱ እስራኤል፤ እምከመ ሰመየ ስመ እግዚአብሔር ለይሙት ። | ፲፭ | ስደተኛም ቢሆን፤ ከእስራኤል የተወለደም ቢሆን፤ የእግዚአብሔርን ስም ከሰደበ ይገደል ። ዘሌ፣ ፳፪ ፲፮ ። |
| ወዘሰ ብእሲ ዘቀተለ እምኵሉ ነፍሰ ሰብእ ለይቅትልዎ ። | ፲፮ | ከሰው ወገን ሁሉ ነፍስ የገደለ ሰው ቢኖር፤ ይግደሉት ። ዘዳ፣ ፲፱ ፲፩፣ ዘፀ፣ ፳፩ ፲፪ ። |
| ወእመሰ ቀተለ እንስሳ ይፍዲ ነፍሰ ህየንተ ነፍስ ። | ፲፯ | ከብትን ቢገድል በገደለው ከብት ፈንታ ዓይነቱን ከብት ይክፈል ። ዘሌዋ፣ ፳፩ ፳፩፣ ዘፀ፣ ፳፩ ፳፫ ። |
| ወእመሰ ዘአቍሰለ ካልኦ በከመ ገብረ ላዕለ ካልኡ ከማሁ ይግበሩ ላዕሌሁ ። | ፲፰ | ባልንጀራውን ሥትቶ ያቆሰለ ሰው ቢኖር፤ በባልንጀራው እንዳደረገ እንደሱ ያድርጉበት ። ዘፀ፣ ፳፩ ፳፱ ። |
| ስብረት ህየንተ ስብረት፤ ወዓይን ህየንተ ዓይን፤ ወስን ህየንተ ስን፤ በከመ አቍሰለ ሰብአ ከማሁ ይግበሩ ላዕሌሁ ። | ፲፱ | እጅ እግሩን ቢሰብረው እጅ እግሩን ይሰበሩት፤ ዓይኑን ቢያጠፋው ዓይኑ ይጥፋ፤ ጥርስን ቢሰብር ጥርሱ ይሰበር፤ እርሱ ሰውን እንዳቆሰለ በርሱም ላይ እንደርሱ ያድርጉበት። |
| ወዘዘበጠ ሰብአ ወቀተለ፤ ሞተ ለይሙት ። | ፳ | መትቶ ሰውን የገደለ የሞት ሞት ይሙት ። |
| አሐዱ ውእቱ ኵነኔሆሙ ለግዩርኒ ወለዘእምፍጥረቱኒ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ። | ፳፩ | ከእስራኤል የተወለደውና የስደተኛው ፍርዳቸው (ቅጣታቸው) አንድ ነው፤ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ። ዘሌዋ፣ ፲፱ ፴፬፣ ዘፀ፣ ፲፪ ፵፱ ። |
| ወነገሮሙ ሙሴ ለደቂቀ እስራኤል ወአውፅእዎ ለዘጸረፈ አፍአ እምትዕይንት፤ ወወገርዎ በእብን ኵሉ ተዐይን ወገብሩ ደቂቀ እስራኤል፤ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ። | ፳፪ | ሙሴም ይህን ለእስራኤል ልጆች ነገራቸው፤ የእግዚአብሔርን ስም የነቀፈውን ሰው ከከተማ ወደ ውጭ አውጥተው ሕዝቡ ሁሉ በደንጊያ ወግረው ይግደሉት፤ የእስራኤልም ልጆች እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው አደረጉ። |

## ምዕራፍ ፳፭።

፩ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ በደብረ ሲና ወይቤሎ፡ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል።

እግዚአብሔር ሙሴን በሲና ተራራ ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው ብሎ ተናገረው።

፪ ወበሎሙ አመ በእክሙ ውስተ ምድር እንተ አነ እሁበክሙ፡ ተዓርፍ ምድር ወታሰንብት ለእግዚአብሔር።

እኔ ወደምሰጣችሁ አገር በገባችሁ ጊዜ ምድሪቱ ትረፍ፡ ለእግዚአብሔር ሰባት ዓመት ዕረፍት ታድርግ።

፫ ስድስተ ዓመተ ትዘርእ ገራህተከ፡ ወስድስተ ዓመተ ትገምድ ወይነከ ወታስተጋብእ ፍሬሁ።

ስድስት ዓመት እርሻህን ዝራ፡ ስድስትም ዓመት ወይንህን ቈርጠህ ፍሬውን ሰብስብ። ፪ ዜና መዋ፡ ፴፮ ፳፩።

፬ ወበሳብዕ ዓም ሰንበት ዕረፍታ ውእቱ ለምድር ወታሰነብት ለእግዚአብሔር ገራህተከኒ ኢትዝራእ፡ ወዓፀደ ወይንከኒ ኢትግምድ።

በሰባተኛው ዓመት ግን የምድር ዕረፍት ነው፡ ለእግዚአብሔር ዕረፍት ታድርግ፡ እርሻህን አትዝራ የወይንህንም ዘለላ አትቍረጥ፡ (በዚያች ዓመት አትልቀም)።

፭ ወዘለሊሁኒ ይበቍል ውስተ ገራህትከ ኢትዕፅድ፡ ወአስከለ ወይንከኒ ዘቅዱስ ኢትቅስም በይእቲ ዓመት፡ እስመ ዕረፍታ ለምድር ውእቱ።

በእርሻህ የገባ የበቀለውንም አትጨድ የምድር ዕረፍት ነውና፡ የተለየ የወይንህንም ዘለላ በዚያች ዓመት አትልቀም፡ የምድር የተለየ ዕረፍቷ ነውና። ዘሌ፡ ፳፭ ፲፩።

፮ ወይኩን ውእቱ ዘሰንበታ ለምድር መብልዐ ለከ ወለገብርከ፡ ወለአመትከ፡ ወለገባዒከ ወለፈላሲኒ ዘየኃድር ኀቤከ።

ምድር ዕረፍት በምታደርግበት የበቀለው ይህ የገበው እህል ላንተ ምግብ ይሁንህ፡ ለሴት በርያህና ለወንድ ባርያህም ካንተ ዘንድ ለሚኖር ምንደኛህና ለስደተኛህ ምግብ ይሁናቸው። ዘፀ፡ ፳ ፲።

፯ ወለእንስሳከ ወለአራዊተ ምድርኒ ይኩንክሙ መብልዐ ኵሉ እክሉ።

እህሉ ሁሉ ለእንስሳህና በምድር ላይ ላሉት አራዊት ምግብ (መኖ) ይሁናችሁ።

፰ ወትኌልቍ ለከ ሰብዓተ ሰናብተ ዕረፍተ ዘስድስቱ ዓመት ዘምስብዒት፡ ወእምዝ ትሬሲ ለከ ሰቡዐ ሰናብተ በዘትዜንዉ በመጥቅዕ ውስተ ኵሉ ምድርክሙ በበሠላሳ ወተስዓቱ ዓመት።

ስድስቱን ዓመት ዕጥፍ የምታደርግበት ሰባት ሱባዔ ቁጠር፡ ሰባቱን አንድ ሰባቱን አንድ እያልክ ከቈጠርክ በኋላ በአርባ ዘጠነኛው ዓመት (ኢዮቤልዩ) በአገራችሁ ሁሉ ነጋሪት መትታችሁ አዋጅ የምትነግሩበት ይሁን።

፱ ወበሳብዕ ወርኅ በዕለተ አስተርእዮ ትዜንዉ በመጥቅዕ ውስተ ኵሉ ምድርክሙ ወቀድስዋ ለይእቲ ዓመት ዘኃምሳ ኵላ ዓመታ።

በሰባተኛው ወር በረድኤት በምገለጥበት ቀን ነጋሪት መትታችሁ አዋጅ ንገሩ፡ ያችን አምስተኛይቱን ዓመት ዓመቷን ሁሉ አክብሩዋት። ዘሌዋ፡ ፳፫ ፳፬።

፲ ወስብኩ ተኃድጎ ውስተ ኵሉ ምድርክሙ ለኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስቴታ፡ እስመ፡ ዓመተ ተኃድጎ ውእቱ ወተአምረ ይኩንክሙ፡ ወይእቱ ኵሉ ውስተ ርስቱ፡ ወይሑር ኵሉ ውስተ ሀገሩ።

በአገራችሁም ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ዕረፍት የሚደረግበት ዘመን ነው፡ ብላችሁ አዋጅ ንገሩ፡ ይህም ምልክት ይሁናችሁም ሰው ሁሉ ወደ ርስቱ ወደ ሀገሩ ይግባ።

፲፩ ወትእምርተ ተኃድጎ ይኩንክሙ ውእቱ ዓመት ዘኃምሳ ወኵላ ዓመታ ኢትዝርእኡ፡ ወኢትዕፅዱ እንበለ ዘበቈለ ለሊሁ፡ ወኢትቅስሙ ዘተቀደሰ ባቲ፡ እስመ ትእምርተ ተኃድጎ ውእቱ።

ይህም አምሳኛው ዓመት ዕረፍት የምታደርጉበት ይሁናችሁ፡ በአምሳኛው ዓመት ዘርታችሁ አትጨዱ፡ አውቆ ከበቀለው የገበ በቀር የዕረፍት ምልክት ነውና የተለየውንም የወይን ፍሬ አትልቀሙ። ዘሌዋ፡ ፳፭ ፳፯።

፲፪ ወቅዱስ ይኩንክሙ ብልዑ ዘእምውስተ ገዳም እክለ።

ዓመተ ኅድገት ነውና ለናንተ የተለየ ይሁናችሁ በምድረ በዳ የበቀለውን የገበውን ብሉ።

፲፫ ወበይእቲ ዓመት ዘትእምርተ ተኃድጎ የአቱ ኵሉ ውስተ ርስቱ።

የዕረፍት ምልክት በሚደረግበት (ዓመተ ተኃድጎ) በዚያች ዓመት ሰው ሁሉ ወደየርስቱ ይመለስ (ይግባ)።

፲፬ ወእመኒበ ዘተሠይጠ ኀበ ካልእ ኢያጽሕበ፡ እስመ እምድኅረ ዓመተ ተኃድጎ ይሠየጥ ለካልኡ።

ለባልንጀራው የተገዛው መገዛት ቢኖር፡ ለባልንጀራው የተሸጠም ቢኖር፡ በዓመተ ኅድገት አምጣ ብሎ አያስጨንቀው፡ ዕረፍት ከሚደረግበት ዘመን በኋላ ለሌላው ይገዛልና።

፲፭ ወበመዋዕለ ይዘራእ እክል በውእቱ ዓመት ይፈድዮ በአምጣነ ብዝኆን ለእላንቱ ዓመታት፡ ወያበዝኅ ጥሪቶ።

እህል በሚዘራበት ወራት በነዚያ ዘመኖች ብዛት መጠን በዚያ ዓመት ይከፈለው። ዘሌዋ፡ ፳፯ ፲፰።

፲፮ ወአመ ይትኃደጋ ውእቶን ዓመታት ይትኃደግ ተሠይጦ፡ ወበመዋዕለ ይዘራእ እክል ይፈድየከ።

በነዚያ ዘመኖች ልክ ገንዘቡን ያበዛል፡ እነዚያ ዓመታቶች በተፈጸሙ ጊዜ መግዛት መገዛቱ ይቅር ያህል በሚልበት ወራት ይከፍልሃል።

፲፯ ወኢታጽሕብ ለካልእከ ወፍራህ እግዚአብሔርሃ አምላከከ፡ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ።

ባልንጀራህን አታስጨንቀው ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ፍራ፡ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና።

| | | |
|---|---|---|
| ወግበሩ ኵሉ ኵነኔየ ወፍትሕየ ወዕቀብዎ ወትነብሩ ውስተ ምድርክሙ ተአሚነክሙ ። | ፲፰ | ፍርዴንና ሕጌን ሁሉ አድርጉ ጠብቁትም በሀገራችሁም ተዘልላችሁ ትኖራላችሁ ። ዘሌዋ፥ ፲፰ ፭ ። |
| ወትሁብክሙ ምድር ፍሬሃ፥ ወትበልዑ ወትጸግቡ ። | ፲፱ | ምድርም ፍሬዋን ትሰጣችኋለች በልታችሁም ትጠግባላችሁ ። ዘሌዋ፥ ፳፮ ፭፥ ዘዳ፥ ፲፩ ፲፭ ። |
| ወእመሰ ትብሉ ምንተ ንበልዕ በውእቱ ሳብዕ ዓመት ለእመ ኢዘራእነ፥ ወለእመ ኢያስተጋባእነ እክለ እን እሬኑ ለክሙ በረከትየ ። | ፳ | ነገር ግን ካልዘራንና ካልሰበሰብን በዚያ በሰባተኛው ዓመት ምን እንበላለን ብትሉ፥ እኔ በረከቴን እሰድላችኋለሁ ። ማቴ፥ ፮ ፳፭፥ ዘሌዋ፥ ፳፭ ፭ ። |
| ወእመ ሳድስ ዓመት ትገብር ፍሬሃ ምድር ዘሠለስቱ ዓመት እክለ ። | ፳፩ | ምድርም በስድስተኛው ዘመን፥ የሦስተኛውን ዓመት እኽልን ታፈራለች ። ዘፀ፥ ፲፮ ፳፱ ። |
| ወትዘርኡ እምኔሁ በሳምን ዓም ወትበልዑ እምውእቱ እክል ከራሚ እስከ ታስዕ ዓም፥ እመ ይበጽሕ እክል ትበልዑ ብሉየ ከራሚ ። | ፳፪ | በስምንተኛውም ዘመን ከሱ ትዘራላችሁ፥ ከዚያም እኽል እስከ ዘጠነኛው ዘመን፤ ድረስ የከረመውን ትበላላችሁ እኽልም እስኪደርስ የደረሰውን እህል ትበላላችሁ ። |
| ወምድርኒ ኢትሠየጥ ሥሉጠ፥ እስመ እንቲአየ ይእቲ ምድር፥ እንትሙኒ ግዩራን ወፈላስያን ክንክሙ በቅድሜየ ። | ፳፫ | ምድርም ወጥ ሁና (የወጣች ሁና) አትሸጥም፥ ምድር የኔ ገንዘብ ናትና እናንተም በፊቴ ስደተኞችና መጻተኞች ናችሁና ። ዘሌዋ፥ ፳፭ ፴፥ ዘዳ፥ ፴፪ ፵፫ ። |
| ወበኵሉ ደወለ ምድርክሙ ኀበ ምኵናን ዘዚአክሙ ታቤዝዉ ምድረ ። | ፳፬ | የናንተ ርስት ጕልት በሆነው በአገራችሁ አውራጃ ሁሉ ምድርን አስቤዥ (አስጠምኑ) ። |
| ወለእመ ነድየ ካልእከ ዘምስሌከ ወሤጠ ለከ ምድሮ ወእምዝ መጽአ ዘቅሩቡ ዘይኴንኖ፥ ታቤዝዎ ዘሤጠ ለከ እኁሁ ። | ፳፭ | ካንተ ጋር የሚኖር ባልንጀራህ ተቸግሮ ምድሩን ቢሸጥልህ (ቢያስቤዥህ) ከዚህ በኋላ የሚከፈለው የቅርብ ዘመዱ ቢመጣ፥ ወንድሙ የሸጠልህ ምድሩን አስበዥው ። |
| ወእመኒ አልቦ ዘይኴንኖ፥ ወእምዝ ረከበ ውእቱ ውስተ እዴሁ፥ ወአእከለ ለቤዝዎቱ ይኄልቁ ሎቱ ዓመተ ዘእምአመ ሤጠ ። | ፳፮ | የሚከፈለው ባይኖር ከዚህ በኋላ እሱ በእጁ ገንዘብ አግኝቶ ለመበዠት ቢበቃ፥ ከሸጠበት ዘመን ጀምሮ ዘመኑን ይቍጠሩለት (ይገምግሙለት) ። ዘሌ፥ ፳፭ ፳፰፥ ፩ ፮ ። |
| ወይፈድዮ በመጠነ በጽሐ ለውእቱ ብእሲ ዘነበሁ ሤጠ፥ ወያገብእ ሎቱ ገራህቶ ። | ፳፯ | ለሸጠለት ሰው ተገምግሞ የደረሰበትን ያህል ይከፈለው እርሻውንም ይመልስለት ። ዘሌዋ፥ ፳፭ ፶፫ ። |
| ወእመሰ ኢረከበ ውስተ እዴሁ በአምጣነ ይፈድዮ ይከውን ገራህቱ ለዘተሣየጠ እስከ ዓመተ ተኃድጎ፥ ወበዓመተ ተኃድጎ ያገብእ ሎቱ ገራህቶ ለዘሤጠ ። | ፳፰ | በእጁ የሚከፍለውን ያህል ገንዘብ ባያገኝ ግን እስከ ዓመተ ኅድገት ዘመን እርሻው ለገዛው ሰው ይሁን፥ በዓመተ ኅድገት ጊዜ ግን እርሻውን ይመልስለት ። |
| ወለእመበ ዘሤጠ ቤቶ በውስተ ሀገር እንተ ባቲ ቅጽር እስከ ይፌጽም መዋዕለ ይእቲ ዓመት ይከውኖ ለቤዝዎ፥ ወያቤዝውዎ ። | ፳፱ | ቅጽር ባለበት ከተማ ውስጥ ያለው ቤቱን የሸጠ ሰው ቢኖር፥ የዚያች ቤቱን የሸጠበት ዓመት እስኪጨርስ ድረስ መበዠት ይገባዋል (ይበዥው) ። ዘሌዋ፥ ፳፭ ፴ ። |
| ወእመሰ ተፈጸመት ኵላ ይእቲ ዓመት ወኢቤዘወ ሥሉጠ ይከውኖ ውእቱ ቤት ለዘተሣየጠ፥ ወየሐትትዎ ሎቱ ውእተ ቤተ ዘሀለወ ውስተ ሀገር እንተ ባቲ ቅጽር፥ ወይከውኖ ለውሉደ ውሉዱ ወኢይነሥእዎ እምኔሁ በዓመተ ተኃድጎ ። | ፴ | ያች የሸጠበት ዘመን መላዋ ገንዘቡን ሳይመልስ ብትፈጸም ግን ያ ቤት ለገዛው ሰው ወጥ ሁኖ ገንዘብ ይሁነው ቅጽር ባላት አገር ያለ ያንን ቤት አይመልስለት ለልጅ ልጁ ይሁንለት፥ በዓመተ ኅድገትም ጊዜ አይውሰዱበት ። |
| ወአብያተሰ ዘውስተ ሀገር እንተ አልባቲ ቅጽር ዓውዳ ከመ ገራህተ ምድር ይትቤዘውዎ፥ ወበኵሉ ጊዜ ያቤዝውዎ ወበዓመተ ተኃድጎኒ ያገብእዎ ። | ፴፩ | በዙርያዋ ቅጽር በሌለበት መንደር ያሉ ቤቶችን ግን እንደ እርሻ ይበዥት ሁሉ ጊዜም ያስበዥት በዓመተ ኅድገትም ጊዜ ይመልሱለት ። ዘሌዋ፥ ፳፭ ፴፪ - ፵፰ ። |
| ወአህጉረ ሌዋውያንኒ ይትቤዘው ኵሉ ጊዜ፥ አብያቲሆሙ ዘውስተ አህጉሪሆሙ፥ ያቤዝውዎሙ ለሌዋውያን ። | ፴፪ | የሌዋውያን፤አገር ግን ይቤዠል (ይጠመናል) በአገራቸው ያሉ ቤቶችንም ሁሉ ጊዜ ለሌዋውያን ያስበዥዋቸው ። |
| ወኵሉ ዘተቤዘወ እምኀበ ሌዋውያን፥ ወእሙኒ አብያት ዘውስተ አህጉሪሆሙ ዘገብአ ለአብዕልቲሁ ተሠይጠ ዘአግብኡ ሎቱ በዓመተ ተኃድጎ በደወለ ዚአሆሙ እስመ አብያተ አበዊሆሙ ወአህጉሪሆሙ ለሌዋውያን ውእቱ፥ ወምኵናኑ ዘዚአሆሙ ይኩን በማእከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ። | ፴፫ | ከሌዋውያንም የተበዠው ሁሉ በአገራቸው ያሉ ቤቶችም ቢሆኑ ከተሸጠ በኋላ ለባለ ቤቶቹ የተመለሰ በዓመተ ኅድገትም ዘመን የመለሱለት የአባቶቻቸው ቤቶች ናቸውና፥ የሌዋውያንም አገሮች ናቸውና፥ በአውራጃቸውም ያለው ሁሉ እሱ የነሳቸው የሚሆን ግዛቱም በእስራኤል ልጆች መካከል ለነሳቸው ይሁን ። |

፴፬ ወገራውህኒ ዘድወለ አህጉሪሆሙ ኢይሠየጥ፣ እስመ ደወሎሙ ውእቱ ዘለዓለም ።

በአገሮቻቸው አውራጃ ያሉ እርሻዎችም አይሸጡ፤ ለዘለዓለም ርስታቸው ነውና ። ዘዳግ፣ ፲፭ ፯ ።

፴፭ እመኒ ነድየ ካልእከ ዘምስሌከ፣ ወስእነ ተገብሮ በኀቤከ ተዓቅቦ ከመ ግዩር ወፈላሲ፣ ወይሕዮ ካልእከ ዘምስሌከ ።

ከንተ ጋር ያለ ባልንጀራህ ቢቸገር ባንተ ዘንድም ማረስ (መቆፈር) ቢሳነው እንደስደተኛና እንደ መጻተኛ ተከባክበው ከንተ ጋር ያለ ባልንጀራህም በሕይወት ይኑር።

፴፮ ወኢትንሣእ እምኔሁ ርዴ ወኢእመ ብዙኀ አጕንደየ፣ ወፍራህ እግዚአብሔርሃ አምላክከ፣ እስመ አነ እግዚአብሔር ።

ገንዘብህንም ምንም ብዙ ጊዜ ቢያዘገይብህ ከሱ ወለድ (አራጣ) አትቀበል፤ ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ፍራ፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ። ዘፀ፣ ፳፪ ፳፭፣ ዘዳግ፣ ፳፫ ፲፱ ።

፴፯ ወኢተሀቦ ወርቀከ በርዴ፣ ወእክለከኒ ኢትትረደዮ ።

ብርህን በአራጣ (በወለድ) አታበድረው እኽልህንም በትርፍ አትስጠው ። መዝ፣ ፲፭ ፭፣ ነህ፣ ፭ ፯ ።

፴፰ እስመ አነ እግዚአብሔር ዘአውጻእኩከ እምድረ ግብጽ ከመ አሀብከ ምድረ ከነዓን ወእኩንከ አምላከ ።

የከነዓንን ምድር እሰጣጥህ ዘንድ የፍቅርም አባት እሆንህ ዘንድ ከግብጽ አገር ያወጣሁህ እኔ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ነኝና ። ዘፀ፣ ፳፱ ፱፣ ዘዳ፣ ፲፭ ፲፱ ።

፴፱ ወእመ ተጸነሰ ካልእከ ወተሠይጠ ኀቤከ፣ ኢይትቀነይ ለከ ከመ ገብር ።

ባልንጀራህ ተቸግሮ ላንተ ቢገዛልህ (ባንተ ዘንድ ቢቀጠር) እንደ ባርያ አይገዛልህ ።

፵ አላ ከመ ገባኢ ወከመ ፈላሲ ይኩንከ፣ እስከ ዓመተ ተኃድሶ ይትቀነይ ለከ ።

እስከ ዓመተ ኅድገት ድረስ እንደ ስደተኛና እንደ ምንደኛ ይሁንህ እንጂ እንደ ባርያ አይገዛልህ ።

፵፩ ወበዓመተ ተኃድሶ ይወጽእ ውእቱ ወደቂቁ ምስሌሁ ወይገብእ ኀበ አዝማዲሁ ወውስተ ደወሉ ወየሐውር ብሔሮ ።

በዓመተ ኅድገት ነፃ ይውጣ፤ ልጆቹም ከርሱ ጋር ነፃ ይውጡ፤ ወደ ዘመዶቹ ወደ ርስቱና ወደ አገሩ ይመለስ ።

፵፪ እስመ አግብርተ ዚአየ እሙንቱ፣ እለ አውጻእኩ እምድረ ግብጽ ኢይሠየጡ ከመ ዘይሠየጥ ገብር ።

ከግብጽ አገር ያወጣኋቸው ባሮቼ ናቸውና እንደ ሚሸጥ ባርያ አይሸጡ አይለወጡ ።

፵፫ ወኢታጠውቆ በፃማ፣ ወፍራህ እግዚአብሔርሃ አምላከከ ።

በድካምም አታስጨንቀው፤ ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ፍራ ። ኤፌ፣ ፮ ፱፣ ዘሌዋ፣ ፳፭ ፲፯ ።

፵፬ ወገብረሰ ወአመተኒ መጠነ ረከብከ እምአሕዛብ እለ ዓውድከሙ እምኔሆሙ ታጠርዩ ገብረኒ ወአመተኒ ።

ወንድ ባርያንና ሴት ባርያን ግን ያገኘኸውን ያህል በዙሪያችሁ ካሉ አሕዛብ ሴት ባርያንና ወንድ ባርያን ግዙ።

፵፭ ወእምደቂቆሙኒ ለእለ የኃድሩ ምስሌክሙ እምኔሆሙ ታጠርዩ ወእምአዝማዲሆሙኒ ለኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስተ ምድርክሙ ለጥሪትክሙ ይኩንክሙ ።

ለዘለዓለም ገንዘብ ይሆኑዋችሁ ዘንድ፣ ከናንተ ጋር ከሚኖሩ ከልጆቻቸው በሀገራቸውም ከሚኖሩ ከዘመዶቻቸው ሁሉ ግዙ ።

፵፮ ወለውሉድክሙኒ ትከፍልዎሙ ወይኩኑክሙ ለጥሪት ክሙ ለዓለም፤ ወዘእምአኃዊከ ደቂቀ እስራኤል አሐዱ አሐዱ ኢያጥቆ ለካልኡ በፃማ።

ለልጆቻችሁም አድሏቸው፤ ለዘለዓለምም ገንዘብ ይሁኗችሁ፤ ከወንድሞችህ ከእስራኤል ልጆች አንዱም አንዱም ባልንጀራውን በድካም (በሥራ) አያስጨንቀው ።

፵፯ ወእመሰ ኢረከበ ውስተ እዴሁ ውእቱ ግዩር ወእመኒ ገከቱ ፈላሲ ዘኀቤከ፣ ወይብሉከ ሰብአቲሁ አቤዝወነዮ ለዝከቱ ግዩር አው ለዝንቱ ፈላሲ ዘኀቤከ እምድኅረ ተሣየጥከሆሙ፤ እመኒ ዘሰብአቲሁ ለውእቱ ግዩር ተቤዝዎ ይትቤዘዎ አሐዱ እምሰብአቲሁ ።

ነገር ግን ያ መጻተኛው ከንተ ዘንድ የሚኖር ያ ስደተኛውም ቢሆን፤ በእጁ ገንዘብ ባያገኝ ዘመዶቹ ይህን መጻተኛ ወይም ከንተ ዘንድ የሚኖር ይህንን ስደተኛ ከገዛኸቸው በኋላ እንበዠው ቢሉህ ያነን ስደተኛ ከዘመዶቹ አንዱም አንዱም መበዠትን ይበዠው ።

፵፰ እመኒ እምአኃወ አቡሁ ወእመኒ ወልደ እኁሁ ለአቡሁ ይቤዝዎ፤ አው እምሰብአቲሁ አው እምሥጋሁ አው እምነገዱ ይቤዝዎ ።

ከአባቱ ወንድሞችም ቢሆን፤ ያባቱ ወንድም ልጅም ቢሆን፤ ወይም ከዘመዶቹ፤ ወይም ከወንድሙ፤ ወይም ከወገኑ አንዱ ይበዠው ። ዘሌዋ፣ ፲፰ ፯ ።

፵፱ ወለእመሰ ረከበ ውስተ እዴሁ ለሊሁ ይቤዙ ርእሶ፤ ወየሐስቡ ሎቱ ለዘተሣየጦ እምዓመት ዘተሣየጦ እስከ ዓመተ ተኃድሶ ።

ነገር ግን እሱ በእጁ ገንዘብ ቢያገኝ ራሱን ይበዠው ለገዛውም ሰው ከገዛበት ዘመን ጀምሮ እስከ ዓመተ ኅድገት ድረስ ያለ ደመወዙን ይገምግሙለት (ይቍጠሩለት) ።

፶ ወይሬስዩ ሎቱ ወርቀ ሤጡ ከመ ዘዕለቱ ለገባኢ ዘእምዓመት እስከ ዓመት ዘሀለወ ምስሌሁ ።

የተገዛበትንም ዋጋ ከተገዛበት ዘመን ጀምሮ ከርሱ ጋር እስከ ኖረበት ዘመን ድረስ ያለውን እንደ ምንደኛ የዕለት ዋጋ ያድርጉለት ። ኢያ፣ ፯ ፩፣ ኢሳ፣ ፲፮ ፲፬ ።

፶፩ ወእመ ወሰከ እምሰመንቱ ዓም ይሁብ ቤዛሁ እምወርቀ ሤጡ ።

ከስምንተኛው ዘመን በላይ ቢጨምር ግን ከተገዛበት ዋጋ ወርቅ መበዠውን ይስጥ ። ዘሌዋ፣ ፳፯ ፲፮፣ ፳፯ ፳፰።

፶፪ ወእመሰ ኅዳጥ ተርፈ ዓመት እስከ ዓመተ ተኃድጎ የሐስቦ ሎቱ ዓመታቲሁ ።
ከገባበት ዘመን ጀምሮ እስከ ዓመተ ኅድገት ድረስ ያለው ዓመት ጥቂት ቢቀር የተገዛበትን ዓመት ይቍጠሩለት (ይገምግሙለት) ።

፶፫ ወይሁብ ቤዛሁ ከመ ዓስበ ገብኢ ዘእምዓመት እስከ ዓመት ዘሀለወ ምስሌሁ፤ ወኢያጽሕብ ከመ ቀዳሚ ።
ከተገዛበት ዓመት ጀምሮ ከርሱ ጋራ እስከኖረበት ዘመን መበገሩውን እንደ ዕለት ምንደኛ ይስጠው፤ እንደ ቀድሞውም አያስጨንቀው፡፡ ዘሌዋ፡ ፳፭ ፲፯ ።

፶፬ ወእመሰ ኢተቤዘወ ከመዝ እመ ዓመተ ተኅድጎ ይወጽእ እምኔሁ ምስለ ደቂቁ ።
እንዲህ ባይበገርው ግን በዓመተ ኅድገት ጊዜ ከልጆቹ ጋር ከሱ ነፃ ይውጣ ።

፶፭ እስመ አግብርተ ዚአየ እሙንቱ ደቂቀ እስራኤል ዘአውጻእኩ እምድረ ግብጽ፤ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ።
የእስራኤል ልጆች ባሮቼ ናቸውና፤ ከግብጽ ምድር ያወጣኋቸው እኔ ፈጣሪያቸው እግዚአብሔር ነኝ ።

## ምዕራፍ ፳፮ ።

፩ ወኢትግበሩ ለክሙ ግብረ እደ ሰብእ ወኢግልፎ ወኢታቅሙ ለክሙ ምስለ ወሐውልተ እብን በውስተ ምድርክሙ ከመ ትስግዱ ሎቱ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ።
ለናንተ የሰው እጅ ሥራ ከወርቅ ከብር የተሠራ ጣኦት አታድርጉ፤ ከድንጋይ የተቀረጸ ጣኦትንም አትሥሩ፤ ትሰግዱለትም ዘንድ በሀገራችሁ ትክል ድንጋይና ምስልን አታቁሙ፤ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ።

፪ ወዕቀቡ ሰንበታትየ ወፍርሁ እምቅዱሳንየ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ።
ቅዳሚ ቅዳሜን ጠብቁ፤ (አክብሩ) ወዳጆቼ ነቢያትንም (ካህናትን) ፍሩ፤ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ።

፫ ወለእመ ሖርክሙ በትእዛዝየ ወዐቀብክሙ ኵነኔየ ወገበርክምዎ እሁበክሙ ዝናመ በበጊዜሁ ወበበዘመኑ ።
በትእዛዜ ጸንታችሁ ብትኖሩ ሕጌንም ጠብቃችሁ፤ ብትሠሩት በየጊዜውና በየዘመኑ ዝናም እሰጣችኋለሁ ።

፬ ወምድርኒ ትሁብ እክሊ ወዕፀወ ገዳምኒ ይሁቡ ፍሬሆሙ፤ ወይትራከብ ማእረር ምስለ ቀስም፤ ወቀስምኒ ይትራከብ ምስለ ዘርእ ።
ምድርም እህልን ትሰጣለች፤ የምድረ በዳም ዛፎች ፍሬያቸውን ይሰጣሉ፤ የእህሉ መከር ከወይኑ መቍረጥ የወይኑም መቍረጥ ከእክሉ ዘር ጋር ይገናኛል ።

፭ ወትበልዑ እክለክሙ ለጽጋብ፤ ወትነብሩ እንዘ ትትአመኑ ውስተ ምድርክሙ ።
እህላችሁንም እስክትጠግቡ ድረስ ትበላላችሁ፤ በሀገራችሁም ከመከራው ተዘልላችሁ ትኖራላችሁ ።

፮ ወእሁበክሙ ሰላመ ውስተ ምድርክሙ ወትነውሙ፤ ወአልቦ ዘያደነግፀክሙ ወአጠፍኦሙ ለአራዊተ ምድር እምብሔርክሙ ።
በሀገራችሁም ሰላምን እሰጣችኋለሁ፤ ትተኛም አላችሁ፤ የሚያስደነግጣችሁም የለም፤ የምድር አራዊቶችንም ከሀገራችሁ አጠፋቸዋለሁ ። መዝ፡ ፫ ፭ ።

፯ ወትቀትልዎሙ ወይመውቱ በቅድሜክሙ ፀርክሙ ።
ጠላቶቻችሁን ትገድሏቸዋላችሁ፤ በፊታችሁም ይሞታሉ ። ኢሳ፡ ፴፭ ፱፡ ሕዝ፡ ፭ ፲፯ ።

፰ ወሐምስቱ እምኔክሙ ያነትዕዎሙ ለዐሠርቱ ምእት፤ ወምእት እምኔክሙ ያነትዕዎሙ ለእልፍ ወይወድቁ ጸላእትክሙ በሐፂን ።
ከናንተ አምስቱ መቶውን ድል ይነሷቸዋል፤ መቶውም እልፉን ድል ይነሷቸዋል፤ ጠላቶቻችሁ በፊታችሁ በጦር ተደብድበው ይወድቃሉ ። ዘዳግ፡ ፴፪ ፴ ።

፱ ወእኔጽር ላዕሌክሙ፤ ወእባርከክሙ ወአዐብየክሙ ወአቀውም ኪዳንየ ምስሌክሙ ።
እናንተን ግን (በዓይነ ምሕረት) እመለከታለሁ፤ እበዛችሁም አለሁ፤ ከፍ ከፍም አደርጋችኋለሁ፤ ከናንተም ጋር መሐላዬን አጸናለሁ ። ፪ ነገሥ፡ ፲፫ ፳፫ ።

፲ ወትበልዑ ከራሚ፤ ወከራሚ ከራሚ ወታወፅኡ ከራሚ ከመ ታብኡ ሐዲሰ ።
ድልቡን የድልቡን ድልብ ትበላላችሁ፤ አዲሱንም እህል ታገቡ ዘንድ የከረመውን ታወጣላችሁ ።

፲፩ ወእተክል ማኅደርየ ኀቤክሙ ወኢታስቆርርክሙ ነፍስየ ።
ማደሪያዬን በናንተ ዘንድ እተክላለሁ (አጠናለሁ)፤ ሰውነቴም አትጸየፋችሁም ። ሕዝ፡ ፴፯ ፳፯ ።

፲፪ ወአንሶሱ ምስሌክሙ፤ ወእከውነክሙ አምላከክሙ ወአንትሙኒ ትከውኑኒ ሕዝብየ ።
ከናንተ ጋር እኖራለሁ፤ (የፍቅር) አባትም እሆናችኋለሁ፤ እናንተም ወገኖቼ ትሆኑኛላችሁ ። ኤር፡ ፯ ፳፫ ።

፲፫ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ዘአውፃእኩክሙ እምድረ ግብጽ እንዘ አግብርት አንትሙ ወሰበርኩ መዋቅሕቲክሙ ወአውፃእኩክሙ ገሃደ ።
እናንተ ባሮች ስትሆኑ ከግብጽ ምድር ያወጣኋችሁ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና እገዛዛችሁንም እዋፍቼ ተገልጬ አወጣኋችሁ ። ዘሌ፡ ፳፭ ፴፰ ።

፲፬ እመሰ ኢሰማዕክሙኒ ወኢገበርክሙ ትእዛዝየ ዘአዘዝኩክሙ ወተቈጥዓት ነፍስክሙ ኵነኔየ ከመ ኢትግበሩ ኵሎ ትእዛዝየ ወከመ ትኅድጉ ሥርዓትየ ከማሁ እነኒ እገብረክሙ ።
ቃሌን ባትሰሙኝ፤ ትእዛዜንም ባታደርጉ ግን ከዳችሁኝ እንጂ ያመናችሁኝ አይደለም፤ ትእዛዜን ሁሉ እንዳትፈጽሙ፤ ሥርዓቴንም ትተው ዘንድ ሰውነታችሁ ሕጌን ተጸየፈች (ሰለቸች)፤ እኔም እንዲህ አደርግባችኋለሁ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወአመጽእ ለእኪት ላዕሌክሙ ዐበቀ ፡ ወደዌ ሲሕ ወዘይደጒፅክሙ አዕይንቲክሙ ። | ፲፮ | መከራንም በናንተ ላይ አመጣታለሁ (ዓበቅ) እክክን (ሲሕ) ቍርጥማትን ፡ ዓይናችሁን የሚያጠፉ በሽታንም አመጣባችኋለሁ ። |
| ወትትመሰው ነፍስክሙ ወትዘርኡ ለከንቱ ዘርእክሙ ወይበልዕዎ ፀርክሙ ። | ፲፯ | ሰውነታችሁ (እንደ ሰም) ትቀልጣለች ፡ ዘራችሁንም ላትበሉት (በከንቱ) ትዘራላችሁ ጠላቶቻችሁ ያጠፉዋ ችኋልና ። ኢያሱ ፴፩ ፫ ፡ ኤር ፭ ፲፯ ። |
| ወአቀውም ገጽየ ላዕሌክሙ ፡ ወትወድቁ ቅድመ ፀር ክሙ ወያነትዑክሙ እለ ይጸልኡክሙ ፡ ወትነትዑ እንዘ አልቦ ዘይዴግነክሙ ። | ፲፰ | ገጸ መዓቴን አጸናባችኋለሁ ፡ በጠላቶቻችሁም ፊት ትወድቃላችሁ ፡ የሚጠሉዋችሁ ጠላቶቻችሁ ያሳድዷች ኋል ማንም የሚያሳድዳችሁ ሳይኖር ትሸሻላችሁ ። |
| ወእመ እስከ ዝንቱ ኢሰማዕክሙኒ እዌስክ መቅሠፍ ትየ ሰብዓተ መቅሠፍተ በእንተ ኃጣውኢክሙ ። | ፲፱ | እንዲህ እስክትሆኑ ድረስ ደርሳችሁ ካልሰማችሁኝ ስለ ኃጢአታችሁ በመቅሠፍት ላይ ሰባት መቅሠፍት እጨምርባችኋለሁ ። ፪ ሳሙ ፪ ፭ ፡ መዝ ፲ ፲፱ ። |
| ወእሰብር ጽእለተ ትዕቢትክሙ ወእሬስይ ለክሙ ለሰ ማይ ከመ ሐዊን ወለምድርኒ ከመ ብርት ። | ፳ | የትዕቢታችሁን ስድብ አጠፋለሁ ፡ ሰማይን እንደ ብረ ት ፡ ምድርንም እንደ ናስ አደርጋታለሁ ። |
| ወይከውን ለከንቱ ኃይልክሙ ፡ ወኢትሁበክሙ ምድ ር ዘርአ ፡ ወዕፀወ ገዳምኒ ኢይሁቡክሙ ፍሬሆሙ ። | ፳፩ | ኃይላችሁም ለከንቱ ይሆናል ፡ ምድር የዘራችሁበትን አታበቅልም ፡ የምድረ በዳ ዛፎችም ፍሬያቸውን አይሰጡ ዋችሁም ። መዝ ፪ ፳፯ ፡ ዘዳግ ፳፰ ፲፰ ። |
| ወእመኒ እምድኅረ ዝንቱ ሖርክሙ ግድመ ወኢፈቀ ድክሙ ትስምዑኒ እዌስከክሙ ሰብዓተ መቅሠፍተ በከመ ኃጣውኢክሙ ። | ፳፩ | ከዚህ በኋላ አግድማችሁ ብትሄዱ ፡ ትሰሙኝም ዘንድ ካልወደዳችሁ እንደ ኃጢአታችሁ ብዙት ሰባት መቅሠ ፍት አመጣባችኋለሁ ። ሐጌ ፮ ፲ ። |
| ወእፌኑ ላዕሌክሙ አራዊተ ምድር እኩያነ ወይበል ዑክሙ ወያጠፍኡ እንስሳክሙ ወውኁዳነ ያተርፉክሙ ወበድወ ይሬስዩ ፍናዌክሙ ። | ፳፪ | የክፉ የምድር አውሬዎችንም አመጣባችኋለሁ ይበሉ ዋችኋል ፡ ከብቶቻችሁንም ያጠፋሉ ፡ ጥቂት ያተርፉላ ችኋል መንገዳችሁንም ምድረ በዳ ያደርጉታል ። |
| ወእመኒ እስከ ዝንቱ ኢፈራህክሙኒ አላ ሖርክሙ ግ ድመ ምስሌየ አነኒ አሐውር በመዓት ግድመ ምስሌክሙ ወእትቤቀለክሙ አነኒ ምስብዒተ በእንተ ኃጣውኢክሙ ። | ፳፫ | ከኔ በጠገብ ኖራችሁ እንጂ እንዲህ እስከ መሆን ድረ ስ ደርሳችሁ ካልፈራችሁኝ እኔም በቁጣ ከናንተ በጠ ገብ እኖራለሁ እኔም ስለ ኃጢአታችሁ ዕጥፍ እበቀላች ኋለሁ ። |
| ወአመጽእ ላዕሌክሙ መጥበሕተ እንተ ትዴግነክሙ ወትትቤቀለክሙ በቀለ ኪዳንየ ፡ ወትጕይዩ እምውስተ አህጉሪክሙ ። | ፳፬ | እየተከተለች የምታጠፋ ጦርንም አመጣባችኋለሁ ፡ መሐላዬም በቀልን ትበቀላችኋለች ከአገሮቻችሁም ትሸ ሻላችሁ ። ፪ ሳሙ ፳፬ ፳፮ ፡ መዝ ፲፰ ፳፮ ። |
| ወእፌኑ ሞተ ላዕሌክሙ ወትገብኡ ውስተ እደ ፀር ክሙ ሰበ አሕመመክሙ ኃጢአ እክል ዘትሴሰዩ ። | ፳፭ | ሞትን አመጣባችኋለሁ የምትበሉት የእህል መጥፋት በስጨነቃችሁም ጊዜ በጠላቶቻችሁ እጅ ትወድቃላችሁ። |
| ወያበስላ ዓሥሩ አንስት ኅብስተ በአሐዱ እቶን ወይ ሁበክሙ ኅብስተክሙ በመድሎት ትበልዑ ወኢትጸግቡ ። | ፳፮ | ዐሥሩ ሴቶች በአንድ ምድጃ እንጀራን ይጋግራሉ ፡ እንጀራችሁን ለክተው ይሰጡዋችኋል ፡ ትበላላችሁ ፡ ነገር ግን አትጠግቡም ። መዝ ፻፭ ፲፮ ፡ ኢሳ ፫ ፩ ። |
| ወእመኒ እስከ ዝንቱ ኢሰማዕክሙኒ አላ ሖርክሙ ምስሌየ ግድመ ፡ አነኒ አሐውር ምስሌክሙ በመዓት ግድመ ። | ፳፯ | ከኔ ጋር በጠገብ ኖራችሁ እንጂ ይህ ሁሉ እስኪፈጸ ምባችሁ ድረስ ደርሳችሁ ካልሰማችሁኝ እኔም በቁጣ እንደናንተ በጠገብ እኖራለሁ ። |
| ወእቀሥፈክሙ አነኒ ምስብዒተ በከመ ኃጣውኢክሙ ወትበልዑ ሥጋ ደቂቅክሙ ፡ ወሥጋ አዋልዲክሙ ። | ፳፰ | እኔም እንደ ኃጢአታችሁ መጠን ሰባት መቅሠፍት አመጣባችኋለሁ ፡ የወንዶችና የሴቶች ልጆቻችሁንም ሥጋ ትበላላችሁ ። ኢሳ ፶፱ ፲፰ ፡ ኤር ፳፩ ፭ ። |
| ወእደመስስ ምስለክሙ ወእሜሩ ግብረ እደዊክሙ ዘዕ ፀው ወእዘሩ አብድንቲክሙ ላዕለ ምስለ አማልክቲክሙ ወትትቋጥዐክሙ ነፍስየ ። | ፳፱ | ከፍ ያሉ ኮረብታችሁን (መስጊዳችሁን) አፈርሳለሁ ፡ ምስላችሁን አደመስሳለሁ ፡ ከዕንጨቶች የተሠራ የእጃች ሁን ሥራ (ጣኦትን) አጠፋለሁ ፡ ሬሳችሁንም በጣኦታቱ ምስል ላይ እበትነዋለሁ ፡ ሰውነቴም ትበሳጭባችኋለች ። |
| ወእገብሮን ለአህጉሪክሙ መዝበረ ፡ ወእደመስስ ቅድ ሳቲክሙ ወኢያጼኑ መዓዛ መሥዋዕቲክሙ ። | ፴ | ከተሞቻችሁን በድማ አደርጋቸዋለሁ ፡ ንዋየ ቅድሳ ታችሁን አጠፋለሁ ፡ መዓዛ መሥዋዕታችሁንም አላሸትም (አልቀበልም) ። ነህ፡ ፪ ፫ ፡ ኤር፡ ፬ ፯ ፡ ሕዝ፡ ፱ ፯ ። |

፴፩ ወእሬስያ አነ ለምድርክሙ በድወ ወይደመሙ በእንቲአሃ ፀርክሙ እለ ይነብሩ ውስቴታ ።

እኔ አገራችሁን ምድረ በዳ አደርጋታለሁ ፤ በውስጧ የሚኖሩ ጠላቶቻችሁም ስለ እሷ ጥፋት ይደነቃሉ ።

፴፪ ወእዘርወክሙ ውስተ አሕዛብ ወታጠፍአክሙ መጥበሕት በኀበ ሖርክሙ ።

በአሕዛብ አገር እበትናችኋለሁ ፤ በሄዳችሁበትም አገር ጦር ታጠፋችኋለች ። ኤር፡ ፱ ፲፭ ፤ ዘዳግ፡ ፳፰ ፴፮ ።

፴፫ ወትከውን ምድርክሙ በድወ ወአህጉሪክሙኒ ይከውና ምዝበሩራነ ።

ምድራችሁ በድማ ትሆናለች ፤ ከተሞቻችሁም ፍራሽ ይሆናሉ ፤ (ይፈታሉ) ። ዘዳግ፡ ፱ ፳፯ ።

፴፬ ወይእተ አሚረ ይኤድማ ለምድር ሰናብቲሃ በኵሉ መዋዕለ ሙስናሃ ።

ያን ጊዜ በጥፋቷ ወራት ሁሉ ምድርን ዕረፍቷ ደስ ያሰኛታል ። ፪ ዜና መ፡ ፴፮ ፳፩ ።

፴፭ ወአንትሙኒ ትሄልዉ ውስተ ምድረ ጸላእትክሙ ፤ ወይእተ አሚረ ታሰንብት ምድር ፤ ወይኤድማ ለምድር ሰናብቲሃ በኵሉ መዋዕለ ሙስናሃ ፤ ወታሰንብት ከመ ኢያሰንበተት በሰንበታቲክሙ እመ ሀሎክሙ ትነብሩ ውስቴታ ።

እናንተም በጠላቶቻችሁ አገር ትኖራላችሁ ፤ የዚያን ጊዜ ምድር ዕረፍት ታደርጋለች በጠፋችበትም ወራት ሁሉ ምድርን ዕረፍቷ ደስ ያሰኛታል በኖራችሁበት ጊዜ እናንተ ዕረፍት እንዳደረጋችሁ ያላረፈችውን ያህል ዕረፍት ታደርጋለች ። ዘሌዋ፡ ፳፭ ፪ ።

፴፮ ወላዕለ እለ ተርፉኒ እምኔክሙ አመጽእ ድንጋፄ ውስተ ልበሙ ፤ በምድረ ርስቶሙ ፤ ወይሜምዖ እምድምፀ ቈጽል ዘይትሐወስ ወይነትዑ ከመ ዘይነትዕ እምፀር ፤ ወይወድቁ እንዘ አልቦ ዘይዴግኖሙ ።

በአገራቸው በቀሩትም ሰዎች ላይ በርስታቸው ምድር ሳሉ በልቡናቸው ድንጋጤ አሳድርባቸዋለሁ ፤ ከሚንኰሻኰሽ ቅጠል ድምፅ የተነሣም ይሸበራሉ ፤ ከጠላት እንደሚሸሽ ሰው የሚያሳድዳቸው ሳይኖር ይሸሻሉ ።

፴፯ ወይትሜወሮ ብእሲ ለእኁሁ ከመ ዘውስተ ቀትል እንዘ አልቦ ዘይዴግኖሙ ፤ ወኢትክሉ ተቃውሞቶሙ ለፀርክሙ ።

በሰልፍ ውስጥ ያለ ሰው ወንድሙን ቸል እንዲለው እሊህም የሚከተላቸው ሳይኖር ወንድም ወንድሙን ቸል ይለዋል ፡ ጠላቶቻችሁንም መቋቋም አትችሉም ።

፴፰ ወትጠፍኡ በውስተ አሕዛብ ፤ ወትውሕጠክሙ ምድረ ፀርክሙ ።

በአሕዛብ አገር ትጠፋላችሁ ፡ የጠላቶቻችሁም ምድር ትውጣችኋለች (ታጠፋችኋለች) ።

፴፱ ወእለ ተርፉ እምኔክሙ ይደመሰሱ በእንተ ኃጣውኢሆሙ ወበእንተ ኀጣውአ አበዊሆሙ ይትመሰዉ በምድረ ፀሮሙ ።

ከናንተ የቀሩትም በኃጢአታቸው ምክንያት ይደመሰሳሉ ፤ ስለ አበቶቻቸውም ኃጢአት በጠላቶቻቸው አገር ቀልጠው ይቀራሉ ። ዘዳግ፡ ፳፰ ፷፭ ፤ ሕዝ፡ ፬ ፲፯ ።

፵ ወያየድዑ ኀጣውኢሆሙ ወኃጣይአ አበዊሆሙ ፤ ከመ ክሕዱኒ ወተዓወሩኒ ወከመ ሖሩ ግድመ በቅድሜየ ።

እንደ ካዱኝ ቸልም እንዳሉኝ ፤ በፊቴም አግድመው እንደሄዱ የራሳቸውንና የአበቶቻቸውን ኃጢአት ይናገራሉ (ይናዘዛሉ) ። ዘኁ፡ ፭ ፯ ፤ ኢዮብ ፴፱ ፴፩ ።

፵፩ ወአነኒ ሖርኩ ምስሌሆሙ ግድመ በመዓት ፤ ወአጠፍኦሙ በምድረ ፀሮሙ ፤ ወይትኃፈር ልበሙ ዘኢኮነ ግዙረ ፤ ወይእተ አሚረ ይገንዩ ለኃጣውኢሆሙ ።

እኔም በቍጣ ከነሱቸው አግድሜ ሄድኩባቸው በጠላቶቻቸውም አገር አጠፋቸዋለሁ ፤ ያን ጊዜ ያልተገረዘ (ከፍቅረ ጣኦት ያልተለየ) ልቡናቸው ያፍራል ፤ ያን ጊዜም ስለ ኃጢአታቸው ይለማመጣሉ ። ዘፀ፡ ፯ ፲፱ ።

፵፪ ወውእተ አሚረ እዜከር ኪዳንየ ዘምስለ ያዕቆብ ፤ ወኪዳንየ ዘምስለ ይስሐቅ ፤ ወኪዳንየ ዘምስለ አብርሃም እዜክር ፤ ወለምድርኒ እዜክራ ።

ያን ጊዜ ከያዕቆብ ከይስሐቅና ከአብርሃም ጋር የተማማልኩትን መሐላዬን አስባለሁ ፤ ምድርንም አስባታለሁ ።

፵፫ ወትትኃደግ ምድር እምኔሆሙ ወይእተ አሚረ ትትዌከፍ ምድር ሰናብቲሃ ሶበ ማሰነት በእንቲአሆሙ ፤ ወእሙንቱኒ ይትዌከፉ ኃጣውኢሆሙ እስመ ተዓወሩ ኵነኔየ ፤ ወተቈጥዓት ነፍሶሙ ትእዛዝየ ።

ከነሱቸውም የተነሣ ምድር በዶዋን ትቀራለች ፤ ያን ጊዜ ምድር በነሱ ኃጢአት ምክንያት ከጠፋች በኋላ ዕረፍቷን ትቀበላለች (ዕረፍት ታደርጋለች) ሕጌን ቸል ብለዋልና ሰውነታቸውም ትእዛዜን ሰልችታዋለችና እነሱቸውም የኃጢአታቸውን ፍዳ ይቀበላሉ ።

፵፬ ወአኮ እንዘ ሀለዉ ውስተ ምድረ ጸላእቶሙ ዘተዐወርክዎሙ ፤ ወኢተቈጣዕክዎሙኒ ከመ እጥፍኦሙ ፤ እስመ ኃደጉ ኪዳንየ ዘኀቤሆሙ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክሙ ።

በነሱቸው ዘንድ ያለ መሐላዬን አፍርሰዋልና ፤ በሀገራቸው ሳሉ ነው እንጂ በጠላቶቻቸው አገር ሳሉ ቸል ያልኋቸው አይደለም ፤ አጠፋቸውም ዘንድ አልተቈጣኋቸውም ፤ እኔ እግዚአብሔር ፈጣሪያቸው ነኝና ።

፵፭ ትዘከርኩ ኪዳኖሙ ዘቀዳሚ ዘከመ አውፃእክዎሙ እምድረ ግብጽ እምቤተ ቅንየት እንዘ ይሬእዩ አሕዛብ ከመ እኩኖሙ አምላኮሙ አነ እግዚአብሔር ።

እኔ እግዚአብሔር የፍቅር አባት እሆናቸው ዘንድ አሕዛብ እያዩ ከግብጽ ምድር ከባርነትም አገዛዝ እንዳወጣኋቸው የቀደመው መሐላቸውን አሰብኩ ።

፴፮ ዝንቱ ውእቱ ትእዛዝ ወኵነኔ ወሕግ ዘወሀበ እግዚ
አብሔር ማእከሌሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ወማእከሌሁ
በደብረ ሲና በእደ ሙሴ ።

እግዚአብሔር በሱና በእስራኤል ልጆች መካከል በሲ
ና ተራራ በሙሴ እጅ የሰጠው ሕግ ትእዛዝና ፍርድ ይህ
ነው ። ዘዳግ፡ ፯ ፩ ፡ ፲፪ ፩ ፡ ዘሌዋ፡ ፳፭ ፩ ።

## ምዕራፍ ፳፯ ።

፩ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ ንግሮሙ ለደ
ቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ።

እግዚአብሔር ሙሴን ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለ
ህ ንገራቸው ብሎ ተናገረው ።

፪ ብእሲ ብእሲ እመበ ዘበጽዐ ብጽዓተ ህየንተ ቤዛ ነፍሱ
ለእግዚአብሔር ይኩን ሤጡ ለተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም
እስከ ስሳ ዓም ፡ ሐምሳ ዲድርክመ ብሩር በመዳልው
ዘቅዱስ ።

አንዱም አንዱም ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ለእግዚአብሔር
ሊሰጥ የተሳለው ስለት ቢኖር ፡ ከሃያ ዘመን በላይ እስከ
ስሳ ዘመን የሆነው የወንዱ ዋጋ እንደ መቅደሱ ሚዛን አም
ሳ የብር ሰቅል ይሁን ። ዘኍ፡ ፯ ፪ ፡ መሳ፡ ፲፩ ፴ ።

፫ ወለአንስትሰ ይኩን ሤጣ ሠላሳ ዲድርክመ ብሩር ።

የሴቲቱም ዋጋ ሠላሳ የብር ወቄት ይሁን ።

፬ ወእመሰ ዘእምሐምስቱ ዓም እስከ ዕሥራ ዓም ፡ ይኩን
ሤጡ ለተባዕት ዕሥራ ዲድርክም ።

ከአምስት ዓመት በላይ እስከ ሃያ ዓመት ያለውን ል
ጁን ሊሰጥ የተሳለ ቢኖር ፡ የወንዱ ዋጋ ሃያ ወቄት ይሁን።

፭ ወለአንስትሰ ዓሥሩ ዲድርክመ ብሩር ።

የሴቲቱም ዋጋ ዐሥር ወቄት ይሁን ። ኢዮ፡ ፳፰ ፲፯።

፮ ወእመሰ እምአሐዱ ወርኅ እስከ ሐምስቱ ዓም ይኩን
ሤጡ ለተባዕት ሐምስተ ዲድክርመ ብሩር ፡ ወለአንስትሰ
ሠለስተ ዲድርክመ ብሩር ።

ከአንድ ወር እስከ አምስት ዓመት ድረስ የሆነው የወ
ንዱ ዋጋ አምስት የብር ወቄት ይሁን ፡ የሴቲቱ ግን ሦስት
የብር ወቄት ይሁን ።

፯ ወእመሰ ዘእምስሳ ዓም ወላዕሉ ፡ ለእመ ተባዕት ውእ
ቱ ይኩን ሤጡ ዐሠርተ ወሐምስተ ዲድርክመ ብሩር ፡
ወለአንስትሰ ዓሠርተ ዲድርክመ ብሩር ።

ከስድሳ ዓመትና ከዚያም በላይ ያለው የወንዱ ዋጋ
አሥራ አምስት ብር ወቄት ይሁን ፡ የሴቲቱ ግን ዐሥር
ብር ወቄት ይሁን ።

፰ ወእመሰ ኅጡእ ውእቱ ለአምጣነ ሤጡ ይቀውም ቅድ
መ ካህን ወይበዕዖ ሤጠ ካህን በአምጣነ በቁ ውስተ እዴሁ
በዘይክል ውእቱ ዘበዕዐ ከማሁ ይበዕዖ ካህን ሤጠ ።

ለዋጋው መጠን ቢያጣ ግን ሂዶ ከካህኑ ፊት ይቁም ፡
ካህኑም የተሳለውን በእጁ ባለው ገንዘብ መጠን ይገምት
ለት ፡ ያ የተሳለው ሰው መክፈል በሚችል ገንዘብ መጠን
ካህን ይገምተው ። ዘሌዋ፡ ፳፯ ፲፯ ፡ ፳፭ ፳፯ ።

፱ እመሰ እምእንስሳ እምዘይክውን ለአብእ ቍርባን ለእ
ግዚአብሔር እም ኔሁ ዘእምጽአ እምውስተ ቅዱስ ኢይወ
ልጥ ሠናዮ በእኩይ ፡ ወኢ እኩዮ በሠናይ ።

ስለት የሚሳለው ሰው ለእግዚአብሔር ቍርባን ለማቅ
ረብ ከሚገባ ከእንስሳ ወገን ቢሳል ከዚያ ከቅዱስ ወገን
ያመጣው ሰው መልካሙን በክፉ ክፉውን በመልክም
አይለውጠው ።

፲ ወእመሰ ወልጦ ወለጠ እንስሳ በዘውጉ ይከውኖ ወተ
ውላጡኒ ቅዱስ ውእቱ ።

ከብቱን መለወጥን ቢለውጠው ግን በሚመስለው
(በዓይነቱ) ይሁን ለውጡም ንጹሕ ይሁን ።

፲፩ ወእመሰ እምኵሉ እንስሳ ዘርኩስ ዘኢያበውኡ እም
ኔሁ ቍርባነ ለእግዚአብሔር ታቀውሞ ለውእቱ እንስሳ
ቅድመ ካህን ።

ነገር ግን ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ከማይገባ ከ
ብት ቢሆን ያንን ከብት በካህኑ ፊት አቁመው ።

፲፪ ወያበዕዖ ሤጠ ካህን ማእከለ ሠናይኒ ወእኩይኒ ፡ ወበ
ከመ በዕዖ ካህን ከማሁ ይኩን ሤጡ ።

ካህን በክፉውና በመልካሙ መካከል ዋጋውን ይገም
ግመው ፡ ዋጋውም ካህን እንደ ገመገመው እንዲሁ ይሁን።

፲፫ ወእመሰ ቤዝዎ ቤዘወ ይዌስክ ሐምስተ እዴሁ ላዕለ
ሤጡ ።

ነገር ግን ራሱ ቢገመግመው (ቢበዠው) በዋጋው ላይ
አምስት እጅ ይጨምር ። ዘሌዋ፡ ፳፯ ፲፭ - ፲፰ ።

፲፬ ወእመሰ በዐዐ ብእሲ ቤቶ ለእግዚአብሔር ወቀደሳ ይበ
ዕዐ ካህን ሤጣ ፡ ማእከለ ሠናይትኒ ወማእከለ እኪትኒ ፡
ወበአምጣነ በዕዐ ሤጣ ካህን ከማሁ ትከውን ።

ሰው ለይቶ ቤቱን ለእግዚአብሔር ቢሳል ካህን በመል
ካሙና በክፉው መካከል ዋጋዋን ይገምግማት ፡ ዋጋዋም
ካህን በገመገማት ልክ ይሁን ።

፲፭ ወእመሰ ውእቱ ዘበዕዐ ቤዘዋ ለቤቱ ይዌስክ ላዕለ ወ
ርቀ ሤጡ ሐምስተ እዴሃ ወትገብእ ሎቱ ።

ነገር ግን የተሳላት ሰው ቤቱን ቢገመግማት በዋጋዋ
ወርቅ ላይ አምስት እጅ ይጨምር ከዚያ በኋላ ትመለስለት።

፲፮ ወእመሰ እምገራውህ ዘዚአሁ በዐዐ ብእሲ ለእግዚአብ
ሔር ወይሬስዮ ሤጠ በአምጣነ እትወተ እክሉ በመስፈርተ
ቆሮስ ዘሰገም ሐምሳ ዲድርክመ ብሩር ።

ከራሱ እርሻዎች ለእግዚአብሔር ሊሰጥ የተሳለ ሰው
ቢኖር ገብስ በሚሰፍሩበት ቆሮስ በሚባል መስፈሪያ በገ
በው እህል ልክ ገምግመዉት ዋጋው አምሳ ወቄት ይሁን።

፲፯ ወእመሰ እምዓመተ ኅድገት በዐዓ ለገራህቱ ውእቱ
በከመ ሐሳበ ሤጡ ።

እርሻውን ከዓመተ ኅድገት ጀምሮ ቢሳላት ዋጋው
እንደ ግምቱ መጠን ነው ። ዘሌዋ፡ ፳፭ ፲፯ ።

፲፰ እመሰ በዓመት ዘእምድኅረ ኅድገት በፅዓ ለገራህቱ፣ ከመ ውእቱ የሐስብ ሎቱ ካህን ወርቆ ለዓመት ዘተርፈ፣ እስከ ዓመተ ኅድገት፣ ወይገድፍ ሎቱ እምሤጡ ።

ነገር ግን እርሻውን ከዓመተ ኅድገቱ በኋላ ቢሳላት ካህን እንደሱ ዕረፍት ከሚደረግበት ዘመን ጀምሮ ለቀረው ወርቁን ይገምግምለት ከግምቱም ያትርፍለት ።

፲፱ ወእመሰ ለሊሁ ዘበፅዓ ለገራህቱ ቤዘዋ ይዌስክ ዲበ ወርቱ ሤጣ ሐምስቱ እዴሁ ወትገብእ ሎቱ ።

እርሻውን የተሳላት ሰው ለራሱ ቢገመግማት በዋጋዋ ላይ አምስት እጅ ይጨምር፣ እርሻዋም ለሱ ትመለስለት ።

፳ እመሰ እምድኅረ ቤዘዋ ለገራህቱ ሤጣ ኀበ ካልእ ብእሲ ኢይቤዝዋ እንከ ዳግመ፣ አላ ትከውን ገራህቱ ቅድስተ ወስብሕተ ለእግዚአብሔር ።

ነገር ግን ከተበገረት በኋላ እርሻዋን ለሌላ ሰው ቢሸጣት እርሻዋ ለእግዚአብሔር የተለየች እርሻ ትሁን እንጂ እንግዲህ ዳግመኛ አይበገርት ።

፳፩ ወበዓመተ ኅድገትኒ ውጽአት ይእቲ እምኔሁ ወትገብእ ሎቱ እምድኅር እንተ ፍልጥተ ለካህን በደወሉ ትከውን ።

ዕረፍት በሚደረግበትም ዘመን ከሱ የወጣች ናት፣ በአውራጃው ለሱ ትሆናለች እንጂ ለካህን እንደተለየች ምድር ለሱ አትመለስለትም ። ዘሌዋ፡ ፳፭ ፴፩ ።

፳፪ ወእመሰ እምገራህት ዘተሣየጠ በዕበ ለእግዚአሔር እምዘኢኮነ ዘደወሉ የሐስብ ሎቱ ካህን ክበበ ሤጡ እምዓመተ ኅድገት ።

ነገር ግን አውራጃው ከልሆነ እርሻ የገዛ ሰው ለእግዚአብሔር የተሳለ ቢኖር ከዓመተ ኅድገት ጀምሮ ካህን የዋጋዋን ልክ ይገምግምለት ። ዘሌዋ፡ ፳፭ ፲ ፲፭ ።

፳፫ ወይሁብ ሤጠ በይእቲ ዕለት ብፅዓተ ለእግዚአብሔር ።

ካህን የመሬቱን ግምት በገመተበት ዕለት ስለቱን ለእግዚአብሔር ይስጥ ። ዘሌዋ፡ ፳፯ ፲፰ ።

፳፬ ወበዓመተ ኅድገት ይገብእ ውእቱ ገራህት ለዝክቱ ብእሲ ዘእምኀቤሁ ተሠይጠ፣ እስመ ዚአሁ ውእቱ ምድሩ ።

በዓመተ ኅድገትም ዘመን ይህ እርሻ ለሸጠው ለዚያ ሰው ይመለስለት፣ አውራጃውም ርስቱም ነውና ።

፳፭ ወኵሉ ሤጡ በመዳልው ቅዱስ ይኩን፣ ዕሥራ አበሊ አሐዱ ዲድርክም ።

ዋጋውም ሁሉ በሚዛን የተለየ ሃያ አበሊ አንድ ድሪም ይሁን፣ (ሃያ አበሊ ፩ ድሪም፣ ፩ ዲሪም ፩ ወቄት ነው)።

፳፮ ወኵሉ በኵር ዘይትወለድ እምእንስሳከ ለእግዚአብሔር ውእቱ፣ ወእልበ ዘይዌልጥ መኑሂ፣ እመኒ ላሕም፣ ወእመኒ በግዕ ለእግዚአብሔር ውእቱ ።

ከከብትህ መጀመሪያ የሚወለደው ለእግዚአብሔር ነው፣ ማንም ማን የሚለውጥ አይኑር፣ በሬም ቢሆን በግም ቢሆን (በኵር በኵሩ) ለእግዚአብሔር ነው ።

፳፯ ወእመሰ እምእንስሳ ዘርኩስ ይዌልጥ በሐሳበ ሤጡ፣ ወእመሰ ለሊሁ ቤዘወ ይዌስክ ኀምስተ እዴሁ ላዕሌሁ፣ ወይገብእ ሎቱ፣ ወእመሰ ኢቤዘዎ ይሠይጥዎ በኍለቈ ሤጡ ።

ነገር ግን ከርኩስ (ከማይገባ) ከብት ቢሆን በዋጋው ልክ ይለውጠው፣ እሱ ቢገመግመው ግን በዋጋው ላይ አምስት እጅ ጨምሮ ይመለስለት፣ ባይገመግመው ግን በዋጋው ልክ ይሽጡት ። ዘሌዋ፡ ፳፯ ፲፩ ፲፪ - ፲፫ ።

፳፰ ወኵሉ ሰብእ ዘአብአ ለእግዚአብሔር እምኵሉ ዘቦ እምሰብእ እስከ እንስሳ፣ ወእመኒ እምገራህቱ ዘደወሉ ኢይሠይጥዎ ወኢይቤዝውዎ፣ ኵሉ መባእ ቅዱስ ዘቅዱሳን ለእግዚአብሔር ውእቱ ።

ካለው ከገንዘቡ ሁሉ ከሰው ጀምሮ እስከ ከብት ድረስ ለእግዚአብሔር ያገባ ሰው ቢኖር በአውራጃው ካለ ከእርሻውም ቢሆን አይሽጡት (አይበገሩት) ለእግዚአብሔር የሚቀርበው መባ ሁሉ ለእግዚአብሔር የተለየ ነው ።

፳፱ ወኵሉ መባእ ዘአብአ ሰብእ ዘይከውን ኢይትቤዘው እስከ አመ ይመውት ።

ከሰውም ወገን የሚሆነውን መባ ያገባ ሰው ቢኖር፣ እስኪሞት ድረስ አይበገሩው ። ዘኍ፡ ፳፩ ፪ - ፲ ።

፴ ወኵሉ ዓሥራት ለምድር ዘእምዘርአ ምድር፣ ወእመኒ ዘእምፍሬ ዕፅ ዘእግዚአብሔር ቅዱስ ውእቱ ለእግዚአብሔር ።

ከምድር አዝመራ የተገኘ የምድር ዐሥራት ሁሉ እግዚአብሔር ከፈጠረው ዕንጨት ፍሬም ቢሆን ለእግዚአብሔር የተለየ ነው ። ዘፍ፡ ፲፬ ፳፣ ዘኍ፡ ፲፰ ፳፩ ።

፴፩ ወእመሰ ቤዝዎ ቤዘወ ሰብእ ዓሥራቲሁ ይወስክ ላዕሌሁ ሐምስተ እዴሁ ።

ሰው ዐሥራቱን ራሱ ሊበገረው ቢወድ ዐዓይነቱ ላይ አምስት እጅ ይጨምር ። ዘሌዋ፡ ፳፯ ፲፫ ።

፴፪ ወኵሉ ዓሥራት ዘላሕም ወዘበግዕ ወኵሉ ዘይትነዳእ በበትር ለኈልቆ፣ ቅዱስ ውእቱ ዓሥራቲሁ ለእግዚአብሔር ።

የላሙም የበጉም ዐሥራት ሁሉ ለመቍጠርም በበትር የሚነዳው ሁሉ ለእግዚአብሔር የተለየ ዕሥራቱ ነው ።

፴፫ ወኢይዌልጥዎ ሠናዮ በእኩይኒ ወኢእኩዮ በሠናይ፣ ወእመሰ ወልጦ ወለጠ ቅዱስ ውእቱ ተውላጡ፣ ወኢይትቤዘዉ ።

መልካሙን በክፉው፣ ክፉውን በመልካም አይለውጡት ቢለውጠው ግን ለውጡ ንጹሕ (መስሉ) ይሁን፣ ነገር ግን አይበገሩው ። ዘሌዋ፡ ፳፯ ፲ ።

፴፬ ዝንቱ ውእቱ ትእዛዝ ዘአዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ በደብረ ሲና ከመ ይንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

ለእስራኤል ልጆች ይነግራቸው ዘንድ እግዚአብሔር ሙሴን በሲና ተራራ ያዘዘው ትእዛዝ ይህ ነው ።